# የኢዴፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ትንታኔ

## ክፍል አንድ (Volume - 1)

## የኢዴፓ ፖለቲካዊ መስመርና ስትራቴጂዎች

(ረቂቅ - ፩)

ሰኔ 1995 ዓ.ም

## ብርቱ ማሳሰቢያ፣

ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው በሰኔ ወር 1995 ዓ.ም ነው። ፖለቲካ በባህሪው የተለዋዋጭ ሂደቶች (Political Dynamism) ውጤት ነው። በዚህም ምክንያት ሰነዱ ከተዘጋጀ ወዲህ ባሉት ጊዜአት በሀገሪቱ በርካታ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንደ ፖለቲካ ኃይል፤ ኢዴፓም የዚሁ ዳይናሚዝም ውጤት ነው። ስለሆነም፣ ፓርቲው ይህንን ሰነድ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመጨረሻውን Version እስከሚያወጣ ድረስ፤ ይህንን ሰነድ የሚያነቡ ሁሉ የተጻፈበትን ወቅት የቋንቋ አጠቃቀምና ስነልቡና ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በአክብሮት እናሳስባለን።

**(የኢዴፓ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ)**

# ክፍል - 1

# የኢዴፓ ፖለቲካዊ መስመርና ስትራቴጂዎች

## 1. የዴሞክራሲ ጥያቄና ትርጉም

### 1.1 ዴሞክራሲ ምንድን ነው?

አሁን በምንገኝበት ዓለም እንደ ዴሞክራሲ ጥያቄ የሰውን ልጅ ትኩረት የሳበ የፖለቲካ አመለካከት የለም ለማለት ይቻላል:: መንግሥታትና የፖለቲካ ቡድኖች፣ የሞያ ማህበራትና ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ የሠብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶችና የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት በሙሉ ስለ ዴሞክራሲ ሳያነሱ የሚውሉበት አጋጣሚ ጥቂት ነው:: ግለሰቦች ሳይቀሩ አስተሳሰባቸው፣ አኗኗራቸውና ተግባራቸው ዴሞክራሲያዊ መሆኑን ለመግለጽ ላይ ታች ይላሉ:: ሁሉም የዴሞክራሲን ካባ አጥልቆ ለመታየት፣ የዴሞክራሲ ዋስና ጠበቃ ሆኖ ለመቅረብና ዴሞክራት ለመምሰል ከባድ ፉክክር ውስጥ ገብቷል:: ይህ በአንድ በኩል ዴሞክራሲ እያገኘ የመጣውን ትልቅ ከበሬታና ትኩረት የሚያሣይ መልካም ገጽታ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የዴሞክራሲን ሀቀኛ ትርጉም ለመረዳት እስኪያስቸግር ድረስ የዘለቀ ውዥንብር እየፈጠረ መሆኑ አይካድም:: በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአውስትራሊያ፣ በኤሽያና በአፍሪካ የሚገኙ ሁሉንም አይነት የፖለቲካ አቅጣጫ የሚከተሉ መንግሥታትና ፓርቲዎች እራሳቸውን ዲሞክራት አድርገው ያቀርባሉ:: ኮሚዩኒስቶችና አምባገነኖች ብቻ ሳይሆኑ ዘረኞች፣ ፋሽስቶችና አሸባሪዎች ሳይቀሩ የራሳቸው ዓላማና ተግባር ከሌላው የተሻለ ዴሞክራሲያዊ እንደሆነ አድርገው ሲከራከሩ መስማት የተለመደ ነው:: የዚህ ዓይነቱ አቀራረብ ስለዴሞክራሲ በሚሰጥ ትርጉም ላይ በተለያየ ጊዜ አከራካሪ ሁኔታዎች ማስከተሉ ባይቀርም እውነቱን ግን ጨርሶ ሊጋርደው አይችልም::

ዴሞክራሲ ምንድን ነው? ትክክለኛው ዴሞክራሲ የትኛው ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳትና መልስ የሚሆኑ ማብራሪያዎችን በማቅረብ በዴሞክራሲ ዙሪያ የሚፈጠረውን ውንዥንብር ማጥራት አስፈላጊ ነው:: ዴሞክራሲ የሚለው ቃል ከበቀለበት ጥንታዊ ግሪክ አንስቶ የመላው ዓለም ቋንቋ መሆን አስከቻለበት የአሁኑ ዘመን ድረስ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ መሠረተ ሀሣብ የሚገለጥበት መንገድ ሆኖ እያገለገለ ነው:: ዴሞክራሲ የሚለውን የግሪክ ቃል ወደ ራሣችን ቋንቋ ስንለውጠው «የሕዝብ ሥልጣን» የሚለውን ትርጉም ይሰጣል:: አሁንም የዴሞክራሲ ትርጉም ከዚሁ መሠረተ ሀሣብ ጋር የተያያዘ ነው:: ልዩነት አለ ከተባለ በጥንታዊ ግሪክ ዴሞክራሲ ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ አሁን ሥራ ላይ ከሚውልበት ሁኔታ ጋር ሲወዳደር የአሁኑ በብዙ ዓይነት መልኩ እየሰፋ መሄዱ ነው:: የጥንታዊ ግሪክ ዴሞክራሲ ለነፃ ሰዎች (free men) ብቻ የሚፈቀድና «ባሪያዎችን» የማያጠቃልል የነበረ ሲሆን የአሁኑ ዴሞክራሲ ደግሞ ለሁሉም የሠው ልጆች እኩል መብትና ነፃነት እንዲኖር እንዲፈቅድ መሆኑ ነው:: ዴሞክራሲን በመተርጐምና በመመዘን ረገድ የፖለቲካ ሳይንቲስቶች ልዩነቶች ቢኖሩአቸውም በሮበርት ኤ.ዳህል የቀረቡት ስምንት ክራይቴሪያዎች ግን እስካሁን ሠፊ ተቀባይነት አላቸው:: እነዚህም አንደኛ የመምረጥ፣ ሁለተኛ የመመረጥ መብት፣ ሶስተኛ የፖለቲካ ሰዎች የመራጮችን ድጋፍና ድምጽ ለማግኘት ያላቸው የመወዳደር መብት፣ አራተኛ ነፃና ትክክለኛ የሆነ ምርጫ፣ አምስተኛ የመደራጀት ነፃነት፣ ስድስተኛ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት፣ ሰባተኛ አማራጭ የመረጃ ምንጮችን የማግኘትና የመጠ ቀም መብት፣ ስምንተኛ በህዝቡ ድምፅም ሆነ በሌሎች የፍላጎት መግለጫ መንገዶች ላይ ተመሰርተው ጠቃሚ ፖሊሲዎችን የሚያወጡ ተቋሞች መኖር ናቸው::

የዘመናችን ዴሞክራሲ የሕዝብ ሥልጣን ውክልና በተሰጣቸው ቡድኖች ወይም የተለያዩ ተቋማት ሥራ ላይ የሚውልበት ሁኔታ በመቻቻልና በድርድር መርህ የተቃኘ ውስብስብ የግንኙነት ሥርዓት ቢሆንም በዋናነት የሚመሠረትባቸው እሴቶች አሉ:: እነዚህ እሴቶች የዴሞክራሲውን ሙሉ ትርጉም የሚሰጡ ብቻ ሳይሆኑ ትክክለኛው ዴሞክራሲ የትኛው ነው? ለሚለው ጥያቄም የማያሻማ መልስ የሚያስገኙ መሠረታዊ ጉዳዩች ናቸው:: እነዚህም፣

1. የሕዝብ ውክልና አለው የሚባል አንድ ቡድን ወይም ተቋም ዴሞክራሲያዊ ሊሆን የሚችለው የግለሰብን መብት የዴሞክራሲ መሠረት አድርጎ ሲቀበልና በሥራ ላይ ማዋል ሲችል ነው:: የማንኛውም ቡድን ወይም ተቋም ቀዳሚ ተግባር እያንዳንዱ ግለሰብ ለፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ መሠረቶች ለእድገትና ለመሻሻል ያለውን የታመቀ ጉልበትና እውቀት አውጥቶ ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም እንዲችል ማድረግ መሆኑን ሲገነዘብ ወይም ለሰው ልጅ ግለሰባዊ መብት የተሟላ ክብርና እውቅና መስጠት እንዳለበት አምኖ ሲንቀሳቀስ፣

2. እያንዳንዱ ግለሰብ ከሥርዓት (ዲሲፕሊን) ከማህበራዊ እሴቶችና ሕዝቦች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደፈለገው ለማሰብ፣ ለመሥራትና ለመኖር፣ የፈለገውን እምነት ለመከተልና ለማራመድ ያለውን ሙሉ ነፃነት ተቀብሎ ከሥራ ላይ ሲያውል፣

3. ሁሉም ሰዎች በተፈጥሮአቸው እኩል በመሆናቸው እኩል መብትና ተጠቃሚነት አላቸው የሚለውን ተቀብሎ ተግባራዊ ሲያደርግ፣

4. ግለሰቦች ነፃነታቸውን በሚጠቀሙበት ጊዜ የሌሎችን መብት በማይጎዳ፣ ይልቁንም የጋራ ጥቅም በሚያስገኝላቸውና እንደ አንድ ቤተሰብ በሚያስተሳስራቸው የትብብር መንፈስ መሆን እንዳለበት ታምኖ በሥራ ላይ ሲውል፣

5. የግለሰቦች መብት፣ ነጻነት፣ እኩልነትና ወንድማማችነት የሚረጋገጥበት፣ የህግ የበላይነት የሠፈነበትና በዚህ ላይ ተመሥርቶ የሕዝብ ሥልጣን ሉዓላዊነት የሚገለጥበት መሆኑ በተግባር በሚታይበት ጊዜ ነው::

እነዚህ የዴሞክራሲ እሴቶች በአንድ ወይንም በሌላ መንገድ በተግባር በማይገለፁበት ጊዜ ዴሞክራሲው የታይታ ዴሞክራሲ ወይም አስመሳይ ዴሞክራሲ ይሆናል:: እስከ አሁን በተግባር ማረጋገጥ እንደተቻለው ትክክለኛውን ዴሞክራሲ በሥራ ላይ ማዋል የቻሉ አገሮችና ሕዝቦች ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው መልካም አስተዳደር አስፍነዋል:: ለሕግ የበላይነት የሚገዛና የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት መሥርተዋል:: የዜጎችን ነፃነት፣ መብትና ደህንነት የሚንከባከብ የማኀበራዊ ዋስትና አገልግሎት ባለቤቶች ሆነዋል:: ፈጣንና ዘላቂ እድገት የሚታይበት የኢኮኖሚ ብልፅግና አግኝተዋል:: አስተማማኝ ሰላምና ፀጥታ አስፍነዋል:: ኢዴፓም በኢትዮጵያ ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈልገው እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን እሴቶች በተሟላ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲ ነው:: በጥቅሉና በአጭሩ የዴሞክራሲን ትርጉም በዚህ ሁኔታ ከተረዳን ቀጥለን ደግሞ የተለያዩ የዴሞክራሲ አማራጮችን ዘርዘር አድርገን ማየት ስለዴሞክራሲ የበጠለ ለመረዳትና የኢዴፓንም የፖለቲካ አቅጣጫ በተሻለ ሁኔታ ለመገንዘብ ይረዳናል::

## 1.2 ሊበራል ዴሞክራሲ

### 1.2.1 ሊበራል ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው?

ሊበራል ዴሞክራሲ ማለት የካፒታሊዝም ሥርዓት ማኀበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ርዕዮተ-ዓለም ነው ብሎ አጠቃላይ ትርጉም መስጠት የሚቻል ቢሆንም ከዚህ አቀራረብ በተሻለ ዘርዘር ማድረጉ ንድፈ ሀሣቡን በተሟላ ይዘቱ ለመረዳት እንደሚጠቅም

ይታመናል:: ሊበራል ዴሞክራሲ ሲባል የተለያዩ አስተያየቶችና አመለካከቶች የሚቻቻሉበት፣ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ወይም ደግሞ የግለሰብ ነፃነት የተረጋገጠበት ነፃ የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚለውን ትርጉም የሚያቅፍ ፅንሠ ሃሣብ ነው:: የሊበራሊዝም አመለካከት ስለነፃነት የሚደጋጋፉ ሁለት ቁምነገሮችን ያቀፈ ነው:: አንደኛው ማንም ግለሰብ ከራሱ ፈቃድ ውጭ የሆነ ሌላ ኃይል (መንግሥትን ጨምሮ) ጣልቃ ሊገባበት አይገባም የሚል ይዘት ሲኖረው ሁለተኛው ደግሞ እያንዳንዱ ግለሰብ ያለውን አመለካከት ለማራመድ፣ የሚፈልገውን የሕይወት አቅጣጫ ለመከተል፣ ነፃ ሆኖ ለማሰብ፣ ለመሥራትና ለመኖር መብት አለው የሚል ይዘት የያዘ ነው:: እዚህ ላይ እያንዳንዱ ግለሰብ ከመንግሥት ጣልቃገብነት የመጠበቅ ነፃነት አለው ሲባል የሊበራል ዴሞክራሲ ጠቃሚ እሴት ከሆነው የሕግ የበላይነት መኖር ጋር የሚኖረው ትርጉም ምንድነው የሚል ጥያቄ መነሳቱ ተገቢ ነው::

መንግሥት የሚባለው ተቋም ሰዎች ሰላምና ደህንነታቸውን እንዲጠብቅላቸው፣ ፍላጐታቸውንና ጥቅማቸውን እንዲያስከብርላቸው ከራሳቸው ነፃነት ቀንሰው በገዛ ፍቃዳቸው የሥልጣን ውክልና የሰጡት ተቋም ነው:: ይህ ተቋም ሰዎች በፈቃዳቸው የሰጡትን የውክልና ሥልጣን በሥራ ላይ በማዋል የሰዎችን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሕግና ሥርዓት አውጥቶ ይንቀሳቀሳል:: እያንዳንዱ ሰው ደግሞ ለዚህ ሕግና ሥርዓት ተፈፃሚነት ግዴታና ኃላፊነት ይወድቅበታል:: እዚህ ላይ መታየት የሚገባው እያንዳንዱ ግለሰብ ከራሡ ነፃነት ቆርሶ መንግስትን ያቋቋመው በራሱ ፍቃድ እንጂ በሌላ ውጫዊ ኃይል ተፅዕኖ አለመሆኑ ነው:: ለመንግሥት የሥልጣን ውክልና ለመስጠት በራሱ ፍቃድ እንደወሰነው ሁሉ ይኸው መንግሥት ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚከተለውን ሕጋዊ አግባብ ለመቀበል ግዴታ እንዳለበትም የተቀበለውና የወሰነው እራሱ ግለሰቡ ነው ማለት ነው:: ሕጉን በማውጣቱ ሥራ እያንዳንዱ ግለሰብ ራሱ በቀጥታ ወይንም እሱ አምኖ በሚወክለውና ፈቃዱን በሰጣቸው ተወካዮቹ አማካኝነት ተሳትፎ ስላደረገ በሕግ የመገዛት ግዴታ በራሱ ላይ የጣለው እራሱ እንጂ ሌላ ኃይል የጫነበት ተድርጐ ሊወሰድ አይችልም:: በዚህ የተነሣ በሁለቱ የሊበራሊዝም መሠረታዊ እሴቶች ማለትም በግለሰቡ ነፃነና በሕግ የበላይነት መካከል ሊጣጣም የማይችል ቅራኔ የለም ማለት ነው::

ሊበራሊዝም ልዩ ልዩ አመለካከቶችና አስተያየቶች የሚቻቻሉበት ነው ሲባል በአንድ መልኩ እያንዳንዱ ግለሰብ አማራጮችን የማግኘት ነፃነቱ የተጠበቀ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የማንም ግለሰብ ነፃነት ትርጉም የሚኖረው የሌላውን ግለሰብ ነፃነት እስካልተጋፋ ድረስ በመሆኑ ነፃነቱ እንዲከበርለት የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ የሌላውን ነፃነት ላለመጋፋት የሚያስችል መቻቻል እንዲኖር  ይሠራል ማለት ነው:: ይህ መቻቻል የሚመጣው የአንዱ ነፃነት ከሌላው እንደማይበልጥ ወይንም እንደማያንስ አምኖ በመቀበል ነው:: ይህም ማለት ሠው በተፈጥሮ እኩል በመሆኑ በሀይማኖቱ፣ በፖለቲካ አመለካከቱ፣ በዘሩ፣ በትምህርት ደረጃው፣ በቀለሙ፣ በፆታ ልዩነት ምክንያት ለአንዱ ከፍ ያለ ለሌላው ዝቅ ያለ ነፃነት እንዳለው ተደርጐ ሊወሰድ አይገባውም:: በነፃነት እረገድ አድሎ የሌለው እኩልነት መኖሩ ተቀባይነት ማግኘት አለበት ማለት ነው:: እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ የነፃነት የወንድማማችነትና የእኩልነት መርሆዎች የሊበራሊዝም እሴቶች ናቸው:: የአሜሪካ ነፃነት አዋጅ እ.ኤ.አ ሐምሌ 4 ቀን 1776 በፀደቀበት ጊዜ ከተቀበላቸው መሠረታዊ ሃሣቦች መካከል «ሁሉም ሰዎች እኩል የተፈጠሩ ናቸው:: በተፈጥሮ ያገኟቸውና ሊነጠቋቸው የማይገቡ መብቶች አሏቸው:: ከነዚህ መካከል ዋናዎቹ ሕይዎት፣ ነፃነት፣ ደስታን መሻት ናቸው» የሚሉ ይገኙበታል:: የአሜሪካንን የነፃነት አዋጅ ካረቀቁት መካከል አንዱ የሆነው ቶማስ ጀፈርሰን መንግሥት የግለሰብ ነፃነትን በመጠበቅ አንፃር ያለበትን ኃላፊነት ሲገልፅ «መንግሥት እንዲኖር የሚያስፈልገው ቸል ሊባል የማይገባውን የሰው ልጅ መብት ለመጠበቅ እንዲቻል ነው» ብሏል:: ሊበራሊዝም እነዚህን እሴቶች በማክበር ላይ የቆመ አመለካከት ነው::

ሊበራሊዝም በአሜሪካና በአውሮፓ አገሮች የመብት ማስከበሪያ ድንጋጌዎች ውስጥ በሠፊው ለመንፀባረቅ የቻለ ተራማጅ አስተሳሰብ ከሆነበት ዋናው ምክንያት ለሰዎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማለትም ለሲቪል ነፃነቶችና የፖለቲካ መብቶች በሚሠጠው ከፍተኛ ዋጋ የተነሣ ነው:: ሊበራሊዝም ከቆመባቸውና ከፍተኛ ግምት ከሚሠጣቸው መርሆዎች መካከል ሃሣብን የመግለጽና የመደራጀት ነፃነት፣ የሐይማኖት ነፃነት፣ የመረጠውን አመለካከት የመከተል ነፃነት፣ የመሰብሰብ፣ ተቃውሞ የማሰማት፣ የመስራት፣ ንብረት የማፍራት ነፃነት፣ በሕይወት የመኖርና ከጥቃት የመጠበቅ ነፃነት፣ ሚዛናዊ የሆነ ፍትሕ የማግኘት፣ በእኩልነት የመታየት ወይም በእኩልነት የመያዝ ነፃነት፣ የሕግ የበላይነት የሚሉት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

በዘመናችን ሊበራል ዴሞክራሲን ያራምዳሉ ከሚባሉት ሀገሮች አንዳንዶቹ እነዚህን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መርሆዎች በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ አካተዋቸዋል:: ሌሎቹ ደግሞ የመብት ድንጋጌዎች (Bill of Rights) በሚል ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሠነድ በማዘጋጀትና የአገራቸው የሕግ አካል እንዲሆኑ የሚያስችል ሕጋዊነት እንዲኖራቸው በማድረግ በሥራ ላይ አውለዋቸዋል:: በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ደረጃም ጠቅላላ ጉባኤው እ.ኤ.አ በዲሴንበር 10 ቀን1948 ዓ.ም ያፀደቀውና ያወጀው ቁጥር 217–A (III) እነዚህኑ መብቶች ያቀፈና «አጠቃላይ የሰብዓዊ መብቶች አዋጅ» የሚባል ሠነድ እንዳለ ይታወቃል:: አንዳንዶቹ ዴሞክራቲክ መንግሥታት ከእነዚህም ዘርዘር ባለ ሁኔታ የተቀመጡ የኤኮኖሚ፣ የባሕልና ማኅበራዊ ደህንነት መብቶችን ያካተቱ ሕጐችን አውጥተው በሥራ ላይ አውለዋል:: እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለበት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ አድርጐ መቀበል ብቻ የመብቶቹ መሟላት ማረጋገጫ ዋስትና እንደሆነ አድርጐ መመልከት ተገቢ አለመሆኑን ነው::

የሊበራሊዝም ሌላው ባሕሪይ አዳዲስ አስተሳሰቦችንና አሠራሮችን ለመቀበል ክፍት የሆነ፣ በየጊዜው በሚፈጠሩ አዳዲስ እውቀቶችና ልምዶች ራሱን እያደሰ፣ እያዳበረና እያሳደገ የሚሄድ መሆኑ ነው:: ሊበራሊዝም የሰከነ፣ በጥናትና በአርቆ አስተዋይነት ላይ የተመሠረተ፣ የሰው ልጅን ነፃነትና መብት የጠበቀ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ መኖር አለበት ብሎ የሚያምን አመለካከት ነው:: እንዲህ ዓይነት የማያቋርጥ ለውጥና መሻሻል እንዲኖር ልዩ ልዩ አመለካከቶች በነፃነት መንሸራሸር አለባቸው ብሎ ያምናል::

በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ በግልና ከሌሎች ጋር በሚኖር ግንኙነት የሚፈጠሩ ችግሮች እንደሚኖሩና እንደችግሮቹ አይነትና ብዛት የመፍትሄ አማራጮቹም ብዙ ዓይነት ሊሆኑ እንደሚችሉ ሊበራሊዝም ያምናል:: ከሰው ልጅ መሠረታዊ ነፃነቶች መካከልም አንደኛው ልዩ ልዩ አማራጮችን ለማመዛዘንና የጠቀመውን ለመቀበል ያለው ነፃነት ነው:: ይህንን ለራሱ የሚበጀውን የመምረጥ ነፃነት እንዲጠቀምበት በቅድሚያ አማራጭ እንዲኖር ያስፈልጋል:: ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወቱ ውስጥ የአመለካከት፣ የአሠራር፣ የአደረጃጀት አማራጮች እንዲኖሩት ያስፈልጋል:: በዚህም ምክንያት ሊበራሊዝም በሀሣብ ነፃ ገበያና በነፃ ገበያ ኤኮኖሚ መርህ ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ነው እየተባለ በተደጋጋሚ ይገለፃል::

### 1.2.2 የሃሣብ ነፃ ገበያ እና ሊበራሊዝም

ሊበራል ዴሞክራሲ የሃሣብ ነፃ ገበያ መኖርን በመርህ ደረጃ በመቀበል የተወሰነ አይደለም:: በተግባርም ምንም ዓይነት ውሳኔ ላይ ከመደረሱ አስቀድሞ የሀሣብ ልውውጥ ማድረግ፣ የተለያዩ ተቃራኒ ሀሣቦች እንዲደመጡና እንዲመዘኑ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል:: እንዲያውም ከዚህ ውጭ የሚወሠን ማንኛውም ውሣኔ ዘላቂ ውጤት ያስገኛል ብሎ አያምንም:: ይህ መርህ በሕብረተሰቡ መካከል በሚኖር ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በጐረቤትና በሥራ ባልደረቦች መካከል ሰዎች በሚኖራቸው ግንኙነት ሥራ ላይ

ሲውል ለግንኙነቶቹ ጤናማነትና ዘላቂነት ያለውን ከፍተኛ ጥቅም በመደበኛ የእለት ተእለት ሕይወታችን ውስጥ የምናውቀው ነው:: ሊበራሊዝም የሀሣብ ነጻ ገበያ መርህን የሚከተለው ለአንድ ወገን ጥቅም ብቻ አይደለም:: በኤኮኖሚው ዓለም ገዥና ሻጭ በንግድ ግንኙነት ሂደት ሁለቱም እንደሚጠቀሙት ሁሉ በፖለቲካና ማህበራዊው ዓለምም ሀሣብን በመስጠትና በመቀበል ግንኙነት ሂደት የሚገኘው ጥቅም የጋራ እንጅ የአንድ ወገን ብቻ አይደለም:: ሃሣብ መስጠትና መቀበል ሲባል አንድን አቅጣጫ ብቻ ይዞ የሚጓዝ አድርጐ መመልከት ስህተት ነው የሚሆነው:: አንዱ ሀሣብ ሠጭ አንዱ ደግሞ ሀሣብ ተቀባይ ብቻ ሆኖ በሚቆምበት ሁኔታ የታጠረ ግንኙነት ሳይሆን በእኩልነት፣ በመከባበርና በመቻቻል መንፈስ ሁሉም ሀሣብ ሠጪ፣ ሁሉም ሀሣብ ተቀባይ ሆነው የሚሠለፉበት የሁለትዮሽ ግንኙነት ነው:: ይልቁንም ከሁለትዮሽ ግንኙነት በላይ የሚሄድ ባለ ብዙ አውታር ግንኙነት ነው:: ዋናው ነገር በጋራ ከመነጋገርና ከመደማመጥ የሚገኘው ውጤት ለሁሉም የሚጠቅም መሆኑን መቀበልና በተግባር ማዋል መቻል ላይ ነው::

ይህ ሀሣብን በመስጠትና በመቀበል ሂደት የሚፈጠር በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አስተሣሠብ የያዘው ሌላ ገጽታም አለ:: ይኸውም አንዱ ብቸኛ ሀሣብ አፍላቂ፣ ሌላው ብቸኛ የሀሣብ ማራገፊያ በማይሆንበት መንገድ የሚኖር ግንኙነት ወይም ደግሞ የአንዱ ሀሣብ መሪና ገዥ የሌላው ደግሞ ተከታይና ተራ ተደርጐ በሚታይበት ሁኔታ መመስረት የሌለበት መሆኑ ነው:: በሊበራል አመለካከት ብቸኛ ሀሣብ አፍላቂ፣ ብቸኛ የሀሣብ መጣያ ሆኖ የሚታይ ማህበራዊ መደብ የለም:: ሁሉም ማህበራዊ አካል አካባቢውና ልምዱ በሚፈቅድለት ደረጃ ሃሣብ ያፈልቃል፣ ይሠጣል:: በዚያው መጠን የሌሎችንም ይቀበላል:: መሪና ገዥ ሀሣብ የሚወጣው ከአንድ ወገን ብቻ ሣይሆን ከሁሉም ወገን በሚገኝ የሃሣብ አስተዋፅዖና ስምምነት መሠረት ነው:: አብዮታዊ ዴሞክራቶች ግን የከፍተኛ ዓይነት ሣይንሳዊ ዕውቀት ብቸኛ ባለቤቶች ራሣቸው እንደሆኑ በመቁጠር ሀሣብ የማፍለቅ ልዩ ሥፍራ እንዳላቸው ይገምታሉ:: የሌላው ሰው ድርሻ ደግም እነርሱ የሚጭኑበትን የሀሣብ ግሣንግስ መሸከም ብቻ እንደሆነ አድርገው ያምናሉ:: ለዚህም ነው ብቻቸውን ሕገመንግሥት እየጻፉ በሕዝቡ ላይ የሚጭኑት:: ለዚህም ነው የዚህች አገርና ሕዝብ ገዥና መሪ ሃሣብ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንዲሆን ብቻቸውን ከወሠኑ በኋላ በመላው የአገሪቱ ክልል ውስጥ የሚገኘውን ሕዝብ በግዴታ እየሰበሰቡ የርዕዮተ ዓለማቸው ማራገፊያ ያደረጉት::

ሊበራሊዝም የሚከተለው መንገድ ግን ከዚህ የተለየ ነው:: በመርህ ደረጃ የሃሣብ ነፃ ገበያ መኖር አለበት ብሎ ስለሚያምን ለሕገ-መንግሥትም ይሁን ለአዋጅና መመሪያ፣ ለፖሊሲም ይሁን ለመርሀ ግብር፣ ለኤኮኖሚ እስትራቴጂም ይሁን የፖለቲካ ፍልስፍና የሚሆን ሃሣብ የማፍለቅ ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ የታደሉ ምርጥ ሰዎች ናቸው የሚለውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና አይቀበልም:: ለማንኛውም ሕገ-መንግሥትና የአገር መተዳደሪያ ሥርዓት፣ ለማንኛውም ህግና መመሪያ፣ ለማንኛውም ፖሊሲና እስትራቴጂ የሚሆን ሀሣብ መፍለቅ ያለበት በሃሣብ ነፃ ገበያ መርህ በሚፈጠር ሠፊ የአስተያየት መንሸራሸሪያ ሂደት አማካኝነት ነው ብሎ ያምናል::

በሊበራል አመለካከት መሪና ገዥ ሃሣብ የሚወጣው በሃሣብ ነፃ ገበያ ውስጥ ሠፊ የሃሣብ ፍጭት ተደርጐ፣ የተለያዩ አስተያዬት ያላቸው ሁሉ አመለካከታቸውን በአደባባይ እንዲያቀርቡትና በሕዝቡ ውስጥ እንዲያሰራጩት የሚያስችል የሀሣብ መንሸራሸሪያ መድረክ ተከፍቶ፣ ሁሉንም በእኩልነት የሚያሳትፍ ክርክርና ውይይት ተደርጐ የአብዛኛው ወገን ስምምነትና ፈቃደኝነት ማግኘት ሲቻል ነው:: መሪና ገዥ ሃሣብ በአዋጅና በጉልበት የሚጫን ባይሆንም ለአብዮታዊ ዴሞክራቶች ይህ ግን ጨርሶ የማይቻል ነው የሚባል አይደለም:: ዋናው ነገር በጉልበት መጫን ቢቻልም እንኳ ዞሮ ዞሮ ተሸካሚው ክፍል አንድም በሚቻለው መጠን በግልጽም ሆነ በህቡዕ ካለፍላጐቱ የተጫነበትን ሸክም ተራ በተራ እያንጠባጠበ ለመቀነስ፣ አልያም ከቀናው ደግሞ ሙሉ በሙሉ ከላዮ ላይ አራግፎ ለማውረድ ጥረት ማድረጉ የማይቀር ነው:: በአገራችንም የዚህ ዓይነቱ ሽክርክሪት ውስጥ መገባቱን ማየት ይቻላል:: የሕወሃት አብዮታዊ ዴሞክራቶች አገር እንገዛበታለን የሚሉትን ሕግና ፖሊሲ ሁሉ

ከሕገ-መንግሥት ጀምሮ እስከ ግለሰብ ንብረት መመዝገቢያ ሥርዓት ድረስ ብቻቸውን ጽፈውና አፅድቀው በሕዝብ ትከሻ ላይ ወርውረዋል።

ከሁሉም በላይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ልዕልና እንዲረጋገጥና በመጨረሻም ገዥ ሃሣብ ሆኖ እንዲወጣ የትምህርት ሥርዓቱ፣ የፍትህ አካላቱ (ፍርድ ቤትና ፖሊስን ጨምሮ)፣ ሲቪል ሰርቪሱን፣ የምርምርና ማሰልጠኛ ተቋማቱን፣ መገናኛ ብዙሀኑን ወ.ዘ.ተ ዋነኛ ግባቸው አድርገው እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችላቸውን ፖሊሲና እስትራቴጂ ጽፈው አሽክመውታል። በብድርና በርዳታ በአገሪቱ ስም ከውጭ በሚገኘው ገንዘብ ማንቁርቱን እየታነቀ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመንግሥት የሚከፍለው ግብር፣ ቀረጥና መዋጮ፣ በአጠቃላይ የአገር ሀብትና ንብረት ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት መመሪያ ማስፈፀሚያ እንዲውል ተደርጐ ይህ ሁሉ ሲወሰን ከአብዮታዊ ዴሞክራቶች በስተቀር ሃሣቡን በወጉ እንዲሰጥ የተጠየቀ ሰው የለም።

ይኸም ሆኖ አብዮታዊ ዴሞክራቶችን ፋታ የሚነሣ ተቃውሞ በየአቅጣጫው መገንፈሉን የሚገታ መፍትሔ አልተገኘም። የተቃውሞው ዋነኛ ምክንያት ሌላ ምንም ሳይሆን በሃሣብ ነፃ ገበያ መርህ መሠረት የተገነባ፣ የብዛኛውን ሕዝብ ፈቃድና ስምምነት ያገኘ፣ የአገር መመሪያ እንዲሆን ተቀባይነት ያለው የጋራ ራዕይ ሊያዝ ባለመቻሉ ነው። ሁሉም ነገር በግድ የተጫነ፣ ሁሉም ነገር በግዳጅ ዘመቻ እንዲፈፀም የተደረገ በመሆኑ ነው። ከዚህ አዙሪት መውጣት የሚቻልበት መፍትሔ ማቅረብ የሚችለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሣይሆን ሊበራሊዝም ነው። ሊበራሊዝም ለዚህ ችግር የሚያቀርበው መፍትሔ ከላይ በዝርዝር የተገለፀውን የሀሣብ ነፃ ገበያ መርህን በሥራ ላይ በማዋል በመሆኑ እንዲህ አይነቱን አስተሳሰብ ኢዴፓ ይደግፈዋል።

## 1.2.3 ግለሰባዊነትና ማኅበራዊነት በሊበራል ዴሞክራሲ

ከዚህ ትንተና ላይ በመነሣት የሊበራል ፖለቲካዊ ፍልስፍና በሁለት ተጓዳኝ አስተሳሰቦች ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማየት ይቻላል። አንደኛው ግለሰባዊነት የሚባለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ማኅበረሰቡ ውስጥ ግለሰቦች ያላቸው ግንኙነት የሚገለፅበት ማኅበራዊነት የሚባለው ነው። ይህ የግለሰቦች ማኅበራዊ ግንኙት ዝቅተኛ ተደርጐ ሊታይ የማይገባው የሞራል ግንኘ ነት ነው። ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ መታለፍ የማይገባው የሊበራል ፖለቲካዊ ፍልስፍና አመለካከት ግለሰባዊነትና ማኅበራዊነት አንዱ የሌላው ተፃራሪ አለመሆናቸው ነው። በሊበራል አመለካከት ግለሰባዊነት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የማንኛውም እሴት መገለጫ ሆኖ ነው የሚታየው። በክርስትና እምነት «ሠንበት የተፈጠረው ለሠዎች ነው። ሰዎች ግን ለሠንበት አልተፈጠሩም» የሚል አባባል አለ። ሠንበትን የሚያክል በክርስትና እጅግ የተከበረ ዕለት ለሠው የተፈጠረ መሆኑን በመግለፅ በሃይማኖት ቃል ውሰጥ የሠፈረው መልዕክት የሚያመለክተው ሰው ራሱ የተከበረ መሆኑን ነው።

በዘመኑ ሥነምግባር ፍልስፍና ይህ አስተሳሰብ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገለፃል። አንደኛው መንገድ ግለሰባዊ ፍላጐቶች ብቸኛዎቹ እውነተኛ ፍላጐቶች ናቸው የሚለው ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ሰውን ማክበር ተገቢ ነው፤ ሰውን ማክበር ሲባል ደግሞ ግቡ ሰው ክቡር መሆኑን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል የሚለው ነው። እነዚህ ሁለት አገላለፆች አንዱ አንዱን የሚተካ ባይሆኑም የጋራ ማዕከላዊ ነጥባቸው በሁለቱም ውስጥ ግለሰባዊነት መኖሩ ነው። ከመጀመሪያው አገላለፅ በስተጀርባ ያለው ነጥብ የሚያመለክተው ማንኛውም ነገር እሴት አለው ከተባለ ይህ እሴት ተጨባጭ የሠው ልጅ ተሞክሮ በሚገለፅበት መልክ በአንድ ሰው ወይም በአንድ ነገር ውስጥ መገኘት አለበት የሚለው አስተሳሰብ ነው።ከሁለተኛው አገላለጽ በስተጀርባ ያለው ነጥብ የሚያመለክተው ደግሞ የሰው ልጅ ስብዕና በተለየ ሁኔታ ውድና የተከበረ ነው። ጠቃሚ የሆነ ማኅበራዊ ድርጊት በሕዝብ ውስጥ ያስገኘውን ጥቅም ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ (መሥፈርት) ማቅረብ የሚቻለው እያንዳንዱ ግለሰብ ምን ጥቅም እንዳገኘ በመረዳት ነው የሚለው አስተሣሠብ ነው። ግለሰባዊ ነፃነትን የሚደግፉ

ወገኖች ለዚህ ሀሣብ ተቀናቃኞች ብዙ ጊዜ የሚያነሱት ጥያቄ ገደብና ተፅዕኖ ማድረግ ምን ትርፍ እንደሚያስገኝ በማስረጃ መረጋገጥ አለበት የሚል ነው፡፡ በግለሠብ ነፃነት ላይ ገደብና ተፅዕኖ የሚደረገው ለብዙሃን መብትና ነፃነት ሲባል ነው የሚል መልስ የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ፡፡ መነሻ መሠረታቸውም የብዙሃን ተጠቃሚነት የሚለው የፍልስፍና አመለካከት ነው፡፡ የዚህ አመለካከት ይዘት ባጭሩ ማንኛውም ተግባር ጥሩ የሚሆነው ከፍተኛ ቁጥር ላለው ሕዝብ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ማብቂያ ወደሌለው ክርክር የሚያስገባ ነው፡፡ ለብዙሃን ጥቅም ሲባል የግለሰብ ጥቅም መከልከል ከተጀመረ የዚህ ዓይነቱ ዕጣ ብዙሃን በሚባሉት ሰዎች ላይ ተራ በተራ መዳረሱ የማይቀር ነው፡፡ የሚባለው ነገር ዞሮ ዞሮ መጨረሻ ላይ ትርጉሙን ያጣል፡፡ በእርግጥ የብዙሃኑ ተጠቃሚነት አንፃራዊ መመዘኛ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ ይኸውም አነስተኛ ጉልበት በመጠቀም ወይም አነስተኛ መስዋዕትነት በመክፈል ከፍተኛ ውጤት ማምጣት በሚል አመለካከት ውስጥ አስገብቶ የብዙሃን ተጠቃሚነትን አንፃራዊ ትርጉም ማየት ይቻላል፡፡ ይኸንኑ አስተያየት የሚጋፉ የሊበራሊዝም የመጀመሪያ ወቅት አስተሳሰብ አራማጆች ነበሩ፡፡ በዚህም የተነሣ የመጀሪያው ወቅት ሊበራሊዝም ከነፃነት ይልቅ ለውጤታማነት ያደላል የሚል ትችት ሲሰነዘር ቆይቷል፡፡ ሰዎች ለብሔራዊ ጥቅማቸው ሲሉ በሕይዎት የመቆየት ነፃነታቸውን ሣይቀር አሣልፈው የሚሠጡበት አጋጣሚ መኖሩን እየጠቀሱ ለብዙሃን ጥቅም ሲባል የግለሰብ ነፃነት መገደብ ይቻላል ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች በራሱ በግለሰቡ ፈቃድ በሚፈፀም ገደብና በሌላ ውጫዊ ኃይል አስገዳጅነት በሚጫን ገደብ መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት ያልቻሉ ወይም ያልፈለጉ ናቸው፡፡ አንድ ሰው በራሱ ውሣኔ ነፃነቱን አሳልፎ ለመስጠት ሲፈቅድ ይኸም ያው የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሠን ያለውን ነፃነት እንደተጠቀመበት ነው የሚቆጠረው፡፡ ለብዙሃን ጥቅም ሲባል ግለሰብ ነፃነቱን እንዲያጣ ክልከላና ተፅዕኖ ከተደረገበት ደግሞ ያለግለሰቡ ፈቃድ በግድ የሚፈፀም መሆኑ ስለማይቀር የግለሰቡን ነፃነት እንደመቀማት የሚቆጠር ነው፡፡ እዚህ ላይ በደንብ ሊተኮርበት የሚገባው ነጥብ በሊበራል ፖለቲካዊ ፍልስፍና መርሆ ግለሰብ የእሴቶች ሁሉ ምንጭ መሆኑን በሚመለከት ጠንካራ እምነት መኖሩን ነው፡፡

ሁለተኛው ማኅበረሰቡ ውስጥ ግለሰቦች ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከተውና ዝቅ ተደርጐ ሊታይ የማይገባው ማዕከላዊ ነጥብ ሰዎች እርስ በርስ እንዴት ተከባብረው እንደሚኖሩ ማሳየት ነው፡፡ ማኅበረሰብ የሚኖረው በውስጡ የሚገኙ ሰዎች ሁሉም የጋራ እሴት ፈጣሪና ባለቤት መሆናቸውን በመቀበል ከሞላ ጐደል የእርስ በርስ መግባባት በማስፈናቸው ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም ሰዎች የጋራ መብት ብቻ ሳይሆን ይኸው የጋራ መብት የሚያሳርፍባቸው የጋራ ግዴታም አንዳለ ተቀብለው በሚመሠርቱት ማኅበረሰብ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ እዚህ ላይ ዋነኛው የፓለቲካ ጥያቄ የሚሆነው በሰዎች ግንኙነት ውስጥ የሚከሠቱ ችግሮች እንዴት መፍትሔ ያገኛሉ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ግንኙነቱ የሚመሠረተው የጋራ ጥቅምና ግዴታን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ሁሉም ወገን የበኩሉን ትዕግስትና ቁጥብነት በማሣየት ነገር ግን ደግሞ በዚያው መጠን ሁሉም የየራሱን መብት በሚመለከት ጠንክሮ በመቆም ነው መፍትሔ ማግኘት የሚቻለው፡፡ ከዚህ ውጭ አንዱ በሌላው ላይ ጫና በማድረግ፣ በሆነ ዓይነት መንገድ የበላይነት እፈጥራለሁ ብሎ ቢንቀሳቀስ ግንኙነቱን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ማህበረሠቡ የቆመበትን የጋራ ጥቅምና ግዴታ መርህ ስለሚያጣ የጭቅጭቅና ትርምስ መድረክ ይፈጠራል፡፡ ግንኙነቱ የተመሠረተባቸው ዓላማዎች ዋጋ ቢስ ስለሚሆኑ በአጭር ጊዜ መፍትሔ የማይገኝላቸው ውስብስብ የፖለቲካ ችግሮች ይበቅላሉ፡፡ በዚህ ዓይነቱ ግንኘ -ነት ውስጥ በማያቋርጥ መንገድ ለሚነሱ ውዝግቦችና አለመግባባቶች ዋነኛ መሠረታቸው ለማህበረሠቡ መፈጠር አስፈላጊ የሆኑትን በርካታ ጉዳዩች የሚገዛ ሕጋዊ መደላድል አለመኖር ወይም በተቀመጠው የሕግ አግባብ ለመጠቀም አለመቻል ነው፡፡ በሊበራል አስተሣሠብ ሠዎች በፈጠሩት ማህበረሠብ ውስጥ የሚያጋጥማቸው የግንኙነት እምነት አለ፡፡ ይህ ሕጋዊ መሠረት የሚቆምባቸው የግንኙነት ችግር መፍቻ መርሆዎች ደግሞ ውይይት፣ ነጻነት፣ የቅሬታ መቅረቢይ፣ የአስተያየት መንሸራሸሪያና መለዋወጫ መድረክ፣ ድርድር፣ መስጠትና መቀበልን የማገናዘብ አሠራር፣ ተቀባይነት ያለው ማስተከካያ፣ አንዱ የሌላውን

መብት ለማክበር በሁሉም ወገኖች የሚታይ ቅንነት፣ግዴታን ለማሟላት በሁሉም ወገን የሚኖር ፈቃደኝነትና መተማመን የሚሉት ናቸው።

በእነዚህ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ የማህበረሰብ ተቋም መኖር በቅድሚያ ውይይቶችና ክርክሮች ከኃይልና ማስፈራራት ነፃ ሆነው እንዲካሄዱ፣ ሃሣቦች ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚጋጩባቸውና የሚፋጩባቸው እንዲሆኑ ይጠቅማል። የሀሣብ ልዩነቶችን ጨርሶ ማጥፋት የማይቻል ቢሆንም በኃይልና በማስፈራራት ፋንታ ውይይትና ክርክርን በመጠቀም ቅራኔና ግጭትን ለማሳነስና ለማጥበብ ያገለግላል። እንደዚህ ዓይነት የማህበረሠብ ተቋም የግንኙነት ችግሮችን ለመፍታት የሚያግዝ ሕጋዊ ኃይል ያስገኛል። በእርግጥ ይህ የሕግ ሥልጣን ሁሉንም በእኩልነት የሚገዛና ሁሉንም የሚመለከታቸው ወገኖች በራሳቸው ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚችሉትን እንጂ በዘፈቀደና በግድ የሚጫንባቸው ነገር አይደለም። በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ የግንኙነት ችግሮችን መፍታት ከሰዎች እምነት ጋር የተያያዘና ሁልጊዜም መደረግ የሚገባው ተፈጥሯዊ ተግባር ነው። ሰዎች የግንኙነት ችግሮቻቸውን የሚያስወግዱበት አስተማማኝ ሁኔታ መኖሩን ሲገነዘቡ ለማህበረሰቡ የሚኖራቸው ስሜት ጤነኛ ነው የሚሆነው። ማህበረሰቡን እንደራሳቸው ቤት ማየታቸው የተለመደ ነገር ነው። እራሳቸውን ከዚህ ማህበረሰብ ጋር አስማምቶ ለመኖር የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋሉ። ማኅበረሰቡን ነፃ የመኖሪያ አካባቢ እንጂ የማገቻ ሥፍራ አድርገው አይመለከቱትም። ማኅበረሰቡን የመጨቆኛ አካባቢ አድርገው የሚመለከቱበት ሁኔታ የሚፈጠረው የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የማያስችል ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ የግንኙነት ሥርዓት ሲከሰት ነው። የግንኙነቱን እርከን የሚያሳጥር አደረጃጀት በመፍጠርና እንደ አስፈላጊነቱ በአዲስ ዕቅድ ለግንኙነቱ ጤናማ መሆን የሚያግዝ ተጨማሪ ግንባታ እያካሄዱ የግንኙነትን ጤናማ ጐኖች የሚያጠናክር እርምጃ መውሰድ ይቻላል። ይህን በማድረግ ፈንታ ትኩረቱ ችግሮችን ለጊዜው የሚሸፍን ጥገና በማድረግ ላይ ብቻ የሚያተኩር ከሆነ ሰዎች የሚገኙበትን ማኅበረሰብ ሊተማመኑበት አይችሉም። ሌላም ሌላም ተዘርዝሮ የማያልቅ ችግር ሊፈጠር ይችላል።

ከዚህ ጐን ለጐን መታወቅ ያለበት ሁኔታ ቢኖር የማኅበረሰቡ ህልውና ጨርሶ ይጠፋል ማለት አለመሆኑን ነው። የግንኙት ችግሮች ያሉበት ማኅበረሰብ ሰላምና መረጋጋት፣ ልማትና እድገት እንደማያገኝ ግልጽ ቢሆንም ከምድረ ገፅ ይወገዳል ማለት ግን አይደለም። ጦርነትንና ድህነትን ቋሚ ወዳጆቹ አድርጐ መኖሩ አይቀርም። በእርግጥ ይህ ዓይነቱ ኑሮ ትርጉም የሌለውና አሳዛኝ መሆኑ የግድ ነው። እንዲህ ዓይነቱን አደጋ የሚያስቀረው ደግሞ ኃይልና ጉልበት ሳይሆን መተማመንንና ዝምድናን የሚያጠናክር፣ የግል ጥቅምና ግዴታን በእኩልነት ደረጃ ለመጠበቅ የሚያስችል ውይይትና ምክክር ማድረግ ነው። ይህንን ተግባር በቋሚነት የሚያስፈፅሙ ተቋማት ማኅበረሰቡ ውስጥ እንዲፈጠሩ ማድረግ የመፍትሄ አፈላለግ ሥራን ቀላልና ቀልጣፋ ያደርገዋል። እያንዳንዱ የማኅበረሰብ አባል ሊያበረክተው የሚችለውን አስተዋፅኦ በሥርዓት የተደራጀ እንዲሆን ያስችላል። የተደራጁ ሰዎች ተሳትፎ መፍጠር ሲባል እንደ አብዮታዊ ዴሞክራቶች ሰውን በመደብና በዘር እየከፋፈሉ አጥፊና ጠፊ ማድረግ ማለት ግን አይደለም።

አብዮታዊ ዴሞክራቶች የኢንዱስትሪ ማኅበረሰብ ልዩ ባሕሪይ የሆነውን ካፒታሊዝም በደመወዝ የሚተዳደረውን ወዛደር እንደሚፈጥርና ወዛደሩ ደግሞ በሙያ ማኅበሩ ተደራጅቶ የመደብ ጠላቱን ካፒታሊዝምን ታግሎ ከምድረ ገፅ እንደሚያጠፋው ያምናሉ። የኢንዱስትሪ ማኅበረሰብ ጉልበቱና እውቀቱን እየሸጠ የሚኖር ክፍል እንደሚፈጥር ትክክል ቢሆንም እነዚህ ሰዎች በሙያ ማኅበር የሚደራጁት አንዱን የሕብረተሰብ ክፍል ለማጥፋት ግን አይደለም። በሙያ ማኅበር የሚደራጁት በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ በሰዎች መካከል በሚኖር ግንኙ ነት የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታትና የበኩላቸውን ድርሻ እየተወጡ ግንኙነቱን ጤናማ ለማድረግ ነው። የሙያ ማኅበር የሚያቋቁሙትና በዚህም ዙሪያ የሚሰባሰቡት የተደራጀና ሥርዓት ያለው የችግር አፈታት አቅም ገንብተው ጥቅማቸው ጉዳት እንዳያጋጥመው

ለመጠበቅ ነው:: ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የሚደራጁበት ተቋም መፍጠራቸው ከሌሎች ጋር የመሥራቱን ግንኙነት ጤናማ ለማድረግ በሚያስፈልጉ ውይይቶችና ድርድሮች ሁሉ የተቀነባበረ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል ድርጅታዊ አቅም ስለሚያስገኝላቸው እንጂ ቅራኔ ለመፍጠር አይደለም:: ከዚህ ዓይነቱ የመደብ ቅራኔ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ገዥው ፓርቲ ሰዎችን በዘራቸው እያቧደነ ወደከፍተኛ ቅራኔና ግጭት የሚያመራ የፖለቲካ አቋም ማራመዱን አጥብቀን የምንቃወመውና የምንጠላውም ከዚሁ ጤናማ የሊበራሊዝም መርህ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ነው::

ከዚህ ወሠን አልፎ አጥፊና ጠፊ አስከ መሆን መድረስ የሊበራል ዴሞክራሲ መርህ አይደለም:: ችግሩን ለመፍታት ሲባል አንዱን ወገን እስከማጥፋት የሚደርስ የኃይል መንገድ ዘላቂ ውጤት አለማምጣቱ ብቻ ሳይሆን የማንንም ወገን ጥቅም የማያስጠብቅ በመሆኑ የሚመረጥ መንገድ አይደለም:: በጥቅምና በአመለካከት ልዩነት መኖሩ ምንግዜም ሊጠፋ የማይችል የሰዎች ባህርይ እንደመሆኑ ማድረግ የሚቻለው እየተወያዩና እየተደራደሩ ለማጥበብ መሞከር ብቻ ነው:: የጥቅምና የአመለካከት ልዩነቶችን በሀሣብ ትግል እያቻቻሉ መኖር እንጂ የአብዮታዊ ዴሞክራቶች በመደብ ትግል የመደብ ጠላትን ማስወገድ የሚለው የኃይል መንገድ ማቆሚያ የሌለው የጥፋት መንገድ ነው:: የሰው ልጅ በተፈጥሮ ማኅበራዊ ነው ሲባል በሰዎች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት ጨርሶ ሊወገድ የማይችል ነው ማለት ነው::

ይህንን የማይቀር ግንኙነት ሥርዓት ባለውና በተደራጀ መንገድ መደገፍ ከተቻለ ሰዎች ግዴታዎቻቸውን ለማሟላትና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የተሻለ አቅም ይፈጥርላቸዋል ማለት ነው:: ኅብረተሰብ የሚባለው ቃል የሰዎችን ብዙ ዓይነት የግንኙነት ገፅታ አቅፎ የያዘ በመሆኑ ለመረዳት ቀላል አይደለም:: የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ውስጥ በሚፈጥራቸው ግንኙነቶች ማግኘት የሚፈልጋቸውን ጥቅሞቹን ለማረጋገጥ በጊዜያዊነትም ሆነ በዘላቂነት የሚያስፈልጉትን ተቋማት ይፈጥራል:: በነዚህም ተቋማት ዙሪያ ኅብረተሰቡ ይተሳሰራል፣ ይደራጃል:: የሚተሳሰርባቸው መንገዶች ደግሞ በቅርፅም ሆነ በይዘት በጣም የተለያዩ፣ በቁጥርም የበዙ፣ የተቆላለፉና የተወሳሰቡ ናቸው:: ሕብረተሰብ ሲባል የሰዎች ትስስር በአጠቃላይ የሚገለጽበት ጽንሰ-ሃሣብ ነው:: ለምሣሌ ከማንኛውም የሰዎች መተሳሰሪያ ድርጅት ይበልጥ መሠረታዊ የሆነውን ቤተሰብን ብንወስድ የሰው ልጅ በቋሚነት ከሚያስፈልጉት የግንኙነት መንገዶች አንደኛው ነው:: በጉርብትና ምክንያት ሰዎች የሚፈጥሩት ግንኑነት አለ:: በኛ ሀገር ሁኔታ እድር፣ እቁብ፣ ጅጌ፣ ደቦ፣ ማኅበርና ሌሎችም የመሰባሰቢያና የመገናኛ መንገዶች አሉ:: የሕዝባዊ ማኅበራት፣ የሞያ ድርጅቶች፣ የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶችም እንደዚሁ ሌሎች የመተሳሰሪያ መንገዶች ናቸው::

በአጭሩ በራስና በሌሎች ፍላጐት መካከል፣ በግለሰብና በሕዝብ ፍላጐት መካከል ያለው ግንኘ -ነት ችግር እንደሚኖርበት የታወቀ ቢሆንም ችግሩ ግን መፍትሄ የማይገኝለት አይደለም:: ሰዎች የግልና የጋራ ፍላጐት በአንድነት እንዴት ሊኖራቸው ይችላል ብሎ መጠየቅ ተገቢ ቢሆንም ይህ ግን ሁልጊዜም በተግባር ሲፈጸም ማየት የተለመደ ነው:: በጠቅላላው የሰው ልጅ እንዴት ማኅበራዊ ወደመሆን እንደተሸጋገረ የሚነሳው ጥያቄ አርቲፊሻልና አንዳንዴም አላስፈላጊ ነው:: ባጭሩ ሰው ማኅበራዊ ወደመሆን የተሸጋገረው ሰው በመሆኑ ነውና::

## 1.2.4 የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ያለው ትርጉም

ቀደም ሲል ስለሊበራል ዴሞክራሲ ባነሳንበት ጊዜ ሊበራሊዝም እንደ ፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም በኮሙኒዝምና በወግ-አጥባቂነት መካከል እንደሚገኝ መግለፃችን ይታወሳል:: ይኸም ማለት በአንድ በኩል ኮሙኒዝም ከግራ ወገን ቆሞ የሚከተለውን አመፅና ነውጥ ወይም አብዮት አይደግፍም ለማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ወግ-አጥባቂነት ከቀኝ ወገን ቆሞ የሚያራምደውንና ሁሉም ነገር እንደነበር ይቀጥል፣ መነካት፣ መታደስ፣ መሻሻል፣ ማደግና መለወጥ የለበትም የሚለውን አስተሳሰብ አይቀበልም:: ሊበራሊዝም ለውጥና ተሃድሶ

ሁልጊዜም መኖር ይገባዋል ብሎ ያምናል፡፡ ይህ ደግሞ ከሰው ልጅ ፀባይና ፍላጐት ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ የሰው ልጅ ፍላጐት ሁልጊዜም አንድ ቦታ ላይ ተቸክሎ የሚቆይ ነገር አይደለም፡፡ መሠረታዊ ፍላጐቶቹን ማሟላት ራሱ በመጠን፣ በዓይነት፣ በጊዜ እየተለዋወጠ የሚሄድ እንጅ መጀመሪያውም መጨረሻውም አንድ ቦታ ላይ ተወስኖ የሚያልቅ ነገር አይደለም፡፡ በቀን አንድ ጊዜ የሚበላ ሠው ሁለት ጊዜ ለመብላት ይጥራል፡፡ ሁለት ጊዜ በቀን መብላት ከቻለ በኋላ በቀን ሶስት ጊዜ ለመብላት ጥረቱን ይቀጥላል፡፡ ከዚያም የምግቡን ዓይነት ወደማሻሻል ይዞራል፡፡ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚለብስ ሰው በዓመት ሁለት ጊዜ ለመልበስ ይፈልጋል፡፡ ይኸንን ለማሟላትም ይጥራል፡፡ ጥረቱም ከተሣካለት በዚህ ረክቶ አይቆምም፡፡ የልብሱን ዓይነትና ጥራት ማሣደግ ይፈልጋል ወዘተ እያለ ይቀጥላል፡፡ የአንዱ ፍላጐት መሟላት ሌላ አዲስ ፍላጐት ይቀሰቅሳል፡፡ የሰው ልጅ ፀባይና ፍላጐት እንደዚህ የሚያድግ፣ የሚሻሻልና የሚለወጥ ነው፡፡

የሰው ልጅ ፍላጐት ታዳጊና ተለዋዋጭ ነው ሲባል ቁሣዊውን ፍላጐቱን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ አስተሳሰቡ፣ ባሕሉ፣ የአኗኗር ዘይቤው ሁሉ ለዕድገት፣ ለለውጥና ለመሻሻል የተጋለጡ ናቸው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ በመነሣት ሊበራሊዝም ሁሉም ነገር እንደነበረ መቀጠል አለበት የሚለውን የወግ አጥባቂነት አስተሣሠብ አይደግፍም፡፡ በሁሉም መስክ ማደግ፣ መታደስ፣ መሻሻልና መለወጥ በሠው ልጅ ሕይዎት ውስጥ የማይቀር ግዴታ እንደሆነ ሊበራሊዝም ይቀበላል፡፡

ነገር ግን ዕድገት፣ መሻሻል፣ ተሃድሶና ለውጥ በአብዮት፣ በአመፅና በነውጥ መምጣት አለበት የሚለውን የኮሙኒስቶች መንገድ አይከተልም፡፡ በምትኩ የተጠና፣ በዕውቀትና በሠከነ አሠራር የሚካሄድ ለውጥ አደገኛ ጉዳት የማያስከትል መሆኑ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ፣ አስተማማኝና ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ አብዮት የሚባለው የነውጥ እንቅስቃሴ በዘመቻና በግዳጅ የታጀበ ነው፡፡ የሰውን ደካማ ስሜቶች በማነሳሳትና በችኮላ የሚካሄድ ግብታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች ሳይወዱ በግድ የሚሳተፉበት ስለሚሆን የግለሰቦችን ነፃነት የሚያጠፋ ነው፡፡ አመፁ በስሜታዊነት የተሞላ ስለሚሆን በግለሰቦች ነፃነት ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በአገር ላይ የሚያደርሰው ጥፋት በማንኛውም መንገድ ሊገመት የማይችል እጅግ አስከፊና አደገኛ ነው፡፡ ሀብትና ንብረት ማውደም ብቻ ሳይሆን ባሕልንም ያጠፋል፡፡ አብዮት የሰውን ሕይዎት በከንቱ የሚያጠፋና በሕይዎት ላይ ለሚያደርሰው ጥፋት አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ የማይቻልበት ነው፡፡ ይኸንን በራሣችን አገር ያየነውና የምናውቀው ነው፡፡ በየትም አገር የተካሄዱ አብዮቶች ያስገኙት ውጤት ካደረሱት ጥፋት ጋር ፈፅሞ ለንጽጽርም የሚቀርብ አይደለም፡፡ የጥፋቱ መዘዝ ከትውልድ ትውልድ እስከመሸጋገር የሚዘልቅ ነው፡፡

ሊበራሊዝም ከግራውም ከቀኙም መሃል ያለውን ስፍራ በሚይዝበት ጊዜ ከሁለቱም አስተሳሰቦች ለሰው ልጅ አደገኛና አጥፊ የሆኑትን በማስወገድ ከግራና ከቀኝ ጽንፈኝነት በተለየ ሁኔታ ለማመዛዘን፣ ልዩነቶችን ለማቻቻልና አብረው የሚኖሩበትን ዕድል ለመፍጠር የሚያስችል ተገቢ ስፍራ ነው፡፡ ለዚህ አቋሙ መሠረት አድርጐ የሚወስዳቸውና ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው እሴቶች ግለሰባዊነት፣ በበቂ ምክንያት መመራት፣ ነፃነት፣ ወንድማማችነት፣ እኩልነት፣ ፍትሃዊነትና መቻቻል ናቸው፡፡ ሊበራሊዝም በትምህርት፣ በሀብት፣ በፆታ፣ በቀለም፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በአመለካከት ወዘተ. ልዩነት ያላቸውን ግለሰቦች ነፃነት፣ እኩልነትና ወንንድማማችነት ጠብቆ ለማኖር የሚያስችል፣ ፍትሃዊነትና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ በዜጐች ፈቃድና ስምምነት የተዘጋጀ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትና በዚሁ ላይ የሚመሠረት ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንዲኖር ይደግፋል፡፡

በሊበራሊዝም አመለካከት አንድ መንግሥት ዴሞክራሲያዊና ሕጋዊ የሚባለው የሥልጣን ምንጩ ሕዝብ ሲሆንና በሕዝብ ፈቃድ ሥልጣኑን እንዲለቅ በተጠየቀ ጊዜ ሳያንገራግር ለባለቤቱ የሚያስረክብ ሲሆን ነው ብሎ ያምናል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ መንግሥት ደግሞ በምንም ዓይነት የግለሠብ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም የሚባልና ሁሉንም ነገር

ዳር ላይ ቆሞ ከመመልከት የዘለለ ኃላፊነት እንዳይወስድ ጥብቅ ክልከላ የሚደረግበት ሊሆን አይገባውም ብሎ ያምናል። በሊበራሊዝም መነሻ ወቅት ከእርሱ ቀደም ሲል በነበሩ አስተሳሰቦች በመማረክና የተፈጥሮ ነፃነት፣ የብዙሃን ተጠቃሚነትና ሌሴፌር ተከታዮች የሚያራምዱትን መስመር በማቀንቀን የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት የማያስፈልግና አደገኛ ነው በሚል አጥብቆ ይቃወም ነበር።

ይሁን እንጂ የእያንዳንዱ ግለሰብ ጥፋት ሳይሆኑ የሰዎች ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ግንኙነቶች የሚያስከትሏቸውና ከግለሰቦች ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ችግሮች ሲያጋጥሙ ግለሰቦች ከራሣቸው ነፃነት ቆርሰው በፍቃዳቸው ውክልና የሰጡት መንግሥት እነዚህን ችግሮች በመፍታት ረገድ ሠፊ አስተዋፅኦ ማድረግ ይገባዋል የሚለውን አቋም የዘመናችን ሊበራሊዝም በሚገባ ተቀብሎታል። ይኸም ሲባል መንግሥት በግለሰቦች የዕለት ከዕለት ሕይወት ውስጥ እየገባ ግለሰቦች ለራሣቸው ደህንነት ምንም ዓይነት ኃላፊነት እንደማይሰማቸው መቁጠርና ስብዕናቸውን ዝቅ የሚያደርግ ሥራ መሥራት አለበት ማለት አይደለም። የዘመናችን ሊበራለዝም አስተሳሰብ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ ከግለሰቦች አቅም ውጭ የሚፈጠሩ እንደ ሥራ አጥነት፣ የዋጋ ግሽበት፣ ድህነትና የመሳሰሉ ችግሮች ሲከሠቱ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ መንግሥት ትልቅ ሚና መጫዎት ይችላል፣ ይገባልም የሚል አቋም አለው። የግለሰቦችን ነፃነት በማይጐዳና የእነሱንም ፈቃድና ስምምነት በሚያረጋግጥ መንገድ እስከተፈፀመ ድረሰ ተቀባይነት ያለው ነው። የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ተቀባይነት የማይኖረው በዘፈቀደና በኃይል የሚጫን በሚሆንበት ጊዜ ነው።

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲህ ዓይነቱ የዘፈቀደና የኃይል አሠራር እንዲኖር የማይጠበቅ ቢሆንም ስህተት ሊሠራ የሚችልበት አጋጣሚ ጨርሶ አይፈጠርም ማለት ግን አይቻልም። ለምሣሌ በመንግሥት በኩል ለዜጐች ይጠቅማል ተብሎ የሚታሠብ፣ ነገር ግን የዜጐች ስምምነትና ፈቃድ በሌለበት ሁኔታ አንድ ፖሊሲ ሥራ ላይ ይዋል ቢባል የፈለገውን ያህል ጥቅም እንደሚኖረው ቢገመትም ፈቃዳቸውን ባልሰጡት ዜጐች ዘንድ እንደጥፋት መቆጠሩ የማይቀር ነው። እንደዚህ ዓይነቱን ስህተት ለማረምና ለመቆጣጠር የሚቻልበትን ዕድል የዴሞክራሲ ሥርዓት በሠፊው የሚፈቅድ እንደመሆኑ ዜጐች በሰላማዊ ሠልፍ፣ በሥራ ማቆም አድማ፣ ፔቲሽን በመላክና በመሳሰሉት ዘዴዎች ተጠቅመው የማይፈልጉት ፖሊሲ እንዲቀየር መጠየቅና ተፅዕኖ ማድረግ ይችላሉ። በምርጫ ጊዜ ደግሞ ስምምነታቸውንና ፈቃዳቸውን ሳያገኝ የማያምኑበትን ፖሊሲ የሚጭንባቸውን መንግሥት ድምፃቸውን ይነፍጉታል። ሌላ የሚስማማቸውን መንግሥት በምርጫ ይተካሉ። መንግሥትም እንዲህ ዓይነት ቁጥጥር እንደሚደረግበት ስለሚያውቅ የዜጐቹን ፈቃድና ሰምምነት ሳያገኝ የሚደረግ ጫና ከሚያስከትልበት መዘዝ ለመጠንቀቅ የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል።

የመንግሥት ተሣትፎ ዳር ድንበር በሕግ የሚወሠን መሆኑ መሠረታዊ ጉዳይ ቢሆንም ትክክለኛውን የተሣትፎ ደረጃ ማስመር የሚቻለው ግን በዜጐች ስምምነትና ፈቃድ ነው። ብዙ ጊዜ መንግሥት እስከምን ደረጃ ድረስ እጁን ሊያስገባ ይችላል? እየተባለ ለሚነሣው ጥያቄ ቅልብጭ ያለ መልስ መስጠት ቀላል ባይሆንም በሕግ እስከተፈቀደለት ድረስ ወይንም የዜጐች ፈቃድና ስምምነት እስከተገኘ ድረስ ብሎ መመለስ ይቻላል።ከዚህ ውጭ ለሕዝብ ጥቅም፣ ለአገር ጥቅም፣ ለሰላም፣ ለልማት፣ ለዴሞክራሲ በሚል ሽፋን የዜጐችን ነፃነት መግፈፍ በኮሚኒስቶችና በፋሽስቶች የሚፈፀም እንጂ የዴሞክራቶች ባሕሪይ አይደለም። ዜጐች ያልፈቀዱትንና ያልተስማሙበትን ማንኛውም ጉዳይ በፖሊሲ መልክ በዜጐች ላይ በግድ መጫን የግለሠብ ነፃነትን የሚያሣጣ የመጀመሪያው ወንጀል ሲሆን ተቃውሞና ቅሬታ ሲያሰሙ በኃይል ማፈን ደግሞ ሌላው ከባድ ወንጀል ነው። ኮሚኒስቶች ለዚህ ጥፋታቸው የሚያቀርቡት ማስተባበያ ለሕዝብ ጥቅም ሲሉ የፈፀሙት መሆኑን ነው። ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የግለሰብን ነፃነት ማፈንና ማጥፋት ከተቻለ መቸም ቢሆን የሚረጋገጥ የሕዝብ ጥቅም ፈጽሞ ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም ነፃነታቸውን የሚያጡት ግለሰቦች የሚገኙት በዚሁ ይጠቀማል በሚባለው ሕዝብ መካከል ነው። አንዱን ለይቶ መጉዳትና አንዱን ለይቶ መጥቀም የባሠ ፍትሕ አልባነትና ጥፋት ስለሚሆን የአንድን ግለሰብ ነፃነት አጥፍቶ የሕዝብ

ጥቅም ማሟላት የሚባል ነገር የለም። በሕዝብ ውስጥ ያለው የእያንዳንዱ ግለሰብ ነፃነት ሲጠበቅ ነው የሕዝብ ጥቅም በተሟላ መንገድ ሊጠበቅ የሚችለው። ስለዚህ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ተፈላጊም ተገቢም የሚሆነው የዜጐችን ፈቃድና ስምምነት መሠረት ሲያደርግና በሕግ የበላይነት ሲመራ ብቻ ነው። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ጠቃሚ የሊብራል ዴሞክራሲ ዋና ዋና እሴቶች ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግ ጠቃሚ ነው ብሎ ኤዴፓ ያምናል።

## 1.3 ሶሻል ዴሞክራሲ

ከዜጐች ፍላጐትና ቁጥጥር ውጭ የሆኑና በኢኮኖሚና ማኀበራዊ እንቅስቃሴ ሂደት የሚከሠቱ ችግሮችን በማቃለሉ ሥራ የመንግሥት ተሣትፎ መኖር አስፈላጊ ነው የሚለው አመለካከት የመንግሥት ሚና በጣም የተገደበ መሆን አለበት ከሚለው የቀድሞው የሊብራሊዝም አቋም በብዙ ርቀት ወደፊት የገሠገሠ ነው። ይህ አመለካከት ራሱ ሊብራሊዝም ለመታደስ፣ ለማደግና ለመለወጥ ያለውን ምቹነት የሚያረጋግጥ ነው። ሊብራሊዝም በሠው ልጅ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚከሠቱ አዳዲስ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ እየተከታተለ፣ ጥቅምና ጉዳታቸውን እያመዛዘነ የሚያከብራቸውን መንግሥታዊ መርሆዎችና እሴቶች ይበልጥ በሚያዳብርና በሚያበለጽግ መንገድ ራሱን ከሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም ይጥራል። እንደዚህ ራስን ከተለወጡ ሁኔታዎች አንፃር እየገመገሙ የማስተካከል ጥረት የሚደረገው ሊበራሊዝም የቆመባቸውን መሠረቶችና ምሰሶዎች በማፈራረስ አይደለም። እነዚህኑ መሠረቶች ይበልጥ ጠንካራ እንዲሆኑ በሚያስችል አኳኋን ነው።

ከ19ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ ጀምሮ የቀድሞው የሊበራል አስተሳሰብ ወደ ዘመናዊው ሊበራሊዝም ተቀይሯል። ይኸውም ስድ ካፒታልዝም ወይንም ቁጥጥርና ማስተካከያዎች የማይደረጉበት ካፒታሊዝም ፍትሃዊነቱ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ አይቀርም ከሚለው ሥጋት በመነሣት ጥልቅ ጥናትና ግምገማ ከተደረገ በኋላ የተደረሰበት ግንዛቤ ነው። የመንግሥት ተሳትፎ በተገደበበት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ የሚከሰቱ ተጨባጭ ችግሮች የካፒታዝምን ሥርዓት ዕድገት ሠንገው በያዙበትና በዚህ ሥርዓት ውስጥ የሚኖሩ ዜጐች ነፃነታቸውን ጠብቆ ለመኖር በየግላቸው ምንም ለማድረግ ባልቻሉበት ጊዜ የሥልጣን ውክልና የሰጡትና መንግሥት የሚባለው የተደራጀ ተቋም እጁን እንዲያስገባ፣ ተሣትፎውም እንዲጨምር አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ።

ሥራ አጥነት፣ የዋጋ ግሽበት፣ ድህነትና የመሣሠሉት ችግሮች በዜጐች ስህተት ሣይሆን የነፃ ገበያው ሂደት የሚያመጣቸው ከእያንዳንዱ ግለሰብ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ክስተቶች መሆናቸው ታወቀ። እነዚህን ለመቆጣጠር የሚያስችል የማክሮ-ኢኮኖሚ ፖሊሲ እያወጡ ችግሮችን መፍታት የመንግሥት ተግባር መሆኑ በሚገባ ጉልህ እየሆነ መጣ። በተለይም እ.ኤ.አ ከ1920ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የተከሠተው የኤኮኖሚ ድቀት፤ ሥራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነትን፣ ድህነትና የሕይዎት ዋስትና ማጣትን በማስከተሉ በዚህ ሥርዓት ውስጥ የሚኖሩ ዜጐች ነፃነት ጥያቄ ውስጥ ወደቀ። ሥርዓቱን ራሱን ከባድ አደጋ ውስጥ የሚያስገባ ማኀበራዊ ቀውስ ተፈጠረ። የተከሰተውን ችግር በመፍታት የዜጐቹን ነፃነት የማስከበርና ሥርዓቱን ከገባበት ቀውስ የማውጣት ከባድ ኃላፊነት ከመንግሥት በኩል እንደሚጠበቅ የሚያጠራጥር ነገር አልነበረም። በመሆኑም የዋጋ ማረጋጊያ፣ የሥራ አጥነትን ችግር መፍቻ፣ የኑሮ ውድነትና የድህነት መቀነሻ መንገዶች በመንግሥት ተቀይሠው ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደረገ። የመንግሥት ጥረትም የተሣካ በመሆኑ ቀውሱን መቀልበስና ሥርዓቱንም ከገባበት ድቀት በማውጣት እንዲያገግም ማድረግ ተቻለ። ዜጐችም ማህበራዊ ቀውሱ ከፈጠረባቸው አሠቃቂ ችግሮች መውጣት በመቻላቸው የመንግሥት ተሣትፎ የግል ነፃነታቸውን በሚያጠናክር መንገድ እስከሆነ ድረስ አስፈላጊነቱ እንደማያከራክር አመኑበት። በዚህ መንገድ ከተጨባጭ ተግባር በተቀሠመ ልምድና ከዜጐች በተገኘ ስምምነት ቁጥጥር የማይደረግበት ካፒታሊዝም ትርፉ አዲስ ዓይነት ቀውስ መፍጠር መሆኑንና ይህንን

*ለመከላከል ሲባል በኢኮኖሚ አመራር የመንግሥት ተሣትፎ አስፈላጊነትን እንደመርህ የተቀበለው ዘመናዊው ሊብራሊዝም ከሶሻል ዴሞክራሲ ጋር የሚያመሣስለውን ባሕሪይ እያሣደገ መጣ:: በዚህም የተነሣ ዘመናዊው ሊብራሊዝም አንዳንዴ ማኅበራዊ ሊብራሊዝም ወይም የማኅበራዊ ደህንነት ሊብራሊዝም እስከመባል ደረሰ::*

*በሶሻል ዴሞክራሲና በዘመናዊው ሊብራሊዝም መካከል ያለው መመሣሠል የሚመሠረተው ሁለቱም በግለሰብ ነፃነት፣ በእኩልነትና በሕግ የበላይነት ላይ የቆሙ በመሆናቸው ነው:: የግለሰብ ነፃነትና የሕግ የበላይነት የሚሉት በራሣቸው ለመረዳት የማያስቸግሩ በመሆናቸውና በዚህ ጽሑፍ የተለያዩ ርዕሶች ሥር እየተደጋገሙ የተብራሩ ሲሆን እኩልነት የሚለውን በመጠኑ ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: እኩልነት ሲባል የአንዱ ግለሰብ ነፃነትና መብት ከሌላው አያንስም ወይም አይበልጥም ለማለት ነው:: የሁሉም ግለሰብ ነፃነት እኩል የሞራል ዋጋ የሚሰጠው በመሆኑ እኩል ዕድል ማግኘት አለባቸው ማለት ነው:: እኩልነት ሲባል ሀብትንም ሆነ ድህነትንም እኩል ማዳረስ ማለት ሳይሆን ሠርቶ ድህነትን ለማሸነፍና ሀብት ለማግኘት የሚያስችል እኩል እድል መስጠት ማለት ነው:: እያንዳንዱ ግለሰብ በችሎታውና ለመሥራት ባለው ፍላጐት አንፃር ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘት አለበት ማለት ነው:: እኩልነት በችሎታና በሥራ ተጠቃሚ የሚያደርግ ዕድል በእኩል ደረጃ የማግኘት መብት ማለት ነው:: ከዚህ አንጻር ሶሻል ዴሞክራሲና ዘመናዊ ሊብራሊዝም ከፍተኛ ቁርኝትና ተመሣሣይነት አላቸው:: ሁለቱም ከቀረጥ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በማኅበራዊ ዋስትና መልክ በድህነት ኑሮ ውስጥ ለገቡ ዜጐች መልሶ በማከፋፈል ማኅበራዊ ፍትሕን ለማስፈን ጥረት ያደርጋሉ::*

*ሶሻል ዴሞክራሲ ከሊብራሊዝም የሚለየው በፖለቲካ የሚቆምበት ሥፍራ ሊብራሊዝም ከሚገኝበት ማዕከል ወደግራ ያዘነበለ መሆኑና በኤኮኖሚና በማኅበራዊ አቋሙ ደግሞ በከፍተኛ ዕቅድ የሚመራና በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚገኝ የሀብት ባለቤትነት በነፃ ገበያ ከሚመራ ካፒታሊዝም ጋር ተቀይጦ የሚገኝበት፣ ከፍተኛ ቀረጥ ሰብሳቢና የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓት መልሶ ለድሃው ኅብረተሰብ የማከፋፈልን አሠራር በጥብቅ የሚከተል መሆኑ ነው:: ከኢንዱስትሪና ከንግድ ከፍተኛና ተመጣጣኝ ቀረጥ ሰብስቦ መልሶ በማኅበራዊ ደህንነት ፕሮግራም በማከፋፈል ፍትሓዊነትን የማረጋገጥ ጥያቄ ተደርጐ ነው የሚወሰደው:: ይህ ፍትሓዊነት የሚረጋገጠው ሀብት ካላቸው የተሰበሰበውን ቀረጥ ለድሃው ሕዝብ ምግብ፣ ሕክምና፣ ትምህርት፣ መጠለያ፣ ወዘተ... የመሳሰሉትን አገልግሎቶች በማኅበራዊ ደህንነት ፕሮግርም አማካይነት ማቅረብ ማለት ነው::*

*በስዊዲን፣ በዴንማርክ፣ በኖርዌይ፣ በጀርመን፣ የሚገኙ ፓርቲዎች፤ የፈረንሣዩን ሶሻሊስት ፓርቲና የእንግሊዙን ሌበር ፓርቲ ጨምሮ የዚህን ዓይነት አቅጣጫ የሚከተሉ በመሆናቸው በጥቅሉ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲዎች ተብለው ነው የሚታወቁት:: በተለይ ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ማብቂያ እ.ኤ.አ እስከ 1990ዎቹ ድረስ በስዊድን ሕገ-መንግሥት ውስጥ ሶሻል ዴሞክራሲ በአገሪቱ የተዘረጋው የመንግሥት ሥርዓት አጠቃላይ ምንነት መግለጫ ሆኖ ሠፍሮ እንደነበር ይታወሳል:: በጀርመን ሕገ-መንግሥትም እንደዚሁ ሠፍሯል:: ሶሻል ዴሞክራሲ ሌላ ምንም ማለት ሳይሆን ሊብራል ዴሞክሲና የመንግሥት ማኅበራዊ ደህንነት ሥራን የሚጠብቅ ከፊል ሕጋዊ መብት አንድ ላይ የተቀናጁበት የፖለቲካ ንድፈ-ሃሳብ ማለት ነው:: ይኸም ማለት የግለሰቦችን ነፃነት ይበልጥ ለማስፋት እንዲቻል በዜጐች ተቀባይነት ያገኘና በሕግ የሚደገፍ የማኅበራዊ ደህንነት ተግባር በመንግሥት መሪነትና አስተባባሪነት የሚካሄድበት ሥርዓት ማለት ነው::*

*እንዲህ ዓይነት የማኅበራዊ ደህንነት ተግባር በሠፊው እንዲካሄድ በማድረግ ዜጐች የጡረታ፣ የአደጋ ጊዜ ክፍያ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የወሊድ፣ የሕጻናት አበል፣ የአካል ጉዳተኞች፣የሥራ አጥና የሌላም ማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር ለመከተል እንዲቻል የሀገር ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ ማደግ ይኖርበታል:: ምርት ማምረትና ሀብት ማፍራት የሚችሉ የንግድ፣ የኢንዱስትሪ፣ የእርሻ እንቅስሴዎች በሠፊው መከናወን አለባቸው:: የአገልግሎት መስጫ ተቋሞች በሠፊው መዘርጋት አለባቸው::*

እንደዚህ ዓይነት የማምረትና አገልግሎት የመስጠት እንቅስቃሴ ሲኖር ዜጐች የሥራ ዕድል ይከፈትላቸዋል። የሥራ ዕድሉን ካገኙ ደግሞ ለራሣቸው ማኅበራዊ ደህንነት በሚጠቅም ልዩ ልዩ የኢንሹራንስ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍና በፈቃዳኝነት ላይ የተመሠረተ የተወሠነ የክፍያ አስተዋፅዖ ለማድረግ ያስችላቸዋል። ለመንግሥት የተለያዩ ኮርፖሬሽኖችና ማኅበራዊ ደህንነት ፕሮግራሞች መደገፊያ የሚሆን ሀብት ማፍራት ይችላሉ። መንግሥት ደግሞ ከቀረጥና ከተለያዩ የማኅበራዊ ዋስትና መዋጮዎች የሚገኘውን ገንዘብ እያቀናጀ ዝቅተኛ ኑሮ ለሚኖሩ፣ የመሥራት አቅም ለሌላቸው፣ ሥራ ላጡና ለመሳሰሉት ዜጐች የሕክምና፣ የትምህርት፣ የመኖሪያ ቤት፣ ወዘተ. ወጪዎችን በማገዝ የማኅበራዊ ደህንነት ድጋፍ ይሰጣል። በሌላ አገላለፅ ከቀረጥ ከፋዩ የሚሰበሰበውንና ዜጐች እንዳቅማቸው የሚያዋጡትን የልዩ ልዩ ኢንሹራንስ መዋጮ ለተቸገሩት መልሶ በማከፋፈል ማኅበራዊ ፍትህ ለማስፈን ጥረት ይደረጋል። ወይንም የዜጐችን እኩልነት የሚያረጋግጥና ነፃነታቸውንም ይበልጥ የሚያሰፋ የማኅበራዊ ደህንነት እንቅስቃሴ ይካሄዳል። እዚህ ላይ በደንብ መታወቅ የሚኖርበት ማኅበራዊ ደህንነት ፕሮግራምና ሀብት መልሶ የማዳረስ ሥራ በዋናነት በመንግሥት የሚከናወን ቢሆንም እኩልነትንና ማኅበራዊ ፍትሕን የማረጋገጥ ጉዳይ እንደመሆኑ ዜጐችን በጠቅላላ የሚመለከት፣ የእነሱም ፈቃድና ተሣትፎ ያለበት የጋራ ተግባር መሆኑ ነው። በዚህም የተነሣ ቀረጥ የመክፈል ግዴታ መኖርና የማኅበራዊ ደህንነት ፕሮግራም ተሣታፊ መሆን በዜጐች ተቀባይነት ያገኘ አሠራር እንጂ በመንግሥት የሚጫን ነገር አይደለም። ከዚህ በላይ ለመዘርዘር የተሞከሩትን የሶሻል ዴሞክራሲ ጠቃሚ አስተሳሰቦች ከወቅቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አጋር አጣጥሞ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ብሎ ኢዴፓ ያምናል።

## 1.4 የስምምነት ወይም የድርድር ዴሞክራሲ (Consensus Democracy)

በዴሞክራሲ አጠቃላይ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ እንደየሀገሩ ልዩ ሁኔታ ተስማሚ የዴሞክራሲ አማራጮችን መከተል የተለመደ ነው። የዴሞክራሲን መሰረታዊ ትርጉምና መርሆዎች የሚያሟላ ነገር ግን ከአንድ የተወሰነ ሕብረተሰብ ማህበራዊ አደረጃጀትና ልዩ ባህርይ አንፃር የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አማራጭ መከተል በቲዎሪም በተግባርም የተደገፈ ነው። በአለማችን ውስጥ ሰዎች ካላቸው ርዕዮተዓለማዊ እምነት በመነሳት ወግ አጥባቂ የሆነ መስመር፣ ኮሚኒስታዊ የሆነ መስመር፣ ዴሞክራሲያዊ የሆነ መስመር ወዘተ. ሊያራምዱ ይችላሉ። የዴሞክራሲን መስመር በሚያራምዱት መካከል እንኳ ሳይቀር በዚሁ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው የተለያዩ አማራጮችን ሊያራምዱ ይችላሉ። ሊበራል ዴሞክራሲ፣ ሶሻል ዴሞክራሲ፣ የስምምነት ዴሞክራሲ ወዘተ. በዴሞክራሲ ማዕቀፍ ውስጥ ሊቀርቡ ከሚችሉ ልዩ ልዩ አማራጮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። በዴሞክራሲ ማዕቀፍ ውስጥ ሊቀርቡ ከማይችሉት መካከል አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንዱ ነው። ይህ አማራጭ ሰልፉ ከዴሞክራሲ ጋር ሳይሆን ከኮሚኒዝም ጋር ነው።

በዚህም መሰረት ኢዴፓ የዴሞክራሲን አጠቃላይ ትርጉምና መርህ በመጠበቅ ለስምምነት ወይም ለድርድር ዴሞክራሲ (Consensus or Bargaining Democracy) ልዩ ትኩረትና ግምት መስጠት ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል።

የስምምነት ወይም የድርድር ዴሞክራሲ ማለት በመንግስት አደረጃጀትና አሰራር ውስጥ ሰፊ የዜጎች ተሳትፎ እንዲኖር የሚያደርግ፣ የመንግስት ስልጣንን ለማጋራት፣ ለማከፋፈልና ለመወሰን የሚያስችል፣ የተለያየ ባህል፣ የተለያየ ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ አመለካት ወዘተ. ያለው ሕብረተሰብ በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችለውን የመስጠትና የመቀበል፣ የመቻቻልና የድርድር መርህ የሚከተል አስተሳሰብ ነው። በዚህም ምክንያት የስምምነት ዴሞክራሲ ሌላው መጠሪያ የድርድር ዴሞክራሲ (Bargaining Democracy) ነው።

ይህ የዴሞክራሲ አማራጭ ለኢትዮጵያ ልዩ ሁኔታ የሚስማማ ባህሪ አለው ከምንልባቸው መሰረታዊ ምክንያቶች መካከል ቢያንስ ዋነኛ የሆኑትን ሁለቱን ጉዳዮች ማንሳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የሀገራችን ሕብረ-ብሔራዊነት ነው፡፡ ይህም ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ባህሎች፣ ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ አመለካከቶች አሉ፡፡ በዚህም የተነሳ የሀገራችን ሕዝብ የተደበላለቀ ባህልና እምነት ያለው ፕሉራል ሕብረተሰብ እንደመሆኑ በአንድ በኩል እያንዳንዱ የሕብረተሰብ ክፍል የራሱን ባህል፣ ቋንቋ፣ ማንነት፣ ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ እምነት ወዘተ. መጠበቅ አለበት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ልዩነቶቹን በሚያቻችል የጋራ ጥቅም ላይ ተመስርቶ በሰላምና በእኩልነት የሚኖርበትን ጠንካራ አንድነት መፍጠር አለበት፡፡ ይህንን እድል የሚያስገኝለት የተሻለ የዴሞክራሲ አማራጭ ደግሞ የስምምነት ወይም የድርድር ዴሞክራሲ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በአለማችን ውስጥ ካሉት የዴሞክራሲ ሞዴሎች መካከል በንድፈ ሀሳብም ሆነ በተጨባጭ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተሻለ ተቀባይነትና ውጠ ͅታማነት ያለው የስምምነት ዴሞክራሲ ሞዴል በመሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ከዴሞክራሲ አጠቃላይ መርህ ሳይወጡ እንደየሀገሩ ልዩ ሁኔታና እንደሕዝቡ ማህበራዊ አወቃቀር ተስማሚ አማራጭ መከተል አዲስ ነገር አይደለም፡፡ በመሆኑም በአለማችን ውስጥ በርካታ ስምና አቀራረብ ያላቸው ልዩ ልዩ የዴሞክራሲ አማራጮች እንዳሉ ቢታወቅም ሁሉም በሁለት የዴሞክራሲ ምድቦች (Categories) ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ አንደኛው ምድብ የብዙሃን ዴሞክራሲ ሞዴል (Consensus Model of Democracy) የሚባለው ነው፡፡

የብዙሃንና የስምምነት ዴሞክራሲ ሞዴሎች ንጽጽር የሚነሳው ዴሞክራሲ ማለት በሕዝብና ለሕዝብ የተቋቋመ መንግስት ነው ከሚለው የዴሞክራሲ መሰረታዊ ትርጓሜ ነው፡፡ ይኸንን የዴሞክራሲ ትርጉም ተከትሎ ለሚነሳው ጥያቄ በሚሰጡት ምላሽ የተነሳ በብዙሃንና በስምምነት ዴሞክራሲ ሞዴሎች መካከል ልዩነት አለ፡፡ ዴሞክራሲ በሕዝብና ለሕዝብ የተቋቋመ መንግስት ነው ከተባለ በሕዝቡ ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶችና ምርጫዎች በሚኖሩበትና ስምምነት መፍጠር ሳይቻል በሚቀርበት ጊዜ መንግስት የሚያደርገው ምንድን ነው? ወይም ለየትኛው ሕዝብ ፍላጎት ድጋፍና ምላሽ ሊሰጥ ይችላል? ለሚለው አሻሚ ጥያቄ የብዙሃን ሞዴልና የስምምነት ሞዴል አንድ አይነት መፍትሔ የላቸውም፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ጥያቄ የብዙሃን ዴሞክራሲ ሞዴል የሚሰጠው መልስ «ለአብዛኛው ሕዝብ» የሚል ሲሆን የስምምነት ዴሞክራሲ ደግሞ «ከአብዛኛው ሕዝብ የበለጠ መጠን ላለው ሕዝብ» የሚል ነው፡፡ የብዙሃን አስተዳደር ከአናሳዎች አስተዳደር የተሻለ መሆኑን በሚመለከት በሁለቱም የዴሞክራሲ ሞዴሎች መካከል ተመሳሳይ አቋም ቢኖርም የስምምነት ዴሞክራሲ ሞዴል የብዙሃን ድምጽ በሚለው ጠባብ አሰራር ራሱን ገድቦ መቆም አይፈልግም፡፡ የዚህን ብዙሃን የሚለውን መጠን በተቻለ መንገድ ከፍ ለማድረግ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም የስምምነት ዴሞክራሲ ሕጎችና ተግባሮች ዋነኛ አላማ በመንግስት ውስጥ በተለምዶ የብዙሃን ተሳትፎ ከሚለው መጠን ከፍ ያለና በጣም ሰፊ የሆነ የዜጎች ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ይህንን መፍጠር የሚቻለው ደግሞ መንግስት ሊከተላቸው በሚገቡ ፖሊሲዎች ላይ ሰፊ የሆነ የዜጎች ስምምነትና መግባባት ሲኖር ነው፡፡

በብዙሃን ሞዴል የፖለቲካ ሥልጣን የአብዛኛውን ሕዝብ ድጋፍ ብቻ ባገኙት ወገኖች እጅ የተከማቸ ነው፡፡ እንደውም ብዙውን ጊዜ በብዙሃን ድጋፍ ምትክ የአብላጫ ድምፅ (Majority Vote) ብቻ ባላቸው እጅ የተሰባሰበ ነው፡፡ በሀገራችን አሁን በስራ ላይ ያለው ሕገመንግስትም የፖለቲካ ሥልጣን እንዲያዝ የሚያስችለው የምርጫ ስርዓት የአብላጫ ድምፅ ስርዓት እንዲሆን ደንግጓል፡፡ በስምምነት ሞዴል የፖለቲካ ስልጣን የሚያዝበት መንገድ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ በዚህ ሞዴል ስልጣን የብዙሃን ድጋፍ ብቻ ባገኙ ወገኖች እጅ እንዲከማች

አይፈቀድም። በዚህ ፋንታ በተለያዩ መንገዶች ስልጣንን ለማጋራት፣ ለማከፋፈልና ለመወሰን ብርቱ ጥረት ይደረጋል። በሁለቱ ሞዴሎች መካከል ያለው ሌላ ልዩነት የብዙሃን ሞዴል በእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክርና በተቀናቃኝነት መንፈስ የተሞላ ከመሆኑም በላይ በባህርይው አግላይ ነው። የስምምነት ሞዴል ደግሞ በመቻቻል፣ በድርድር፣ በመስጠትና በመቀበል መርህ የሚመራ እንደመሆኑ በባህርይው አቃፊና አሰባሳቢ ነው።

የስምምነት ዴሞክራሲ የአብዛኛው ሕዝብ ድጋፍ በመገኘቱ ረክቶ የማይቆምና በተቻለ መንገድ የአብዛኛው ሕዝብ ድጋፍ የሚለው መጠኑ ከፍ ያለ እንዲሆን ወይም በሌላ አገላለፅ ከሞላ ጎደል የሁሉም ዜጎች ስምምነት እንዲገኝ ለማድረግ የሚያስችል የውይይትና የድርድር ዘዴ ስለሚጠቀም የድርድር ዴሞክራሲ እስከመባል ደርሷል። ሌላው ልዩነታቸው በብዙሃን ሞዴል እይታ ዴሞክራሲ በመንግስት ስልጣን የሚፈራረቁ ፓርቲዎች የሚሳተፉበት ባለሁለት ፓርቲ ስርዓት እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑ ነው። ዴሞክራሲን በአብዛኛው ሁለት ተቃራኒ ፓርቲዎች ብቻ አድራጊ ፈጣሪነት እንዲያዝ በማድረግ ተቀባይነት የሌለው ነው። በስምምነት ሞዴል አመለካከት ዴሞክራሲ በአብዛኛው በድርድርና በስምምነት መርህ የሚመሩ ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ ፓርቲዎች በሚመሰርቱት የጥምር መንግስት ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉበት የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ተደርጎ ነው የሚታየው። በዚህ ሞዴል እምነት የመንግስት ለውጥ ማለት ብዙውን ጊዜ አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ብቻውን ወደ መንግስት ስልጣን የሚወጣበት ሁኔታ ሳይሆን በመንግስት ስልጣን ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ፓርቲዎች ጥንቅር በከፊል የሚኖርበት ማለት ነው። ስለዴሞክራሲ የብዙሃን ሞዴል ያለው ትርጓሜ ዴሞክራሲ ማለት በአብዛኛው ሕዝብ ድጋፍ የተመሰረተ መንግስት ማለት ነው የሚል እንደመሆኑ በዚህ አስተሳሰብ መሰረት መግዛት ያለባቸው ብዙሃኖቹ ብቻ ናቸው። የአናሳዎቹ ድርሻ ግን ተቃውሞ በማሰማት ብቻ የተወሰነ ነው። ይህ አመለካከት በስምምነት ዴሞክራሲ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም አሸናፊ ፓርቲዎች ተሸናፊዎቹን እንዲያገሉና የመንግስት ፖሊሲዎችን በመወሰን ረገድ አንድም ተሳትፎ እንዳያደርጉ በመከልከል ሁሉንም መንግስታዊ ውሳኔዎች ብቻቸውን እንዲወስኑ ስለሚያደርግ ነው። ለዚህ አይነቱ ከባድ ጉድለት የብዙሃን ሞዴል የሚያቀርበው መከራከሪያ ዛሬ አናሳ የሆነ አግራጭ ተቃዋሚ ፓርቲ ነገ ብዙሃን ለመሆንና የአብዛኛውን ሕዝብ ድጋፍ አግኝቶ የመንግስት ሥልጣን የመያዝ ተራ ስለሚደርሰው የአናሳ ፓርቲ መገለል የሚያስከትለው ጉዳት ከባድ አይደለም የሚል ነው። በአሁኑ ጊዜ የብሪቲሽ ባለሁለት ፓርቲ ሥርዓት የሚመራውም በዚህ መንገድ ነው። ይሁን እንጂ ከሁለቱ ፓርቲዎች መካከል አንደኛው ከሥልጣን ውጭ ተገልሎ ለረጅም ጊዜ የሚቆይበትን ችግር ጨርሶ መፍታት የሚያስችል መንገድ አይደለም። ለምሳሌ በብሪቲሽ ባለሁለት ፓርቲ ሥርዓት እ.ኤ.አ ከ1951-1964 በነበሩት 13 ተከታታይ ዓመታት የሌበር ፓርቲ ከመንግስት ሥልጣን ውጭ ሆኖ የቆየበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። በእነዚህ የተራዘሙ ወቅቶች የታየውን የሥልጣን መገለል እንኳ ሳይቀር በተለይ ወጥ የሆነ ሕብረተሰብ ባለበት ሀገር ዋና ዋናዎቹ ፓርቲዎች በፖሊሲ አመለካከት የተራራቀ ልዩነት ስለሌላቸው የብዙሃን ዴሞክራሲና የብዙሃን አገዛዝ እንዲቃረኑ ሊያደርግ አይችልም የሚል ክርክር አለ። ነገር ግን ዴሞክራሲ በሕዝብ የተመሰረተ መንግስት ነው በሚለው ትርጓሜ ሲመዘን የአንድ ፓርቲ ከሥልጣን የሚዘልበት ሁኔታ ራሱ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ከመሆን አያመልጥም። በተለይ ደግሞ የተለያየ ባህል፣ እምነትና አመለካከት በሰፊው በሚንፀባረቅበት ወጥ ያልሆነ ሕብረተሰብ ባለበት ሀገር የዚህ አይነቱ አመለካከት ኢ-ዴሞክራሲያዊ ብቻ ሳይሆን አደገኛም ነው። ምክንያቱም አናሳዎቹ ለረጅም ጊዜ በመንግስት ስልጣን ተሳትፎ ለማድረግ ያላቸውን እድል ከተነፈጉ እንደተገለሉና እንደተረሱ አድርገው ስለሚሰማቸው ለሥርዓቱ ያላቸው እምነት ሙሉ በሙሉ ይሟጠጣል። ለመንግስት ድጋፍ ከመስጠት በመቆጠብ ብቻ ሳይወሰኑ ከፍተኛ ቀውስና ብጥብጥ ሊያስከትል ወደሚችል ጠንካራ ተቃውሞም ይገባሉ። በመሆኑም ወጥ የሆነ ባህል፣ አመለካከትና እምነት በሌለበት ሕብረተሰብ ውስጥ የብዙሃን አገዛዝ በዴሞክራሲ ፋንታ የብዙሃን አምባገነንነትን ስለሚፈጥር መቆሚያ የሌለው የሲቪል ሕብረተሰብ ቁጣና ተቃውሞ ያስከትላል። ስለዚህ እንደዚህ

አይነት ሕብረተሰብ የሚያስፈልገው የብዙሃን ድምጽ የሚገባውን መጠን ከፍ በማድረግ ከሞላ ጎደል የዜጎችን ስምምነት ለማግኘት እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ከሚል ፉክክር ይልቅ በውይይትና ድርድር መግባባትና ስምምነት እንዲኖር ዕድል የሚሰጥ፣ ከማግለል ይልቅ ለማሰባሰብና ለማሳተፍ በር የሚከፍት፣ የዴሞክራሲ አማራጭ ነው።

ይህ አማራጭ ደግሞ የስምምነት ሞዴል እንደሆነ ጥርጥር የለውም። የስምምነት ሞዴል ዝቅተኛ የባህል፣ የአመለካከትና የእምነት ክፍፍል አላቸው በሚገባ ሕብረተሰቦችም ሳይቀር ተስማሚነት እንዳለው ግልፅ እየሆነ በመምጣቱ የብዙሃን ሞዴል (የዌስት ሚኒስትር ሞዴል) ተከታይ በሆኑትና በተወሰነ ደረጃ ወጥ ሕብረተሰብ ባላቸው ሀገሮችም ጭምር ትኩረት እያገኘ ነው።

የስምምነት ዴሞክራሲ ሞዴልን በስራ ላይ በማዋል ውጤታማ ልምድ አላቸው ተብለው እንደምሳሌ ከሚጠቀሱት መካከል ስዊዘርላንድ፣ ቤልጅየምና ወደ አንድ ፌዴራላዊ መንግስትነት ደረጃ በመሸጋገር ላይ ያለው የአውሮፓ ሕብረት ዋነኞቹ ናቸው። ከሁሉም በላይ የስምምነት ሞዴል መለያ ከሆኑት መካከል አንዱ የሆነው ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤት የሚጎድላት ከመሆኑ በስተቀር የዚህ አማራጭ ዴሞክራሲ እውነተኛዋ ሞዴል ተደርጋ የምትታየው ስዊዘርላንድ ነች።

የስምምነት ሞዴል መለያ ከሆኑት መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል ሰፊ መሰረት ባለውና የመንግስትን አስፈፃሚ አካል ስልጣን በማጋራት መርህ የተገነባ ጥምር መንግስት፣ በሕግ አውጭውና በሕግ አስፈፃሚው መካከል ሚዛናዊ የሥልጣን ክፍፍል መኖር፣ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት፣ በተመጣጣኝ ውክልና ላይ የተመሰረተ የምርጫ ሥርዓት፣ እርስ በርስ የሚቀናቀኑ ሳይሆኑ እየተቻቻሉና እየተባበሩ የሚሰሩ ግፊት ሰጪ ቡድኖች፣ (Pressur Group) ያልተማከለና የመንግስት ሥልጣን መዋቅር ለሕዝቡ የቀረበበት ፌዴራላዊ አደረጃጀት፣ ተመጣጣኝ በሆነ ደረጃ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያላቸው ባለሁለት ምክር ቤቶች፣ ጥብቅ የሆነ ሕገመግግስታዊ ሥርዓት፣ ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤትና ከሕግ አስፈፃሚው ተፅዕኖ የተጠበቀና በነፃነት ለመስራት የሚያስችል ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ማዕከላዊ ባንክ መኖር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የእነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ፋይዳ እንደ እኛ ላለ ሕብረ ብሔራዊ ሕዝብ የሚኖረው ትርጉም ትልቅ እንደሆነ ለማንም የተሰወረ አይደለም።

ኢዴፓ የስምምነት ዴሞክራሲ ለሀገራችን ልዩ ሁኔታ የሚስማማ ባህሪ አለው የሚለው የዚህ ሞዴል መለያዎችና መርሆዎች ጠቃሚነትን በማመን ነው። ይህ የዴሞክራሲ አማራጭ በሀገራችን እንዲገነባ የምንፈልገውን ዴክራሲያዊ ስርዓት መሰረታዊ መርሆዎች የሚያሟላ ብቻ ሳይሆን ሕብረብሔራዊ ለሆነው ልዩ ባህርያችን እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ተመጣጣኝ የውክልና ሥርዓት፣ ሚዛናዊ የመንግስት ሥልጣን ክፍፍል፣ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት፣ ተመጣጣኝ ሥልጣን ያላቸው ባሁለት ምክር ቤቶች፣ ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤትና የመሳሰሉትን እንድንመሰርት እድል የሚሰጥ በመሆኑ ነው። ይህ አማራጭ በአንድ በኩል የዴሞክራሲን መሰረታዊ መርሆዎችና ጠቃሚ እሴቶች አሟልቶ የያዘ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለእኛ ሀገር ልዩ ሁኔታ ተስማሚ አማራጭ ነው። ይህ አማራጭ በሌላው የአለም ክፍል በተግባር ተፈትሾ ውጤታማ መሆኑ በመረጋገጡ ብቻ ሳይሆን የብዙሃን ሞዴል ያለበትን ጉድለቶች ለማሟላት ባለው ችሎታም የብዙዎችን ትኩረት የሳበና ተቀባይነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ ነው። ስለዚህ በሀገራችን እውነተኛው የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲገነባና ትርጉም ያለው ዘላቂ ልማት እንዲኖር የሚፈልጉ ዜጎች ሁሉ ልዩነቶቻችንን እያቻቻልን፣ በውይይትና በድርድር ሰፊ መግባባት እየፈጠርን በሰላም አብረን ለመኖርና ለማደግ የሚያስችለንን የስምምነት ዴሞክራሲ እንዲደግፉት፣ ለተግባራዊነቱ

እንዲረባረቡና እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዲያጠናክሩት ያስፈልጋል ብለን እናምናለን። ይህ አማራጭ በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችለን ብቻ ሳይሆን አብሮ ለመልማትና ለማደግ የተሻለ አማራጭ እንደመሆኑ ከሕልውናችን፣ ከአንድነታችን፣ ከሰላማችን፣ ከልማትና ብልጽግናችንም ጋር የተሳሰረ ነው። ስለሆነም መላው ዜጎች ለዚህ የዴሞክራሲ፣ የሕልውና፣ የአንድነት፣ የልማትና የብልፅግና መገኛ ቁልፍ አማራጭ ትኩረት ሰጥተው በዚህ ዙሪያ እንዲቆሙና ተገቢ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ማንኛውም ጥሩ የሚባልና በተግባር ውጤት ያስገኘ አማራጭ ዜጎች አምነው ካልተቀበሉትና ተግባራዊ ካላደረጉት በራሱ ምንም አይነት ፋይዳ እንደሌለው ስለምናምን ለሀገራችን ሰላምና ለሕዝባችን ብልፅግና መረጋገጥ ዋስትና እንደሚሆን ለሚታመንበት የስምምነት ዴሞክራሲ ማንኛውም ለሀገሩ መልካም ራዕይ ያለው ዜጋ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

በአጠቃላይ የኢዴፓን የፖለቲካ ዓላማ (ርዕዮተ ዓለም) በአጭሩ ጠቅለል አድርገን ስናስቀምጠው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ጠቃሚና ተስማሚ የሊበራል፣ የሶሻልና የመቻቻል ዴሞክራሲን እሴቶች ከኢትዮጵያ ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚያጣጥም የዴሞራሲያዊ ስርዓት መገንባት ነው።

# 2. ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ

ዴሞክራሲን በትክክለኛ ይዘቱ ተቀብሎ በሥራ ላይ በማዋል ዴሞክራሲን ያለ ለማስመሰል በሚከናወን የማታለል ተግባር መካከል የሰማይና የመሬት ያህል እርቀት አለ። ዴሞክራሲን በሚመለከት በኛና በገዥዎቻችን መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት መሠረቱ ይኸው ነው። ዴሞክራሲ ለታይታና ለማስመሰል ተብሎ የሚንጠለጠል መፈክር ሊሆን አይገባውም ብለን እናምናለን። በተግባር ሊገለፅ የማይችል የወረቀት ላይ ተስፋ ሆኖ የሚታይ ወይንም ዓለም አቀፍ እርዳታና ምፅዋት መለመኛ ሆኖ የሚያገለግል ሠነድ ማዘጋጀት አይደለም ዴሞክራሲ ማለት ብለን እናምናለን። ዴሞክራሲ እንደእኛ በመብት እረገጣ ለሚሰቃይ ሕዝብ፣ እንደኛ ግለሰብዓዊ ነፃነቱን ተገፎ ለሚባክን ሕዝብ፣ እንደኛ በድህነትና በበሽታ እግር ከወርች ተጠፍሮ ለሚማቅቅ ሕዝብ፣ እንደኛ አስተማማኝ ሰላም አጥቶ በስጋት ለሚባንን ሕዝብ፣ እንደኛ የትምህርት ዕድል፣ ሥራ የማግኘት ዕድል፣ የጡረታና ሌላም ማኅበራዊ ዋስትና የማግኘት ዕድል ተነፍጎት ሜዳ ላይ ለወደቀ ሕዝብ፣ እንደኛ የልማት እድል አጥቶ በአለም የእድገት ሰንጠረዥ ላይ የመጨረሻውና ከድህነት ወለል በታች በሆነው ደረጃ ላይ ለሚገኝ ሕዝብ፣ እንደኛ አንድነቱ አደጋ ላይ ወድቆ ስለወደፊቱ ሕልውናው ተስፋ ማድረግ ለተቸገረ ሕዝብ፣ እንደኛ ጠቃሚ የባህል ቅርሱንና አኩሪ ታሪኩን ተነጥቆ ባዶነት እንዲሰማው ግፍ ለተፈጸመበት ሕዝብ ዴሞክራሲ ከምንም ከማንም በላይ አስፈላጊ ነው። እነዚህ የጠቀስናቸውና ሌሎችም ያላነሳናቸው ብዙዎቹ ችግሮቻችን የሚመነጩት ከዴሞክራሲ ሥርዓት አለመኖር ነው። የዴሞክራሲ ሥርዓት ሁነኛ መገለጫ ከሆነው ከመልካም አስተዳደር እጦት ነው። ስለሆነም መፍትሄ የሚያገኙትም ዴሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ እስከ አሁን የተደረጉ ምርጫ መሰል ቲያትሮች በብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች ዴሞክራሲ እንዳለ ለማስመሠል ከሚካሄዱ የታይታ ምርጫዎች ጋር የሚመደቡ ናቸው። መራጮችና የተቃዋሚ ፓርቲ ተወዳዳሪዎች በወታደር ከበባ ሥር ሆነው ግልፅ ሽብር እየተካሄደባቸው፣ በዐይነ ቁራኛ እየተጠበቁ፣ በካድሬ ሠራዊት እየተዋከቡ፣ ማስፈራሪያ፣ ዛቻ፣ እሥራትና ግድያ እየደረሰባቸው፣ በአንፃሩ ደግሞ ሕዝብ የማያውቃቸውንና የማይፈልጋቸውን ሰዎች ገዥው ፓርቲ በድርጅታዊ ሥራ ለምርጫ እያቀረበ በግድ እንዲመረጡ የተደረገበት፣ በብዙ የምርጫ ክልሎች ደግሞ ተቃዋሚዎች ፈፅሞ እጩ ተወዳዳሪ አቅርበው እንዳይወዳደሩ ተከልክለው የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ካለ አማራጭ ብቻቸውን እየቀረቡ ተመረጡ የተባለበት ሁኔታ ነው የታየው። ገዥው ፓርቲ መሬትን

ጨምሮ የአገሪቱን ንብረት ሁሉ በብቸኝነት እየተቆጣጠረ፣ የምርጫ አፈፃፀሙን እንዲከታተል የተደራጀውን ተቋም ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዲንቀሳቀስ በማድረግ ፋንታ ከማዕከል እስከ መጨረሻው የምርጫ ጣቢያ የራሱን አባላት ባስፈፃሚነት አሰልፎ፣ በየደረጃው ከማዕከል እስከ ቀበሌ በተዘረጋው የመንግሥት መስተዳድር መዋቅር ውስጥም የሚገኙት የገዥው ፓርቲ አባላት በመሆናቸው ራሣቸው ተመራጭም፣ የምርጫ አስፈፃሚና ተቆጣጣሪም ሆነው እንዲያገለግሉ ተደርጐ ነው ምርጫ ተካሄደ ሲባል የነበረው::

ኢትዮጵያ ውስጥ አለ የሚባለው ዴሞክራሲ እስካሁን ድረስ ሥልጣን በኃይል የጨበጡ አምባገነኖች ካሳዩት ሁሉ የበለጠ አስመሳይ እንደሆነ መጠራጠር አይቻልም:: ሕገ-መንግሥት የጻፈ ሁሉ ዴሞክራት እንደማይባል ቢታወቅም ለወጉ ያህል ሕገ-መንግሥት ተጽፏል:: ይህ ሕገ-መንግሥት ሲረቀቅና ሲፃፍ በመጨረሻም ሲፀድቅ የሕዝብ ተሣትፎ ብዙም ትኩረት የተሠጠው አይደለም:: ሁሉንም እንዳሻቸው አቡክተው የጋገሩት አሁን ሥልጣን ላይ የተቀመጠው ገዢ ፓርቲ መሪዎችና ካድሬዎች ናቸው::

ሕዝቡ የመብት ጥያቄ በሠላማዊ መንገድ ባነሣ ቁጥር እያፈሱ ከማሰርና በጥይት ከመቁላት የዘለለ መልስ ሠጥተው የማያውቁት ገዥዎቻችን የመሠብሠብና ሠላማዊ ተቃውሞ የማድረግ ሕገ-መንግሥታዊ መብት አረጋግጠናል ይላሉ:: ጋዜጣና መጽሔት ላይ ሃሳባቸውን ከመግለፅ ያለፈ ወንጀል ያልተገኘባቸውን ነፃ ጋዜጠኞች እያሰሩና እያንገላቱ በሚፈፅሙት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት በዓለም አቀፍ ደረጃ ግንባር ቀደም የነፃ ፕሬስ ጠላቶች በሚል የተመዘገበ ሪከርድ ቢኖራቸውም ሃሳብን የመግለጽ ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና አስገኝተናል ከማለት ተቆጥበው አያውቁም:: በሰብዓዊ መብት ረገጣ ከባድ ወቀሳ ከውስጥም ከውጭም በየጊዜው የሚቀርብባቸውና የተመዘገበ የሰብዓዊ መብት እረገጣ ወንጀል እንዳለባቸው የሚያውቁት ገዥዎቻችን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን የሕገ-መንግሥቱ አካል በማድረግ ለሰብዓዊ መብቶች መረጋገጥ ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ እያደረግን ነው ይላሉ:: ተዘርዝሮ የማያልቅ ብዙ የማስመሰል ተግባር ሲፈጸም በሚገባ ተመልክተናል:: ለዚህም ነው አሁን በእኛ አገር አለ የሚባለውን ዴሞክራሲ ትክክለኛ ዴሞክራሲ እንደሆነ አድርጐ ለመቀበል የማይቻለው::

ገዥው ፓርቲ የግሉ ንብረት ከሆኑት የመገናኛ ብዙሃን ተቋሞቹ በተጨማሪ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃንን በብቸኝነት እየተጠቀመ፣ የፖሊስ፣ የደህንነት፣ የመከላከያና በአጠቃላይ የፍትሕ ተቋማትን ለገዥው ፓርቲ አሸናፊነት እንዲሠሩ በሚያደርግ ግዳጅ እያሠማራ፣ ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች እንደፈለጉ ተንቀሣቅሰው የምርጫውን ሂደት እንዳይታዘቡ እንቅፋት እየፈጠረ «ነፃ ምርጫ አካሄድን » እያለ ይፎክራል:: በምርጫው ሂደት የመምረጥ ነፃነታቸውን የተነፈጉ ዜጎች፣ የመወዳደር መብታቸውን የተነጠቁ የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎች፣ እስራት፣ ማስፈራራትና ግድያ የተፈፀመባቸውን ወገኖች በደል መርምሮ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችል ገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚና የፍትሕ ተቋም በሌለበት ሁኔታ ነፃ ምርጫ ማድረግ ይቅርና በሰላም ወጥቶ ለመመለስ የሚያስችል ዋስትና ሊኖር አይችልም:: የይስሙላ ምርጫዎች በተካሄዱበት ጊዜ ሁሉ ለመታዘብ የቻሉ ገለልተኛ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ምርጫ ታዛቢዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ እንዳልተደረገ ምስክርነት የሰጡ መሆኑ ቢታወቅም ገዥዎቻችን በምርጫ ሥርዓት የሕዝብ ውክልና አግኝተናል ከማለት ተቆጥበው አያውቁም:: በእርግጥ ለተራበና ለታረዘ እንዲሁም የተለያዩ አመለካከቶችን ማመዛዘን ለማይችል ኋላቀር ሕዝብ እስካሁን የተደረገው በራሱ ከበቂ በላይ ነው እያሉ ይህንኑ የህውሃት የምርጫ ቲያትር እንደመልካም ጅማሮ መታየት እንደሚገባው የሚሰብኩ ከውስጥም ከውጭም እንዳሉ ይታወቃል:: በተለይም በአሜሪካና በአውሮፓ ዴሞክራሲን ለመገንባት ከ200 ዓመታት በላይ ጊዜ ስለጠየቀና አሁንም ገና ብዙ የሚቀሩ የዴሞክራሲ ተባግሮች ስላሉ በኢትዮጵያ በ 12 ዓመታት ብቻ ከዚህ በላይ አይጠበቅም እያሉ የሚመክሩ የውስጥና የዉጭ ዜጐች መኖራቸው አዲስ ነገር አይደለም:: የውጭዎቹ ከዴሞክራሲ በፊት ዳቦ ያስፈልጋችኋል እያሉ ሲመክሩ በአንድ በኩል ርሃባችንንና ድህነታችንን ከመገንዘብ በመነጨ ቅንነት እንደሚሆን መገመት ቢቻልም በሌላ በኩል ደግሞ ዳቦውን

ለማግኘት ይህንን ያህል ረጅም የሆነ ዘመን ሳይቻለን የቀረው የዴሞክራሲ ሥርዓት ስለሌለን መሆኑ እንዳልጠፋቸው ስለሚታወቅ ከንቀትና ከጥላቻ በመነጨ የሚሠጡት አስተያየት ነው ብሎ ለመጠራጠር የሚያስገድድ ነው፡፡

ዴሞክራሲ የሌለው ሕዝብ ሀብቱን፣ ንብረቱንና ሕይወቱን ለመቆጣጠር ነፃነት የሌለው ሕዝብ ነው፡፡ በነፃነት እያሠበ፣ በነፃነት እየሠራና በነፃነት እየኖረ ኑሮውን ለማሻሻል ይቅርና ቁራሽ ዳቦ አግኝቶ ረሃቡን ለማስታገስ እንኳ ዕድል የተነፈገው ሕዝብ ነው፡፡ በዚህም የተነሣ ሁሉንም ዓይነት ነፃነት ተቀምቶ በከባድ ችግር ውስጥ እንዲኖር የተገደደ ሕዝብ ነው፡፡

የምዕራቡ ዓለም ዴሞክራሲ በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ ማለፉ የሚካድ ነገር አይደለም፡፡ እነሱ ዴሞክራሲን ለመከተል ሲወስኑ ብዙ የሚቀሰም የዴሞክራሲ ልምድ በሌለበት ሁኔታ ላይ ተመሥርተው ነበር፡፡ እኛ ግን የነሱን ልምድ ከራሳችን የረጅም ጊዜ የዴሞክራሲ ጥማት ጋር አገናኝተን ልንጠቀምበት ከወሰንን 200 ዓመት የግድ የምንጠብቅበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ ከዚህ በጣም ባነሰ ጊዜ የዴሞክራሲ ባለቤት መሆን እንችላለን፡፡ ዋናው ነገር ዴሞክራሲ እንደሚጠቅመን አውቀን፣ ከዴሞክራሲ ሌላ አሁን ከምንገኝበት አዘቅት የምንወጣበት የተሻለ መንገድ እንደሌለ ተገንዝበን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመፍጠር ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረጉ ላይ ነው፡፡ ዴሞክራሲን በሙሉ ልብ ለመከተል ውሳኔ ማድረግ አንድ ጠቃሚ ነገር ቢሆንም ብቻውን ውጤት እንደሚያመጣ መጠበቅም የዋሕነት ነው፡፡ ምዕራብያዊያን ዴሞክራሲያቸውን የገነቡት ዴሞክራሲ የሚፈቅደውን ሠላማዊ ትግል አካሂደው ነው፡፡ ዴሞክራሲ አንዴ በሚነደፍ የዘመቻ ፕሮግራምና በአዋጅ ብቻ የሚፈጠር ቀላል ነገር አይደለም፡፡ የዴሞክራሲ ባህል ስር እንዲሰድ በተከታታይ የሚከናወን የማስተማርና ለዚህ ተግባር የሚያግዙ የዴሞከራሲ ተቋማት የመፍጠር አድካሚ ሥራ ይጠይቃል፡፡ ሕዝቡ ተዘጋጅቶ ያለቀለት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማግኘት መብት እንዳለው የመስበክ ጉዳይ ሳይሆን ዴሞክራሲን የመፍጠር ግዴታና ኃላፊነት የራሱ መሆኑን አውቆ እንዲታገል የማብቃት ሥራ ይጠይቃል፡፡ ዴሞክራሲን ማንም በስጦታ መልክ እንደማያቀርብለት አውቆ ከማንም እንዳይጠብቅና በራሱ አነሣሽነት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምስረታ እንዲንቀሳቀስ የማስቻል ሥራ ይጠይቃል፡፡ በዚህ መንገድ ሠላማዊ ትግል እያደረጉ ዴሞክራሲን የመገንባቱ ተግባር ከባድ ፈተና ቢኖረውም ሌላ የተሻለ አማራጭ መንገድ እስከሌለ ድረስ በሙሉ ልብና ኃይል ልንረባረብበት የሚገባ ነው፡፡ ይህንን ካላደረግን አሁን በዴሞክራሲ ስም እየተፈጸመ ያለውን ግፍና በደል ተሸክመን ለመኖር እንገደዳለን፡፡

እስካሁን ድረስ እዚህ አገር አለ የሚባለውን ዴሞክራሲ ለመቀበል የማንፈልገው የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ጊዜ የሚጠይቅና በትንሽ አመታት ተገንብቶ እንደማይጠናቀቅ ስለማናውቅ አይደለም፡፡ ይልቁንም የዴክራሲን ሥርዓት ለማምጣት የሚያስችል ምልክት እንኳ መኖሩን ለማየት ባለማቻላችን ነው፡፡ ለዴሞክራሲ መፈጠር የሚያግዝ ፍላጐት፣ ዝግጅትና ቅንነት እንደሌለ በተግባር በማየታችን ነው፡፡ ሰው ሀሣቡን በመግልጹ ብቻ፣ በመረጠው የፓለቲካ ድርጅት ውስጥ ገብቶ ተሳትፎ በማድረጉ ብቻ፣ በሰላማዊ መንገድ ተከራክሮና ተወዳድሮ የሕዝብ ውክልና ለማግኘት በምርጫ ተሳትፎ በማድረጉ ብቻ ወንጀለኛ ሆኖ በሚታይበት ሥርዓት ውስጥ፣ በጥይት በሚገደልበት፣ ንብረቱ በሚዘረፍበትና በሚቃጠልበት፣ ከሥራ ቦታውና ከመኖሪያ አካባቢው በሚባረርበት፣ወህኒ በሚወረወርበትና ሰቆቃ በሚደርስበት ስርዓት ውስጥ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ምሥረታ ፍላጐት መኖሩን፣ ዝግጅትና ቅንነት መኖሩን ማየት አልቻልንም፡፡ አማራጭ እንዳይቀርብ ሥልታዊ መሰናክሎች አስቀድመው እየተዘጋጁ በሚካሄድ ምርጫ ውስጥ የዴሞክራሲ ጅምር መኖሩን ለመመስከር የሚያስችለን በቂ ምክንያት አላገኘንም፡፡

የተለያየ እምነት፣ የተለያየ ችሎታና የሥራ ልምድ፣ የተለያየ የማሳመንና የመታመን ችሎታ ያላቸው ሰዎች በእኩል ለምርጫ ውድድር ቀርበውለት ሕዝብ የፈለገውን በራሱ ነፃ ውሳኔ ለመምረጥ የሚያስችለው በር ተከርችሞ በተዘጋበት ሥርዓት ውስጥ የዴሞክራሲ ስርዓት

ምሰሶ የሆነው እውነተኛ ምርጫ እንዲኖር ቀና ዝግጅትና ፍላጎት እየታየ ነው ብለን ለመቀበል አልቻልንም። አንዱ በሕዝብ ሀብት፣ ገንዘብ፣ተሽከርካሪ፣ የመገናኛ አውታር፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ፖሊስና እስር ቤት እየታገዘ፤ ሌላው በነዚህ ተቋማትና አካላት እየታፈነ በሚገኝበትና ሕዝቡም በነፃነትና በፍላጐት እንዳይመርጥ በካድሬ ግፊት፣ ተፅዕኖና ወከባ ሥር በወደቀበት ስርዓት ውስጥ ለዴሞክራሲ ዝግጅትና ፍላጐት መኖሩን ለማየት አልቻልንም። የሕዝብን ደህንነትና ሠላም መጠበቅ የሚገባው የፖሊስ ተቋም የአንድ ቡድን የበላይነት በሁሉም መስክ እንዲረጋገጥ በሚያደርግ የተላላኪነት ግዳጅ እንዲሰራ በተደረገበት ስርዓት ውስጥ፣ ከሁሉም በላይ አገሪቱንና ሕዝብን ከውጭ ጠላት እንዲከላከልና እንዲጠብቅ የሕዝብ አደራና ኃላፊነት የተሸከመ የመከላከያ ኃይል ሣይቀር ለአንድ ቡድን ታማኝ አገልጋይ ሆኖ በሕዝብ ላይ እንዲዘምት በሚደረግበት ሥርዓት ውስጥ ለዴሞክራሲ መፈጠር ዝግጁነት፣ ፍላጐትና ቅንነት ስለመኖሩ የሚያስተማምኑ ምልክቶችን ማየት አልቻንም።

ስለዚህ የዴሞክራሲ ምልክት የማይታይበት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሆነን ዴሞክራሲን የምንናፍቅ ሆነናል። አስመሳይ ዴሞክራሲ በሚሰበክበት፣ የዴሞክራሲ ትክክለኛ ትርጉም ለማሳየት እስኪያስቸግር ድረስ የዴሞክራሲ መፈክር የሚያስተጋባ፣ የዴሞክራሲ ጭንብል ያጠለቀ፣ የዴሞክራሲን ሐረግ የሚመዝ፣ የዴሞክራሲን ቃላት በንግግሩ ውስጥ የሚጠቀም፣ በዴሞክራሲ የሚምልና የሚገዘት፣ ነገር ግን ደግሞ በእለት ከእለት ተግባሩ ዴሞክራሲ እንዳይበቅል አባራ ሲያለብስ፣ የዴሞክራሲን መቀበሪያ ጉድጓድ ሲምስ፣ ለዴሞክራሲ ማደግ አስተዋጽኦ ያላቸውን ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ተቋሞች ሲክስና ሲያፈርስ በሚውል ሥርዓት ውስጥ ሆነን ዴሞክራሲን እንድናልም ተገደናል። ዋናው ጉዳይ ከዚህ የምንወጣበት አማራጭ የትኛው እንደሆነ የመለየትና በዚህ አማራጭ እየተጠቀሙ ዴሞክራሲን የማግኘት ጠንካራ ትግል ማድረጉ ላይ ነው። የተጫነብንን ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ያገዛዝ ቀንበር ከትከሻችን ለማውረድም ሆነ እንዲኖር የምንፈልገውን ትክክለኛ የዴሞክራሲ ሥርዓት በአገራችን ተዘርቶ ሊበቅልና ሊያፈራ የሚችለው በመመኘት ብቻ አይደለም። በጾምና በጸሎት ብቻም አይደለም። መልካም መመኘት፣ የተመኙት እንዲገኝ መጾምና መጸለይ መጥፎ ነገር ባይሆንም በራሱ በቂ ነው የሚባል ግን አይሆንም። በመሆኑም ዴሞክራሲ በትክክለኛ መልኩና ባህሪይው እንዲመጣ ሠላማዊ ትግላችንን በጽናት በማካሄድ በስፋት መንቀሣቀስና በቅንጅት ወደፊት መግፋት ይኖርብናል ብሎ ኢዴፓ ያምናል።

# 3. ሕገ-መንግሥት

## 3.1. ሕገ-መንግሥት ምንድን ነው?

ሕገ-መንግሥት ማለት በአንድ አገር ውስጥ የሚገኝ የመንግሥት ሥርዓት የሚመራባቸውንና የተመሠረተባቸውን መርሆዎችና አስተሣሠቦች የያዘ ሠነድ ነው። የዜጐችንና ልዩ ልዩ ተቋሞችን መብትና ሥልጣን፣ በመንግሥት የሥልጣን አካላት መካከል፣ በባለሥልጣናትና በዜጐች፣ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሣይ ሠነድ ነው። ሕገ-መንግሥት በአንድ አገር ውስጥ ያሉትን የመንግሥት ተቋሞች አደረጃጀት፣ አሠራርና ግንኙነት ከማሣየት አልፎ እርስ በእርስ ሊኖራቸው የሚገባውን የሥልጣን ክፍፍል የሚገልጽ ሠነድ ነው። ህገ-መንግስት በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈጻሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ያለውን ግንኙነትና የሥራ ክፍፍል በግልጽ ለይቶ ያስቀምጣል።

ብዙዎቹ አገሮች እነዚህን የተጠቀሱትን ግንኙነቶችና አሠራሮች በጽሑፍ የሚዘረዝር ሕገ-መንግሥት አላቸው። ነገር ግን የአንድ አገር የመንግሥት ሥርዓት የሚመራበትን መንገድ በሚመለከት ሁሉንም ጉዳዮች በዝርዝርና በተሟላ መንገድ በአንድ ሠነድ ውስጥ ለማስፈር አይቻልም። መሠረታዊ የሆኑትን መርሆዎችና ሕጐች በሕገ-መንግሥት በማስፈር በሕገ-መንግሥቱ ላይ ተመሥርተው የሚወጡ ዝርዝር አዋጆች፣ ደንቦች፣ ድንጋጌዎችና መመሪያዎች እንዲካተቱ ይደረጋል። ይህ የሚፈፀመው ሕገ-መንግሥቱ ለሕግ አውጪው

አካል በሚሠጠው ሥልጣን መሠረት ነው። ሕገ-መንግሥት ከተለያየ አቅጣጫ ተዘርዝረው በሚቀርቡ የሕግ ድንጋጌዎች፣ አዋጆች፣ የፍርድ ውሣኔዎች፣ ስምምነቶች፣ ልማዶች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እየታገዘ የሚሄድ መሠረታዊ ሠነድ ነው። የዚህ ዓይነቱ ሠነድ መኖር መንግሥታት ከሕዝብ ያገኙትን ሥልጣን ሕግ ከሚወስነው ገደብ በላይ እያለፉ እንዳይጠቀሙበትና የግለሰቦችን ነፃነት የሚጋፋ ተግባር እንዳይፈጽሙ ለማድረግ የሚረዳ ነው። ሕገ-መንግሥት የአንድን አገር መንግሥታዊ ሥርዓት ዋነኛ ገፅታ የሚገልፅ ብቻ ሳይሆን ቁልፍ የሆኑትን የመንግስት አካላት ቅንብርና በመንግሥት ተግባር ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ የሚያሳይ ነው።

በሊበራል ዴሞክራሲ አመለካከት በመንግሥትና በዜጐች መካከል ያለውን ግንኙነት በሕገ-መንግሥት ውስጥ መደንገግ የሚያስፈልገው በግለሰቦች ነፃነት ላይ የዘፈቀደ አሠራር እዳይኖር ጥበቃ ለማድረግ ነው። በዚህም መሠረት ሕገ-መንግሥት በአንድ በኩል የዜጐችን መብት የመጠበቅ በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን የተሰጣቸውን ክፍሎች ሥልጣንና ኃላፊነት የመወሠን ጣምራ ተልዕኮ አለው ማለት ነው። የመንግሥትን ተግባር የሚያከናውኑ ባለሥልጣናት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ በቂ ሥልጣን በሕገ-መንግሥት ሊሰጣቸው የሚገባ ሲሆን በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጭ የግለሰብ ነፃነትን በሚጐዳ አኳኋን እንዳይጠቀሙበት የሚከላከል የሕግ ክልል ማበጀትና ያለአግባብ ሲጠቀሙበት ደግሞ የሕግ ቅጣት የሚሰጥበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። የመንግሥት ሥልጣን የሚሰጣቸው ሰዎች ከሥልጣን ክልላቸው ወጥተው መሥራት ብቻ ሳይሆን ወደለየለት የጭካኔ አገዛዝ የሚገቡበት አጋጣሚ እንዳለ በተደጋጋሚ ጊዜ የታየ ጉዳይ ነው። የመንግሥት መሪዎች ወደዚህ ዓይነቱ የጭካኔ አገዛዝ ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጓቸው በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ቢታወቅም በጣም መሠረታዊ የሆኑት ግን ሁለት ናቸው። እነዚህም አንደኛ ባለሥልጣኖቹ የተሰጣቸውን ኃላፊነትና ውክልና በመናቅ ለግል ጥቅማቸው ቅድሚያ በሚሰጡበትና ሆን ብለው ወደ ሥልጣን ብልግና ለመግባት ቆርጠው ሲነሱ፤ ሁለተኛው ደግሞ ሕዝቡ ራሱ ለጭካኔ አገዛዝ የሚመች ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ነው።

ባለሥልጣኖቹ በራሣቸው የሥልጣን ጥም እየተገፉ ወደ ጭቆና አገዛዝ ሲገቡ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙበት ሽፋን የሚሠሩት ሥራ ሕዝብን ለመጥቀም ሲባል የሚፈፀም አስመስሎ ማቅረብን ነው። በአፍሪካ ሥልጣን ላይ የነበሩና አሁንም ያሉ ጨካኝ መሪዎች በዜጐቻቸው ላይ የጭካኔ እርምጃ እየወሠዱ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የተደረገ ነው እንደሚሉ በተደጋጋሚ ጊዜ የታየ ነው። ለሕዝብ ጥቅም የሠሩ መስሏቸው በእውቀት ማነስና በድንቁርና ዜጐቻቸውንና አገራቸውን የጐዱ ጥቂት መሪዎች እንዳሉ ባይካድም አብዛኛዎቹ ግን ሆን ብለው በሕዝብ ንቀትና በማን አለብኝነት የጭካኔ አገዛዝ አስፍነው የዜጐች ሕይወት፣ ተስፋና ምኞት ላይ የሚቀልዱ ናቸው። ይህ በገዥዎቹ በኩል ያለውን ብቻ የሚያሳይ ሲሆን በዜጐች ጥፋት ጭምር የሚፈፀመው ደግሞ ሌላ ነው። ዜጐች በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ቁጥጥር የማድረግና የራሣቸው ነፃነት እንዳይደፈር የመከላከል መብት እንዳላቸው አውቀው ካልተጠነቀቁ ለጭካኔ አገዛዝ መምጣት ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገዋል ማለት ነው። አገዛዙ በዘፈቀደ የሚጭንባቸውን ሁሉ ለመሸከም ፈቃደኝነት እስካሳዩ ድረስ ጭነቱ ሊቀንስ አይችልም።

የጠየቁትን ሁሉ ሳያንገራግር የሚያሟላና እንደከብት ወደሚነዱት አቅጣጫ ለመንዝ የተዘጋጀ ሕዝብ ከተገኘ ለጭካኔ አገዛዝ መብቀልና ማደግ የሚመች ለም መሬት ማለት ነው። ሂትለር ያንን ሁሉ የጭካኔ ሥራ የፈፀመው ትዕዛዙን ተቀብሎ ለመፈፀም ቀድሞ የሚሠለፍ በሚሊዮን የሚቆጠር ታዛዥ በማግኘቱ ነው። የጀርመንን ትምህርት፣ ፕሬስ፣ ሬዲዮ፣ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤትና ጦር እንደፈለገው ለመጠቀም ድጋፍ የሚሠጥ ስለተገኘ ነበር። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ነጥቦች ቢኖሩም ከዚህ ዓይነቱ የጭካኔ አገዛዝ ለመውጣት ያለው ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲፈጠርና እየተጠናከረ እንዲሄድ ማድረግ ሲቻል ነው።

*የጭካኔ አገዛዝን ለማስወገድም ሆነ ተመልሶ እንዳይመጣ ለማድረግ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለመትከል ከመታገል የተሻለ አማራጭ የለም። ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለማስፈን የሚጠይቀው ትግል እጅግ ከባድና የተወሳሰበ ነው። ምክንያቱም አንዳንዶቹ የአፍሪካ መሪዎች ጫካ ውስጥ ሆነው ያረቀቁትን የፖለቲካ ፕሮግራም ሳይቀር ሕገ-መንግሥት ነው እያሉ በሕዝብ ላይ ስለሚጭኑና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የፈጠሩ በመምሰል ሠፊ ውዥንብር ስለሚነዙ ነው።*

*ሕገ-መንግሥት የአንድ አገር ዜጎች በግልፅ ተወያይተው፣ ተከራክረው፣ ከሞላ ጐደል የጋራ ጥቅማቸውን ያሟላል ብለው ባመኑባቸው ጉዳዮች ዙሪያ መግባባት ፈጥረው በፍላጐትና በነፃነት የሚያወጡትና የሚያፀድቁት ሠነድ ነው። ሕገ-መንግሥት ከሌሎች ሕጐች ጋር ሲነፃፀር የሕጐች ሁሉ የበላይ ሕግ ተደርጐ የሚወሰድና ረዘም ላለ ጊዜም በሥራ ላይ መቆየት ያለበት በመሆኑ በዜጐች ነፃነት ላይ ትልቅ ትርጉም ያለው ነገር ነው። ስለሆነም የዜጐች የተለያዩ ጥቅሞችና አመለካከቶች፣ እምነቶችና ፍላጐቶች የሚቻቻሉበት አንድ የጋራ ዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ እንጂ የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ጥቅም አራምዳለሁ የሚል የፖለቲካ ቡድን ፕላት ፎርም አይደለም።*

*ሕገ-መንግሥት ፓርቲዎች በምርጫ ወቅት ይዘውት የሚቀርቡት የምርጫ መወዳደሪያ ሠነድ ተደርጐ መታየት የሌለበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት አጀንዳ ጋር የግድ መያያዝ ያለበትም አይደለም። ምክንያቱም ሕገ-መንግሥት ሲዘጋጅ የተለያዩ አመለካከቶችና እምነቶች፣ ጥቅሞችና ፍላጐቶች የሚቻቻሉበት የቃል ኪዳን ሠነድ ሆኖ እንዲቀርብ ካልተደረገና አንድ ዓይነት የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ብቻ ያሰባሰበ የፓርቲ ፕሮግራም ከሆነ ሕገ-መንግሥት የሚያሠኘውን መሠረታዊ ይዘት ስለሚያጣ ነው። ለዚህም ነው የተለያየ አመለካከት፣ እምነትና ጥቅም ያላቸው ዜጐች መክረውና ዘክረው አንድም በሪፈረንደም አሊያም በተወካዮች አማካይነት ሊያረቁትና ሊያፀድቁት ይገባል የሚባለው። ከዚህ ውጭ የሚዘጋጅና በሕዝብ ጫንቃ ላይ የሚጫን «ሕገ-መንግሥት» የፈለገውን ያህል የዴሞክራሲ ቃላቶች ቢጠቀም፣ የፈለገውን ያህል የሰብዓዊ መብት አንቀጽ ቢኖረው ለጭቆና ሥርዓት ሽፋን ከመሆን የዘለለ ትርጉም አይኖረውም። የሕገ-መንግሥት ዴሞክራሲያዊ መሆን አለመሆን የሚመዘነው በውስጡ በያዛቸው ጥሩ ጥሩ ሃሣቦች ብቻ አይደለም። ዋናው መመዘኛ መብቴን አስጠብቅበታለሁ፣ ነፃነቴን አረጋገጥበታለሁ፣ የሥልጣን ባለቤትነቴን ሥራ ላይ አውልበታለሁ የሚል ዕምነት በድምጽ ሠጪው ዜጋ ውስጥ መኖሩ ነው። ይህ ከሌለ ድካሙ ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው።*

*ሕገ-መንግሥት ሊኖረው የሚችለው ቅርጽና ይዘት የሚወሠነው ብዙ መመዘኛዎችን አሟልቶ ሲገኝ ነው። በመጀመሪያ በሥራ ላይ የሚውልበትን አገር ታሪክ፣ መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ፣ ማኅበራዊ አወቃቀር፣ የኤኮኖሚ ዕድገት፣ የሃይማኖት እምነትና የባሕል ንፅፅር ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሕግና በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ የግለሰብ ነፃነት ማስጠበቂያና የዴሞክራሲ መብት ማረጋገጫ መርሆዎችን ያገናዘበ መሆን አለበት። በሦስተኛ ደረጃ የዜጐችን ነፃ ውሣኔና ፈቃድ ማግኘት አለበት።*

*የሕገ-መንግሥት ውጤታማነት የሚረጋገጥበት ሌላው መንገድ ተቃራኒ ፍላጐቶችን ለማስታረቅ በሚጠቀምበት ዘዴ ነው። ዴሞክራሲ በተገነባባቸው አገሮች ፍላጐቶችና ጥቅሞችን የሚያቻችሉ የጋራ መግባቢያ እሴቶች በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ በተገቢው መንገድ የተዘጋጀ ስለሆነ መቻቻል የዘመኑ የፖለቲካ ባሕል ለመሆን በቅቷል።*

*አሁን በመላው ዓለም ያሉትን የሕገ-መንግሥት ሥርዓቶች በተለያየ መንገድ መመደብ ይቻላል። ሕገ-መንግሥት በአራት መልኮች ይገለፃል። አንደኛው ፌደራላዊ ነው? ወይስ አሀዳዊ ነው? የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ፕሬዝዳንታዊ ወይስ ፓርላማዊ የሚለው ነው። ሦስተኛው መንገድ ሕገ-መንግሥቱ ያለ ብዙ ውጣ ውረድ በቀላሉ ሊቀየር የሚችል*

ነው? ወይስ አንዳንድ አንቀፆቸችን በቀላሉ ለመቀየር የማይቻል ግትር ወይም ጥብቅ ነው? የሚለው ነው፡፡ አራተኛው ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ የተጻፈ ነው ወይስ ያልተጻፈ ነው የሚለው ነው፡፡

በፌደራላዊ ሕገ-መንግሥት የሉዓላዊነት ሥልጣን በተለያዩ አካላት የተከፋፈለ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ እያንዳንዳቸው ነጻ በሆኑና ነገር ግን በስምምነት በዘረጉት ሥርዓት ተቀናጅተው በሚሠሩበት የተለያዩ አካላት የተከፋፈለ ነው፡፡ እነዚህም የየራሣቸው ሉዓላዊነት ያላቸው አካላት የፌዴራል መንግሥት ሕግ-አውጭና የእያንዳንዱ ክልል መንግሥታት ሕግ-አውጭ የሚባሉት የፌደራል መንግሥት አካላት ናቸው፡፡ እዚህ ላይ በጥንቃቄ ማስተዋል የሚያስፈልገው የዚህ ዓይነቱ ፌደሬሽን በተለያዩ መንግሥታት መካከል እንደሚኖረው የትብብር መልክ ለምሳሌ የጋራ ብልጽግና አገሮች እንዳላቸው የትብብር ግንኙነት ወይንም እንደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል መንግሥታት የጉባኤ ግንኙነት አይነት ተደርጐ መታየት የማይገባው መሆኑን ነው፡፡ ፌደሬሽን ምንም እንኳን የየራሣቸው የሉዓላዊነት ሥልጣን ያላቸው የክልላዊ መንግሥታት ግንኙነት ነው ቢባልም በስምምነት የተወሠነ አንድ የጋራ ሉዓላዊነትም የተፈጠረበት ግንኙነት ነው፡፡ የፌደሬሽን ግንኙነት በአንድ በኩል የክልል መንግሥታት በተወሠኑ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን የመወሠን ሥልጣንና ሉዓላዊነት የሚያረጋግጡ በት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ፈቅደው አባል ለሆኑበት የፌደራል መንግሥት ከሉዓላዊነታቸው የተወሠነውን ቀንሰው የሚሠጡበትና ነገር ግን ደግሞ በእኩልነት የሚሣተፉበት የጋራ ሉዓላዊነታቸው መግለጫ የሆነ የፌደራል መንግሥት ግንኙነት ነው፡፡ በአሃዳዊ መንግሥት ደግሞ ሕግ-አውጭው አንድ አካል ከመሆኑ በተጨማሪ ለአካባቢ (ለክልል) መንግሥታት ሕግ የማውጣት ዕድል በተወሠኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው በውክልና መልክ ነው፡፡ የአካባቢ መንግሥታት ሕግ ማውጣት ከተፈቀደላቸው አሃዳዊውን ሕግ-አውጭ ወክለው እንጂ በራሣቸው ሉዓላዊነት ላይ ተመሥርተው አይደለም፡፡ የአሃዳዊ መንግሥት ሕግ-አውጭ አካል ለክልል መንግሥታት የሚሠጣቸው ሕግ የማውጣት ተሣትፎ ከሥልጣን ተቆርሶ የሚሠጥ፣ በእሱ ስም የሚፈጸም የውክልና ሥልጣን ነው፡፡ ባስፈለገ ጊዜ የሠጣቸውን የውክልና ሥልጣን መልሶ ይነጥቃቸዋል፡፡

በፌደራል ሕገ-መንግሥት የተሳሠሩ የክልል መንግሥታት ግን ማንም የማይነጥቃቸው የራሣቸው ሕግ የማውጣት ሉዓላዊነት ያላቸው ሲሆኑ ከአሃዳዊው አሠራር በተቃራኒ ከሉዓላዊነታቸው ቆርሰው በፌደራል ደረጃ በጋራ ለሚያቋቁሙት መንግሥት ሉዓላዊነት እንዲኖረው ያስችሉታል፡፡ የፌደራሉ መንግሥት ሉዓላዊነት የሚመሠረተው በክልል መንግሥታት ፈቃድና ስምምነት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የፌደራል ግንኙነት ድክመት ተደርጐ የሚወሠደው በአንድ አካል የተጠቃለለ ሉዓላዊ ሥልጣን አለመኖሩ የሥልጣን ክፍፍሉን የተወሳሰበ ያደርገዋል፣ እንዲሁም ሕገ-መንግሥት የማሻሻልን ተግባር የተገተረና ሊወጡት በማይቻል ውጣ ውረድ የተቆላለፈ ነው የሚለው አስተያየት ነው፡፡ ነገር ግን ዞሮ ዞሮ የመግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት ሕዝብ እንደመሆኑ የፌደራል አደረጃጀት ደግሞ ሥልጣንን በላይኞቹ አካላት መካከል በማከፋፈል ብቻ የተወሠነ ሳይሆን ወደሕዝቡ የማቅረብ አሠራር ስለሚፈቅድ ጠቀሜታው ይበልጥ የጐላ መሆኑን መጠራጠር አይቻልም፡፡

የመንግሥት የሥልጣን ክፍፍል መኖር በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት ሥርዓት ውስጥ እንደ ቁልፍ መርሆ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ ይህ መርህ አስፈላጊ የሆነባቸው መሠረታዊ መነሻዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የሕዝብን ጥቅም በሚጐዳ አኳኋን አደጋ ሊያመጣ የሚችል የሥልጣን መሰባሰብ (የስልጣን መማከል) አንድ ቦታ ላይ የሚሆንበት ሁኔታ ለማስቀረት የተለያየ የሥራ ድርሻ ላላቸው የመንግሥት አካላት ሥልጣንን ማከፋፈል ይሻላል ከሚል አስተሳሰብ የሚነሣ ነው፡፡ ሦስቱም የመንግሥት ሥልጣኖች ማለትም ሕግ-አውጭው፣ ሕግ-አስፈፃሚውና ሕግ-ተርጓሚው በተመሳሳይ እጆች ወይም በጥቂት ሰዎች፣ ከዚያም በላይ በአንድ ሰው እጅ ውስጥ ከተከማቸ ፍፁማዊ የሆነ ሥልጣን ይፈጠራል፡፡ ሥልጣን በሕግ-አስፈጻሚው እጅ ውስጥ ተሰባስቦ ከገባ መጥፎም ይሁን ጥሩ ሕግ ራሱ

በፈለገው መንገድ ያወጣል፣ ዜጐችን ሕግ ጥሳችኋል እያለም ራሱ ይቀጣል:: እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ደግሞ የተወሠኑ ባለሥጣኖች ከሣሽም፣ ተከራካሪም፣ ዳኛም ሆነው እንዳሻቸው በዜጐች ነፃነትና መብት ላይ እንዲቀልዱ መብት ይሰጣል ማለት ነው:: ስለሆነም ሥልጣንና ኃላፊነት ለሦስቱም የመንግሥት አካላት ተከፋፍሎ መሰጠት አለበት የሚለው ሀሣብ ተመራጭ ሆኖ ተገኘ:: በዚህም መሠረት ሕግ የማውጣቱን ሥራ በዜጐች ምርጫ ለሚቋቋመው ፖርላማ ወይም ሕግ-አውጭ አካል፣ ሕጉን የማስፈፀሙን ሥራ ደግሞ የመንግሥትን ተግባር እንዲያከናውን በፓርላማው ለሚመደበው የመንግሥት አስፈፃሚ አካል እንዲሁም ሕግ የመተርጐሙን ሥራ ለሕግ-ተርጓሚው አካል (ለፍርድ ቤቶች) ማከፋፈል በማስፈለጉ ዴሞክራሲያዊና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የመሠረቱ አገሮች የመንግሥት ሥርዓታቸውን የሚመሩት በዚህ ዓይነቱ ህገ-መንግስታዊ የሥልጣን ክፍፍል መርህ ነው::

## 3.2. የሕገመንግስት ዓይነቶችና አመዳደብ

አሁን በመላው አለም ያሉትን የሕገመንግሥት ሥርዓቶች በተለያየ መንገድ መመደብ ይቻላል:: ከእነዚህ መለያ መንገዶች መካከል የተጻፈና ያልተጻፈ ሕገመንግስት የሚለው አንዱ ነው:: የተጻፈ ሕገመንግስት ሲባል ለመንግሥት አሠራር የሚረዱ የሕግ ሀሣቦች በጽሁፍ መልክ የተዘጋጁበት ሕገመንግስት ማለት ነው:: የተጻፉ ሕገመንግስቶች ተብለው ከሚታወቁት ውስጥ እ.ኤ.አ በ1787 የወጣው የአሜሪካ ሕገመንግስት ይገኝበታል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የተወሠኑ ማሻሻያዎች ከመጨመራቸው በስተቀር ለ215 (ሁለት መቶ አስራ አምስት) ዓመታት ገደማ በስራ ላይ ነው:: የተጻፈ ሕገመንግስት ሶስት ዋና ዋና ቁምነገሮችን ይይዛል:: እነዚህም አንደኛ የዋና ዋናዎቹን የፖለቲካ ተቋሞች ተግባሮቻቸውን፣ ያላቸውን ሥልጣንና የእርስ በእርስ ግንኙነት ይገልጻል:: ሁለተኛ የተወሠኑ መብቶችን ይዘረዝራል:: ሶስተኛ መሠረታዊ የእምነት ዝንባሌዎችን ያጠቃልላል:: ሕገመንግስት ሌላም በጣም አስፈላጊ የሚሆንበት ሁኔታ አለ:: ለምሣሌ ሀገሮች በአዲስ መልክ ተቋቁመው የመንግሥት ስራ ሲጀምሩ፣ ወይም የዘር፣ የኃይማኖት፣ የቋንቋ ልዩነቶች በሠፊው በሚታይበት ሀገር ማንነታቸውን የሚጠብቅ ዋስትና መሰጠቱን ለማረጋገጥ ወይንም ሠፊ በሆነ ሀገር ውስጥ የተለያዩ ርቀት ያላቸው የአገሪቱ ክፍሎች በአንድ ማዕከል ስር መሆናቸው ያሏቸውን ጥቅሞችና ፍላጐቶች የማያሟላ መሆኑ ሲታመንበት የተወሠነ የፌዴራል ሕግ ለማውጣት፣ የተለያዩ ማዕከላትን ለመፍጠር፣ በፌደራሉና በክልሎች መካከል ያለውን የሥልጣን ክፍፍል ለመለየት ሲያስፈልግ ሕገመንግሥት ማዘጋጀት የተለመደ ነው::

ሌላው የሕገመንግስት መለያ መንገድ ግትር (rigid) እና ለስላሣ፣ በቀላሉ ሊቀየር የሚችል (flixible) የሚል ነው:: በማንኛውም ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት የሕገመንግሥት ማሻሻያ ሕግ መወሠን የተለመደ ነው:: ምክንያቱም ከአዳዲስ አስተሣሠቦች ጋር መራመድ እንዲቻልና በሕገመንግሥት አውጪዎች በቅድሚያ ያልታዩ ጠቃሚ ነገሮች ቢኖሩ ለማካተት አልያም ደግሞ ከተለወጡ ሁኔታዎች ጋር የማይሄዱ አንቀጾች ቢኖሩ ለመቀነስ ስለሚያስችል ነው:: አንዳንድ አገሮች ሕገመንግስት በቀላሉ የሚቀየርበት አሠራር ከተዘረጋ ባለሥልጣኖች ጠ ቃሚ የሆኑ ድንጋጌዎችን እንደፈለጉ ከሕገመንግሥቱ እያስወገዱ ወደ ሥልጣነ ብልግና የሚያመሩበት እድል እንዳይፈጥሩ በመስጋት በቀላሉ የማይሻሻልበትን መንገድ ይመርጣሉ:: ሌሎች ደግሞ የፀኑና ሊለወጡ የማይገባቸው የክልል መንግሥታት መብቶች ዋስትና ያጣሉ በሚል ስጋትና ሌሎቹ ደግሞ የዜጐች መሠረታዊ ነጻነቶች እየተቀናነሱ ይሄዳሉ በሚል ስጋት ሕገመንግሥት በቀላሉ የሚቀየርበትን አሠራር አይፈልጉም:: ከእነዚህ በተለየ መንገድ አንዳንዶቹ ምንአልባት አነስተኛ ድምጽ የነበራቸው ፓርቲዎች የማሸነፍና ወደ ሥልጣን የመምጣት ዕድል ቢያጋጥማቸው መጠነ ሠፊ ሕገመንግሥታዊ ለውጥ ሊያደርጉ ይችላሉ ከሚል ሥጋት የሕገመንግሥት ማሻሻያ ስርዓቱ በቀላሉ የማይቻል እንዲሆን ያደርጉታል:: እነዚህ የተጠቀሱ ምክንያቶች የሚያሣዩት በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ሕገመንግሥት የሚሻሻልበት ሁኔታ ቀላል እንዳይሆን የመፈለግ ዝንባሌ መኖሩን ነው::

ሕገ-መንግስትን በማሻሻል ረገድ ያለው ግትር (ጥብቅ) አሠራር በተለያየ ደረጃ በተለያዩ አገሮች መኖሩ የታወቀ ቢሆንም በቀላሉ እንዲቀየሩ የሚፈለጉ ጉዳዮችን በመምረጥ ረገድ ያለው ልዩነት በጣም የሠፋ ነው፡፡ ብዙዎቹ ዴሞክራሲን የገነቡ አገሮች የግለሠብ ነጻነቶችንና የአገር ደህንነትን ለአደጋ ያጋልጣሉ ብለው የሚሠጉባቸውን በቀላሉ እንዳይቀየሩ ጥብቅ መንገድ ሲከተሉ ሌሎች በተለይ ዴሞክራሲ ያልተመሠረተባቸው አገሮች ደግሞ ሥልጣናችንን በቀላሉ እናጣለን ብለው የሚሠጉበትን የሕገመንግሥት ክፍል በቀላሉ እንዳይቀየር የሚያደርግ አሠራር ይደነግጋሉ፡፡ የተወሠኑ አገሮችን ልምድ ብንወስድ ለምሣሌ ደቡብ አፍሪካ ጥብቅ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል ብላ የምትገምታቸውን የሕገመንግሥት ጉዳዮች ለማሻሻል ያስቀመጠችው ድንጋጌ የሁለቱን ምክር ቤቶች 2/3ኛ ድምጽ ማግኘትን ነው፡፡ አውስትራሊያ ደግሞ ሁለቱም ምክር ቤቶች (ፓርላማውና ሴኔቱ እንደማለት ነው) ማሻሻያውን ከደገፉት በኋላ ለሕዝብ ውሣኔ ቀርቦ በ6ቱም ክልሎች የድምጽ ሠጪውን ሕዝብ አብላጫ ድምጽ ሲያገኝ የሚሻሻልበትን አሠራር ትከተላለች፡፡ ሕንድ ደግሞ ብዙዎቹ የሕገመንግሥቱ አንቀጾች በአብዛኞቹ የክልል መንግሥታት ህግ አውጭ አካላት ከተደገፉ የሚሻሻሉበትን አሠራር በመከተል ለክልል መንግስታት ዋስትናን የሚያረጋግጥ አቅጣጫ ታራምዳለች ፡፡ አሜሪካም እንደዚሁ ሁለቱ ምክር ቤቶችና የአብዛኞቹ ስቴቶች ድጋፍ በሚረጋገጥበት አሠራር የሕገመንግስት ማሻሻያ እርምጃ ትወስዳለች፡፡ የተወሠኑት የሕገመንግስት አንቀጾች ሳይሻሻሉ የሚቆዩበትን የጊዜ ሠሌዳና ማንኛውም ስቴት (ግዛት) ከራሱ ዕውቀት ውጭ በሴኒቱ ውስጥ ያለው ድምጽ የመስጠት መብት ሊነጠቅ የማይችልበትን ብቅ ድንጋጌዎች አስፍራለች፡፡ ይህም የስቴቶችን (የግዛቶችን) መብት ዋስትና የማረጋገጥ ጉዳይ ተደርጐ የሚወሠድ ነው፡፡

ሕገ-መንግሥት በማሻሻል ረገድ ግትር የሆነ አሠራር መከተሉ የሚያመጣው ጉዳት አለ የሚሉ ወገኖች ከሚያነሷቸው ጉዳዮች መካከል ከፍተኛ ጉዳት ደተርጐ የሚታየው ነጥብ ሕገመንግሥቱን በአዲስ መልክ ከተፈጠሩና ከተለወጡ የመንግሥት አሠራር ፍልስፍናዎች፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም ሣይቻል ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል የሚለው ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ መንግሥታት ከመደበኛው አሠራር በተለየ አቅጣጫ ሕገመንግሥታዊ ስምምነቶችን እያፀደቁ ሕገመንግሥታቸውን ከአዳዲስ ለውጦች ጋር የማጣጣም ሥራ ይሠራሉ፡፡ የሕገመንግሥት ማሻሻያ ሀሣቦች መታየት ይኖርባቸዋል ወይም መታየት አይኖርባቸውም የሚለውን የሚወስን ፍርድ ቤት ያላቸው አገሮች በዚህ መንገድ ይሄዳሉ፡፡ ሕገመንግስታቸው በሥራ ላይ ሲውል ካስገኘው ጥቅምና ጉዳት እየተነሱ ረጋ ብሎ በመወያየትና ስምምነት ላይ በመድረስ ማሻሻያ የሚያደርጉም አሉ፡፡ ካናዳ ለምሣሌ ለክልል መንግሥታት ገዥዎች አጠቃላይ የቬቶ ሥልጣን የሚሠጠው ሕግ በስምምነት ቀስ በቀስ እየተስተካከለ መጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ሕገመንግስታቸው በቀላሉ ሊሻሻል የሚችልበትን አሠራር የሚከተሉ አገሮችም አሉ፡፡ ኒዊዚላንድ ከሌሎቹ አገሮች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ልልነት (ለስላሳ) አሠራር የምትከተል አገር ነች፡፡ ብዙውን ጊዜ መደበኛ የማስተካከያ ሥርአቶች እየተከተሉ የሚሠሩ ቢሆንም በዜጐቻቸው ፍላጐት ተመስርተው ቀለል ባለ አካሄድ ማሻሻያዎችን ያደርጋሉ፡፡ ይህ አይነቱ አሠራር ዜጐች ራሣቸው ሕገመንግሥታቸው ጊዜ ያለፈባቸውን አስተሣሠቦችና አሠራሮች በመከተሉ የተነሣ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ቅጥም እንቅፋት ሆኖአል ብለው ባመኑ ጊዜ ለውጥ እንዲኖር ግፊት ያደርጋሉ፡፡ ለውጡም እንደሁኔታው ጥናትንና ምርምርን በተከተለ መንገድ ይፈፀማል፡፡ በዚህ አኳኋን ዜጐች ህገ-መንግስት የመለወጥ መብታቸውን በተግባር መጠቀም ሲችሉ የፖለቲካ ነጻነት ምን ያህል መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ በግልጽ ይማሩበታል፡፡ ምንም እንኳ ጀርመን የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ለማድረግ የፌዴራሉን ፓርላሜንት (ቡንደስታግ) እና የፌዴራል ምክር ቤቱን (ቡንደስራት) 2/3ኛ ድምጽ መገኘት የምትጠይቅ ቢሆንም የፌዴራሉ ሕገመንግሥታዊ ፍርድ ቤት ከዜጐች የሚቀርቡትን

*የሕገመንግሥት ቅሬታዎች እየመረመረ የሚሠጠው ውሣኔ የዜጐችን መብት ይበልጥ የሚከበር እንዳደረገው በተግባር የሚታይ ነው። ለምሣሌ የጀርመን ሕገመንሥት በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች እኩል መታየት የሚችሉበትን ሁኔታ አስመልክቶ የደነገገውን ተፈጻሚ ሕግ እንዲሆን የወሠነው የፌዴራሉ ሕገመንገስታዊ ፍርድ ቤት ነው። በአውስትራሊያ ደግሞ እ.ኤ.አ በ*1953 *የኮሚኒስት ፓርቲውን ለማገድ መንግሥት ለውሣኔ ሕዝብ ያቀረበውን ሀሣብ ሕዝቡ በመቃወም ውድቅ ያረገበት አሠራር፣ በፈረንሣይ ቀደም ሲል ከፓርላማ አባላትና ከአካባቢ የመንግሥት አካላት በተውጣጡ የተወሰኑ የምርጫ ኮሌጆች ይመረጥ የነበረውን ፕሬዝዳንት በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጥ ይችል ዘንድ እ.ኤ.አ ጥቅምት* 25 *ቀን* 1962 *ለውሣኔ ሕዝብ በቀረበው ማሻሻያ ላይ ሕዝቡ በቀጥታ ውሣኔ ያጸደቀበት አሠራር፣ በቅርቡም ብዙዎች የአውሮፓ መንግስታት ለአውሮፓ ሕብረት አባልነት የሕዝባቸውን ፈቃድና ውሣኔ በመጠየቅ ሀሣቡ እንዲደግፍና እንዲነቅፍ ያስቻሉበት አሠራር ዜጐች በአገራቸውና በሕልውናቸው ላይ ያላቸውን የመወሠን መብት በተግባር ያረጋገጡባቸው ናቸው።*

*የሕገመንግስትን ዓይነቶች የመለያ ሌላው መንገድ ፌደራላዊ ነው? ወይስ አሀዳዊ ነው? የሚለው ነው። በአሀዳዊ ሕገመንግስት የሉዓላዊነት ሥልጣን ለአንድ ሕግ አውጭ አካል ብቻ የተሠጠ ነው። ነገር ግን በፌደራላዊ ሕገ-መንግስት የሉዓላዊነት ሥልጣን በተለያዩ አካላት የተከፋፈለ ነው። በሌላ አገላለጽ እያንዳንዳቸው ነጻ በሆኑና ነገር ግን በስምምነት በዘረጉት ሥርዓት ተቀናጅተው በሚሠሩ የተለያዩ አካላት የተከፋፈለ ነው። እነዚህም የየራሣቸው ሉዓላዊነት ያላቸው አካላት የፌዴራል መንግስት ሕግ አውጭና የእያንዳንዱ ክልል መንግሥታት ሕግ አውጭ የሚባሉት የፌደራል መንግሥት አካላት ናቸው። እዚህ ላይ በጥንቃቄ ማስተዋል የሚያስፈልገው የዚህ ዓይነቱ ፌደሬሽን በተለያዩ መንግሥታት መካከል እንደሚኖረው የትብብር መልክ ለምሳሌ የጋራ ብልጽግና አገሮች እንዳላቸው የትብብር ግንኙነት ወይንም እንደተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል መንግሥታት የጉባኤ ግንኙነት ተደርጐ መታየት የማይገባው መሆኑን ነው። ፌደሬሽን ምንም እንኳን የየራሣቸው የሉዓላዊነት ሥልጣን ያላቸው መንግሥታት ግንኙነት ነው ቢባልም በስምምነት የተወሠነ አንድ የጋራ ሉዓላዊነትም የተፈጠረበት ግንኙነት ነው። የፌደሬሽን ግንኙነት በአንድ በኩል የክልል መንግሥታት በተወሠኑ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን የመወሠን ሥልጣንና ሉዓላዊነት የሚያረጋግጡ በት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ፈቅደው አባል ለሆኑበት የፌደራል መንግሥት ከሉዓላዊነታቸው የተወሠነ ቀንሰው የሚሠጡበትና ነገር ግን ደግሞ በእኩልነት የሚሣተፉበት የጋራ ሉዓላዊነታቸው መግለጫ የሆነ የፌደራል መንግሥት ግንኙነት ነው። በአሃዳዊ መንግስት ደግሞ ሕግ አውጭው አንድ አካል ከመሆኑ በተጨማሪ ለአካባቢ መንግሥታት ሕግ የማውጣት ዕድል በተወሠኑ ጉዳዮች ላይ የሚሠጠው በውክልና መልክ ነው። የአካባቢ መንግሥታት ሕግ ማውጣት ከተፈቀደላቸው አሃዳዊውን ሕግ አውጭ ወክለው እንጂ በራሣቸው ሉዓላዊነት ላይ ተመስርተው አይደለም። የአሃዳዊ መንግስት ሕግ አውጭ አካል ለክልል መንግስታት የሚሠጣቸው ሕግ የማውጣት ተሣትፎ ከሥልጣን ተቆርሶ የሚሠጥ፣ በእሱ ስም የሚፈጸም የውክልና ሥልጣን ነው። ባስፈለገ ጊዜ የሠጣቸውን የውክልና ሥልጣን መልሶ ይነጥቃቸዋል።*

*በፌደራል ሕገመንግሥት የተሣሠሩ የክልል መንግሥታት ግን ማንም የማይነጥቃቸው የራሣቸው ሕግ የማውጣት ሉዓላዊነት ያላቸው ሲሆኑ ከአሃዳዊው አሠራር በተቃራኒ ከሉዓላዊነታቸው ቆርሰው በፌደራል ደረጃ በጋራ ለሚያቋቁሙት መንግስት ሉዓላዊነት እንዲኖረው ያስችሉታል። የፌደራሉ መንግሥት ሉዓላዊነት የሚመሠረተው በክልል መንግሥታት ፈቃድና ስምምነት ነው። አንዳንድ ጊዜ የፌደራል ግንኙነት ድክመት ተደርጐ የሚወሠደው በአንድ አካል የተጠቃለለ ሉዓላዊ ሥልጣን አለመኖሩ የሥልጣን ክፍፍሉን የተወሣሠበ ያደርገዋል፣ እንዲሁም ሕገመንግስት የማሻሻልን ተግባር የገተረና ሊወጡት*

በማይቻል ውጣ ውረድ የተቆላለፈ ነው የሚለው አስተያየት ነው:: ነገር ግን ዞሮ ዞሮ የመግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት ሕዝብ እንደመሆኑ የፌደራል አደረጃጀት ደግሞ ሥልጣንን በላይኛቹ አካላት መካከል በማከፋፈል ብቻ የተወሠነ ሣይሆን ወደሕዝቡ የማቅረብ አሠራር ስለሚፈቅድ ጠቀሜታው ይበልጥ የጐላ መሆኑን መጠራጠር አይቻልም::

አንዳንድ ጊዜ፣ በተለይ አሁን በምንገኝበት ዘመን በፌደራልና በአሃዳዊ መንግሥታት መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ ሆኖ የማይታይበት ሆኔታ ያጋጥማል:: በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣንን ወደታች ወደ ሕዝቡ በማቅረብ አንዳንድ አሃዳዊ ሕገመንግሥት ባላቸው አገሮች ከፍተኛ ግምት የሚሠጠው ተግባር የሚታይበት ሁኔታ አለ:: ለምሣሌ ደቡብ አፍሪካ የተወሠኑ የክልል መንግሥታት ሠፊ ሕግ የማውጣት ሥልጣን እንዲኖራቸው የተደረገበት አሠራር አለ:: ችግሩ ማዕከላዊው ፓርላማ ከፈለገ ሥልጣናቸውን የሚቀይርበት ወይም የሚያስቀርበት ዕድል መኖሩ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ አንዳንዶቹ አሃዳዊ ሕገመንግሥታት በሕግ አሠራራቸው ከሌሎች በበለጠ ጥንካሬ ፌደራላዊ ሆነው የሚታዩ ናቸው:: ለምሣሌ በአውትራሊያ ሁሉም የክልል መንግስት በሴኔቱ ያላቸው ውክልና እኩል ሲሆን በካናዳ ደግሞ ኦንታሪኦና ኩቤክ ከሌሎቹ ስምንት ግዛቶች የበለጠ ሴናተሮችን ይወክላሉ:: በሶስተኛ ደረጃ ጥቂት መንግሥታት ለምሣሌ እንደ አውስትራሊያ ያሉት የፌደራሉን ሥልጣን ለይተው በግልጽ ከወሠኑ በኋላ ቀሪውን ለክልል መንግሥታት ይሠጣሉ:: በአራተኛ ደረጃ መደበኛውን አሠራር የተከተለ የሕገመንግሥት ለውጥ ሳያስፈልግ የፌደራሊዝሙ ደረጃ የሚቀየርበት ሁኔታ አለ:: በአንድ ወቅት የአውስትራሊያ ፌደራል መንግስት ከፍተኛ ደረጃ ጥንካሬ ባሣየበት ጊዜ ይኼ ሁኔታ በግልጽ ታይቷል::

ከዚህ በተለየ ሁኔታ በእንግሊዝ አሃዳዊ መንግስት ውስጥ የፌደራሊዝም ገጽታዎች ጐላ ብለው ይታያሉ:: ለምሣሌ እ.ኤ.አ በ1920 የወጣው የአየርላንድ መንግስት ድንጋጌ ሠሜን አየርላንድን የራሷ ሁለት ሕግ አውጪ ም/ቤቶችና አስፈጻሚ አካል ያላት እንድትሆን ያደረገበትን ሁኔታ ማስታወስ ይቻላል:: ብዙዎቹ የዩናይትድ ኪንግደም ሚኒስትሮች ሥልጣናቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ክልል እንግሊዝና ዋለስ ናቸው:: ለስኮትላንድም ከአየርላንድ ጋር በእኩል ደረጃ የሚታይ ባይሆንም የተለየ አደረጃጀት ተሠርቶላታል:: በሚያካሄዱት ተግባር ከማንኛውም የእንግሊዝ መንግሥት ሚኒስትሮች ቁጥጥር የማይደረግባቸውና ዋና ጽ/ቤታቸውን ስኮትላንድ ያደረጉ የራሷ ሚኒስትሮች አሏት:: በስራቸው ከእንግሊዝ አካላት ቁጥጥር ነጻ የሆኑ መምሪያዎች አሏቸው:: የራሷ የሕግ ሥርዓትና የሕግ ኦፊሰሮች (ባለሥልጣኖች) አሏት:: የዚህ ዓይነቱ ሥልጣንን ወደታች የማውረድ ተጨባጭ እርምጃ ቢኖርም ዞሮ ዞሮ የዩናይትድ ኪንግደም መንግስት በይዘቱ አሃዳዊ መሆኑን አይቀይረውም:: ምክንያቱም ዌስት ሚኒስቴር የሚገኘው ፓርላማ በሁሉም ዘንድ የሚከበር ሕግ የማውጣት የበላይነቱ እንደተጠበቀ ነው:: በዚህ ፓርላማ የሚወጣውን ሕግ ሁሉም ተቀብለው መፈፀም ይኖርባቸዋል::

አራተኛው የሕገመንግሥት ዓይነቶች መለያ ፕሬዝዳንታዊ ወይም ፓርላማዊ የሚባለው ነው:: ይህም ማለት፣ አስፈጻሚው አካል ከሕግ አውጭው አካል ጋር የሚቀራረብ ሥልጣን እንዲኖረው ሆኖ በሚሠራበት ሕገመንግሥት ውስጥ ለምሣሌ የአሜሪካ ፕሬዝደንትና ኮንግረስ ተቀራራቢ ሥልጣን በሕግ ከተሠጠበት ሁኔታ ጋር የሚመሣሠሉት ፕሬዝዳንታዊ ሕገመንግሥታት ይባላሉ:: በአሜሪካ ፕሬዝደንቱ የመንግሥት አስፈጻሚ፣ ኮንግረሱ ደግሞ የሕግ አውጪነት ሥልጣን እንዳላቸው በሕገመንግሥቱ የተቀመጠ ቢሆንም የሕግ አውጪውንና አስፈጻሚውን ሥልጣን በሚዘረዝረው የሕግ ድንጋጌ ለፕሬዝደንቱም ሆነ ለሕግ አውጪው አካል የተሠጠው ሥልጣን ከሞላ ጐደል ከፍተኛና ተመጣጣኝ ሊባል የሚችል በመሆኑ ሕገመንግሥቱ ፕሬዝደንታዊ መባሉ ከዚህ ከፕሬዝደንቱ ጐላ ያለ የሥልጣን ባለቤትነት ጋር የተያያዘ ነው:: ፕሬዝዳንቱ በቀጥታ በሕዝብ የሚመረጥና ራሱን የቻለ ሠፊ ሥልጣን የተሠጠው መሆኑ፣ ተጠሪነቱም በቀጥታ ለመራጩ ሕዝብ እንጂ ለሕግ አውጭው

አለመሆኑ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ ከፓርላማው የተለየ መሆኑን ለማሣየት ነው፡፡ ከዚህ በተለየ አስፈፃሚው ለሕግ አውጭው አካል ተጠሪ የሆነበት አሠራር ሲኖር ደግሞ ያለው ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ፓርላሜንታሪ ነው ማለት ነው፡፡

## 3.3 የሕገ መንግሥት መርሆዎች

### 3.3.1 የመንግሥት ሥልጣን ክፍፍል መኖር

የመንግሥት ሥልጣን ክፍፍል መኖር በዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት ሥርዓት ውስጥ እንደ ቁልፍ መርሆ ተደርጐ ይወሠዳል፡፡ ይህ መርህ አስፈላጊ የሆነባቸው መሠረታዊ መነሻዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የሕዝብን ጥቅም በሚጐዳ አኳኋን አደጋ ሊያመጣ የሚችል የሥልጣን መሠባሠብ አንድ ቦታ ላይ የሚሆንበትን ሁኔታ ለማስቀረት የተለያየ የሥራ ድርሻ ላላቸው የመንግሥት አካላት ሥልጣጣንን ማከፋፈል ይሻላል ከሚል አስተሣሠብ የሚነሣ ነው፡፡ ሶስቱም የመንገሥት ሥልጣኖች ማለትም ሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈፃሚውና ሕግ ተርጓሚው በተመሣሣይ እጆች ወይም በጥቂት ሠዎች፣ ከዚያም በላይ በአንድ ሠው እጅ ውስጥ ከተከማቸ ፍጹማዊ የሆነ ሥልጣን ይፈጠራል፡፡ ሥልጣን በሕግ አስፈጻሚው እጅ ውስጥ ተሠባስቦ ከገባ መጥፎም ይሁን ጥሩ ሕግ ራሱ በፈለገው መንገድ ያወጣል፣ ዜጐችን ሕግ ጥሳችኋል እያለም ራሱ ይቀጣል፡፡ እንዲህ አይነቱ አሠራር ደግሞ የተወሠኑ ባለሥጣኖች ከሣሽም፣ ተከራካሪም፣ ዳኛም ሆነው እንደሻቸው በዜጐች ነጻነትና መብት ላይ እንዲቀልዱ መብት ይሰጣል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ስልጣንና ኃላፊነት ለሶስቱም የመንግስት አካላት ተከፋፍሎ መሰጠት አለበት የሚለው ሀሣብ ተመራጭ ሆኖ ተገኘ፡፡ በዚህም መሠረት ሕግ የማውጣቱን ሥራ በዜጐች ምርጫ ለሚቋቋመው ፓርላማ ወይም ሕግ አውጭ አካል፣ ሕጉን የማስፈፀሙን ስራ ደግሞ የመንግስትን ተግባር እንዲያከናውን ለሚመደበው የመንግሥት አስፈፃሚ አካል እንዲሁም ሕግ የመተርጐሙን ሥራ ለሕግ ተርጓሚው ወይም ጁዲሺየሪ ለሚባለው አካል ማከፋፈል በማስፈለጉ ዴሞክራሲያዊና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት የመሠረቱ አገሮች የመንግሥት ሥርዓታቸውን የሚመሩት በዚህ ዓይነቱ የሥልጣን ክፍፍል መርህ ነው፡፡

ሌላው የሥልጣን ክፍፍል አስተሣሠብ የተመሠረተው የመንግስት ሥልጣን አካላት የስራ ክፍፍል እንዲኖራቸው ብቻ ሣይሆን ተለያይተው መቋቋምም አለባቸው በሚል ግንዛቤ ነው፡፡ የሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ አካላት በጥብቅና በጥንቃቄ ተለይተው የየራሣቸው ተቋም ኖሯቸው መደራጀት አለባቸው የሚለው መርህ የአሜሪካን ሕገመንግሥት መልክ የወሠነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአንግሊዝ ደግም ትልቅ ድርሻ የተሠጠው አሠራር አይደለም፡፡ እንዳውም በእንግሊዝ የሕግ ተርጓሚው ሚና ግልጽ ሆኖ የሚታይ ባይሆንም የዳኝነት ነጻነት መኖር አለበት የሚለው ነጥብ ግን ተቀባይነት ያለውና የሚሠራበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሥልጣን  አካላቱን በጥብቅ መለየት የሚለው ግን ችግር የሚፈጥርና ወደ ግጭትም ሊያስገባ የሚችል ስለሚሆን በሶስቱም አካላት ያለው የተወሠነ ግንኙነት ተጠብቆ መቆየት አለበት የሚል መንገድ ይከተላሉ፡፡ በጥቂቶች እጅ የተሠባሠበ ሥልጣን መኖር የለበትም ከሚለው አቋማቸው ጐን የተወሠነ ግንኙነት በመካከላቸው መኖሩ ተፈላጊ ነው የሚለውን መስመር ይዘው ይሠራሉ፡፡ በአሜሪካ ሕገመንግሥት ደግሞ መለያየት ብቻ ሣይሆን በደንብና በጥብቅ መለያየት አለባቸው የሚል አስተሣሠብ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ሥልጣንን በብቸኝነት የያዙ የመንግሥት ሥርዓቶች፣ የአንድ ፓርቲ አመራር የሚከተሉና ወታደራዊ ጁንታዎች ወይም ሕገመንግሥታዊ አምባገነኖችና የፖሊስ መንግሥት  ተብለው የሚጠሩት ፈላጭ ቆራጮች ያለባቸው መሠረታዊ ችግር የእነዚህ የሥልጣን አካላት የሥራ ክፍፍልና ተለይቶ አለመደራጀት ችግር ነው፡፡ ሕግ የሚወጣው፣ የሚፈፀመውና የሚተረጐመው በአንድ ወይም በጥቂት ግለሠቦች ነው፡፡ የመንግሥት ሥልጣን አካላት በጥብቅ ተለይተው እንዲደራጁ የሚለው አስተሣሠብ የእርስ በርስ ቁጥጥርን በማስፈን

የሥልጣን ሚዛንን ማስጠበቅ ይቻላል ከሚለውና ቢያንስ በአስፈጻሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ልዩነት መኖር አለበት የሚለውን ከሚደግፈው ከሕግ የበላይነት መርህ ጋር በጥብቅ የተሣሠረ ነው:: ሁለቱንም ለየብቻ ለመመልከት የሚሞከር ሲሆን በቅድሚያ የእርስ በርስ ቁጥጥርና የሥልጣን መመጣጠን (ሚዛን) የሚለውን መርህ እናያለን::

## 3.3.2 የእርስ በርስ ቁጥጥርና የሥልጣን ሚዛን ( Check and Balance ) መርህ

የእርስ በርስ ቁጥጥርና የሥልጣን ሚዛንን የመጠበቅ መርህ በንድፈ ሀሣብ ደረጃ በሁሉም ዴሞክራሲያዊ የሕገመንግሥት ሥርዓቶች ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በአፈጻጸም ግን አንዱ የመንግስት ሥርዓት ከሌላው የሚለይበት ሁኔታ አለ:: ይኽንን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ አሁንም የእንግሊዝና የአሜሪካን ልምዶች ማገናዘብ ይቻላል:: ይኽንን መርህ በሚመለከት እንግሊዞች በሥራ ላይ የሚያውሉበት መንገድ አሜሪካኖቹ ከሚሠሩበት ይለያል:: እንግሊዞች የመንግሥት ሥልጣን አካላትን መለያየት ችግር የሚያስከትልና ወደግጭትም የሚያስገባ ስለሚሆን በመንግሥት አሠራር ውስጥ የሚፈለገው ቅንጅት ይጠፋል፣ የመንግሥት ድካምና ጥረትም ይመክናል የሚል እምነት ስላላቸው የሥራ ክፍፍል ማድረግ በቂ ነው ከሚለው ነጥብ ይነሣሉ:: ከሥራ ክፍፍሉ ጐን ደግሞ ቅንጅትም አብሮ ይኖራል ስለሚሉ ቁጥጥሩ በሕግ አውጭና በሕግ አስፈጻሚ፣ በሕግ ተርጓሚና በሕግ አስፈጻሚው መካከል ሣይሆን ከዚህ በተለየ መንገድ መፈፀም አለበት ነው የሚሉት:: ይኽንንም ሥርዓት የጋራ ቁጥጥርና ሚዛን አጠባበቅ (Mutual Checks and Balances ) ብለው ነው የሚጠሩት:: በዚህም መሠረት የሕግ አውጭው ሥልጣን በሀውስ ኦፍ ኮመንስና በሀውስ ኦፍ ሎርድስ መካከል ስለተከፋፈለ፣ የካቢኔው ሥልጣን ከንግስቲቱ ሁልጊዜ በሚቀርብበት ተቃውሞና ወቀሣ፣ የሲቪል ሰርቪሱ አስተዳደር በሕግ አውጭው ክትትል ስለሚደረግበት ቁጥጥሩና ሚዛኑ በዚህ መንገድ ይሠራል ብለው ያምናሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በሌሎችም መስኮች የሥልጣን ክፍፍል ስላለ ሚዛኑን መጠበቅ ይቻላል ይላሉ:: ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት በየግዛቱ የሚካሄዱት የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎች በተወሠነ ደረጃ ከመንግሥት አስፈጻሚው አካል ቁጥጥር ነጻ መሆናቸውንና ሀሣብ ሊገለጽባቸው የሚችሉ መንገዶችን መንግሥት የማይቆጣጠራቸው መሆኑን ነው::

አሜሪካኖቹ ደግሞ ከዚህ በተለየ መንገድ የሥልጣን አካላት በጥብቅ መለያየት የሥልጣን ብልግና አደጋን ይቀንሣል፣ የመንግሥትንም ስራ ብቃት ያሣድጋል ብለው ያምናሉ:: ከዚህ በተጨማሪ የእርስ በርስ ቁጥጥር መኖሩ የሥልጣን ሚዛንን ያስጠብቃል ነው የሚሉት:: በዚህም መሠረት በአሜሪካ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት እያንዳንዱ የመንግሥት ዲፓርትሜንት አንዱ በሌላው ላይ የእርስ በርስ ቁጥጥር ብቻ የሚቆም ሣይሆን በሁለቱ ሕግ አውጭ ም/ቤቶች መካከል፣ በግዛቶችና በብሔራዊ መንግስታት መካከልም የሚሠራበት ነው:: እያንዳንዱ ዴፓርትሜንት ከአንድና ከዚያም በላይ በሆኑ ሌሎች ዲፓርትመንቶች ሥራ ተሣትፎ እየደረገ የሚቆጣጠርበት ስልጣን አለው::ለምሣሌ ፕሬዝዳንቱ በኮንግረሱ ውሣኔ ላይ ያለው ድምጽን በድምጽ የመሻር (Veto Power) ሥልጣንና ኮንግረሱ በተራው የፕሬዝዳንቱን ድምጽን በድምጽ የመሻር ውሣኔ በመቃወም (Over-ride ) ያለው ሥልጣን፣ በሕግ አውጭው ሥልጣንና በሕግ አስፈጻሚው ውሣኔዎች ላይ ሕግ ተርጓሚው ሕጋዊ ቁጥጥር የሚያደርግበት አሠራር፣ ፕሬዝዳንቱ ዳኞችን ለመሾም የሴኔቱን ድጋፍ ማግኘት ያለበት መሆኑ እንዲሁም ኮንግረሱ ፕሬዝዳንቱን ለመክሰስ ያለው ሥልጣንና የመሣሠሉት የእርስ በርሱን ቁጥጥርና የሥልጣን ሚዛን አጠባበቁን ውጤታማነት የሚያሣዩ ናቸው:: በግዛቶችና ከዚያም በታች ባሉ የመንግሥት አካላት ይኸው መርህ ይሠራበታል:: ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን ተቀባይነት ያለው እንዲሆንም አድርጐታል::

## 3.4 በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ስርዓት ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 3.4.1 ሉዓላዊነት

*በሕገ-መግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ ስላለው የፓርላማ ሉዓላዊነት ገለፃ ከማድረግ በፊት ሉዓላዊነት የሚባለውን ፅንሠ-ሃሳብ ራሱን በመጠኑ ማብራራት ያስፈልጋል:: ሉዓላዊነት በቆየው ትርጉሙ ንጉሣዊ አገዛዝ ከመለኮታዊ ኃይል የተሰጠውን ገደብ የሌለው ከፍተኛ ሥልጣን ለመግለጽ ያገለግል እንደነበር ይታወቃል:: አሁን ያለው ትርጉም ደግሞ ከዚህ የተለየ ነው:: ሉዓላዊነት የሚለው ፅንሰ ሃሣብ አንድ መንግሥት በተወሠነ የዓለም ክፍል ውስጥ የሚገኝን ሕዝብና የጂኦግራፊ ክልል በባለቤትነት ለመያዝ፣ ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ያለውን መብት የሚመለከት ነው:: ይኸም ማለት አሁን የዓለም ሕብረተሰብ በተቀበለውና በሚጠቀምበት ሕግ መሠረት እውቅና አግኝቶ የያዘውን የጂኦግራፊ ክልልና በዚሁ ውስጥ የሚገኘውን ሕዝብ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር አንድ መንግሥት ያለው መብት በሌላ ውጫዊ ኃይል ሊጣስና ሊነጠቅ የማይገባና የማይቻል መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ይህ ትርጉም የጽንሠ-ሀሣቡን ውጫዊ ገፅታ የሚያመለክት ሲሆን ውስጣዊ ገጽታውን የሚያመለክት ትርጉምም እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል::*

*የሉዓላዊነት ትርጉም በውስጣዊ ገፅታው ሲታይ ደግሞ በሕጋዊ መንገድ የተገኘ የሥልጣን ባለቤትነትንና ቁጥጥርን ይመለከታል:: በዚህም መሠረት አንድ መንግሥት በስልጣን መንበር ላይ ስለተቀመጠ ብቻ ሉዓላዊ ሥልጣን አለው ለማለት አይቻልም:: አንድ መንግሥት ሉዓላዊ ሥልጣን ሊኖረው የሚችለው የአገሬው ሕዝብ ሥልጣን እንዲይዝ ተስማምቶ የፈቀደ እንደሆነ ብቻ ነው:: በዚህ መንገድ የተያዘ ሥልጣን ሕጋዊ ሥልጣን ከመሆኑ በተጨማሪ አንድ መንግሥት በሥልጣን ክልሉ ውስጥ የሚገኘው ሕዝብ ውሣኔዎቹን እንዲያከብርና እንዲፈጽም ለማስገደድ የሚያስችል ሉዓላዊነት እንዲኖረው የሚያደርግ ነው:: ከዚህ ውጭ የተያዘ ሥልጣን ሕጋዊነትና ሉዓላዊነት ያለው ሳይሆን በተለያዩ የማስገደጃ ዘዴዎች ላይ የተመሠረተ የኃይል ሥልጣንና ሉዓላዊነት እስካለው ድረስ ሕግ በሚፈቅድለት መሠረት ውሣኔ ለመለወጥና ውሣኔዎቹ በዜጐች እንዲከበሩ ለማድረግ የፖሊስን፣ የፍርድ ቤትንና የመሳሰሉትን የሕግ ማስከበሪያና መቆጣጠሪያ ተቋማት ሊጠቀም ይችላል:: በዚህ መንገድ ሥልጣንና ኃይልን አንድ ላይ አጣምሮ ቢይዝ ሕጋዊነቱንም፣ ሉዓላዊነቱንም ሊያጣ አይችልም::*

*ሊበራል ዴሞክራሲን የሚከተሉ መንግሥታት ሥልጣንና ኃይልን አንድ ላይ እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸውን ሕጋዊነትና ሉዓላዊነት የሚያገኙት ሕዝብ በምርጫ ወቅት ከሚሠጣቸው ስምምነትና ፈቃድ ነው:: በተቃራኒው ኃይል ብቻ ኖሯቸው ሥልጣን የሌላቸው መንግሥታት ሕዝብ በምርጫ አማካይነት ፈቃድና ስምምነቱን ያልሰጣቸው በመሆኑ ሕጋዊነትም ሉዓላዊነትም አይኖራቸውም:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሕጋዊነትና ሉዓላዊነት ያለው ሥልጣን ቢኖራቸውም ይኸንን ሥልጣናቸውን የሚያስፈጽሙበት ኃይል የሌላቸው መንግሥታት ያጋጥማሉ:: ይህ የሚሆነው በውጭ ወረራ፣ በመፈንቅለ መንግሥትና በሌላም የኃይል እርምጃ ሕዝብ በምርጫ ፈቃድና ተሰማምቶ የሰጣቸውን ሥልጣን ተነጥቀው ለስደት የሚዳረጉ መንግሥታት በሚያጋጥምበትና ሥልጣናቸውን ለመጠበቅም ሆነ ለማስመለስ ኃይል በሚያጡበት ጊዜ ነው:: ስለዚህ ሥልጣንና ኃይል ያላቸው መንግሥታት ሲኖሩ ሕጋዊነት ያላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ በሕጋዊ መንገድ የጨበጡትን ሥልጣን ለመጠበቅና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ኃይል ጭምር ያላቸው ናቸው ማለት ነው:: ከዚህ ሌላ ሥልጣን ኖሯቸው ኃይል የሌላቸው ከሆነ በሕዝብ ፍቃድና ስምምነት ያገኙትን ሥልጣን ለመጠበቅና በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችለውን አቅም በአንድ ወይም በሌላ ሕገወጥ መንገድ ያጡ ናቸው ማለት ነው::*

አልፎ አልፎ ሥልጣንም ኃይልም የሌላቸው መንግሥታት ያጋጥማሉ:: ይህ የሚሆነው መጀመሪያ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለምሣሌ በመፈንቅለ መንግሥት፣ በአመፅ ወይንም በወረራ ሥልጣን ይይዙና ከተወሠነ ጊዜ በኋላ በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ለምሣሌ ሕዝቡ አልገዛም ብሎ ሲያምፅና ከቁጥጥር ውጪ ሲሆን ወይንም ዓለም-አቀፍ መገለል የሚያስከትል ውግዘትና ማዕቀብ ይኖርና እንደመጀመሪያው እያስፈራሩና እያፈኑ መግዛት ሲሳናቸው ነው:: እንደዚህ ዓይነቶቹ መንግሥታት የሚያጋጥማቸው ችግር ሥልጣንም ኃይልም ማጣት ብቻ ሳይሆን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ሕጋዊነትና ሉዓላዊነት የሌላቸው መሆኑም ጭምር ነው::

በዚህ ገለፃ መሠረት መገንዘብ የሚቻለው ሉዓላዊነት በሕጋዊ መንገድ፣ በዜጎች ፈቃድና ሥምምነት የተገኘ ሥልጣንን የሚመለከት መሆኑን ነው:: ሕጋዊ በሆነ አግባብ የተመሠረተ ሉዓላዊነት በተለያየ መንገድ ሊገለፅ የሚችል ነው:: በመሆኑም ፖለቲካዊ ሉዓላዊነት፣ ኤኮኖሚያዊ ሉዓላዊነት፣ ፓርላማዊ ሉዓላዊነት ወዘተ. እየተባለ ሊገለጽ የሚቻል ሲሆን አሁን ለማየት የሚፈለገው በቅድሚያ የፓርላማ ሉዓላዊነትን፣ ቀጥሎ ደግሞ የፖለቲካ ሉዓላዊነትን ነው::

## 3.4.1.1 የፓርላማ ሉዓላዊነት

በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ዜጎች በራሣቸው ፈቃድና ስምምነት ተወካዮቻቸውን መርጠው በሚያቋቁሙት መንግሥት የሥልጣን ባለቤት ይሆናሉ:: ለመንግሥት ሥልጣን ዜጎች የመረጧቸው ተወካዮች የሚገኙበት ተቋም ፓርላማ (የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት) የሚባለው ሲሆን የሕዝብ ሥልጣን ባለቤትነትና የበላይነት የሚገለጽበት ሕጋዊ አሠራር ደግሞ የፓርላማ ሉዓላዊነት ይባላል:: ቀደም ሲል ስለሉዓላዊነት አጠቃላይ ምንነት ሲገለጽ እንደተብራራው አሁንም የፓርላማ ሉዓላዊነት ሲባል ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን የያዘ ፅንሠ-ሀሣብ ነው:: በዚህም መሠረት ፓርላማ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በዜጎች ፈቃድ የተመሠረተ ሕጋዊ የውክልና ምክር ቤት መኖሩን የሚያመለክት ነው:: በሊበራል ዴሞክራሲ አመለካከት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን ተከትሎ የሚመሠረት የሕዝብ ሥልጣን በአንድ ወይም በተወሰኑ ጥቂት ሰዎች እጅ ሥር ስለማይወድቅ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለአንድ አካል፣ የማስፈጸም ደግሞ ለሌላ አካል እንዲሁም የመተርጐም ሥልጣን ለሌላ መከፋፈል ይኖርበታል:: እናም ሕግ የማውጣት ሥልጣን የያዘው አካል የፓርላማ ሉዓላዊነት ወይንም የሕዝብ ሥልጣን ሉዓላዊነት የሚገለጥበት ፓርላማ የሚባለው አካል ነው::

እዚህ ላይ ዓለማችን ውስጥ በፓርላማ ሉዓላዊነት ላይ የተለያየ ዓይነት የአሠራር ልምድ እንዳለ መገንዘብ ተገቢ ነው:: ይኸውም ፕሬዝዳንታዊ ሕገ-መንግሥት ባለባቸው አገሮች የሕግ-አውጪነቱ ሥልጣን በከፊል ለፓርላማ ተሰጥቶ በከፊል ለሕግ-አስፈጻሚው (ፕሬዝዳንቱ) የተሰጠ በመሆኑ ሁለቱም የሕዝብ ሥልጣን ሉዓላዊነት የሚገለጥባቸው ሆነው ያገለግላሉ:: ፓርላማው ፕሬዝዳንቱን የሚቆጣጠርበት መንገድ ሲኖረው ፕሬዚደንቱም በተራው ፓርላማውን የሚቆጣጠርበት አሠራር አለ:: የዚህ ዓይነቱ የሉዓላዊ ሥልጣን ክፍፍልና የእርስ-በርስ ቁጥጥር በአሜሪካና በፈረንሣይ መንግሥታት አሠራር ውስጥ ይንፀባረቃል:: እንደውም በፈረንሣይ ፕሬዝዳ ንታዊ ሕገ-መንግሥት ሥርዓት ውስጥ ፕሬዝዳንቱ ፓርላማውን መበተን፣ ውሣኔ-ሕዝብ መጥራትና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ የሚችል ሲሆን ፕሬዝዳንቱ ብቻ ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው የመንግሥት አስፈጻሚ አካልም በፓርላማው ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግበት ሠፊ ዕድል አለው:: ለምሣሌ በብሔራዊ ምክር ቤቱና በሴኔቱ ሊታዩ የሚችሉ ማንኛቸውም ጉዳዮች በአጀንዳ እንዲያዙለትና እንዲመክርባቸው የማድረግ ብቻ ሳይሆን በቀረቡት አጀንዳዎች ላይ ተገቢ ያልመሰለውን ማሻሻያ ሁለቱ ምክር ቤቶች ቢያደርጉ የመቃወም እንዲሁም ለሕዝበ-ውሣኔ እንዲቀርብ የማድረግ ሥልጣን ጭምር ተሠጥቶታል:: አዲስ የፓርላማ ምርጫ እንዲደረግ ለሕዝብ ጥያቄ እስከማቅረብ ድረስ ይችላል:: በአሜሪካ ደግሞ ፓርላማው (ኮንግረሱ) ሕገ-

መንግሥታዊ ሥርዓቱን ተከትሎ መሥራቱን ሕግ-ተርጓሚው የአሜሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይከታተለዋል። ከዚህም አልፎ የፓርላማው ውሣኔ ሕገ-መንግሥቱን መሠረት ያደረገ አይደለም ወይንም ከሕገ-መንግሥቱ ጋር ሊቃረን የሚችል ነው ብሎ ካመነ ሕግ-ተርጓሚ የሆነው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥራ ላይ እንዳይውል ሊከለክለው ይችላል። ፕሬዘዳንቱም የኮንግረሱን ውሣኔ የሚሽርበት ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን አለው።

ፓርላሜንትሪ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ባለባቸው አገሮችም ቢሆን የፓርላማ ሉዓላዊነት በተመሣሣይ መንገድ ሥራ ላይ እንደማይውል የታወቀ ነው። ለምሣሌ አውስትራሊያና እንግሊዝ ሁለቱም ፓርላሜንታሪ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የሚከተሉ ቢሆንም በአውስትራሊያ ፓርላማው ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ያስቀመጠለትን ሕጋዊ ድንጋጌ ተከትሎ እንዲሠራ የሚደረግበት ቁጥጥርና ገደብ ያለ ሲሆን በእንግሊዝ ደግሞ የፓርላማው ሥልጣን ምንም ዓይነት ገደብ የማይጣልበትና ፍጹም ነው። የእንግሊዝ ፓርላማ በሌሎቹ ፓርላሜንታሪ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች የሚደረገው ዓይነት ቁጥጥር ፈፅሞ የማይደረግበትና ነፃ ነው። ከሁሉም በላይ ማንኛውንም ሕግ ሊያግድ፣ ሊያሻሽል ወይንም ወደጐን ገሸሽ ሊያደርግ ይችላል። የዚህ ዓይነት ሥልጣኑን በማንኛውም ሕግ ላይ (በራሱ ሕልውና ላይ ሳይቀር) ተፈፃሚ ሊያደርገው ይችላል። በተጨባጭ የእንግሊዝ ፓርላማ ሥልጣን «ሕገ-ወጥነትን» ሕጋዊ ለማድረግ እስከ መቻል የሚዘልቅ ነው የሚሉ ብዙ የፖለቲካ ሰዎች አሉ። ምክንያቱም የፍርድ ቤትን ውሣኔ ወደጐን ትቶ በራሱ ውሣኔ የሚሄድ ሥልጣን ያለው ፓርላማ ስለሆነ ነው።

በእንግሊዝ ፓርላማ አሠራር ላይ የዳኝነት አካሉ እጁን አያስገባም። የአሜሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚያደርገው ወይንም በፓርላመንታሪ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት የሚመራው የጀርመን ፌደራል ሕገ-መንግሥታዊ ምክር ቤት እንደሚያደርገው የእንግሊዝን ፓርላማ ውሣኔ ከሕገ-መንግሥት መንፈስ የወጣ ነው ብሎ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚያደርግ አካል የለም። ከዚህ ጐን የእንግሊዝ ፓርላማ ሉዓላዊነት የማይገደብና ፍፁም የሆነበት ሕጋዊ መሠረት እንዳለው መገንዘብም ጠቃሚ ነው።ይኸውም የመጀመሪያው ምክንያት ፓርላማው ሥልጣኑን ተግባራዊ በሚያደርግበት ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ካቢኔው በሚያቀርበው አቅጣጫ መሠረት የሚመራ መሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ ግን የእንግሊዝ ሕዝብ ይኸንን አሠራር ተስማምቶ የፈቀደ መሆኑ ነው። በመጨረሻም መታየት ያለበት ቁም ነገር ፕሬዘዳንታዊ ሕገ-መንግሥት ሥርዓት ተከታይ አገሮች ሥራ ላይ እየዋለ ያለው የፓርላማ ሉዓላዊነት በአፈፃፀም ረገድ አንዱ ከአንዱ ይለያይ እንጅ መሠረታዊ መርሁና ግቡ ግን ዞሮ ዞሮ አንድ ነው። እሱም በዜጎች ስምምነትና ፈቃድ የተመሠረተ የሕዝብ ሉዓላዊነት የሚገለጽበት መሆኑ ነው። የፓርላማ ሉዓላዊነት ማለት የሕዝብ ሥልጣን የበላይነት ማለት ነው። የዚሁ የሕዝብ ሥልጣን የበላይነት የሚረጋገጠው ደግሞ ዜጎች ሕግ የማውጣት ውክልና የሰጡት ፓርላማ (የእንደራሴዎች ምክር ቤት) ሕግ ከሚፈቅደው ሥርዓት ውጭ ያልተገደበ፣ የመወሰን ነፃነቱ የማይገሰስና የውሳኔው ተፈጻሚነት የማይጣስ መሆኑ ነው።

### 3.4.1.2 ፖለቲካዊ ሉዓላዊነት

የፓርላማ ሉዓላዊነት በሚገለጽበት ጊዜ ሕግ ከሚፈቅደው አሠራር ውጭ ገደብ የማይጣልበትና ከፍተኛ የተፈፃሚነት ኃይል ያለው የሕዝብ ሥልጣን መገለጫ መሆኑ ተብራርቷል። ሕግ ከሚፈቅደው አሠራር ውጭ ተፈፃሚ የሚሆን የሕዝብ ሥልጣን አለመኖሩ የሚያመለክተው የሕግ የበላይነት ከሚባለው መርህ ውጭ የሆነ የሥልጣን ሕጋዊነት ማረጋገጫ አለመኖሩን ነው። ይሁን እንጅ ሕግ በራሱ የመጨረሻው ሥልጣን ይሆናል ማለት ሳይሆን ሕዝብ የወከላቸውን ሰዎች የያዘው ፓርላማ የሚኖረው ሥልጣን የመጨረሻና ሕጋዊ እንዲሆን ያስችላል ማለት ነው። በፓርላማ ውስጥ የሚገኙ የሕዝብ ተወካዮች ጥሩ ወይም መጥፎ ሕግ ሊያወጡ ይችላሉ። የሚያወጡት ሕግ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንዲጠናከር የሚያስችል ወይም አምባገነን መንግሥት እንዳይኖር የሚያደርግ

ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን የፈለገው ዓይነት ሕግ ይሁን ፓርላማ እስከወሠነ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

አንዳንድ ጊዜ የሕግ የበላይነት መኖር ፓርላማ ሥልጣኑን ተጠቅሞ መጥፎ ውሣኔ እንዳያሳልፍ የሚከላከለው ብቸኛ መርህ ላይሆን ይችላል:: የሕግ የበላይነት የሚለው መርህ ራሱ የሕግ-አውጭው አካል (ፓርላማ) ያቀፋቸው ሰዎች እንደሚወስኑት ጉዳይ በተለያየ መንገድ ሊተረጉሙት የሚችሉትና ፍፁም አንድና ተመሣሣይ የሆነ ግንዛቤ የሚያዝበት መርህ ተደርጐ ሊወሰድ የማይችል ነው:: ይህ ከሆነ ሕዝቡን ከጨቋኝ ሥልጣን መጠበቅ የሚቻልበት መንገድ ምንድን ነው ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው:: በፓርላማ ሥልጣን በሕዝብ ላይ ሊደርስ የሚችል ድንገተኛ አደጋ ቢፈጠር ፈጣን መከላከያ መንገዶች ስለመኖራቸው በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ፓርላሜንታሪ የሆነ መንግሥት የሚፈተንባቸው የተወሠኑ ሕጐች፣ መርሆዎችና ተቋሞች ስለመኖራቸው ግን እርግጠኛ መሆን ይቻላል::

አንድ በግልጽ ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ ፓርላማው ለመራጩ ሕዝብ ፍላጐት የሚገዛ ነውን? የሚለው ጥያቄ ነው:: ነገር ግን ይኸ ጥያቄ ራሱ ሌሎች ብዙ ጥያቄዎችን የሚያስከትል ነው:: ለምሣሌ ምርጫዎች ትክክለኛውን የጊዜ ገደብ ተከትለው መካሄድ አለመካሄዳቸውን ሕዝቡ፣ የተለያየ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚወክሉ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ለውድድር ቀርበውለት በነፃነት ሊመርጥ መቻል አለመቻሉን፣ ሁሉም ዕድሜያቸው ለመምረጥና ለመመረጥ የደረሱ ዜጎች ይህንኑ መብታቸውን በነጻነት ሊጠቀሙ መቻል አለመቻላቸውን፣ ሥልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ አሸናፊነት ለመጠበቅ ሲባል በዘር፣ በሃይማኖት፣ በሀብት፣ በፖለቲካ እምነትና በመሳሰሉት ምክንያቶች የተገለሉ ዜጐች መኖር አለመኖራቸውን፣ መንግሥት መራጩ ሕዝብ ከሠጠው የምርጫ ውሣኔ የሚቃረን ውጤት ያቀርባል ወይንስ ትክክለኛውን ውጤት አክብሮ ይቀበላል የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ማንሣት ይቻላል:: ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች በሙሉ አወንታዊ መልስ ከተገኘ የሕዝቡ ምኞትና ፍላጐት በፓርላማው ይከበራል የሚለውን መልዕክት ያስተላልፋል:: በመጨረሻም በዚህ አወንታዊ አሠራር የሚመራ ፓርላማ የሚያሳልፈው ውሣኔ ከመራጩ ሕዝብ አብዛኛው ሊቀበለው የሚችለው እንደሚሆን የማያጠራጥር ነው:: ስለዚህም የፓርላማው ሉዓላዊነት ሕጋዊ የሚሆነው መራጩ ሕዝብ ባለው ፖለቲካዊ ሉዓላዊነት ምክንያት መሆኑ በግልፅ ይረጋገጣል ማለት ነው::

የሆነ ሆኖ ምርጫ የሚካሄደው በአራት ወይም በአምስት ዓመት የጊዜ ርቀት ውስጥ ነው:: በጦርነት ጊዜ ደግሞ ከዚህም የረዘመ ቆይታ ሊፈጠር ይችላል:: በዚህ ጊዜ አንድ ኃላፊነት የጐደለው መንግሥት ገና ከመጀመሪያው የዘፈቀደ የአሠራርና በሕግ የማይገዛ የኃይል ድርጊት አሰፍናለሁ ብሎ ቢወስን ሕዝቡ ሁኔታው ሳይዘገይ አስቀድሞ የሚገነዘብበትና መከላከያ መፍትሔ የሚፈልግበት መንገድ ምን ሊሆን ይችላል ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል:: እዚህም እንደገና የሚሰጠው ፍርድ ለተወሠኑ ተገቢ ጥያቄዎች በሚገኘው መልስ ላይ የተመሠረተ ነው የሚሆነው:: በዚህ ረገድ መነሣት ያለባቸው ጥያቄዎች በፓርላማው ውስጥ ተቃዋሚዎች አሉ ወይንስ የሉም? ገዥውን ፓርቲ ለመተቸት የሚያስችል አስተያየት ለማሰማት ዕድሉ አላቸው ወይንስ የላቸውም? የፕሬስ ተቋማት መንግሥትን ለመተቸት ነፃ ናቸው አይደሉም? ዳኞች በዜጎችና በባለሥልጣኖች መካከል የሚነሣ የሕግ ክርክር ሲኖር ወገንተኝነት ሳያሳዩ በገለልተኝነትና በነፃነት መወሠን ይችላሉ ወይንስ አይችሉም? የሚሉት ናቸው:: ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ በሙሉ አሉታዊ ከሆነ ግን አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ የማይታለፍ ነው የሚሆነው::

በዚህም መሠረት የሕግ የበላይነት የሚለው መርህ ሕግ-አውጪ አካሉ የሕዝብ ወኪልም ኃላፊነት የሚሠማው የሕዝብ ሥልጣን አካልም መሆኑን ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ሌሎች ተጨማሪ መርሆዎች መጠናከር ይኖርበታል:: እነዚህም አንደኛ ፓርላማው የመራጩን ሕዝብ ፍላጐት የሚወክሉ ሰዎችን በአባልነት የያዘ መሆን ይኖርበታል:: ሁለተኛ ሰዎች የራሣቸውን አስተያየት እንዲገነቡና በግልጽም እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸው ይገባል:: ሦስተኛ ማንኛውም ዜጋ ከሌሎች ዜጎች ጋር ለመደራጀት ያለው ነጻነት ሊከበርለት ይገባል:: አራተኛ

በማኅበረሰቡ ውስጥ ለሚገኝ ማንኛውም ቡድን ለምሣሌ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ ፖሊሶች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የተወሠኑ የፓርቲ አባላት በሕግ ተቀባይነት የሌለው ልዩ መብት ሊሰጣቸው አይገባም የሚሉት ናቸው:: በእንደነዚህ ዓይነት መርሆዎች ካልተጠናከረ በስተቀር የሕግ የበላይነት መርህ ብቻውን ትርጉም አይኖረውም:: ኃላፊነት የማይሰማው መንግሥት ከሚያሰፍነው የዘፈቀደ አገዛዝ መከላከያ ሆኖ ሊያገለግልም አይችልም:: ለምሣሌ በነፃ ሃሣብን የመግለጽና በነፃ የመደራጀት ነጻነት ላይ ተፅዕኖና ጣልቃ-ገብነት እስከተፈፀመ ድረስ የተወሠነ ጊዜ እየጠበቁ ምርጫ ማወጅ ፎርማሊቲን የመጠበቅ ጉዳይ ብቻ እንጅ የሕግ የበላይነትን የማክበር ጉዳይ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም:: ነገር ግን ከላይ ከተጠቀሱት መርሆዎች ጋር ከተቀናጀ የሕግ የበላይነት ራሱ መሠረታዊ ጥቅም ይኖረዋል::

## 3.4.2 የሕግ የበላይነት

የሕግ የበላይነት የሚለው መርህ ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙን ለመረዳት ከባድ ባይሆንም በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ብዙ ችግሮች እንደሚያጋጥሙ የታወቀ ነው:: በሕብረተሰቡ ውስጥ ውሣኔ የመስጠት ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ውሣኔያቸውን የሚሠጡት በተቀመጡ አጠቃላይ ሕጐችና መርሆዎች ላይ ተመሥርተው ነው:: እነዚህ ውሳኔዎች ደግሞ በፍርድ ቤቶች፣ በፖሊስ፣ በአስተዳዳሪዎች ወይንም በሌሎች አካላት አማካይነት በተሰጣቸው የሥልጣን ክልል ውስጥ እንዳሉ ተግባራዊ መሆን የሚገባቸው ናቸው:: እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ በውሣኔ አወጣጡ ሂደት ገለልተኝነት እንዴት ይረጋገጣል? የሚለው ነው:: ችሎት ፊት በሚቀርብ እያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ግለሰብ ዳኞች ትክክለኛና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ብይን ሊሰጡ አይችሉም የሚለው ሥጋት ብዙ ከተመዘነ በኋላ እንደመፍትሔ የተቀመጠው ዳኞች በተለያዩ ጉይዮች ላይ በቅድሚያ የተቀመጠን ሕግ እንዳለ ተግባራዊ ከማድረግ የተለየ ኃላፊነት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው:: ይኸንን አስተሳሰብ ተከትሎ እኩልነትንና ነፃነትን በማረጋገጥ ወሳኝ አስተዋፅኦ ያደርጋል ተብሎ የታመነበት የሕግ የበላይነት መርህ ብቅ አለ:: በዚህ መርህ መሠረት ሕግ-አውጭዎች የችግሮቻቸውን አጠቃላይ ባሕሪይ በመመልከት እነዚህን ለመዳኘት የሚያስችል አጠቃላይ ሕግ ያወጣሉ:: ዳኞች ደግሞ ችሎት ፊት የሚቀርብላቸውን እያንዳንዱን ጉዳይ በሕግ-አውጪዎች አስቀድሞ ከተቀመጠው ሕግ ውስጥ ተገቢ በሆነው ድንጋጌ ላይ የተመሠረተ ብይን ይሰጣሉ:: ዳኞች መወሠን ያለባቸው በቅድሚያ በተቀመጠው ሕግ ላይ ተመሥርተው ሕጉ በሚያዘው መሠረት እንጂ በግል ስሜታቸው፣ መስሎ በታያቸውና በምርጫቸው አይደለም:: የመወሠን ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ሰው ዳኛ መሆን ቢችልም ዳኝነት የሚሰጠው አስቀድሞ በወጣ ሕግ ላይ ተመሥርቶ ስለሆነ ዳኛ በተለዋወጠ ቁጥር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተለያየ ፍርድ ሊሠጥ አይገባውም:: እንደዚህ ከሆነ የሕግ የበላይነት መሆኑ ቀርቶ የሰዎች የበላይነት ይሆናል ማለት ነው::

የሕግ የበላይነት መሠረታዊ ይዘት ማንም ሕግን ተላልፎ የተነኘ ዜጋ ለተመሳሳይ ጥፋት ተመሳሳይ ቅጣት በሚያገኝበት ሕጋዊ ሥርዓትና በመንግሥት ብቻ ሊቀጣ ይገባዋል የሚል ነው:: እንዲሁም ማንም ይፈፅመው ማን በዘር፣ በቀለም፣ በሀብት፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከትና በሌላም መመዘኛ ልዩነትና አድሎ ሳይደረግ ለተመሳሳይ ጥፋት ተመሳሳይ ቅጣት በመስጠት መሆን አለበት ማለት ነው:: ከዚህ ሌላ ሕግ ተፈፃሚ የሚሆነው ከግል ስሜት፣ ከወገንተኝነትና ከተፅዕኖ ነፃ ሲሆን ነው:: ስለዚህ የሕግ የበላይነት መኖር መንግሥትና ባለሥልጣኖቹ ከሚፈጽሙት ኃላፊነት የጐደለው ተግባር ዜጎች እንዲጠበቁ የሚያደርግና የመንግሥት አንድ አካል በሆነው የፍትሕ ዘርፍ ጥበቃ የሚደረግለት ነው::

የሕግ የበላይነት በሊበራል ዴሞክራሲ ውስጥ መሠረታዊ መርህ ነው:: ይህ መርህ ዜጎች እርስ በርሣቸው ባላቸው ግንኙነት የሚፈጥሩትን ተግባር የሚገዛና እንደዚሁም መንግሥት በዜጎች ላይ የሚከተለውን አሠራር የሚቆጣጠር መሣሪያ ነው::

*እያንዳንዱ ዜጋ ነፃነት እንዲኖረው ይገባል፡፡ ነፃነቱ ደግሞ የሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ያስፈልጋል፡፡ አንድ መንግሥት ተቀባይነት እንዲኖረው ዜጎች ከሁከትና ሥርዓት-አልበኝነት እንዲሁም ከጭቆናና ከአፈና የሚጠበቁበት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መከተል ይኖርበታል፡፡ ኃላፊነት የጐደለውና የዘፈቀደ አሠራር እንዳይኖር የሚከላከል ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ማቋቋም ይኖርበታል፡፡ የሕግ የበላይነት የሚባለው አስተሳሰብ ይህንን መሠረታዊ የሰው ልጅ መብት ለመጠበቅ እንዲረዳ የተወጠነና ተቀባይነትም ያገኘ አስተሳሰብ ነው፡፡ የሕግ የበላይነት እያንዳንዱ ዜጋ በዕለት ከዕለት ሕይዎቱ እንደፈለገው መንዝ እንዲችል የመከላከያ ጋሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ኃላፊነት የጐደለው መንግሥት ከሚፈጥረው ተፅዕኖ ለመከላከል የተዘጋጀ የመከላከያ መስመር ነው፡፡ ሥርዓት እንዲጠበቅ ሕግ አስፈላጊ ሲሆን ማንኛውም የሥርዓት ማስከበሪያ ሥልጣን ሥራ ላይ መዋል ያለበት ሁልጊዜም በሕጉ መሠረት ነው፡፡ የሕግ የበላይነት መርህ ጋር የተያያዙት መሠረታዊ ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡*

*የመጀመሪያው ማንኛውም ግለሰብ ሕጉን እንዲያውቅ መደረግ አለበት የሚለው ነው፡፡ ይህም ማለት እያንዳንዱ ግለሰብ የሕግ ዕውቀት ባለው ሰው አማካይነት ሕጉን በትክክልና በግልፅ እንዲያውቅ ከተደረገ ተግባሩን ከሕግ ጋር በተጣጣመ መንገድ ለማቀድና ለመፈፀም የሚያስችል እርግጠኝነት በተወሰነ ደረጃ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ በግለሰቦች ነፃነት ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት እንዲኖር አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ይህም በሕጋዊ መንገድ መፈፀም አለበት፡፡ ይህም ማለት ማንኛውም የመንግሥትና የባለሥልጣኖች ውሣኔ በሕግ የተደገፈ መሆን አለበት ወይንም ማንም ባለሥልጣን በግለሰቦች የኑሮ ዘይቤ ውስጥ ሕግ ከሚፈቅደው አሠራር ውጭ ጣልቃ መግባት አይኖርበትም ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ዜጎች የተወሠነ ሕግ በመተላለፋቸው ክስ ካልተመሠረተባቸው በስተቀር እስር እንደማይደርስባቸው እርግጠኝነት እንዲኖራቸው ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ሦስተኛው ዜጎች ከመቀጣታቸው በፊት ጥፋት መፈፀማቸው ሕጋዊ በሆነ ሥርዓትና ወገንተኛ ባልሆነ ነፃ ችሎት ፊት መረጋገጥ ይኖርበታል የሚለው ነው፡፡ አራተኛው ፍትህ በራሱ ግብ ተደርጎ መወሠድ ይኖርበታል የሚለው ነው፡፡ ይህም ማለት የሚሰጠው ብይን አንድን ግለሰብ ይጠቅማል ወይንስ ይጐዳል በሚል ስሌት የሚመሠረት ሳይሆን ሕጉ በሚደነግገው መሠረትና ተፅዕኖ በሌለበት ነፃ ሕሊና ላይ መመሥረት አለበት ማለት ነው፡፡ ውጤቱ ማንንም ይጥቀም ማንንም ይጉዳ ዋናው ነገር በሕጉ መሠረት ብይን መሠጠቱ ሲሆን በዚህም መንገድ የተገኘ ፍትሕ በራሱ እንደ ግብ የሚቆጠር ነው፡፡*

*የሊበራል ዴሞክራሲን መርህ በሚከተል መንግሥት ውስጥ የሕግ የበላይነትን አስመልክቶ የሚነሳው ነጥብ በአንድ በኩል ሕግ የተላለፈ ዜጋ በሕግ ፊት ቀርቦ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ለተመሳሳይ ጥፋት ተመሳሳይ ቅጣት በሚወሰንበት ነፃና ትክክለኛ አሠራር መፈጸም አለበት የሚለው ሀሣብ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የዜጎች ማኅበራዊ ሁኔታ፣ ዘር፣ ፆታ፣ ሀብት፣ ትምህርትና የመሳሰሉት ጉዳዮች በውሳኔው ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተጽእኖ እንዴት ማስቀረት ይቻላል? የሚለው አመለካከት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚታየውን ቅራኔ ለማቻቻል ብዙዎቹ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታት ለዜጎች እኩል ጥበቃ የሚደረግበትን የመፍትሔ አቅጣጫ ይከተላሉ፡፡*

## 3.4.3 እኩል ጥበቃ

*እኩል ጥበቃ የሚለው አስተሳሰብ ኃላፊነት የማይሰማቸው መንግሥታትና ባለሥልጣኖች ከሚያደርሱት ተፅዕኖና ከሚፈጽሙት አድልዎ ዜጎችን ለመከላከልና መብታቸውም በእኩልነት ደረጃ እንዲጠበቅላቸው የሚያስችል ሕጋዊ ሥርዓት መኖር አለበት በሚለው የዴሞክራሲያዊ መንግሥታት አቋም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ከመነሻው የአሠራር ትክክለኝነትና የሕግ ሥርዓትን ለማሟላት በብዙ አገሮች ይሠራበት ከነበረው ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተለያየ ይዘት ያለው አስተሳሰብ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል እንደ ሀብት፣ ትምህርትና የመሳሰሉት*

ጉዳዮች እኩል ባልሆኑበት ሁኔታ እኩል ጥበቃና ትክክለኛ የአሠራር ሥርዓት ማስፈን የሚለው የተለመደ የእኩልነት ማረጋገጫ መንገድ ውጤታማነቱ አጠያያቂ መሆኑን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሀቀኛና ተጨባጭ የሆነ እኩል ጥበቃ የማይታለፍ መሠረታዊ ጥያቄ መሆኑን ተቀባይነት በማግኘቱ ከድሮው ትርጉሙ የሠፋ ይዘት ሊይዝ ችሏል፡፡ በተለይም በአሜሪካ እኩል ጥበቃ የሚለው አስተሳሰብ ከቀድሞው ሥነ-ሥርዓታዊ ዋስትና ሙሉ በሙሉ ሀቀኛ ወደ ሆነ የእኩልነት ግንዛቤ ተሸጋግሯል፡፡ ይህ የእኩልነት ግንዛቤ በሁሉም መስኮች ተግባራዊ ሆኗል ባይባልም በአሜሪካ በተወሠኑ ጉዳዮች ተጨባጭ ወደሆነና ሕጋዊ ዋስትና ወዳለው እኩልነት መረማመድ ችሏል፡፡

እኩል ጥበቃ እንዲኖር ዋስትና የሚሆኑ ድንጋጌዎች በአሜሪካ ሕገ-መንግሥት ማሻሻያ አንቀጾች ውስጥ የተካተቱ ሲሆን የተለያየ መልክ ያላቸውን የዘር ልዩነቶችን ለማስወገድና እኩልነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ነጮችና ጥቁሮችን በአንድ ክፍል ውስጥ አብረው እንዲማሩ ያስቻለው የሕግ ጥበቃ፣ የአሜሪካን ዜጎች የመምረጥና የመመረጥ የእኩልነት መብት ለማረጋገጥ የኮንግረስ አባላትን የምርጫ ክልሎች ወሠን እንደገና ለማስተካከል የተወሰደው ሕጋዊ እርምጃና የመሳሰሉት እኩል ጥበቃ የሚለው አስተሳሰብ ሀቀኛ እኩልነትን ለማምጣት ወደሚያስችል አቅጣጫ እያደገ ለመምጣቱ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የዘር መድልዎ ያስከተለውን መጥፎ ውጤት ለማካካስ «ገንቢ እርምጃ» በሚል አሠራር በአሜሪካ ውስጥ በየመስኩ ጠቃሚ ፕረቶች አሁንም ይደረጋሉ፡፡ በሌሎችም ምዕራብያዊያን አገሮች በ20ኛው ክፍለ ዘመን እኩል ጥበቃ የሚለው አስተሳሰብ ሠፊ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል፡፡ ለዜጎች እኩልነት ጥበቃ ማድረግ የሚቻለው ይህንኑ ዓላማ የሚደግፉ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን በማስፈር ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ የሚታዩ ተግባራዊ እርምጃዎችም ሊወሰዱ እንደሚገባ ግንዛቤ በመገኘቱ ዜጎች እኩል እድል የሚያገኙ ብት ገንቢ እርምጃ በሥራ ላይ እየዋለ ነው፡፡ እዚህ ላይ ለዜጎች እኩል ዕድል መፍጠርና እኩልነታቸውም ተጨባጭ እንዲሆን ገንቢ እርምጃ መውሰድ የሚሉትን መሠረተ-ሃሣቦች በመጠኑም ማየት ያስፈልጋል፡፡

## 3.4.4 እኩል ዕድል መፍጠር

ለዜጎች እኩል እድል መፍጠር (Equal Opportunity) የሚለው አስተሳሰብ መሠረቱ እያንዳንዱ ግለሰብ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ ወይም በፆታው ምክንያት ከማንኛውም ዓይነት ተሣትፎ ሊከለከልና ሊገደብ አይገባውም የሚል ነው፡፡ የፈረንሣዩ ናፖሊዮን በክህሎቶችና በሥራ ብቃት ላይ ብቻ የተመሠረተ የሥራ እድገት እንዲኖር የሚያስችል ተቋማዊ ተሃድሶን በመደገፍ የወሰደው እርምጃና በእንግሊዝም በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ለሚገኙ ከፍተኛ ቦታዎች የሚመለመሉ ሠራተኞች በአብዛኛው ከኦክስፎርድና ከካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲዎች የሚወጡ የቀለም ትምህርት ምሩቃን ብቻ የነበረበት ሁኔታ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ የቀጠለ ቢሆንም በ1960ዎቹ በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ዘረኝነት መኖሩ ከፍተኛ ትኩረት አገኘ፡፡ በ1960ዎቹና በ70ዎቹ ከዘርና ከደመወዝ ክፍያ ጋር የተያያዙ የዘርና የፆታ ልዩነቶች ሕገወጥ መሆናቸው በአውሮፓ ኢኮኖሚ ኮሚሽንና በአውሮፓ ፍርድ ቤቶች ታወጀ፡፡ በአሜሪካም ለዜጎች እኩል እድል መፍጠር የሚለው አስተሳሰብ በሁሉም የንግድና ኢንዱስትሪ ተቋሞች እንዲሁም የሕዝብና የመንግሥት ድርጅቶች ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን ለዜገጎች እኩል እድል በመስጠት በቅጥርና በእድገት አሠራራቸው ላይ ይኸንኑ በተጨባጭ ተግባራዊ አደረጉ፡፡ ለዜጎች እኩል እድል መፍጠር የሚለው አስተሳሰብ በዜጎች እኩል ናቸው ወይንም በዜጎች መካከል በትውልድ፣ በዘር፣ በፆታ፣ ወይም በሃይማኖትና በሌላም ላይ የተመሠረተ ልዩነት መደረግ አይገባውም ከሚለው መርህ የሚመነጭ ሲሆን በተለያየ መልክ ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡ በመጀመሪያ እኩልነት ሲባል በሕብረተሠቡ ውስጥ የተወሠኑ ቡድኖች ብቻ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር በማስወገድ ሁሉም ዜጎች ካለአንዳች ክልከላ የራሣቸውን ሕይወት እንዲመሩ እድል ማግኘት ይገባቸዋል የሚለውን ይዘት ያቀፈ አስተሳሰብ ነበር፡፡ ይህ አስተሳሰብ «ሁሉም ሰዎች እኩል የተፈጠሩ ናቸው» ከሚለው ሞራላዊ ግንዛቤ ጋር በጥብቅ የተሳሰረና መደበኛውን የእኩልነት መንፈስ የሚያንፀባርቅ ነበር፡፡ የዚህ

ዓይነቱ እኩልነት ሁሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውን የሕግ የበላይነት መርህ ለማስከበርና ባርነትን ለማስቀረት፣ እንዲሁም ሁሉም ፆታዎች የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዳይኖራቸው የሚከለክለውን ገደብ ለማስወገድ የሚደረገውን ተሃድሶ የሚደግፍ ነበር::

ምንም እንኳን መደበኛው የእኩልነት ትርጓሜ በጥቂት ዜጎች ላይ የተፈጠረውን ትክክለኛ ያልሆነ አድልዎ ያለበት በደል ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ባይካድም የተወሰኑ የሕብረተሰቡ አባላት ከሌሎች የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችለውን ወሣኝ የማኀበራዊና ኤኮኖሚያዊ መሠረቶች ማስቀረት አልቻለም:: ስለዚህ ይህንን ችግር ያስቀራል ተብሎ የሚገመት ሌላ የእኩልነት መልክ መኖር እንዳለበት ተደረሰበት:: ይኸኛው የእኩልነት መልክ ማኀበራዊ እኩልነት የሚባለው ነው:: ማኀበራዊ እኩልነት ማለት በተለይም በልዩ ልዩ ምክንያት ተጠቃሚ ያልሆኑትን የሕብረተሰብ ክፍሎች ደረጃና ችሎታ እንዲሻሻል ማድረግን የሚመለከት ነው:: ለዜጎች እኩል እድል መፍጠር ሲባልም በድህነት ውስጥ የሚገኙትንና አቅም የሌላቸውን የሕብረተሰብ አባላት በማቴሪያል ለመርዳት የሚያስችል የድጋፍ መሠረት መገንባት ማለት ነው:: ይህም ሀብትን ለዜጎች መልሶ ለማከፋፈል የሚያስችል እርምጃ በመውሰድ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነው:: ሀብትን ለዜጎች መልሶ የማከፋፈል እርምጃ ሲባል ደግሞ ለዜጎች እኩል እድል የሚያስገኝ ገንቢ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል የማህበራዊ ደህንነት ሁኔታን መፍጠር፣ የተበደሉትን የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ ሴቶችን፣ አናሣ ብሔረሰቦችን፣ የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በሥራ ማግኘት ዕድል፣ በክፍያና በመኖሪያ ቤት አድልዎ የተፈፀመባቸውን ሁሉ ለመርዳት የሚያስችል ፕሮግራም መንደፍና በሥራ ላይ ማዋል ማለት ነው::

## 3.4.5 ገንቢ እርምጃ

ገንቢ እርምጃ (Affirmative Action) የሚባለው የማስተካከያ ዘዴ በታሪክ በሕብረተሠቡ ውስጥ በነበረ አድልዎ ምክንያት ጥቅማቸውን እንዲያጡ የተደረጉ ዜጐችን ለመደገፍ የሚቀየስ ፕሮግራምን የሚያመለክት ነው:: እንዲሁም በመንግሥት ፖሊሲም ይሁን በሕዝቡ ውስጥ ሰፍኖ በቆየ መጥፎ አመለካከት የተነሣ በደል የደረሰባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች የተለየ አያያዝ እንዲያገኙ የሚያስችል ፖሊሲ መከተልና መደገፍ ብቻ ሳይሆን የነበረውን አድልዎ ለመቀልበስ የሚያስችል እርምጃ መውሠድን ይጨምራል:: በዚህ ዓይነቱ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚፈለጉት ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጥቅሞችን እንዳያገኙ የተከለከሉና በፖለቲካም የተገለሉ አናሣ ብሔረሠቦች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህ አስተሳሰብ በአሜሪካና በአውሮፓ የመንግሥት ፖሊሲ እስከመሆን ለመድረስ የበቃ ቢሆንም በአፈፃፀም ረገድ ብዙ መሰናክሎች አሉበት::

ለምሣሌ የአሜሪካ መንግሥት አስፈጻሚው አካል ከሚወስዳቸው ገንቢ እርምጃዎች መካከል ሁሉም ከፌደራል መንግሥት ጋር የኮንትራት ግንኙነት የመሠረቱ ድርጅቶች ለተገለሉት አናሣዎች የሥራ ዕድል እንዲሠጡና የማሻሻያ እርምጃ እንዲወስዱ ያበረታታል:: እንዲያውም ከእነዚሁ ከአናሣዎቹ የተወሠነ መጠን ድርሻን (በመቶኛ) በድርጅታቸው ውስጥ እንዲቀጥሩ ያደፋፍራል:: የሆነ ሆኖ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ጋር በተያያዘ ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ ልዩ ድጋፍ የማድረጉ አሠራር ብዙ ጊዜ የሚያከራክር መሆኑ አልቀረም:: አንዳንድ የአሜሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔዎች ዩኒቨርሲቲዎቹ ለመቀበል የሚችሉበት አሠራር እስከ ምን ድረስ መሄድ እንዳለበት የሚያመለክቱ ሲሆን አንዳንዶቹ ውሳኔዎች ደግሞ ገንቢ እርምጃ የሚለውን አሠራር ለመከተል ያለውን ዕድል ውስን የሚያደርጉ ናቸው:: በአውሮፓም የማህበረሠቡ ፍርድ ቤት በሚያሣርፈው ተፅዕኖ መግሥታት አድልዎ የተመላበት አሠራር እንዳይኖር ጥረት እያደረጉና ገንቢ እርምጃ ለሚለው አስተሣሠብም የበለጠ ትኩረት ሠጥተው በመንቀሣቀስ ላይ ናቸው::

ገንቢ እርምጃ ለዜጎች እኩል እድል መፍጠር ከሚለውም አስተሳሰብ የበለጠ ሥር ነቀል ፕሮግራም ነው:: ለዜጐች እኩል እድል መፍጠር በሚለው አስተሳሰብ ጥቅማቸው የተጓደለባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በሥራ ፍለጋ፣ በሥራ መግቢያ የጽሑፍና የቃል ፈተና እንዲሳተፉ ዕድሉ ከተፈጠረላቸው ከዚያ በላይ ልዩ ድጋፍ ማድረጉ ፍትሓዊ አይሆንም የሚል ግንዛቤ ሲኖር ገንቢ እርምጃ በሚባለው አስተሳሰብ ደግሞ ይኸ በቂ እንዳልሆነ ተደርጐ ይወሠዳል:: ስለሆነም ጥቅማቸው በተለያየ አድሏዊ አሠራር የተጓደለባቸው ዜጎች የሥራ፣ የቤት፣ የትምህርትና የመሣሠሉትን አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ገንቢ እርምጃ መወሰድ አለበት የሚል እምነት አለ:: ይህንን በእርግጠኛነት ከሚያስገኙ መንገዶች መካከል የኮታ አሰራርን መጠቀም አንዱ ነው ተብሎ ይታሰባል:: በዚህ ብቻም ሳይገታ ገንቢ እርምጃ የሚለው አሠራር ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ አድልዎ የተፈፀመባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች አሁንም ማግለል የቀጠሉትን ወገኖች የሚቀጣ ጠንካራ አሠራር መገንባት አለበት የሚል እምነት አለ::

### 3.4.6 ሰብዓዊ መብቶች

ሰብዓዊ መብቶች በማንኛውም ሕብረተሠብ ውስጥ ለሚገኝ ማንኛውም ሠው ሊኖረው የሚገባውን መሠረታዊ መብቶች አጠቃለው የያዙ ናቸው:: በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እነዚህ የሠው ልጅ መብቶች ከፍተኛ ትኩረት የሚሠጣቸው ብቻ ሳይሆኑ የሕገ-መንግሥቱ ከፍተኛ እሴቶች ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው:: ሰብዓዊ መብቶች ከሲቪል መብቶች (እንደየአገሩ የተለያዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ) በተለየ መንገድ ሁሉን አቀፍ (ዩኒቨርሳል) መብቶች ናቸው::

ሰብዓዊ መብቶች የዳበሩት ቀደም ሲል በተለያየ መንገድ ሲንፀባረቅ ከቆየውና የተፈጥሮ መብት (Natural Right) ከሚባለው አመለካከት በመነሳት ሲሆን ይኸውም መንግሥትም ይሁን ሌሎች ዜጎች በግለሰብ መብት ላይ ጣልቃ እንዳይገቡ ሊገደቡ ይገባል የሚለውን አስተሳሰብ መሠረት ያደረገ ነው:: ይህ ደግሞ መንግሥት የሚያከናውነው ተግባር የተወሠነ መሆን አለበት ከሚለው የሊበራሊዝም ዓላማና ጠቃሚ የአመለካከት ገፅታ ጋር የሚጣጣም ነው:: ሰብዓዊ መብቶች የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ሊከበሩለት የሚገቡ መብቶችን የሚያሟሉና ሁሉንም የሰው ልጆች የሚመለከቱ በመሆናቸው በሁሉም ዘንድ አጠቃላይ ተቀባይነትና ስምምነት ለማግኘት በቅተዋል:: ጆንሎክ የተባለው እንግሊዛዊ ፈላስፋ በሰብዓዊ መብቶች የሚካተቱት «ሕይዎት፣ ነፃነትና ንብረት» ናቸው ሲል የአሜሪካ ነፃነት ድንጋጌ አውጭዎች ደግሞ በሰብዓዊ መብቶች የሚታቀፉት «ሕይዎት፣ ነፃነትና ደስታን መሻት» ናቸው ማለታቸው ይታወሳል:: ዋናው ነገር በአንድ በኩል እነዚህ መብቶች የሰው ልጅ በሙሉ ሊኖሩት የሚገቡ መብቶች መሆናቸውና በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን መብቶች መከልከል የሰውን ስብዕና እንደመካድ ስለሚቆጠር መንግሥትም ሆነ ሌላ ግለሰብ ሊያስወግዷቸው ወይንም ሊከለክሏቸው የማይገቡ መብቶች መሆናቸው ነው::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ ከተቀበላቸው መካከል የመኖር መብት፣ ነፃነት፣ ደህንነት፣ የግልና የቤተሰብ መብት (ማግባትና ቤተሰብ መመሥረትን ይጨምራል) ትክክለኛ ዳኝነት የማግኘት መብት፤ እንዲሁም የማሠብ፣ የሕሊና፣ የሃይማኖት፣ ሃሣብን የመግለጽና የመሠብሠብ መብት፤ ከዚህም ሌላ ከሠቆቃ፣ ከከፋ አያያዝ፣ ከባርነት፣ ከግዳጅ ሥራ፣ ከሁሉም ዓይነት አድሎና ከሕግ ውጭ ከሚፈፀም ጥቃት የመጠበቅ መብት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: የዚህ አዋጅ ስምምነቶች የመማር መብትንም አፅድቀዋል:: የእነዚህ መብቶች መጣስ እንደወንጀል የሚቆጠር መሆኑ ተቀባይነት አግኝቷል:: ፍርድ ቤቶችም በእነዚህ መብቶች መጣስ ምክንያት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለማየትና ሰብዓዊ መብቶችን የመጣስ አደጋን እንዲከላከሉ የሚያስችል ሥልጣን ይኖራቸዋል:: ከዚህም በተጨማሪ መንግሥታትና ግለሠቦች ለሕዝብ አገልግሎት የተቋቋሙ ድርጅቶችና አካሎች እነዚህን ሰብዓዊ መብቶች ጥሰው ከተገኙ ድርጊታቸው ሕገ-ወጥና የተወገዘ ሲሆን እንዳውም ገንቢ በሆነ መንገድ እንዲጠብቋቸው በሕጐቻቸውም ውስጥ እንዲያካትቷቸው ይጠበቃል:: የፍትህ አካላትም እነዚህ የሠብዓዊ መብቶች ሕጋዊ ጥበቃ ማግኘታቸውን በዳኝነት ሂደት ለማረጋገጥ በሚጫወቱት ከፍተኛ ሚና ትልቅ ግምት ይሰጣቸዋል::

## 3.4.7 የተለያዩ አገሮች ልምድ

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲያቃልላቸው የሚፈለጉ ሁለት መሠረታዊ የመንግሥት ችግሮች አሉ። አንደኛ የአንድ አገር መሪዎች ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል በቂ ሥልጣን እንዲኖራቸው እንዴት መፍቀድ ይቻላል የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአንድ አገር መሪዎች ከሚፈለገው በላይ ሥልጣን አግኝተው አሳማኝ ባልሆነ መንገድ የግለሰቦችን መሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች እንዳይገድቡና በዜጎች የእለት ከዕለት አኗኗር ውስጥ በዘፈቀደ ጣልቃ እንዳይገቡ እንዴት መከላከል ይቻላል የሚሉት ናቸው። ለመንግሥት ባለሥልጣኖች በቂ ሥልጣን የመስጠቱ አላማ የፓርላማ ሉዓላዊነትን በማስፈን ወይንም ፓርላማው የፈለገውን ሕግ የማውጣት ሕጋዊ መብት እንዳለው በማረጋገጥ የሚሟላ ሲሆን የግለሰቦች መሠረታዊ ነፃነቶች በመንግሥትና በባለሥልጣኖች እንዳይጣሱ የመካላከሉ ዓላማ ደግሞ የግለሰብ ነፃነቶች በሕግ የበላይነት መርህ እንዲጠበቁ በማድረግና በዚሁ መርህ የመንግሥትና የባለሥልጣኖች ተግባር በሕግ ተወስኖ የተመጠነ እንዲሆን በማድረግ ሊሟላ ይችላል።

ሕግ ሁለት ዓላማዎች አሉት። አንደኛው የግለሰቦች ተግባር ሕጋዊ ገደብ እንዲኖረው ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በሥልጣን ላይ ያሉትን ሰዎች የተሰጣቸውን ኃላፊነት ክልል በግልፅ ወስኖ በማስቀመጥና የግለሠብ ነፃነቶች ጥበቃ እንዲያገኙ ማድረግ ነው። ይህም ማለት መንግሥትና የመንግሥት ባለሥልጣኖች፣ ግለሰቦችና ቡድኖች ሁሉም በሕግ የሚገዙ ሲሆን ከሕግ በላይ የሚሆን ማንም ኃይል መኖር አይገባውም ማለት ነው።

በመጨረሻ መታወቅ የሚገባው ከፍተኛ ቁምነገር ማንኛውም ሕጋዊ ሥርዓት ዜጎች በትክክል ከሚፈልጉት ነገር ጋር እስካልተጣጣመ ድረስ የሕግ የበላይነት የሚባለውን መርህ ጨምሮ ዋጋ ቢስ መሆኑን ነው። ሌላው መሠረታዊ ጉዳይ የግለሰቦች መብት ማስጠበቂያ የመጨረሻ ኃይል ያለው በእያንዳንዱ ዜጋ እጅ ውስጥ እንጂ በማንኛውም የሕገ-መንግሥት ማስተካከያ ወይም በማንኛውም የፓርላማ ምርጫ አለመሆኑ ነው። ዜጎች ነፃነታቸውን ለመጠበቅ ዝግጁ ካልሆኑ በስተቀር የሞራል ኃላፊነት የጐደለው መንግሥት ፓርላማውንም ለመበተን፣ ምርጫውንም ዋጋ ቢስ ለማድረግ በሚያስችለው መንገድ ሕጉን ሊያስተካክለው ይችላል። ስለዚህ ቀደም ሲል የተጠቀሠውን ሀሣብ እንደገና ለማስታወስ ነፃነት ያለው በእያንዳንዱ ዜጋ ልብ ውስጥ ነው። ነፃነት በእያንዳንዱ ዜጋ ልብ ውስጥ ከጠፋና ሞቶ ከተቀበረ ነፃነትን ማስከበር የሚችል ሕገ-መንግሥት፣ ሕግና ፍርድ ቤት ሊኖር አይችልም።

## 3.5 ሕገ-መንግሥት በኢትዮጵያ

ሕገ-መንግሥት በዜጐች የተሟላ ንቁ ተሣትፎ መዘጋጀቱና በዜጐች ፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ነፃ ውሣኔ ፀድቆ ሕጋዊ ኃይል ማግኘቱ ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች መካከል የሕገ-መንገሥቱ ይዘት ከዜጐች ፍላጐት ጋር የተጣጣመ መሆኑ አንዱና ዋነኛው ነው። በሕገ-መንግሥቱ ይዘትና በዜጐች ፍላጐት መካከል መጣጣም አለ ማለት ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ በዜጐች መካከል መፈጠር የሚገባው አገራዊ መግባባት እንዲኖር ጠንካራ መሠረት ተጥሏል ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ብሔራዊ ስምምነት በተጨባጭ የሚኖረው ሕገ-መንግሥቱ በዜጐች የተሟላ ንቁ ተሣትፎ ሲዘጋጅ፣ በዜጐች ፈቃድና ነፃ ውሣኔ ሲፀድቅ ነው። በሌላ አገላለጽ ሕገ-መንግሥቱ ዜጐች ከሞላ ጐደል በጋራ በተስማሙባቸውና በተቀበሏቸው መርሆዎች ላይ የተመሠረተና በተለያየ መንገድ በአመለካከት፣ በእምነትና በፍላጐት ያሏቸውን ልዩነቶች ያገናዘበ ሕገ-መንግሥት እንዲሆን ይጠበቃል። እነዚህን መሠረታዊ ጉዳዮች አሟልቶ የተዘጋጀ ሕገ-መንግሥት ሲኖር፣ በዚህ ላይ ተመሥርቶ የተደራጀና የሚሠራ የፖለቲካ ሥልጣን ሲኖር በአንድ አገር ውሰጥ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት አለ ማለት ይቻላል። ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ የሚጻፍ ሕገ-መንግሥትና የሚቋቋም የፖለቲካ ሥርዓት መስሎ ለመታየት የሚደረግ ማታለልና ማጭበርበር ነው። የፈለገውን ያክል የሰብዓዊ መብት ጋር የሚያያዙ አንቀጾች ቢሠፍሩ፣

*የፈለገውን ያክል የዴሞክራሲ ጥቅስ ቢደረደር ከማስመሰል ያለፈ የአምባገነንነትና የዘረኝነት ሽፋን ከመሆን ያለፈ ጥቅም የላቸውም።*

*በእነዚህ መመዘኛዎችና ግንዛቤዎች በመመርኮዝ በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ ይቻላል። በእርግጥ በኢትዮጵያ ውስጥ የተጻፈ ሕገ-መንግሥት አለ። ነገር ግን በዜጎች ንቁና የተሟላ ተሣትፎ ተዘጋጅቶ በዜጎች ፈቃደኝነትና ፍላጐት ላይ በተመሠረተ ነፃ ውሣኔ ፀድቆ ሕጋዊ ኃይል እንዲኖረው የሚያስችለውን ተቀባይነት አግኝቷል የሚባል አይደለም። ኢትዮጵያ ከአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ሶስት የተፃፉ ሕገመንግስቶች ያየች ቢሆንም ሁሉም በሕዝብ ፈቃድና ነፃ ተሳትፎ የተቀረፁ አይደሉም። በተለያዩ አጋጣሚዎች ስልጣን በእጃቸው ማስገባት የቻሉ ገዥዎች አንዴ የያዙትን የመንግስት ስልጣን ለማቆየት የሚረዳ ሕገመንግስታዊ ሽፋን እንዲሆናቸው በማሰብ ራሳቸው በፈለጉት መንገድ እየፃፉ በሕዝብ ላይ በግዴታ የጫኗቸው ሕገመንግስታቸው እንዳለፉት ሁለት ሕገመንግስቶች ሁሉ አሁንም ዜጐች በግልና በጋራ ተስማምተው በተቀበሉት መርህ መሠረት የተለያዩ ጥቅሞችና አመለካከቶች የሚቻቻሉበትን ዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ ለመፍጠር የሚያገለግል ሕገ-መንግሥት ኢትዮጵያ የላትም። በተቃራኒው ኢትዮጵያ አሁን ያላት ሕገ-መንግሥት ከአንድ ቡድን የፖለቲካ ጥቅም ጋር እንዲጣጣም ተደርጐ በአንድ ቡድን ርዕዮተ-ዓለም ዕይታ ተቃኝቶ ከአንድ ቡድን በመነጨ ሀሣብ ላይ ተመስርቶና አንድ ቡድን ለራሱ በሚስማማው መንገድ ባዘጋጀው ጠባብ መድረክ ተዘጋጅቶ በሕዝብ ላይ በግድ የተጫነ ሕገ-መንግሥት ነው። በዚህ መልክ ተጽፎ በሕዝብ ላይ የተጫነ ሕገ-መንግሥት ሕጋዊ ኃይል እንዲኖረው የሚያደርገውን ተቀባይነት ካለማግኘቱም በላይ ሕጋዊነቱ ጥያቄ ውስጥ የወደቀ ነው። ሕገ-መንግሥቱና በዚሁ መሠረት አሁን የተመሠረተው የፖለቲካ ሥርዓት የሕዝብ የተሟላ ተሣትፎ፣ ፈቃድና ነፃ ውሣኔ ባለማረጋገጣቸው ሕጋዊነት[1] ማጣታቸውን ተከትሎ በየጊዜው የሚያዘጋጇቸው ምርጫዎች፣ የሚያወጧቸው አዋጆችና መመሪያዎች እንደፎርማሊቲ የሚታዩና በኃይል ብቻ የሚፈፀሙ ናቸው። ሕገ-መንግሥቱን ሕዝብ የሚቀበለው ለማድረግና ሕጋዊነት የተላበሰ እንዲሆን ለማድረግ በርካታ ችግሮች አሉ። ከእነዚህም መካከል ዋና ዋና የሚባሉትን ጥቂት ነጥቦች በማብራራት ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል።*

*የመጀመሪያው ችግር የሕገ-መንግሥቱ ቁልፍ እሴቶች በሰብዓዊ መብት አንቀጾች የተሸፋፈኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርሆዎች መሆናቸው ነው። ለምሣሌ በሕገ-መንግሥቱ ምዕራፍ ሁለት ሥር የሕገ-መንግሥቱ መርሆዎች ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል ሠብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚገልፀው አንቀጽ 10 ይገኝበታል። በዚህ አንቀጽ ክፍል አንድ ሥር ሰብዓዊ መብቶች የተዘረዘሩ ሲሆን በክፍል ሁለት ስር ደግሞ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተዘርዝረዋል። በክፍል አንድ ሰብዓዊ መብቶች ተብለው የተዘረዘሩትና ከአንቀጽ 14 እስከ አንቀጽ 28 የሠፈሩት ድንጋጌዎች ወደጐን እየተተው ኢህአዲግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ያለፍርድ ቤት ውሣኔ ዜጐች ይገደላሉ፣ የአካል ጉዳት ይደርስባቸዋል፣ ይታሠራሉ፣ ጭካኔ በተሞላበት ኢሰብአዊ በሆነና ክብርን በሚያዋርድ መንገድ እየተያዙ ይቀጣሉ፣ የቀረበባቸው ክስና ምክንያት ሳይነገራቸው በ48 ሰዓታት ውስጥ በፍርድ ቤት የዋስ መብት እንዲጠበቅላቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ ውድቅ እየተደረገ ይታሠራሉ። የተከሰሱ ሰዎች ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ፍትሕ አለማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን በፍርድ ሂደት ላይ ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብታቸው አይጠበቅም። በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሠሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብታቸው፣ ከትዳር ጓደኛ፣ ከቅርብ ዘመድና ጓደኛ፣ ከሃይማኖት፣ ከሕግ አማካሪና ከሐኪም ጋር የመገናኘት መብታቸው አይጠበቅም።*

*ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዳውም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሣሹ ወይም*

ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚለው አይከበርም:: ይሁን እንጂ ዛሬ በሀገራችን ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ-ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይንም አይቀጣም የሚለው አይጠበቅም:: ማንኛ ውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው የሚለው ተፈፃሚነት አላገኘም:: ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል ቢባልም በተግባር የሚፈፀመው ከዚህ በተቃራኒው ነው:: ሰዎች በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ በትውልድና በመሳሰሉት ልዩነት ይደረግባቸዋል:: ሁሉም ሰዎች እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና አያገኙም:: ማንኛውም ሰው ግላዊነቱና ሕይወቱ አይከበርም:: መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ ውጪ ይመረመራል:: ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች ይቀደዳሉ ወይም ምስጢራዊነታቸው አይጠበቅም:: በቴሌፎን፣ በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ይጠለፋሉ::

የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታቸውን አይወጡም:: ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሠኑት ጥፋቶች በስፋት ይካሄዳሉ፣ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የእሥራትና የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሠወር፣ ኢሰብአዊ የድብደባ ድርጊት መፈፀም በስፋት ይካሄዳሉ:: ይህንን ወንጀል በሚፈፅሙና በሚያስፈፅሙ ላይ የሚወሰድ ሕጋዊ እርምጃ ግን የለም::

በሕገ-መንግሥቱ ክፍል ሁለት ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተብለው ከአንቀጽ 29 እስከ አንቀጽ 44 ከተዘረዘሩት ውስጥ አብዛኛዎቹ ሥራ ላይ እንዲውሉ ተፈልጐ ሳይሆን የዴሞክራሲ መብት ያረጋገጠ ሕገ-መንግሥት ጽፈዋል ለመባል የሠፈሩ ናቸው:: አሁን ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ሥራ ላይ እንዲውሉ ዝግጁነት እንደሌለ ብዙ ማረጋገጫዎችን ማቅረብ ይቻላል:: ሀሣብን የመግለፅ ነፃነት በወረቀት ላይ የተጻፈ ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ በተግባር እንደሚታየው እንደወንጀል እየተቆጠረ የሚያሳስርና የሚያስቀጣ ነው:: የቅድሚያ ምርመራ የተከለከለ ነው ይባል እንጂ በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ከገዥው ፓርቲ በስተቀር ተቃዋሚዎች የሚያቀርቧቸው የጽሑፍና የቃል አስተያየቶች፣ መረጃዎችና መግለጫዎች እንዲሁም የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያዎች ጭምር እየተመረመሩ ተቀናንሰውና ይዘታቸው ተበላሽቶ ይሠራጫሉ:: መረጃ ለሚፈልጉ የግል ፕሬሶች መረጃ የሚሰጥ የመንግሥት ባሥልጣን የለም:: የመንግሥት ኃላፊዎች በሚጠሩት ፕሬስ ኮንፈረንስ የግል ጋዜጦች እንዲገኙ አይፈቀድም:: የግል ጋዜጦች ወደተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች በሚሠራጩበት ጊዜ ወደ ሕዝብ እንዳይደርሱ በተለያየ መንገድ ተፅዕኖ ይደረግባቸዋል:: የመንግሥት የፕሬስ ተቋማት የአሠራር ነፃነት የላቸውም፣ የተለያዩ አስተያየቶችን እንዲያስተናግዱ የሚያደርግ አሠራርም የላቸውም::

በሰላም ለመሰብሰብና ሰላማዊ ሠልፍ ለማድረግ ነፃነት የለም:: አዳራሽና አደባባይ ለሰላማዊ ህዝባዊ ስብሰባና ሠልፍ ለመጠቀም ከባድ ተፅዕኖ ይደረጋል:: ሰላማዊ ሠልፍ የወጡ ሲቪሎችን በአደባባይ በጥይት መጨፍጨፍ እንደቀላል ነገር የሚታይ፣ ይቅርታ የማይጠየቅበትና ተጠያቂም የሌለበት ድርጊት ነው:: የሰዎች የመደራጀት ነፃነት የለም:: የተቃዋሚ ድርጅቶች አባል ሆኖ መገኘት ከመኖሪያ ቤት የሚያስወጣ፣ ከሥራ የሚሳግድና የሚያስቀጣ ወንጀል ተደርጐ ይወሰዳል:: ማንኛውም ሠው በመረጠው የአገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ መሥርቶ የመኖር ነፃነት የለውም:: ቋንቋ አትችልም እየተባለ የመምረጥና የመመረጥ መብቱን ይገፈፋል:: የአንድ ክልል ተወላጅ አይደለህም እየተባለ የሥራ፣ የትምህርት፣ የሥልጠና የመሳሰሉትን ዕድሎች ይከለከላል:: ነፍጠኛ፣ የዚህ ጐሣ አባል፣ ትምክህተኛ፣ ጠባብ እየተባለ ቤቱንና ንብረቱን እየተቀማ በኃይል ይባረራል::

ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው ከመባሉ በስተቀር በተለይ በገጠሩ የአገሪቱ ክፍል ከወንዶች ጋር እኩል የመብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ተጨባጭ ተግባር የለም:: ለሕፃናት በእንክብካቤ እንዲያድጉ የሚያስችል ትኩረትና ድጋፍ የለም:: ወጣቶች የመማርና ሥራ የማግኘት ዕድል በሚገባ አልተሰጣቸውም:: ማንኛውም ሰው በጊዜ ፍትሕ የማግኘት መብት የለውም:: ለዓመታት ፍርድ ቤት እንዲመላለስ ይገደዳል:: ኢትዮጵያዊያን በዘር፣ በቋንቋ፣ በብሔረሰብና በፖለቲካ ምክንያት ልዩነት ይደረግባቸዋል:: ተወካዮቻቸውን በነፃነት እንዳይመርጡ ከፍተኛ ተፅዕኖ፣ ወከባ፣ ሽብርና ማስፈራራት ይፈፀምባቸዋል:: የፈለጉትን ሰው መምረጥ ያስጠይቃል፣ ቤትና ንብረት እንዲዘረፍ ምክንያት ይሆናል:: ከሥራ ለመባረር ሰበብ ይሆናል::

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ማናቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በእኩልነት የመንግሥት እውቅና ይኖራቸዋል የሚለውን በሚፃረር አኳኋን አንዳዶቹን ቋንቋዎች የሥራና የትምህርት ቋንቋ እያደረጉ ሌሎቹን ደግሞ እየከለከሉ በቋንቋዎች መካከል አድልዎ ይደረጋል:: ዜጐች በሚፈልጉት ቋንቋ ልጆቻቸውን ለማስተማር እየተከለከሉ በማይፈልጉት ቋንቋ ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ ይገደዳሉ:: አንድ ቋንቋን ከዜጐች ፍላጐት ውጪ የክልል፣ የዞን ቋንቋ ካደረጉ በኋላ በዚያ ክልልና ዞን ውስጥ የሚገኙ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የክልሉን ቋንቋ ካላወቃችሁ አትመረጡም እየተባሉ መብታቸውን ይነጠቃሉ:: የራሣቸውን ቋንቋ እንደያዙ የመመረጥ መብት የላቸውም::

ሕዝብ ራሱ የሚፈልጋቸውን መሪዎች የመምረጥ መብት የለውም:: የሕዝቡን ባሕልና ወግ የማያውቁ፣ ዜጐች የማይፈልጓቸውና ፈቅደው ውክልና ያልሰጧቸውን ግለሰቦች ገዥው ፓርቲ በአመራርና ኃላፊነት ላይ ያስቀምጣቸዋል:: ሕዝቡ በፌደራልና በክልል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት የለውም:: እንዲያውም በአንዳንድ ክልል የአስተዳደርና አመራር ኃላፊነቱን ለአናሣዎቹ ተሰጥቶ ብዙሃኑ በመስተዳድሩ ውስጥ ምንም መብት እንዳይኖረው የተደረገበት ሁኔታ አለ:: በአንዳንዱ ክልል ደግሞ ለአናሣዎቹ ሚዛናዊ ውክልና እንዲኖራቸው የሚያስችል ዕድል አልተሰጣቸውም::

በሕገ-መንግሥቱ ላይ መሬት ለዜጐች የግል ንብረት እንዳይሆን በመደንገጉ እያንዳንዱ በመሬት ላይ ጉልበቱን፣ የፈጠራ ችሎታውንና ገንዘቡን የሚያፈሰው ግለሰብ ብቻ ሳይሆን አገር በአጠቃላይ ሊጠቀም እንዳልቻለ በተግባር ቢታይም ሕገ-መንግሥቱ ሳይቀየር የሚቀየር ነገር አይኖርም ተብሎ ለእድገታችን መሠረት የሆነው የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ በእምቢተኝነት ተዘግቷል:: ይኸ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ከመወሠኑ በፊት ዜጐች የተለያዩ አማራጮች ቀርበውላቸው በሚገባ ውይይትና ክርክር ተደርጐበት፣ በፍላጐትና በስምምነት የተቀበሉት ወይንም ነፃ ውሣኔ ያደረጉበት አልነበረም:: ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው በግብርና ስለሚተዳደርና 15 በመቶ የሚሆነው በሌላ መስክ የሚተዳደረው ዜጋ ደግሞ በአንድ ወይንም በሌላ መንገድ ከመሬት ጋር ጥብቅ ግንኙነት ስላለው መሬትን መያዣ አድርገን እንዳሻን ልንገዛውና ፍላጐታችንን ልንጭንበት እንችላለን ብሎ በማሰብ አንድ የፖለቲካ ቡድን በሕዝብ ላይ የጫነው ውሣኔ ነው:: የአንድ የፖለቲካ ቡድን ፕሮግራም ግልባጭ የአገሪቱ የመንግሥት ሥርዓት የሚመራበት ሕገ-መንግሥት እንዲሆን ታስቦ አማራጮች ለሕዝብ ውይይት ቀርበው ሣይመከርባቸውና ዜጐች በነጻነት ምርጫቸውን እንዲወስኑ ሳይደረግ በኃይል የተጫነ ነው:: የሕገ-መንግሥቱን ሕጋዊነትና ተቀባይነት ጥያቄ ውስጥ ከሚጥሉት መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል እንደ መሬት ያለውና የአብዛኛውን ዜጋ ሕልውና የሚመለከተው ነጥብ የአንድን ፖለቲካ ቡድን አጀንዳ ተፈፃሚ ለማድረግ ሲባል ብቻ ከሕዝቡ ፈቃድና ፍላጐት ውጭ በሆነ መንገድ መወሠኑ አንዱና ዋነኛ ው ነው::

የአሁኑ ሕገ-መንግሥት በምዕራፍ አራት የመንግሥትን አወቃቀር አስመልክቶ ከአንቀጽ 45 እስከ አንቀጽ 49 ከዘረዘራቸው መካከል የፌደራል ክልሎች የሚመሠረቱበት መሥፈርትና የፌደራል መንግሥት አባላት አወሳሠንና የአከላለል ለውጦችን አስመልክቶ የተደነገጉ

አንቀጾችም የአንድ የፖለቲካ ቡድን አጀንዳ ሕገ-መንግሥታዊ ኃይል እንዲያገኝ በመፈለግ ከሕዝብ ፈቃድ ውጭ በኃይል የተጫኑ ናቸው:: የሚዋቀሩት በሕዝብ አሠፋፈር፣ ቋንቋ፣ማንነትና ፈቃድ ላይ በመመሥረት ላይ እንደሚሆን ቢደነገግም በብዙዎቹ ክልሎች ዋና መሥፈርት ሆኖ በተግባር የዋለው ቋንቋ ብቻ ነው:: ቋንቋ የአከላለል ዋና መሥፈርት ሆኖ ጥቅም ላይ መዋሉ ደግሞ በየክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያንኑ የክልል ቋንቋ ሳይወዱ በግድ እንዲቀበሉ፣ በዚያ ቋንቋ እንዲሠሩና እንዲማሩ ግዴታ ጥሎባቸዋል:: የክልል ቋንቋ ካልቻሉም የመምረጥ እንጂ የመመረጥ መብት አይኖራቸውም:: የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብት ለመጠበቅ ነው ቢባልም የአንደኛውን ቋንቋ ተናጋሪዎች መብት የሚረግጥ የክልል አደረጃጀት የሌላውን መብት የሚጠብቅ ሊሆን እንደማይችል በተግባር እየታየ ነው::

የሕዝብ መብት ማክበርና ማስከበር ዋነኛ መለያችን ነው የሚሉት አብዮታዊ ዴሞክራቶች በሕዝብ መብት ስም የሕዝብ መብት እንደሚረግጡ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው ይኸው በቋንቋ ላይ የተመሠረተው የክልል አደረጃጀታቸው ነው:: ለምሣሌ የሐረሪን ክልል ወስዶ ማየት ይቻላል:: ክልሉ በሐረሪ ቋንቋ ስም የተከለለው በሐረር ውስጥ የሚኖሩትን የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የሶማሌ፣ የጉራጌና የሌሎችም ቋንቋ ተናጋሪዎችን መብት በሚጠብቅ መንገድ አይደለም:: አብላጫ ቁጥር ያላቸው ዜጎች አናሣ ቁጥር ባላቸው 15 በመቶ በማይሞሉት ሥር ሆነው በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ተገቢ ውክልና እንዳያገኙ የሚያደርግ ነው:: የግለሰብ መብት ለሕዝብ መብት ሲባል ቢገፈፍ ነውር እንደሌለው የሚያምኑት አብዮታዊ ዴሞክራቶች እናከብረዋለን የሚሉትን የሕዝብ መብት ከመደፍጠጥ ወደኋላ ብለው አያውቁም:: ገዢዎቻችን ቋንቋን የአከላለል መነሻ አድርገው ሲወስኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሠፋፈር፣ የኢኮኖሚ ግንኙነት፣ የባሕልና የሥነ ልቦና ትስስር ለዚህ እንደማያመች አጥተውት አልነበረም:: ይህ የተመረጠው ምስቅልቅሉና ትርምሱ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ተፈላጊ እሴት ተደርጐ ስለሚወሰድ ብቻ ነው:: ሕዝቡ እርስ በርሱ ግራና ቀኝ ሲጓተት አብዮታዊ ዴሞክራቶች የሚጭኑበትን ግዴታ ሁሉ አልቀበልም ብሎ ለመቋቋም የሚያስችለው የተባበረ አቅም ስለሚያጣ ለአገዛዝ እንደሚመች በጥንቃቄ ተሠልቶ ስለተደረሰበት ነው::

ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ሕዝቦች እየተባለ የተሠራው አከላለል በእያንዳንዱ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ዜጐች የተናጠልና የቡድን መብት የሚያጠፋ፣ ዘረኝነትን የሚያጠናክር፣ የዜጐችን አንድነትና ወንድማማችነት የሚያዳክም ብቻ ሳይሆን በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት በዚች አገር ውስጥ እንዳይበቅል የሚያደርግ አከላለል ነው::

በሕገ-መንግሥቱ ምዕራፍ አምስት የሥልጣን አወቃቀርና ክፍፍልን በሚመለከት ከአንቀጽ 50 እስከ አንቀጽ 52 የተደነገጉት አንቀጾች በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል የሥልጣን ክፍፍል እንዳለ ለማስመሰል የተዘረዘሩ ነጥቦችን የያዙ ቢሆንም በተግባር የሚታየው ግን ከዚህ የተለየ ነው:: እያንዳንዱ ክልል የራሱን መሪዎች በነፃነት እየመረጠ የሚወክልበት ዴሞክራሲያዊ አሠራር የለም:: ማዕከላዊ ሥልጣንን ጠቅልሎ የያዘ አንድ የፖለቲካ ቡድን የራሱን ካድሬዎች በክልል ሥልጣን ላይ እየወከለ የሚያሠራበት ሁኔታ ነው ያለው:: ማንም ክልል የሚወያይበትን አጀንዳ ነፃ ሆኖ እየመረጠና በነፃነት እየተወያየ የሚወስንበት አሠራር የለም:: ሁሉም ከማዕከል ተዘጋጅቶ የሚሰጠውን አጀንዳና የውሣኔ ሃሣብ ተቀብሎ ከማፅደቅ ሌላ ምንም ማድረግ አይችልም:: ከዚህ ውጭ እንዳይወጣም ድርጅታዊ ሥራ በሚባለው የማዕከላዊነት መጠበቂያ ዘዴ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል:: ከማዕከል ተዘጋጅቶ ከሚላክለት አጀንዳ ውጭ የወሠነና ያስወሠነ የክልል ካድሬ አንድ ቀን በሥልጣኑ ላይ ለመቆየት ዕድል እንደሌለው ስለሚያውቅ የሚጨነቀው ለሚገዛው ክልል ሕዝብ ጥያቄ መሟላት ሳይሆን መድቦ ላስቀመጠው የበላይ አካል አጀንዳ ተፈጻሚነት እንደሆነ በተግባር የሚታወቅ ነው::

በምዕራፍ ስድስት በክፍል አንድ ከአንቀጽ 54 እስከ አንቀጽ 60 ስለተወካዮች ምክር ቤት፣ በክፍል ሁለት ደግሞ ከአንቀጽ 61 እስከ አንቀጽ 68፣ እንዲሁም በምዕራፍ ሰባት ከአንቀጽ 69 እስከ አንቀጽ 71 ስለ ፌደራላዊ ሪፐብሊኩ ፕሬዘደንት፣ በምዕራፍ ስምንት ከአንቀጽ 72 እስከ አንቀጽ 77 ደግሞ ስለሕግ አስፈጻሚው አካል፣ በምዕራፍ ዘጠኝ ከአንቀጽ 78 እስከ አንቀጽ 84 ሰለዳኝነት አካላት የተዘረዘሩ ድንጋጌዎች በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈፃሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ያለውን የሥልጣን ክፍፍል የሚያመለክቱ ናቸው::

በመሠረቱ በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጠው ድንጋጌ ሁሉንም ሥልጣን ለአስፈፃሚው አካል ጠቅልሎ የሰጠ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ ሕግ የመተርጐም ሥራ ለዳኝነት አካል ሳይሆን ለፌደሬሽን ምክር ቤት የተሠጠ ነው:: የፌዴሬሽን ምክር ቤት ደግሞ በሕገ-መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ የአተረጓጐም ችግር ሲያጋጥም ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩ እንዲጣራለት የሚያደርገው በሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አማካይነት ነው:: የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን የሚመሩት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንትና ምክትል ፕሬዝደንት ናቸው:: እነዚህ ባለሥልጣኖች የሚመረጡት ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲሆን ሹመታቸውን የሚያፀድቀው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት የተወካዮች ምክር ቤት ነው:: ስለዚህ የዳኝነቱና ሕገ-መንግሥት የመተርጐም ሥራ ያለው በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደግሞ የፌደራሉን መንግሥት አመታዊ በጀት የማዘጋጀት፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ፓሊሲዎችና ስትራቴጅዎችን የመንደፍ፣ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የማወጅ፣ የጦርነት ጉዳዮችን ጨምሮ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የሕግ ረቂቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚሠሩትን ሚኒስትሮች፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ሌሎች ባለሥልጣናትና ዋና ኦዲተርን ጨምሮ የሚመርጠውና የሚያሾመው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደግሞ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው:: ስለዚህ የተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕጋዊ ድጋፍ ከመስጠት የዘለለ ስላልሆነ ሥልጣን ተጠቃሎ የወደቀው በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ነው ማለት ይቻላል::

የተወካዮች ምክር ቤት የአገር በጀት፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ የጦርነት ጉዳዮች የአገሪቱን የውጭ ፖሊሲ፣ የፋይናንስና የገንዘብ ፖሊሲ የሚመለከቱና ሌሎች በማንኛውም ነጥብ ላይ የተመሠረቱ የሕግ ረቂቆች፣ የአስፈፃሚውና የዳኝነት አካላቱ ሹማምንት በሙሉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ታይተው፣ ተገምግመው፣ ተመርጠውና ተቀባይነት አግኝተው ሲቀርቡለት ድጋፍ ከመስጠት ያለፈ ትርጉም ያለው ሥልጣን የለውም:: በተለይ ደግሞ የአንድ ፓርቲ የበላይነት ለዘላለም ተጠብቆ እንዲኖር የሚያደርግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አገዛዝ ባለበት አገር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሚቀርብለት በተለየ ሁኔታ ነፃ ውይይትና ክርክር አካሄዶ አዲስ አይነት ውሣኔ ያሳልፋል ተብሎ አይጠበቅም:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህ ሁሉ ሥልጣን ሳይበቃቸው የአገሪቱን ዋና ከተማ የአዲስ አበባን ምክር ቤት በበላይነት የመቆጣጠር ሥልጣን ወስደዋል:: ይህም አዲስ አበባ ቀድማ በተቃዋሚ ፓርቲዎች እጅ እንዳትወድቅ ታስቦ የተወሰደ ጥንቃቄ መሆኑ ግልፅ ነው:: በቅርቡ የተቋቋመው የሙስና ኮሚሽን ሳይቀር በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጥጥር ሥር እንዲውል ተደርጓል::

ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው የአሁኑ ሕገ-መንግሥት ከዚህ ግባ የሚባል ሥልጣን በጁ የሌለውን የፕሬዝደንቱን ሥልጣን ዘመን ገድቦ ሁሉን ነገር ጠቅልሎ የያዘውን የጠቅላይ ሚኒስትሩን የሥልጣን ዘመን ግን ለስንት ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት እንደሚሠራ ገደብ አላስቀመጠም:: የአንድ ፓርቲ የበላይነት ተጠብቆ እንዲኖር ስለሚፈለግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አገዛዝ እንደ ካሙዙ ባንዳ፣ እንደቦካሣና እንደ ሞቡቱ ሴሴኮ የዕድሜ ልክ ሥልጣን ሰጥቷል ለማለት ይቻላል:: የደርግ ሕገ-መንግሥት ለፕሬዝደንቱ ከሰጠው ሠፊ ሥልጣን የበለጠ የአሁኑ ሕገመንግሥት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰጥቷል ብሎ ለመናገር የማይቻልበት አሳማኝ ምክንያት የለም::

በዚሁ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ አስር የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች ከአንቀጽ 85 እስከ አንቀጽ 92 ተደንግገዋል:: ይሁን እንጂ በተግባር እየታየ ያለው ከተጻፉት መርሆዎች ውጭ እንደሚሠራ ነው:: የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የማያስከብሩና የሕዝቦቿን ጥቅም የሚፃረሩ ዓለም-አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች በተደጋጋሚ ሲፈፀሙ ተስተውለዋል::

ከኤርትራ ጋር የተፈጠረውን ውዝግብ ለመፍታት በመንግሥት የተወሠደው እርምጃ በሕገ-መንግሥቱ ከተደነገገው የውጭ ግንኙነት መርህ ጋር ፈጽሞ ተቃራኒ መሆኑ በግልፅ የታየ ነው:: መከላከያ ሠራዊቱ ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገንተኝነት ነፃ በሆነ አኳኋን እንዲሠራ ማድረግ ፈጽሞ አልተቻለም:: መከላከያ ሠራዊቱ ገዥውን ፓርቲ ሥልጣን ላይ ለማቆየት በሚያስችል አደረጃጀት በመቋቋሙ በገዥው ፓርቲ ላይ የሚደረጉ ሰላማዊ ተቃውሞዎችን በማፈንና፣ ሲቪሎችን በማንገላታት ሥራ እንዲሣተፍ በመላ አገሪቱ ተሠማርቶ የአፈና ተግባር እያከናወነ ይገኛል:: በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ሕዝቡ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት መብት ስላልተሰጠው በመላ አገሪቱ የሚቀሰቀሰውን ተቃውሞ በኃይል የመጨፍለቅ ዘመቻ በስፋት ይካሄዳል:: መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የአገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ አይከተልም:: የዜጐችን የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚያሻሽልና ዜጐች እኩል ዕድል እንዲኖራቸው የሚያደርግ ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል አሠራር የለም:: ፖለቲካውን ለሚደግፉ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ የሚቃወሙት ደግሞ ምንም ዓይነት ጥቅም እንዳያኙ የሚያደርግ የአድልዎ አሠራር ይከተላል::

የአገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ ሕዝቡን አያሣትፍም:: በምትኩ ራሱ ብቻውን ያዘጋጃቸውን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተቀብለው እንዲፈጽሙ ይገደዳሉ:: ሴቶች፣ ሠራተኞች፣ ወጣቶች፣ አረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ሕፃናት፣ ተፈናቃዮች፣ ሥራ-አጦች፣ ሴተኛ አዳሪዎችና የመሣሠሉት የተበደሉ የሕብረተሠቡ ክፍሎች የሚደገፉበት አሠራር የለም:: የግል ባለሀብቶች፣ ምሁራንና ሌሎች ሞያተኞች በነፃነት የሚሠሩበት ሁኔታ ባለመፈጠሩ ገንዘባቸውንና ዕውቀታቸውን ለአገር በሚጠቅምና ራሣቸውንም በሚጠቅም መንገድ ሊያውሉ አልቻሉም:: በዚህም የተነሣ አገር ጥለው የሚሰደዱ ብዙ ናቸው::

በዚሁ የኢህአዴግ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ አስራ አንድ ከአንቀጽ 93 እስከ አንቀጽ 106 የተደነገጉ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ በእርግጥም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶች የተከማቹበት መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው:: ቀደም ሲል በሕገመንግሥቱ የተደነገጉ የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብቶች ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ ትርፍ ነገሮች መሆናቸውን ለመግለጽ ተሞክሯል:: ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆን አንድ አብነት እዚሁ ሕገ-መንግሥት ውስጥ መጥቀስ ይቻላል:: ለምሣሌ በአንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማስወገድ ተፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሕገመንግሥቱ ከተቀመጡት አንቀጽ 1፣ 18፣ 25 እና 39 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በስተቀር ሌሎቹን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ ማገድ እንደሚችል ተደንግጓል:: በመሠረቱ የእነዚህ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተጻፈው የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ሕገ-መንግሥታዊ አምባገነንነት ለመሸፈን ታስቦ እንጂ ግምት የሚሰጠው ነገር ሆኖ እንዳልሆነ መረዳት አያዳግትም:: የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ ቀልብ የሚስቡና የሚከበሩ እሴቶች ሳይሆኑ ትርፍ ነገሮች መሆናቸውን የሚያሳይ ከዚህ የበለጠ ማረጋገጫ ሊመጣ አይችልም:: ሰብዓዊ መብቶች ሲያስፈልግ የሚሰጡ ሳያስፈልግ የሚነጠቁ ሳይሆኑ በማንኛ ውም ሁኔታ ውስጥ መከበር የሚገባቸው የማይሻሩና የማይገሰሱ እሴቶች ቢሆኑም ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚያስጨንቁ ቁምነገሮች ስላልሆኑ በምንም ሁኔታ እንዳይገሠሡ የሚፈለጉት እንደ አንቀጽ 39 የመሣሠሉት አገር በታኝ አንቀጾች ናቸው::

እነዚህን መብቶች የተነጠቀ ዜጋ ሌሎች የሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ተከብረው ቢቀመጡ ምንም ሊፈይዱለት አይችሉም። በሕይዎት የመኖር፣ አካሉ የመጠበቅና በነፃነት የመኖር መብቱን የተቀማ ዜጋ የመንግሥት ሥልጣንና መዋቅር እንዲሁም «የመገንጠል መብት» ቢጠበቅ ምንም የሚጠቅመው ነገር የለም።

ምዕራፍ 4 አንቀጽ 49 በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሄድ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል ተብሎ ቢደነገግም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ ተብሎ ስለተደነገገ የምርጫ ቦርድን ነፃነትና ገለልተኝነት እዚያው በዚያው የሚቀማ ሕግ በመሆኑ በአገሪቱ ውስጥ ነፃ የምርጫ ተቋም መመሥረትም ሆነ ነፃ ምርጫ ማካሄድ አልተቻለም። ጦሩን፣ ፖሊሱን፣ ደህንነቱን፣ ሕግ-አውጭውን፣ ሕግ-ተርጓሚውን፣ አስፈፃሚውን እንዲቆጣጠሩ የሥልጣን ሞኖፖል በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጠላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር የእራሳቸውን የፖለቲካ ሥልጣን የሚያሳጣ የምርጫ ተቋም የሚመሠርቱበትና ነፃ ምርጫ በአገሪቱ እንዲኖር የሚፈቅዱበት ዕድል ይኖራል ብሎ መገመት የሚቻል ነገር አይደለም።

የዚህ ሕገ-መንግሥት ትልቁ ችግር ደግሞ ሕዝቡ በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ እየተጠቀመ ሰላማዊ በሆነ ትግል ሕገ-መንግሥቱ እንዲሻሻልና የዜጐች ልዩ ልዩ እምነቶች፣ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና አመለካከቶች የሚቻቻሉበት ዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ እንዲፈጠር ለማድረግ ይቻላል ተብሎ እንዳይታሰብ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 104ና 105 የተቀመጡት ድንጋጌዎች ፍጹም ቀያጅ ሆነው የተቀመጡ መሆናቸው ነው። ይኸውም በመጀመሪያ በአንቀጽ 104 የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ሃሣብን ለማመንጨት የማሻሻያ ሃሣቡ በሁለቱ ምክር ቤቶች ሁለት-ሦስተኛ ድምፅ፣ ከፌደሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ አንድ-ሦስተኛው የክልል ምክር ቤቶች በድምፅ ብልጫ ሊደግፉት እንደሚገባ ተደንግጓል። እንዲህ ዓይነቱን ድጋፍ ለማግኘት በራሱ የአንድ ፓርቲ የበላይነት እንዲነግሥ በሚፈልግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አገዛዝ ሥር ያለና በነፃነት እየመከረ በነፃነት የማይወስን ምክር ቤት በተቋቋመበት አገር ከገዥው ፓርቲ ፍላጐት ውጭ የማይታሰብና የማይሞከር ነው። ይሁን እንጂ በዚህም ብቻ ሳያበቃ ሀሣቡ እንደገና ለውይይትና ለውሣኔ ለመላው ሕዝብና የሕገ-መንግሥቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል ተብሎ ተደንግጓል። የመጨረሻውን ውሣኔ የሚሰጠው ሕዝቡ መሆኑ ካልቀረ ሌሎች ዙሪያ ጥምጥም መንገዶች ቀርተው ለሕዝቡ ውሣኔ በቀጥታ የሚቀርብበት አሠራር ቢኖር የተሻለ በሆነ ነበር።

በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ 105 ንዑስ አንቀጽ 1 በሕገ-መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩ መብቶችና ነፃነቶች በሙሉ ሊሻሻሉ የሚችሉት በሁሉም የክልል ምክር ቤቶች በድምፅ ብልጫ ሲፀድቁና ሁለቱም የፌደራል ምክር ቤቶች በሁለት-ሦስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁት መሆኑ ስለተደነገገ ቀደም ሲል በአንቀጽ 104 ከተገለፀው በከፋ ሁኔታ ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ዕድል እንደሌለ የሚያረጋግጥ ድንጋጌ መቀመጡን ማየት ይቻላል። ሌሎች ሁሉ የደገፉት የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ከክልል ምክር ቤቶች በአንደኛው ምክር ቤት ለምሳሌ በሐረሪ ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ካልተደገፈ የመላው የአገሪቱ ዜጐች ጥያቄ ተዳፍኖ ይቀራል ማለት ነው። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውም ከዚህ ብዙም የተሻለ የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ መብት የሚያረጋግጥ አይደለም። ይኸውም በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 105 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌዎች የሚሻሻሉት የሁለቱ ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ሁለት-ሦስተኛ ድምጽ ድጋፍ ሲገኝና ከፌደሬሽኑ አባል ክልሎች ምክር ቤቶች ውስጥ ሁለት-ሦስተኛ የክልሎች ምክር ቤቶች የድምፅ ብልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቁት ነው ስለሚል ከክልል ምክር ቤቶች የሁለት-ሦስተኛ ክልሎች ምክር ቤቶችን ድምፅ ብልጫ ማግኘት በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ክልሎች የማይታሠብ ነው። ምክንያቱም ክልሎቹ መጀመሪያውኑ በዜጐች ፈቃድና ነፃ ውሣኔ የተቋቋሙ ስላልሆኑ የገዥውን ፓርቲ አጀንዳ ጥለው በሌላ አጀንዳ ላይ ለመምከርና ለመወሰን የሚያስችል ነፃነት ስለሌላቸው ነው። እዚህ ላይ አንድ ትዝብት በዚህ ሕገ-መንግሥት ላይ ለመጨመር ካስፈለገ

በአንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል (ለ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነጠቁ የተፈረደባቸውን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ዜጐች በሕጋዊ አግባብ እንዲሻሻሉ ጥያቄ ቢያቀርቡ ለማሻሻል በማይቻልበት መንገድ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 105 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተዘጉበት ሁኔታ መኖሩ አብዮታዊ ዴሞክራቶች ከዜጐች መብትና ነፃነት በላይ የሚንከባከቡት ሥልጣናቸውን መሆኑን የሚያሳይ ጥሩ ማስረጃ ነው፡፡

ይህ ሕገ-መንግሥት በዓለም ካሉት ሕገ-መንግሥቶች ሁሉ ለማሻሻል የሚቻልበትን ዕድል የማይፈቅድ ግትር ሕገ-መንግሥት ከመሆኑም በላይ የብዙሃን ፓርቲ ሥርዓቶችን በተጨባጭ የማይፈቅድ፣ የአንድ ፓርቲ የሥልጣን የበላይነት ለዘላለም እንዲኖር የሚፈቅድ፣ ለስሙ መብት አላቸው የሚባሉ ተቃዋሚዎች በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች ጥቂት ተወካዮችን አስመርጠው ማስገባት ከቻሉ በሕገ-መንግሥት ስም የተጻፈን የአንድ ፓርቲ ፕሮግራም ከማስፈፀም ውጭ ሌላ ዕድል እንዳይኖራቸው የከለከለ ነው፡፡ በመሆኑም አገሪቱ አሁን የምትመራው በዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት ሥርዓት ሳይሆን አናሳዎች የብዙሃኑ ገዥ በሚሆኑበት በሕገ-መንግሥታዊ አምባገነን ሥርዓት ውስጥ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በሕገ-መንግሥቱ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚዘረዝሩ አንቀጾች የሠፈሩት በሥራ ላይ እንዲውሉ ታስቦ ሳይሆን በዚሁ ሕገ-መንግሥት ውስጥ የተቀመጡትን የአንድ ፖለቲካ ቡድን አጀንዳዎች ወይም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶች መሸፈኛ ሆነው እንዲያገለግሉ ነው፡፡ ከነዚህ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የበለጠ ዋጋ የሚሰጣቸው እሴቶች ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ አገዛዝ አስፈላጊ እንደሆኑ የሚታመንባቸው የዘርና የጐሣ መከፋፈል፣ መንግሥት የአብዛኛው ሕዝብ መተዳደሪያ በሆነው መሬት ላይ ያለው ባለቤትነት ቋንቋን ብቻ መሠረት ያደረገው ፌደራላዊ አከላለል፣ የአንድ ፓርቲ ሥልጣን የበላይነትንና የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት ዋነኛ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ሕገ-መንግሥታዊ አምባገነንነት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ከማስፈር በስተቀር አፈናንና ጭቆናን አስወግዶ እንደማያውቅ፣ ለዜጐች እውነተኛ መብትና ነፃነት ፈቅዶ እንደማያውቅ በእኛ አገር ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች በተግባር የታየ ጉዳይ ነው፡፡ በኛ አገር ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክሲያዊ ሥርዓት ሳይሆን ሕገ-መንግሥታዊ አምባገነናዊ አገዛዝ እንደሰፈነ ለማረጋገጥ ብዙ ምርምር የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ በአንድ በኩል በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የሰብዓዊና ዴሞክሪሲያዊ መብቶችን ደርድሮ በሌላ በኩል ደግሞ በተግባር እነዚህን መብቶች ሙሉ በሙሉ የሚቀማ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ነው ሊባል ፈጽሞ አይችልም፡፡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በሕገ-መንግሥት መዘርዘር ብቻውን ዴሞክራሲያዊ የሚያሠኝ ቢሆንማ ኖሮ የኃይስላሴም ንጉሣዊ አገዛዝ፣ የደርግም ወታደራዊ አገዛዝ የሚወቀሱበትና የሚከሰሱበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም ነበር፡፡

የአሁኖቹ አብዮታዊ ዴሞክራቶች ከቀድሞዎቹ ገዥዎቻችን የሚለዩት አምባገነንነትን ከዘረኝነት ጋር አዋህደው በመጠቀማቸው ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በባሕሪይና በተግባር የሚያመሳስላቸው ነገር ብዙ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የተጻፈ ሕገ-መንግሥት አላቸው፣ ሁሉም ሕገ-መንግሥታቸውን የጻፉት የሕዝቡን ፍላጐትና ጥቅም ወደጐን በመተው የራሣቸውን ሥልጣን ለመጠበቅ በሚያስችላቸው መንገድ ነው፡፡ ሁሉም በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ የሰብዓዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ጽፈዋል፡፡ ሁሉም በሕገ-መንግሥታቸው ለፃፏቸው የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አክብሮት የሚሰጡ ሳይሆኑ ለየራሣቸው አጀንዳ መሸፈኛ አድርገው የሚጠቀሙባቸው ትርፍ ነገሮች ናቸው፡፡ ሁሉም ሕገ-መንግሥት ጽፈን ያቀረብነው ለሕዝብ ጥቅም አስበንና ተቆርቁረን ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡

# 4. የዴሞክራሲ ሥርዓትና መገናኛ ብዙሃን

በዴሞክራሲ ሥርዓትና በመገናኛ ብዙሃን መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ስለብዙሃን መገናኛ ምንነት መጠነኛ ግንዛቤ መጨበጥ ተገቢ ነው፡፡ የብዙሃን መገናኛ (Mass Media) ማለት ከበርካታ ሕዝብ ጋር የሚደረግን ፈርጀ ብዙ ግንኙነትና የግንኙነቱን ዘዴዎች የሚመለከት ሰፊ ትርጉም ያለው ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ የብዙሃን መገናኛ ሁሉንም አይነት እውቀት፣ መረጃና መዝናኛ የሚያመርቱና የሚያከፋፍሉ ተቋሞችን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ ብዙሃን የሚለው ፅንሰ ሀሳብ ግንኙነቱ በብዙ ሕዝብ መካከል የሚደረግ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን መገናኛ (ሚዲያ) የሚለው ደግሞ የመገናኛውን ዘዴዎች የሚመለከት ነው፡፡

በታሪክ ሚዲያ በዋናነት ጋዜጦችን የያዘ እንደነበር ሲታወቅ በዘመናችን ደግሞ ልዩ ልዩ አይነት አገልግሎቶችን አጠቃሎ የያዘ የግንኙነት ዘዴ ሊሆን መቻሉ ግልፅ ነው፡፡ መፅሔቶች፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና የኮምፒውተር ቴክኒዎሎጂን የሚጠቀም አዳዲስ የመገናኛ ዘዴዎችን የሚያጠቃልል ሰፊ አገልግሎት ሆኗል፡፡ የመገናኛ ብዙሃን ሚና የሕዝብ ግንኙነትን ቀልጣፋ በማድረግ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የባህል፣ የቴክኒዎሎጂና የአመለካከት እድገት እንዲፋጠን በማገዝም የሚንፀባረቅ ነው፡፡ የትምህርትና የሕክምና መስፋፋት ካለመገናኛ ብዙሃን ድጋፍ እንደማይገኝ የታመነ ነው፡፡ በሕዝቦችና በሀገሮች መካከል የሚፈጠር የኢንቨስትመንት ግንኙነት፣ የዲፕሎማሲ ትስስር፣ የካፒታል ፍሰት፣ የምርትና የአገልግሎት ዝውውር ካለመገናኛ ብዙሃን አስተዋፅኦ ይቀላጠፋል ተብሎ የሚታሰብ ነገር አይደለም፡፡ በአለማችን የሚከሰቱ ፖለቲካዊ ሁነቶች ከአንዱ ወደሌላው ጫፍ የሚሰራጩት በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ነው፡፡ አብዛኞቹ የፖለቲካ መረጃዎች በመገናኛ ብዙሃን መሰራጨት ባይችሉ ኖሮ ሊያጋጥም የሚችለውን ችግር መገመት አያዳግትም፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ስርዓት ሙሉ በሙሉ በፖለቲካዊ ቁጥጥር ሰር ሲወድቅና የአደረጃጀትም ሆነ የአሰራር ነፃነት የሌለው በሚሆንበት ጊዜ እውነተኛ፣ ሚዛናዊ፣ ገለልተኛና ተጨባጭ መረጃ ለማሰራጨት የሚያስችል አቅም አይኖረውም፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ መገናኛ ብዙሃን የሚጠበቅበትን የማሳወቅ፣ የማስተማርና የማዝናናት ሚናውን በአግባቡ ለመወጣት የማይችል ብቻ ሳይሆን ተራ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ የመሆን ከባድ አደጋም ያጋጥመዋል፡፡ ሚዲያ ከመንግስትና ከፖለቲካ ቡድን ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ራሱን በቻለ መንገድ ሲንቀሳቀስ ልዩ ልዩ የፖለቲካ አመለካከቶች እንዲንሸራሸሩና ክርክር እንዲደረግባቸው የሚያስችል መድረክ በመሆን ዴሞክራሲ የሚስፋፋበትና ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት የሚረጋገጥበት ሆኖ ያገለግላል፡፡ በነፃነት የሚደራጅና የሚመራ መገናኛ ብዙሃን ሲኖር ባት ማታ የመንግስትን ወይንም የተወሰነ ፖለቲካ ቡድንን ውስን አጀንዳ የሚሰብክ ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት ፋንታ የአንባቢውን፣ የተመልካቹንና የአድማጩን ፍላጎት የጠበቀ ሰፊ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡

## 4.1 በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን ሚና

በዘመናችን በአለም አቀፍ ደረጃ ከፓርላማ መድረክ በተጨማሪ የሚደረጉ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ለማደራጀት ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ መድረክ ቢኖር የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ነው፡፡ የመገናኛ ብዙሃን የውስጥና የውጭ ክስተቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ምንጭ ሆኖ ስለሚያገለግል ሕዝቡ ሚዲያ አንብቦ፣ አዳምጦና ተመልክቶ ስለማያውቃቸው ጉዳዮች አዲስ መረጃ ያገኛል፡፡ በዚህም አማካይነት ፖለቲካዊ ግንዛቤውን ያሳድጋል፡፡ ሌላው የመገናኛ ብዙሃን ጥቅም ሕዝቡ ሀገሩንና ሕልውናውን በሚመለከቱ ፖሊሲዎች አወጣጥ ሂደት ተሳትፎ እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ ነው፡፡ የአንድ ሀገር ፖሊሲ በጥቂት የአገዛዝ ቡድን አባላት እውቀትና ፍላጎት ብቻ የተወሰነ እንዳይሆንና የሕዝቡ

አስተያየት በመንግስት ፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ጎልቶ እንዲንፀባረቅ ሚዲያ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። አናሳዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ችላ እንዳይባሉና ትኩረት እንዲያገኙ አጉልቶ በማንፀባረቅ መገናኛ ብዙሃን ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ከዚህ ሌላ መገናኛ ብዙሃን የሚጫወተው ጠቃሚ ሚና ቢኖር ሕዝቡ የመንግስትን አሰራር እየተከታተለ ለመቆጣጠርና ጉድለቶቹን ለማረም የሚችልበትን እድል መፍጠር ነው። ሕዝቡ ከሚዲያ በሚያገኘው መረጃ እየታገዘ በመንግስት የሚከናወኑ ተግባሮች በጥንቃቄ መካሄዳቸውን በየጊዜው ለመከታተል ይችላል። የመንግስትም የአፈፃፀም ሪከርድ እየገመገመ ጉድለት ያለበትን ግለሰብ ባለሥልጣንና የመንግስት ተቋም ለመንቀፍ፣ ለማረምና እርምጃም ለመውሰድ ዝግጁ ይሆናል። በዚህ መልክ የተዘጋጀ ሕዝብ ሲኖር ደግሞ መንግስት ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ተጠያቂነት እንዳለበት አውቆ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ያስችላል።

በሁሉም የዴሞክራሲ ሥርዓቶች መገናኛ ብዙሃን በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋሉ። እንደአሁኑ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎትና ሚና ጎልቶ ባልወጣበት በ10ኛው ክፍለ ዘመን ሕዝቡ ፖለቲከኞችን የሚገመግምበት ብቸኛ መንገድ በየጊዜ በሚዘጋጁ ስብሰባዎች ላይ እየተገኘ የፖለቲከኞችን ዲስኩር በማዳመጥ ነበር። በዚያን ወቅት በስብሰባ ላይ አንደበተ ርቱዕ ሆኖ መገኘት የሚያስመሰግን ፖለቲካዊ ችሎታ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። ነገር ግን ሁኔታው በዚህ መልክ ሊቀጥል አልቻለም። በመጀመሪያ ደረጃ ፖለቲከኞች በአንድ የተወሰነ መድረክ በአካል እየተገኙ ከሚያሰሙት ዲስኩር የበለጠ በፕሬስ አማካይነት ሀሳባቸውን በሚያስተላልፉበት ጊዜ ለብዙ ሰው መልዕክታቸውን ለማዳረስ እንደሚችሉ ግንዛቤ እየተገኘ መጣ። ከዚያም ቀጥሎ ሬዲዮ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ቴሌቪዥንና ኢንተርኔት በመጠቀም ፖለቲከኞች ሀሳባቸውን በእያንዳንዱ ሰው መኖሪያ ቤት ውስጥ ለማድረስ ስለተቻለ የመገናኛ ብዙሃን አስተዋፅኦ ምትክ የማይገኝለት መሆኑ ይበልጥ ተቀባይነት አገኘ። እንደዚህ አይነቱ የሀሳብ ማስተላለፊያና የመረጃ ማሰራጫ መንገድ መከፈት በየሀገሩ በሚካሄድ የምርጫ ዘመቻዎች ላይ ጠቃሚ ተፅዕኖ ማሳደር ቻለ። በተለይም ቴሌቪዥን በየሀገሩ በሚደረጉ ምርጫዎች ላይ ያስከተለው ለውጥና ውጤት ከፍተኛ ነው። እጩ ተወዳዳሪዎች በቴሌቪዥን ቀርበው ፊት ለፊት እየተከራከሩ ሀሳባቸውን ለብዙ ሕዝብ ማስተላለፍ የሚችሉበትን እድል በመፍጠሩ በምርጫ ዘመቻ ወቅት እንደአንድ አስፈላጊ የምርጫ ዘዴ እየታየ ነው። የቴሌቪዥን ክርክር በሁሉም የዴሞክራሲ ሥርዓቶች ጥቅም ላይ የሚውል ቢሆንም በተለይ ደግሞ በቀጥታ የሕዝብ ምርጫ ፕሬዝዳንቶቻቸውን በሚመርጡ ሀገሮች በሰፊው የሚሰራበት ዘዴ ነው። ፓርላሜንታሪ የመንግስት አይነት ባለባቸው ሀገሮችም ቢሆን በፓርቲ መሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ምርጫው የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ሥልጣን ለመጨበጥ የሚደረግ ውድድር መሆኑን አጉልቶ በሚያንፀባርቅ ደረጃ የቴሌቪዥን ክርክር ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል።

በዚህም ምክንያት በፖለቲከኞች መካከል የሚካሄድ የቴሌቪዥን ክርክር በአንድ በኩል በፓርቲ ጉዳይ ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ጥንቃቄ የተሞላበት አሰራር እንዲኖር ሲያግዝ በሌላ በኩል ደግሞ ለመንግስት ስልጣን ከሚደረግ የምርጫ ውድድር ጋር በተያያዘ የአካባቢ ፓርቲ አባላት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ጠቃሚነት ቀንሶታል። በእርግጥ ይህ ሁኔታ የቴሌቪዥን አገልግሎት የተስፋፋባቸውንና አብዛኛው መራጭ በቤቱ ውስጥ የቴሌቪዥን ተጠቃሚ ለመሆን በበቃባቸው ሀገሮች ያለውን እውነታ ብቻ የሚያንፀባርቅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የቴሌቪዥን ጥቅም በቴሌቪዥን ክርክር ብቻ የታጠረ ሳይሆን ከዚህም የሰፋ ነው። ከምርጫ ወቅት በፊት ፓርቲዎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴና ልዩ ልዩ ክስተቶች በጥንቃቄ እየቀረፀ ለተመልካች በማቅረብ በምርጫ ውድድር ወቅት ደግሞ ከውድድሩ ጋር በተያያዘ የሚዘጋጁ ስብሰባዎችን፣ የድጋፍ ሰልፎችን፣ ጋዜጣዊ መግለጫዎችንና ልዩ ልዩ ፖለቲካዊ ድርጊቶችን አቀነባብሮ በማሰራጨት ተመልካቾች ስለአንድ ፓርቲ ገንቢ ስዕል

በአዕምሯቸው እንዲቀርፁና ግንዛቤያቸውን የሚያሰፋ መረጃ እንዲያገኙ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

በዴሞክራሲ ስርዓቶች ውስጥ ሚዲያ የፖለቲካ ክስተቶችን አቅጣጫ የመወሰንና ሀገራዊ አስተያየቶችን የመምራት ችሎታ እንዳለው ተደርጎ ስለሚወሰድ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዘ የባለቤትነትና የግንኙነት ጥያቄ እንደ አንድ ጠቃሚ ጉዳይ የሚታይ ነው። የመንግስትን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና የፖለቲካ ሰዎችን ጉድለቶች እየተከታተሉ ይፋ በማድረግ የተደበቁ እውነቶችን በአደባባይ አውጥቶ ከማጋለጥም በላይ የሕዝብን አስተያየት አቅጣጫ የማስያዝ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት አንዳንዴ «አራተኛው የመንግስት ስልጣን አካል» እየተባለ የሚጠራበት ሁኔታ አለ። በመሆኑም ከመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ክርክር ሚዲያ የፖለቲካ አጀንዳን የመቅረፅ ችሎታ እንዳለው በማመንና ባለማመን መካከል የሚታይ ነው። በዴሞክራሲ ስርዓቶች ውስጥ መገናኛ ብዙሃን አንድን የተወሰነ ነጥብ በሰፊው ለሕዝብ በማስተጋባትና በተለየ ጥንቃቄ አቀነባብሮ በማሰራጨት የአንባቢዎች፣ አድማጮችና ተመልካቾች ትኩረት ወደዚህ ርዕስ እንዲሰባሰብ በማድረግ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው። የሚሰራጨው ሀሳብ የሚያስከትለው ውጤት መጥፎነትና ጥሩነት የሚወሰነው ከሚዲያው በስተጀርባ ባለው ፍላጎት ላይ መሆኑ ባይካድም ሚዲያው አንድን ሀሳብ በማሰራጨት በሕዝቡ ግንዛቤ ላይ ሊያሳርፍ የሚችለው ተፅዕኖ መኖሩን ስለማያስቀረው የመገናኛ ብዙሃንን የፖለቲካ አጀንዳ የመቅረፅ ችሎታ አሳንሶ መመልከት አይቻልም። ከዚህ ነጥብ ጋር ተያይዞ መነሳት የሚገባው ጥያቄ ሚዲያው በወገንተኝነት ፍላጎት ከተመራ ወይንም ገለልተኝነትና ሚዛናዊነት ከሌለው የሚከተለው ውጤት ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ነው። የሚዲያን ተቀዳሚ ትኩረት የሚዲያው ባለቤት ወደሚከተለው አቅጣጫ ለመጎተት ወይንም ባለቤቱ ወደሚደግፈው የፖለቲካ አጀንዳ ለመሳብ ጥረት የሚደረግ ከሆነ የሚዲያው ሀቀኛነትና ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ መሆኑ የማይቀር ነው። ውጤቱም የተጠቃሚውን ሕዝብ አመለካከት ሚዛናዊነት የሚያዛባ ስለሚሆን የሚዲያ ባለቤትነት፣ ሀላፊነትና መብት በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ሊካተት የሚገባው ነው።

የመገናኛ ብዙሃንን አገልግሎት በሕጋዊ ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ለመምራት በሚፈለግበት ጊዜ ታሳቢ የሚደረጉት ጉዳዮች በጣም በርካታ ቢሆኑም የተወሰኑትን መሰረታዊ የመርህ ጉዳዮች ማንሳት ይቻላል። የመጀመሪያ ትልቅ ነጥብ ማንኛውም ሰው ሀሳቡንና አስተያየቱን የመግለፅ ነፃነት ያለው መሆኑን፣ ይህ ነፃነት የሌሎችን መብት በማክበር ላይ የተመሰረተ ሆኖ አስተያየት የማመንጨትና በማናቸውም መገናኛ ዘዴ አማካይነት ያለገደብ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማስተላለፍ ነፃነትን እንደሚያጠቃልልና ይኸም የሰው ልጅ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መብት መሆኑን አምኖ መቀበል ነው። ሀሳብና አስተያየት የሚገለፅባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች ያሉ ሲሆን በንግግር፣ በፅሑፍ፣ በሙዚቃ፣ በቲያትር፣ በስዕልና በመሳሰሉት ሊሆን ይችላል። ሀሳብ የሚመነጭባቸው፣ መረጃ የሚሰበሰብባቸው፣ የመረጃ መቀበያዎችና መተላለፊያ መንገዶችም በርካታ ሲሆኑ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ቴሌፎን፣ ኢንተርኔት፣ ጋዜጣ፣ ፊልም፣ መፅሔት፣ መፅሐፍና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ከእነዚህ ምንጮች መረጃ የመሰብሰብና የማግኘት፣ በእነዚህ አማካይነት መረጃ ለሌሎች የማስተላለፍ መብት አለው። መረጃ ሲባል ደግሞ በንግግርና በፅሑፍ መልክ ወይም በሌላ አይነት አቀራረብ የተዘጋጀ ዜና፣ ጥናት፣ አስተያየት፣ መግለጫ፣ ሪፖርት፣ ወይም ሌላ መረጃ ሊሆን ይችላል።

ይህ መብት ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትን ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ማወቅ የሚፈልገውን ጉዳይ በሚመለከት መረጃ የማግኘትና የማወቅ መብት ያለው መሆኑንም አጠቃሎ የያዘ ነው። ስለዚህ የመገናኛ ብዙሃንን የሚመለከት የሕግ ስርዓት ለመዘርጋት ሲታሰብ ይኸንን

*መሰረታዊ የሰው ልጅ ነጻነትና (ሀሳብን የመግለፅ ነጻነት) ለማወቅ የሚያስችለውን መረጃ የማግኘት መብት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ጥንቃቄ ይደረጋል።*

*ሁለተኛው መሰረታዊ ነጥብ ሀሳብን በልዩ ልዩ መንገድ የመግለፅና መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማስተላለፍ ነፃነት ገደብ የማይደረግባቸው መሆናቸው ነው። ይህ ነፃነት የሌሎችን መብት የሚያከብር እንዲሆን የሚፈለገው በሰው ልጅ ነፃነት ላይ ገደብ ለመጣል ሳይሆን ራሱን ነፃነቱን ለማስፋት በማሰብ ነው። አንድ ሰው የራሱን ነፃነትና መብት በሚጠ ቀምበት ጊዜ የሌላውን ሰው መብት የማያከብር ከሆነ ዞሮ ዞሮ የተደፈረው መብትና ነፃነት የሰው ልጅ ነፃነትና መብት ስለሚሆን የአንዱን እያከበሩ የሌላውን መግፈፍ እስካለ ድረስ ትርጉም ያለው መብትና ነፃነት አይኖረም። ስለዚህ እንዲከበር የሚፈለገው ነፃነት ሙሉና ትርጉም ያለው እንዲሆን የሚያስችል ሕጋዊ ሥርዓት በመዘርጋ ይኸንኑ ነፃነት በማስፋት የተሟላ ለማድረግ ጥንቃቄ ይደረጋል።*

*ሶስተኛው ነጥብ ከዴሞክራሲ ሥርዓት መመዘኛዎች አንዱና ዋኛው ሀሳብን ለመግለፅ የሚያስችል ሰፊ እድል መኖሩ ማለትም የተለያዩ አስተያየቶችን የፖሊሲ ጉዳዮች ሲቀረፁ ግልፅ ውይይትና ክርክር ለማድረግ፣ ልዩ ልዩ አመለካከቶች፣ መረጃዎች፣ ሀሳቦችና አስተያየቶች በነፃነት የሚንሸራሸሩበት የንግግር ነፃነት መኖሩ ነው። እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችለው አንዱ መንገድ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃንን አደረጃጀትና አሰራር ነፃነት መጠበቅ እንደመሆኑ ይኸንኑ ነፃነት የተቀበለና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ ሥርዓት እንዲኖር ትኩረት ይደረጋል። ወይም ነፃ ፕሬስን የሚያከብርና የሚንከባከብ የሕግ ስርዓት ይመሰረታል።*

*አራተኛው ታሳቢ ነጥብ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤት ማንም ይሁን ማን ወይንም ለምንም አላማ የተቋቋመና የሚሰራ ይሁን የሰውን ልጅ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትና መረጃ የማግኘት መብት የመቀበልና የማክበር ግዴታ ያለበት መሆኑ ነው። በተለይ ደግሞ በመንግስት ገንዘብና ባለቤትነት ተቋቁሞ የሚሰራ መገናኛ ብዙሃን ቀዳሚ አላማ ትርፍ ማግኘት ሳይሆን አገልግሎት መስጠት እንደመሆኑ የተለያዩ አስተያየቶችን በእኩልነት ለማስተናገድ በሚያስችለው አደረጃጀትና አሰራር እንዲመራ የሚያስችል የሕግ ስርዓት እንዲኖር ያስፈልጋል። እዚህ ላይ በመንግስት ገንዘብና ባለቤትነት የሚንቀሳቀስ መገናኛ ብዙሃን አትራፊ በሆነ ስራ እንዳይሰማራ ጨርሶ የተከለከለ አድርጎ መገንዘብ ወይንም ደግሞ ቀዳሚ አላማው ትርፍ ማግኘት ሆኖ የተቋቋመ በግል ወይም በሽርክና የሚመራ የመገናኛ ብዙሃን ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትንና መረጃ የማግኘት መብትን የማክበር አልያም የተለያዩ አስተያየቶችን በእኩልነት የማስተናገድ ግዴታ ፈፅሞ እንደሌለበት አድርጎ መመልከት ተገቢ አይደለም። ልዩነቱ ያለው ለተቋሞቹ መፈጠር ቀዳሚ ተልዕኮ ተደርጎ በሚወሰደው ጉዳይና ለማሳካት በሚጠበቅባቸው አላማ ቅደም-ተከተል መካከል እንጂ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትንም ሆነ መረጃ የማግኘት መብትን በማክበርና ባለማክበር መካከል አይደለም። ስለዚህ በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ያለ የመገናኛ ብዙሃንን በሕጋዊ ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ እንዲሰሩ ለማስቻል በሚደረግ ጥረት ሁሉ እነዚህ የተጠቀሱት መሰረታዊ መርሆዎች ታሳቢ መሆናቸው የግድ ነው። ከሞላ ጎደል ሁሉም የዴሞክራሲ ስርዓቶች የሚጠቀሱትን መርሆዎች ተከትለው እንደሚሠሩ መግለፅ የሚቻል ቢሆንም የተወሰኑትን ሀገሮች ልምድ ለአብነት በማቅረብ ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ በጀርመን የመገናኛ ብዙሃን መብት በመንግስት ሕግ ማዕቀፍ ውስጥ  የተካተተ ሆኖ የፕሬስ ነፃነትን፣ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትንና መረጃ የማግኘት መብትን በሚያረጋግጥ መንገድ ተደራጅቶ የሚሰራ ነፃ ተቋም ነው። በሚዲያ ስራ የሚሳተፉ ክፍሎች ከመንግስት ተፅዕኖ ነፃ ሆነው፣ የሙያውን ስነምግባር ጠብቀውና የኃላፊነት ስሜት ተላብሰው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል።*

የመገናኛ ብዙሃንን የሚመለከተው ሕግ ጋዜጠኞች የመረጃ ምንጮቻቸውን እንዲገልፁ የሚደረግባቸውን ጫና ለመቃወም ያላቸውን መብት እንዲሁም በጋዜጣም ይሁን በሌላ የሚዲያ ዘርፍ አስተያየት የቀረበበት ግለሰብና ተቋም በዚያው ሚዲያ ማስተባበያ የማቅረብና አስተያየት የመስጠት መብትን ያካተተ ነው፡፡ ቅድመ ምርመራ ፈፅሞ የተከለከለ መሆኑ በጀርመን ሕገ መንግስት አንቀፅ 5 ላይ የሰፈረ ሲሆን አሳታሚዎችና ጋዜጠኞች በጀርመን ፕሬስ ካውንስል አማካይነት በራሳቸው ላይ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ በእርግጥ ለጥንቃቄ ሲባል በሕግ ግልፅ ሆኖ በተቀመጠ ሥርዓት ላይ ተመስርቶ ሚዲያው የሕትመቱን ርዕስ፣ የሚታተምበትን ስፍራ፣ ቀን፣ የባለቤቱንና የአሳታውን ስም እንዲያሳውቅ የሚጠየቅበት አሰራር አለ፡፡ ፕሬስ በቀድሞዋ ምስራቅ ጀርመን ሕዝቡን ለማሽከርከር በሚጠቅም መንገድ ገዥው ፓርቲ የሚቆጣጠረውና የሚመራው ቁልፍ መሣሪያ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሁሉም ጋዜጦች የቅድመ ምርመራ ግዴታ ተጥሎባቸው ቆይቷል፡፡ ሁሉም ጋዜጦች በፓርቲው ዶክትሪን ላይ ተመስርተው የሚዘግቡ መሆኑን የማረጋገጥ ተግባር የፓርቲው ኃላፊነት ነበር፡፡ ጀርመኖችን የከፈላቸው ግንብ ፈርሶ ውህደቱ ተግባራዊ መሆን ሲጀምር ነፃ ፕሬስ በቦታው ተተካ፡፡ ቅድመ ምርመራ መደረግ የተከለከለ ሆነ፡፡ የመገናኛ ብዙሃንም ኃላፊነት የአንድን ፓርቲ ዶክትሪን ማራገብ መሆኑ ቀርቶ ማንም ይፈፅመው ማን ወይንም የትም ይፈፀም የት እውነትን እየፈለጉ በወቅቱ ለሕዝብ ማቅረብ መሆኑ ተረጋገጠ፡፡ በዚህም ምክንያት በአለም ደረጃ ያለውን የፕሬስ ነፃነት የሚከታተለውና ለንደን የሚገኘው አለም አቀፍ የፕሬስ ተቋም የጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ የፕሬስን ነፃነት በማክበር ጠንካራ አቋም ካላቸው መንግስታት መካከል አንዱ መሆኑን እውቅና ሰጥቷል፡፡

የጀርመን ፌዴራል ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤት በግልፅ እንዳስቀመጠው «በመንግስት ቁጥጥር ስር ያልወደቀና ለቅድመ ምርመራ ያልተጋለጠ ነፃ ፕሬስ መኖር የአንድ ነፃ ሀገር መሰረታዊ መለያ ነው፡፡» በተለይ የማይቋረጥና መደበኛ በሆነ ነፃ አሰራር የሚመራ ፕሬስ መኖር ከዘመናዊ ዴሞክራሲ የማይነጠል አንድ አካል ነው፡፡ ሕዝቡ ውሳኔ ማድረግ ካለበት ልዩ ልዩ አስተያየቶችን ለማመዛዘን የሚያስችሉ መረጃዎችን የግድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ እንዲህ አይነት መረጃዎችን የሚያገኘው ደግሞ የተለያዩ ብቃት ያላቸው የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎቶች ሲኖሩና በነፃነት ተደራጅተው ሲሰሩ ነው፡፡ ብቁና ብዙ አይነት የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎቶች ካሉ ሕዝቡ ሰፊ ምርጫ ለማግኘት ይችላል፡፡ ይኸንን መሰረተ ሀሳብ መነሻ በማድረግ በጀርመን ውስጥ የሚዲያ አይነት እንዲበዛና ሕዝቡ ሰፊ ምርጫ እንዲኖረው መንግስት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ1991 መጨረሻ በምዕራቡ የጀርመን ክፍል ብቻ በየዕለቱ የሚታተሙ ጋዜጦች ሽያጭ በቀን 29 ሚሊዮን ኮፒ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገቡ ከ25 ሚሊዮን የሚበልጡ ቴሌቪዥኖችና ከ28 ሚሊዮን በላይ ሬዲዮናች በእያንዳንዱ ዜጋ ቤት ውስጥ አሉ፡፡ እድሜያቸው ከ14 ዓመት በላይ የሆኑ ጀርመኖች በአማካይ በቀን 5 ሰዓት በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ይጠቀማሉ፡፡ ይኸውም ለጋዜጦች 30 ደቂቃ፣ ለሬዲዮ 2 ሰዓት ተኩል (2:30) እና ለቴሌቪዥን 2 ሰዓት ይጠቀማሉ ማለት ነው፡ ይህ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ በመምጣቱ የመገናኛ ብዙሃኑ አገልግሎት እየጨመረ መጥቷል፡፡

የሚዲያ አገልግሎት የማያገኘው ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ ከ5% ያነሰ ሲሆን ከ95% በላይ ግን አገልግሎቱ ይደርሰዋል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ መረጃ የሚያገኘው ከ2 እና ከዚያም በላይ ከሆኑ የሚዲያ ዘርፎች ነው፡፡ ብዙዎቹ የፖለቲካ መረጃ ለማግኘት በመጀመሪያ ቴሌቪዥን ይጠቀማሉ፡፡ ከዚያም በጣም ዝርዝር የሆነ መረጃ ሲፈልጉ ጋዜጦችን ያነባሉ፡፡ የአካባቢ ዜና ለማግኘት ሕዝቡ በብዛት የሚጠቀመው የአካባቢ ጋዜጦችን ነው፡፡ ወጣቶች ጋዜጣ የሚያነቡት አልፎ አልፎ ቢሆንም ከዝንባሌያቸውና ፍላጎታቸው ጋር የሚሄዱ ሌሎች ሚዲያዎችን እየመረጡ ለመከታተል እድል አላቸው፡፡

የፌዴራሉ መንግስት የፕሬስና መረጃ ቢሮ በመንግስትና በሕዝቡ መካከል እንደ መገናኛ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። የዚህ ሕዝባዊ ሥልጣን ኃላፊ በተመሳሳይ ሁኔታ የመንግስት ቃል አቀባይ ሆኖ ይሰራል። አንዳንድ ሀገሮች እንደሚያደርጉት የመንግስት ቃል አቀባይ ተግባር የፌዴራል ፕሬስ ኮንፍረንስ ሲካሄድ እየተገኘ ለቦን ጋዜጠኞች ማብራሪያ በመስጠት ብቻ የተወሰነ አይደለም። ይህ አሰራር የጀርመን ቻንስለር በሚሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫና ከፌዴራል ፕሬስ ኮንፍረንስ ጋር በተያያዘ ሚኒስትሮች በሚያካሂዱት ማብራሪያና ውይይት ተፈፃሚነት አለው። ባለሥልጣኖች ወደ ሚዲያው ሄደው መግለጫና ማብራሪያ ይሰጣሉ እንጂ ሚዲያ እነሱን እየተለማመጠና ደጅ እየጠና የሚዘግብበት አሰራር የለም። የፕሬስና መረጃ ቢሮው የፌደራሉ ፕሬዝደንት፣ የፌዴራል መንግስትና የፓርላማ አባላት ስለጀርመን በውጭ ያለው አስተያየት፣ ስለውጭና ስለሀገር ውስጥ ዜናዎች መረጃ እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ይኽንን ኃላፊነት እየተወጣ ብቁ አገልግሎት ለመስጠት የፌዴራሉ ፕሬስና መረጃ ቢሮ 27 የዜና ወኪሎችን፣ በጀርመንኛ ቋንቋ የሚሰራጩ ከ100 በላይ የሬዲዮ ፕሮግራሞችና 25 የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እንዲሁም 22 በውጭ ቋንቋ የሚሠራጩ ፕሮግራሞችን ይገመግማል።

የሕዝብ አስተያየት ምርምር ማካሄድ ደግሞ ሌላው በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው። በመገናኛ ብዙሃን የሚገለፅ አመለካከት በብዙ ሁኔታዎች በጠቅላላው እንደሕዝብ አስተያየት የማይፈረጅ ቢሆንም የታተመ (የተፃፈ) የሕዝብ አስተያየት ተደርጎ መወሰድ ያለበት ነው። ዴሞስ ኮፒ (Demos Copy) የሕዝብ አስተያየት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚጠናበት ዘዴ ሲሆን ውጤቱ ለሕዝብ የሚቀርበው በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ነው። ይህ ጥናት ወካይ ናሙናዎችን አጥንቶ በማቅረብ አሰራር ላይ የሚመሰረት ሲሆን የጠቅላላውን ሕዝብ አስተያየት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመገምገም ብዙውን ጊዜ ከ1 ሺህ እስከ 2 ሺህ የሚደርሱ ሰዎችን አስተያየት መሰረት አድርጎ ያጠናል።

በጀርመን የሕዝብ አስተያየት ጥናቶች የሚያካሂዱ በርካታ ቁጥር ያላቸው የግል ተቋሞች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የፖለቲካ አስተያየት ጥናት የሚያደርጉት የአብዛኛውን ሕዝብ ትኩረት እንደሚስቡ በተግባር የሚታይ ነው። ትላልቆቹ የጀርመን ጋዜጦችና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በቋሚነት የሚወጡ ፅሁፎች (Periodicals) እንዲሁም የቴሌቪዥን ድርጅቶች የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ዝንባሌ አስመልክቶ እነዚህ ጥናቶች የሚያስገኙትን ውጤት በተከታታይ ይዞ በመውጣት ለሕዝብ ይፋ ያደርጋሉ። የፓርቲዎችንና መሪ ፖለቲከኞችን ገፅታ፣ በወቅታዊ ርዕሶች ለምሳሌ በኒውክለር ኃይል፣ በሥራ አጥነትና በፖለቲካ ጥገኝነት ጉዳዮች ላይ ያለውን የሕዝብ አስተያየት በሚመለከት የተካሄዱ ጥናቶችን ውጤት ያቀርባሉ። የፌዴራሉና የክልል መንግስታት እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ በኩል የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ፕላን በሚነድፉበት ጊዜ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ያስከተሉትን ጥሩና መጥፎ ውጤት በሚገመግሙበት ጊዜ በሕዝቡ ውስጥ የሚታዩትን የአመለካከት ለውጦች ጎን ለጎን መረዳት እንዲችሉ እነዚህን የሕዝብ አስተያየት ጥናት ውጠ ቶች በሰፊው ይጠቀሙባቸዋል።

ጋዜጦች በጀርመን ውስጥ ተቀባይነታቸው እየጨመረ ነው። ከቴሌቪዥን እድገትም የበለጠ እድገት አሳይተዋል። ለእያንዳንዱ አንድ ሺህ ነዋሪ በሚደርሰው የጋዜጣ ቁጥር አኳያ ከጃፓን፣ ከዩናይትድ ኪንግደምና ከስዊዘርላንድ ቀጥሎ ጀርመን የአራተኛነትን ቦታ ይዛለች። በተለይም ጋዜጦች የጎላ መድረክ እንደያዙ መረዳት ይቻላል። በሥራ ቀኖች 410 የሚሆኑ ጋዜጦች ታትመው ይወጣሉ። ከ150 በሚበልጡ ቢሮዎች ወደ 1,700 የሚጠጉ የአካባቢና የክልል ሕትመቶችን ያትማሉ። ጠቅላላ የሽያጭ መጠናቸው በቀን ወደ 28.8 ሚሊዮን ኮፒ ገደማ ነው። ትናንሽ ፅሑፎችም እንደዚሁ በዋና ዋና ብሔራዊና አለም አቀፍ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ስፖርትና የአካባቢ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ መረጃዎችን

ለአንባቢዎቻቸው የማቅረብ ስራ ያከናውናሉ። ከሁሉም ጋዜጦች 2/3ኛ በላይ የሚሆነው መጠን ቅድሚያ ክፍያ በሚፈፅሙ ቋሚ ደንበኞች (subscribers) የሚገዛ ሲሆን የቀረው ደግሞ በዋና ዋና ጎዳናዎች የሚሸጥ ነው። በጎዳና ላይ ከሚሸጡ ጋዜጦች መካከል ከፍተኛ ስርጭት ያለው በቀን 4.5 ሚሊዮን ኮፒ ይሸጣል። ይህንን የስርጭት መጠን ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ስናነፃፅረው ምን ያህል ገና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ ያሣየናል።

ሬዲዮና ቴሌቪዥን በጀርመን ውስጥ በመንግስት ብቸኛ ባለቤትነትና ቁጥጥር ስር የወደቁ ተቋሞች አይደሉም። በሕዝብና በግል ባለቤትነት ስር ሆነው የአደረጃጀትና የአሰራር ስርዓታቸው ግልፅነት ባለው የሕግ አግባብ የተቀመጠ ነው። ሕጉ መሰረታዊ የሆነውን ሀሳብን የመግለፅ፣ መረጃን የማግኘት፣ የማሰባሰብና የማሰራጨት ነፃነትን እንዳይገድብ በከፍተኛ ጥንቃቄ የተዘጋጀ ነው። በእነዚህ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፎች ረገድ ጀርመን ጎን ለጎን የሚሄዱ ሁለት አይነት አደረጃጀቶች አሏት። እ.ኤ.አ በ1986 የፌዴራሉ ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤት በወሰነው መሰረት አንደኛው አደረጃጀት የሕዝብ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽኖች የሚባሉትን የሚያቅፍ ሲሆን ሁለተኛው አደረጃጀት ደግሞ የንግድ ብሮድካስቲንግ (Commercial Broadcasting) የሚባሉትን የግል ማሰራጫ ኩባንያዎችን የሚመለከት ነው። ይኸው ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤት የሕዝብ ማሰራጫ ኮርፖሬሽኖች የሕዝቡን አጠቃላይ የሥርጭት ፍላጎት ማሟላት እንዳለባቸውና ለዚህም የግል ኩባንያዎች ተጨማሪ ድጋፍ በመስጠት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ወስኗል። እንደሚታወቀው በጀርመን ውስጥ ለረጅም አመታት የሕዝብ ኮርፖሬሽኖች ብቻ የሚሰሩበት ሁኔታ ሰፍኖ የነበረ ቢሆንም እ.ኤ.አ. በ1984 የግል ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ስርጭት እንዲኖርና ስራውም በውድድር መርህ እንዲካሄድ በመደረጉ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ስርጭት ይበልጥ ነፃና ብቃት ያለው መሆን ችሏል።

የራስ አስተዳደርና የብሮድካስቲንግ ነፃነት በጀርመን የተረጋገጠ ነው። ይህ ነፃነት በአደረጃጀትና በአሰራር የሚገለፅ ሲሆን የሕዝብ ኮርፖሬሽኖች በአጠቃላይ በ3 አካላት ቁጥጥር ስር ናቸው። እነሱም፣

1. የሬዲዮ ምክር ቤት ወይም የቴሌቪዥን ምክር ቤት
2. የአስተዳደር ም/ቤትና
3. ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው።

የሬዲዮና የቴሌቪዥን ም/ቤቶች አባላት ጠቃሚ ከሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶችና ማህበራዊ ቡድኖች የተወከሉ ናቸው። አባሎቻቸው በክልል መንግስታት ም/ቤቶች የተመረጡ ወይም በፖለቲካ ፓርቲዎች በኃይማኖት ተቋሞች በንግድና በባህል ድርጅቶች የተጠቆሙ ናቸው። የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ምክር ቤት ተግባር መሰረታዊ የብሮድካስቲንግ መርሆዎች መከበራቸውንና በፕሮግራም ጉዳዮች ዙሪያ ዋና ስራ አስኪያጅን (Director General) ማማከር ነው።

የአስተዳደር ም/ቤቱ የኮርፖሬሽኑን በጀት ያዘጋጃል፣ የዕለት ለዕለት አስተዳደሩን ስራ ይከታተላል፣ በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ ይሰጣል። አባላቱ የሚመረጡት በሬዲዮ (ቴሌቪዥን) ም/ቤት ሲሆን እነሱ ደግሞ በበኩላቸው ዋና ስራ አስኪያጁን ይመርጡና በብሮድካስቲንግ ም/ቤቱ እንዲፀድቅ ያደርጋሉ። ዋና ሥራ አስኪያጁ የብሮድካስቲንግና የአስተዳደር ም/ቤቶች በሚወስኑት መሰረት የኮርፖሬሽኑን ተግባር ይመራል። ለፕሮግራሙ ይዘት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ኮርፖሬሽኑ ያለውን የውጭ ግንኙነትም ይወክላል።

ይህ የራስ አስተዳደር ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽኖች ከመንግስት ተፅዕኖ ነፃ ሆነውና ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ዋስትና ይሰጣል። ይህ ሲባል ሁሉንም ፖለቲካዊ ጫናዎች ሙሉ በሙሉ ያስወግዳል ማለት አይደለም። ምንም እንኳ የቁጥጥር አካላቱ ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችን ያቀፉበት ሁኔታ ባይኖርም፤ በኮርፖሬሽኖቹ ትላልቅ የሥልጣን ቦታዎች ላይ ግን ማለትም እንደ ዋና ሥራ አስኪያጅ የፕሮግራም ዳይሬክተር፣ ዋና አዘጋጅና የመሳሰሉት ኃላፊነቶች በሹመት የሚያዙ በመሆናቸው በግልፅ የሚታዩ የፓርቲ ፖለቲካዊ የሥልጣን ክፍፍል ገፅታዎች እያደጉ መጥተዋል። ይኸም ከፍተኛ የሕዝብ ትችት የሚቀርብበት ሆኗል።

ኮርፖሬሽኖቹ የዝግጅት ሚዛናዊነት እንዲኖራቸውና ለማንም ወገን ጥቅም የተለየ ድጋፍ እንዳይሰጡ ሕጋዊ ግዴታ አለባቸው። ይኸም ውሳኔ ያገኘን አመለካከት የመግለፅ መብታቸውንና የሥርጭት ውስጣዊ ነጻነታቸውን የሚነዳ አይደለም። ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኖቹ ሀሳብን ለመግለፅ ለሁሉም ወገን እኩል እድል መስጠት እንዳለባቸው የሕግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።

የሕዝብ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽኖች አብዛኛውን ገንዘብ የሚያገኙት ከሕዝብ ከሚሰበስቡት የአድማጮችና የተመልካቾች የፈቃድ ክፍያ ነው። ከንግድ ማስታወቂያም ገቢ የሚሰበስቡ ሲሆን ከግል ኩባንያዎች ጋር ሲነፃፀር ከንግድ ማስታወቂያ የሚያገኙት ገቢ በጣም አነስተኛ ነው። ዋና ዋናዎቹን የእግር ኳስና የቴኒስ ጨዋታዎች ማሰራጨት እጅግ ውድ በመሆናቸውና የሕዝብ ኮርፖሬሽኖች የየክልሉ ፓርላማዎች ሳያፀድቁት በተጠቃሚው ላይ ዋጋ መጨመር ስለማይችሉ እንደነዚህ ዓይነት ፕሮግራሞችን በማሰራጨት በኩል ችግር አለባቸው።

የንግድ ስርጭት (commercial broadcasting) ሌላው አደረጃጀት ሲሆን እ.ኤ.አ ከ1985 በኋላ የንግድ ቴሌቪዥን ማሰራጫ ኩባንያዎች ተስፋፍተዋል። አንዳንዶቹ በስፖርት፣ በመዝናኛና በፊቸር ፊልም ሲያተኩሩ አንዳንዶቹ የፖለቲካ ፕሮግራሞችንም ጭምር ያቀርባል። የንግድ ፕሮግራሞች በሳተላይትና በኬብል የሚተላለፉ ሲሆኑ እነዚህን ፕሮግራሞች በመሬት ላይ በሚገኙ የመቀበያ ፍሪኪዌንሲዎች መቀበልም ይቻላል። በርካታ የውጭ TV ፕሮግራሞች የሚቀርቡት በተመሳሳይ መንገድ ነው። የንግድ ጣቢያዎች በጋራ የሚሰሩ ሲሆኑ አብዛኞቹ በዚህ ስራ የተሰማሩት አታሚ ኩባንያዎች ናቸው። ብቸኛ የገቢ ምንጫቸውም ማስታወቂያ ነው። በእርግጥ ነፃነታቸውን እንዳይነዳቸው መንግስት ጥበቃ ያደርግላቸዋል።

ሕጉ ሬዲዮ ጣቢያዎች ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ ልዩ ልዩ አይነት ዝግጅቶችን እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። የፌዴራሉ ሕገመንግስታዊ ፍ/ቤት እንደ ሕዝብ ኮርፖሬሽን ሁሉ የንግድ ኩባንያዎችም ወደ አንድ ወገን ያጋደለ ዝግጅት እንዳያቀርቡና የተለያዩ ጉዳዮችን በሚዛናዊነት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ደንግጓል።

የአዳዲስ ቴክኒዎሎጂ መፈጠር በጀርመን ያለውን የብሮድካስቲንግ ገፅታ ቀይሮታል። ከኬብል ግንኙነት በተጨማሪ የቀጥታ ሳተላይት ግንኙነቶች አድገዋል። የቀጥታ ሳተላይት ፕሮግራም ግንኙነት ለማንም ኤኮኖሚያዊ አዋጭነት ያለው ግንኙነት ነው። የኬብል ግንኙነት ተጠቃሚ ላልሆኑት ብቻ ሳይሆን በትንሽ ዲሽ (መቀበያ) አንቴና በቀጥታ ማንም መቀበል የሚችለው የግንኙነት ዘዴ በመሆኑ የኬብል ግንኙነት ለፈጠሩትም የተሻለው አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል።

በእርግጥ የሳተላይት ብሮድካስቲንግ ግንኙነት የድንበር ክልል ጥያቄን ማስነሳቱ አልቀረም። ብሔራዊ ወይም አውሮፓዊ፣ ወይም ደግሞ አለማዊ ግንዛቤ ያሸንፍ እንደሁ ገና ቁርጡ አለየለትም። በግልፅ የሚታየው ሀቅ ግን ይህ ሁኔታ ተመልካቾችና አድማጮች ከተለያዩ ፕሮግራሞች መካከል የሚፈልጉትን ለመምረጥ ያላቸውን እድል ሊያሰፋላቸው መቻሉን ነው።

በፈረንሳይም ያለው ልምድ እንደሚያሳየው የፕሬስን ነጻነት፣ ሀሳብን የመግለፅና መረጃ የማግኘትን ነጻነት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ትኩረት የሚያደረግ መሆኑን ነው። በፈረንሳይ ሕገመንግስት መሰረት የፕሬስ ነፃነት ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠ ነው። ቀደም ሲል የድምፅና የቴሌቪዥን ማሰራጫዎች በመንግስት ሞኖፖል ስር የነበሩበትን ሁኔታ በመቀየር የግል ካምፓኒዎችም በመስኩ ተሳትፎ እንዲኖቸው ለማድረግ ብዙ እርምጃዎች ተወስደዋል። እ.ኤ.አ. በየካቲት 1959 የወጣው ሕግ የፈረንሳይ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የኢንዱስትሪና የንግድ ባህርይ ይዘውና የራሳቸው የበጀት አቶኖሚ ያላቸው ተቋሞች ሆነው እንዲሰሩ ከደነገገ በኋላ ከፍተኛ ለውጦች ተመዝግበዋል። የዚህ ሕግ አላማም ቀደም ሲል ክልክል የነበረውን የንግድ ተግባር ማካሄድ እንዲችሉ መፍቀድና ከሁሉም በላይ ከቀድሞው አስተዳደርና አሰራር ዘይቤ ተላቀው በነፃነት የሚደራጁበትንና የሚሰሩበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነበር። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንገድ በዘርፉ የተሰማሩትን ሙያተኞችና ሠራተኞች ሁኔታ በአስተማማኝ መሰረት ላይ እንዲገነባ ማድረግ የሕጉ አላማ አካል ነበር።

የፈረንሳይ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አስተዳደርና አመራር የዋና ዳይሬክተሩ ብቸኛ ስልጣን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችና አካላት የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት ከፍተኛ ምክር ቤትና በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ ተመስርተው የተቋቋሙ ልዩ ኮሚቴዎች በሚሰጡት የምክር አገልግሎት እየታገዘ በሚመራበት አግባብ የተደራጀ ነው። ከዚህ ሌላ ደግሞ የሬዲዮና ቴሌቪዥንን አስተዳደር፣ ፋይናንስና ቴክኒካዊ አሰራር የሚከታተል ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራና ከመንግስት አስፈፃሚ አካላት፣ ከፓርላማና ከሕዝብ የተወከሉ አባላትን የያዘ የቁጥጥር ምክር ቤት አለ። የፈረንሳይ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ተጠሪነት ለአንድ የመንግስት አስፈፃሚ አካል በብቸኝነት የተሰጠ ሳይሆን ለተለያዩ አካላት ተጠሪነት እንዲኖረው ሆኖ የተደራጀ ነው። ማስታወቂያ ሚኒስቴር በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አጠቃላይ የክትትል ስራ (supervisory function) የሚያከናውን ሲሆን የፋይናንስን ቁጥጥር የሚመራው የፋይናንስ ተቆጣጣሪና ከገንዘብ ሚኒስቴር የሚመደብ አካውንታንት ነው። ፓርላማው ደግሞ የአፈፃፀም ሪፖርታቸውን በየአመቱ እያዳመጠ ከመገምገም ሌላ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ከሕዝቡ መሰብሰብ የሚገባቸውን የፈቃድ ታክስ (Licence Tax) የመወሰን ኃላፊነት አለበት። የስርጭት ሰዓትና መሣሪያ የመጠቀም አቅማቸው በጨመረ ቁጥር ወጪአቸውም በየጊዜው እያደገ በመሄድ የፈረንሳይ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን የተወሰነ ወጪ ከተገልጋዩ ሕዝብ በሚሰበሰብ የፈቃድ ታክስ እንዲሸፍኑ ውሳኔ የሚሰጠው ፓርላማው ነው። በፈረንሣይ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልገሎት አሰጣጥ ጥራት ከፍተኛ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን በአገልግሎቱ ጥራት ላይ የሕዝብ ተሳትፎ እንዲኖር ሰፊ ጥረት ይደረጋል።

በዚህም መሰረት በአጫጭር ጊዜያት ውስጥ የሕዝብ አስተያየት ይሰበሰባል ወይም የሕዝብ አስተያየት ሰርቬይ ይካሄዳል። ከዚህ በሚገኘው ውጤት ላይ የተመሰረቱ የማሻሻያ ለውጦች ይደረጋሉ።

በአሜሪካም ሆነ በሌሎች የዴሞክራሲ ስርዓት በገነቡ ሀገሮች በአፈፃፀም ረገድ አንዱ ከሌላው የሚለይበት ሁኔታ ቢኖርም የፕሬስን ነፃነት በማረጋገጥ፣ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትና መረጃ የማግኘት መብትን በማክበር ረገድ ያላቸው አቋም ጠንካራና ተመሳሳይ ነው ማለት

ይቻላል:: ለምሳሌ ቢ.ቢ.ሲ. የሚባለው የእንግሊዝ ማሰራጫ ተቋም በአለም ውስጥ አሉ ከሚባሉት ትላልቅ የዜና ማሰራጫ ተቋሞች አንዱ መሆኑ ይታወቃል:: ይህ ተቋም በግል ባለቤትነት ስር ሳይሆን በእንግሊዝ ውስጥ ከሚገኙ የሕዝብ ኮርፖሬሽኖች (public corporations) አንደኛው ነው:: ይሁን እንጂ የዚህ ተቋም አመራር የሚደራጀውና የሚሰራው በሌሎች የሕዝብ ኮርፖሬሽኖች የሚቋቋሙ ቦርዶች ከሚቋቋሙበትና ከሚመሩበት በተለየ መንገድ ነው:: በሌሎች የሕዝብ ኮርፖሬሽኖች የሚቋቋሙ የቦርድ አባላትን መርጦ የሚመድበው ከኮርፖሬሽኑ ጋር ግንኙነት ያለው ሚኒስትር ነው:: ሚኒስትሩ የቦርድ አመራር አባላቱን መሰየም ብቻ ሳይሆን ማሰናበትም ይችላል:: ብሔራዊ ጥቅምን የሚጎዱ መስለው በሚታዩት ጉዳዮች ላይ ለቦርዱ አጠቃላይ መመሪያ ይሰጣል:: ከዚህም ሌላ ብሔራዊ ፕላንን በማውጣት ወይንም የተጠቃሚዎችንና የሠራተኞችን ጥቅም በሚመለከት ጉዳት ሊያመጡ ይችላሉ በሚላቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ አመራር የመስጠትና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን አለው:: ለምሳሌ የኢነርጂ ሚኒስትር የማዕከላዊ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ቦርድን፣ የብሔራዊ ከሰል ቦርድን፣ የጋዝ ምክር ቤትና የአካባቢ ቦርዶችን ወዘተ. ይመድባል፣ አመራር ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል:: የቢ.ቢ.ሲ. ቦርድ ግን የሚደራጀው ፣ የሚመራውና ቁጥጥር የሚደረግበት በማስታወቂያ ሚኒስትር ወይንም በሌላ የመንግስት አስፈፃሚ ሚኒስትር አይደለም:: የዚህን ተቋም ቦርድ አባላት የመመደብ ኃላፊነት የወደቀው ለአንደኛው የፖለቲካ ፓርቲ ይወግናሉ ተብለው በማይገመቱትና ገለልተኛነታቸው በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ባለው በእንግሊዟ ንግስት አማካይነት ነው:: የስራው ሂደት የሚገመገመውና የሚመረመረውም በአንድ የመንግስት አስፈፃሚ ሚኒስትር ቁጥጥርና ኃላፊነት ስር ሳይሆን በየአምስት አመቱ ውስጥ በሚቋቋም ገለልተኛ የሆነ ኮሚቴ ነው:: ይህ የሚደረገው የፕሬስ ነፃነት፣ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነትና መረጃ የማግኘት መብት በመንግስት ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቅና እንዳይደፈር ለመከላከል ነው::

አሜሪካ ደግሞ በመንግስት ባለቤትነት ስር ያለው የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ስልጣን የያዘውን ፓርቲ አጀንዳ በሕዝቡ ላይ እየጫነ የአንድ ፖለቲካ ቡድን ወይንም የገዥው ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ሆኖ እንዳያገለግል ለመከላከል በማሰብ ከሀገሪቱ ክልል ውጭ ብቻ የሚደመጥ ስርጭት እንዲኖረው በማድረግና በሀገር ውስጥ በሚካሄድ ሥርጭት ግን በዋናነት በሕግ ስርዓት የተቋቋሙና በሙሉ ነፃነት ተደራጅተው የሚሰሩ የግል ማሰራጫዎች ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማስቻል የፕሬስ ነፃነት፣ ሀሳብን የመግለፅና መረጃ የማግኘት መብት በመንግስት ተፅዕኖ ስር እንዳይወድቅ ጥንቃቄ ያደርጋል::

በተወሰኑ ሀገሮች ደግሞ ሥልጣን ላይ ያለ ፓርቲዎችና መንግስታት የመገናኛ ብዙሃንን ለራሳቸው የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀሚያ መሣሪያ አድርገው እንዳይጠቀሙባቸው፣ ለመንግስት ስልጣን የሚተዳደሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማጥላላት ሚዛናዊነት የጎደለው ፕሮግራም እያቀነባበሩ የሚሰራጩበት ሁኔታ እንዳይኖርና የሚዲያ አገልግሎት ነፃነትም ሆነ ሚናዊነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የሚዲያ ቁጥጥር ኮሚቴ (Meidia Monitoring committee) አቋቁመው ይሰራ:: የዚህን ኮሚቴ አባላት ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችና የተደራጁ ሲቪክ ተቋሞች እነዲወጣጡ በማድረግ ቁጥጥር ከአንድ ፓርቲ ወገንተኝነት ነፃ በሆነ ስርዓት እንዲከናወን ይጥራሉ:: ከዚህ ዘዴ ሌላ ዴመከራሲያዊ በሆኑ ሀገሮች ውስጥ ጠ ንካራ የፖለቲካ ባህልና ለመብቱ አጥብቆ የሚከራከር ግልፅ ሕብረተሰብ መኖር፣ ጠንካራ የጋዜጠኞችና አጫታሚዎች መህበር መኖር፣ ከፍተኛ ስነምግባርና የሞያ ብቃት ያላቸው ጋዜጠኞች መኖር የጋዜጠኝነት ፕሮፌሽን የተከበረ መሆንና ሌሎችም ምክንያቶች በሚያ ስራ ቁጥጥር ረገድ የራሳቸው ና አላቸው:: በመሆኑም በነፃነት የተደራጀና የሚራ ብቻ ሳየሆን ኃላፊነት የሚግው መገናኛ ብዙሃን መኖር የዴከራሲ ስርዓት እንደ ገጽታ ተደርጎ ይታያል::

*የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከላይ በምሳሌነት ከተጠቀሱት ሀገሮች ሁኔታ የተለየ ቢሆንም ሀገራችን ካለችበት ደረጃና ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ ልምዶችን በመቅሰም ተስማሚ የመገናኛ ብዙሃን ህግ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡*

## 4.2 ነፃ ፕሬስ በኢትዮጵያ

*በኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ድረስ የዴሞራሲ ስርዓት ስለሌለ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት ለብቻው የሚረጋገጥበት መንገድ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት የሰው ልጅ ሊኖሩት ከሚቡና መሰረታዊ ከሆኑ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መካከል አንደኛው ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሰው ልጅ ሰብዓዊና ዴሞራሲያዊ መብቶች መረጋገጥ የቆመ የዴሞክራሲ ስርዓት ለመመስረት ሳይቻል በመቅረቱ ይኸንን መሰረታዊ የሰው ልጅ መብት ለመጎናፀፍ አሁንም ከባድ መስዋዕትነት እየተከፈለ ነው፡፡*

*ሀሳብን ለመግለፅ የሚያስችሉ የመገናኛ ብዙሃን አገልገሎቶች ከመንግስት ባለቤትነትና ሙሉ ቁጥጥር ነፃ ሆነው የሚደራጁበትና የሚሰሩበት ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ሳይመቻች በመቆየቱ ዜጎች ሀሳባቸውን ለመግለፅ ነፃነት የላቸውም፡፡ መንግስት እየመጠነ ከሚሠጣቸው መበት የበለጠ ቢፅፉና ቢናገሩ በገንዘብና በእስራት ቅጣት ወይንም በስደት ብቻ የሚገላገሉት ነገር አይደለም፡፡ የሕይወት ዋጋ የሚያስከፍል አደጋ ያጋጥማቸዋል፡፡ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት በተለይም የሕትመት መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት የሚቀርብበት ሁኔታ ቀርቶ ግለሰቦችም የሚሣተፉበት አሰራር ተጀምሯል፡፡ ይሁን እንጂ በሕትመት ሚዲያ የተሰማሩ የግል ከፍተኛ የመንግስት ተፅዕኖና ጣልቃገብነት ስለሚፈፀምባቸው ዜጎች ሀሳባቸውን በነፃነት የሚገልጽባቸው የዴሞክራሲ መድረኮች መሆናቸው ቀርቶ ስልጣን የያዘው ፓርቲ ወዳጁንና ጠላቱን ለመለየት የሚጠ ቀምባቸው ለአደን የተዘጋጁ ወጥመዶች ሆነዋል፡፡*

*የመንግስት ስልጣን በሕዝብ ነፃ ምርጫና ፈቃድ ሳይሆን በጠመንጃ በሚያዝበት አገዛዝ ውስጥ ሀሳብን መግለፅ ሁልጊዜም የሚያስቀጣና ውድ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ የተለመደ ነው፡፡ በሀይል የተያዘ የመንግስት ስልጣን የሚመሩ ገዥዎች ለሕዝብ ተጠሪነትና ተጠያቂነት ስለሌላቸው ለዜጎች የማወቅ መብትና ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት መከበር አይጨነቁም፡፡ በጠ መንጃ የያዙትን ሥልጣን በጠመንጃ ከመጠበቅ ያለፈ ቁምነገር ለመስራት የሚያስችል አቅምና ፍላጎት የላቸውም፡፡ የዜጎችን የማወቅ መብትና ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት በሕግ እውቅና የሚሰጡት ይኸንን የሰው ልጅ መሰረታዊ መብት ስለሚያምኑበትና ስለሚጨነቁለት ሳይሆን ለተወሰነ የፖለቲካ አላማ ማሳኪያ እንዲያገለግላቸው ነው፡፡ ዴሞክራት መስለው ለመታየት ተግባራዊ የማያደርጉትን ይኸንን መብት የሕግ እውቅና አግኝቷል እያሉ በየአዋጁ ያስገቡታል፡፡ ይኸ ደግሞ በተለይ የውጭ እርዳታ እንዳይቋረጥባቸውና አለም አቀፍ መገለል፣ እንዳያጋጥማቸው ለሚካሄድ ፕሮፓጋንዳ ይጠቅማቸዋል፡፡ በሀገር ውስጥ ደግሞ ፖሊሲያቸውን የሚቃወሙ ዜጎችን እያደኑ ለማጥቃት ያገለግላቸዋል፡፡*

*የብሮድካስቲንግ አዋጅ እ.ኤ.አ ከ1999 ጀምሮ የወጣ ቢሆንም እስካሁን በተግባር ስላልተፈተሸ የግምገማ ሀሳብ መቅረብ ቢያስቸግርም የአዋጁ ይዘት መንግስት ሀሳብን በመገደብና በመቆጣጠር ከፍተኛ ስልጣን እንዲኖረው ሆኖ የተዘጋጀ በመሆኑ ከሕትመት ሚዲያ የተሻለ ነገር ያስገኛል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ በዚህም ረገድ ለማለት የሚቻለው በመንግስት ከፍተኛ ተፅዕኖና ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር እንዲሠራ ሆኖ የተደራጀ ነፃነት የሌለው ተቋም መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ አባባል በአዋጁ አንቀጽ 9 ስለቦርድ አባላት አሠያየምና በአንቀጽ 10 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ማየት ይበቃል፡፡*

*ስለዚህ በሀገራችን ነፃ፣ ገለልተኛ፣ ተአማኒነት ያለው፣ ሀላፊነት የሚሠማውና ሀቀኛ ኘሬስ እንዲኖር ከተፈለገ በአደረጃጀቱም ሆነ በአሠራሩ ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆነ ተቋም መፈጠር አለበት መንግስት በሕግ ከለከልኩት የሚለውን የሳንሱር አሠራር በሌላ መንገድ የሕግ እውቅና እየሠጠ የዜጐችን ሀሣብና መረጃ የማግኘት መብታቸውን የመገደብ ሥልጣን አንዳይኖረው በሕግ መከልከል አለበት፡፡ ሀሣብን በመግለጽና መረጃ በማግኘት መብት አጠ ቃቀም የሚፈጸሙ ጉድለቶች በፍርድ ቤት ብቻ እየተጠሩ ውሣኔ የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ ከሲቪል ተቋሞችና ከፖለቲካ ፓርቲዎች የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የመገናኛ ብዙሃን ግምገማ ኮሚቴ አቋቁሞ መንግሥትም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች በመገናኛ ብዙሃን ሕገወጥ ተፅዕኖ አለማድረጋቸውን፣ አድሎ በሌለበት መንገድ ለሁሉም እኩል አገልግሎት መስጠታቸውን እየተከታተሉ በሕዝብ ይፋ የሚያደርግበት ስርዓት መኖር አለበት፡፡ በፈቃድ አሠጣጥ፣ በግብር አከፋፈል፣ በሞያ ስልጠና በአገልግሎት አሠጣጥ በመሣሠሉት የግል ሚዲያዎች ተገቢ ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡*

# 5. የውጭ ግንኙነት መርሆዎች

*የውጭ ግንኙነት መርሆዎቻችን የሚመነጬት ከቆምንበት መሠረታዊ የሰላም አላማ ነው፡፡ አላማችን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተደራጀና የሚሰራ ሕብረተሰብ በመፍጠር ለሀገራችን አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋትን፣ ዘላቂ ልማትና እድገትን ማረጋገጥ ነው፡፡ የውጭ ግንኙነታችንም ይኸንኑ አላማ መሰረት አድርጎ የሚነሳ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሀገራችን ለጋራ ሰላም፣ ጥቅምና ወዳጅነት መረጋገጥ ካላት የቆየ ፅኑ ፍላጎት የሚመነጭ ነው፡፡ በሀገራችን የረጅም ጊዜ ታሪክ ውስጥ ከተመዘገቡ መልካም ገፅታዎች መካከል ሰላማዊ ለሆነ አለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ኢትዮጵያ ያበረከተችው አስተዋፅኦ አንደኛው ነው፡፡*

*ከጥንት ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ ጥቃትና በደል ለደረሰባቸው የውጭ ሀገር ሰዎች ጥላ ከለላ በመሆን መልካም ስምና ታሪክ እንዳላት የታወቀ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜ ከውጭ የሚቃጣባትን ጥቃት በፅናት ከመመከት በስተቀር በሌሎች ላይ ጥቃት የማድረስ መጥፎ ታሪክ የላትም፡፡ በፖለቲካ እምነት፣ በኃይማኖት፣ በባህል፣ በቋንቋና በመሳሰሉት የልዩነት ገፅታዎች ሳትወሰን ከጎረቤት ሀገሮች፣ በቅርብና በሩቅ ከሚገኙ ሕዝቦች ጋር የትብብር ግንኙነት ፈጥራ ኖራለች፡፡ በቅርብ ጊዜ ታሪካችንም ቢሆን ኢትዮጵያ ለአለም አቀፍ ግንኙነት ትልቅ አስተዋፅኦ ካደረጉት ሀገሮች መካከል በአርአያነት እንድትጠቀስ የሚያደርግ ተግባር ፈፅማለች፡፡ ለሊግ ኦፍ ኔሽንና ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ምስረታ ግንባር ቀደም ሚና ከተጫወቱት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነች፡፡ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቋቋም ትልቅ ድርሻ ያላት ብቻ ሳትሆን የድርጅቱ ዋና ማዕከል በመሆን መላው የአፍሪካ ሀገሮች የጣሉባትን ኋላቀርነትና ያሳደሩባትን እምነት ሳታጓድል እስካሁን የዘለቀች ሀገር ናት በአፍሪካ ሕብረት ምስረታም የታየው እውነታ በዓለም አቀፍ ግንኙነት ላይ ያላትን አክብሮት ነው፡፡ በገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄ ውስጥ ባላት ተሳትፎ ሚዛናዊ አለም አቀፍ ስርዓት እንዲኖር የሚደረገውን ጥረት በሚገባ አግዛለች፡፡ በሌሎች አለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ ድርጅቶችና የትብብር መድረኮች ሁሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጋለች፡፡ በሀገሮች መካከል የተፈጠሩ ግጭቶችንና አለመገባባቶችን ለማስወገድ በሚያስችል የአስታራቂነት ስራ እየተሳተፈች ጠቃሚ ተግባር ፈፅማለች፡፡ በአለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች በተደጋጋሚ ጊዜ በመሳተፍ የሚያስመሰግን ተግባር አከናውናለች፡፡ በራሷ ላይ የደረሱ የውጭ ጥቃቶችንና ወረራዎችን አምርራ እንደታገለች ሁሉ በሌሎች ላይ የተፈፀሙ ጥቃቶችና ወረራዎችን ታግላለች፡፡ በውጭ ወራሪዎችና ቅኝ ገዥዎች ስር ወድቀው ለተሰቃዩ ሕዝቦች ነፃነት ሁለገብ ድጋፍ አድርጋለች፡፡ በዚህም መልካም ስራዋ የነፃነት አርአያና ምሳሌ ተደርጋ ልትታይ ችላለች፡፡ በተለይም በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካና*

በኤሽያ የውጭ ወረራና ቅኝ ግዛት ሰለባ የሆኑ ሕዝቦች የኢትዮጵያን አርአያነት ተከትለው ለነፃነት እንዲታገሉ የሚያስችል የመንፈስና የሞራል ጥንካሬ ምንጭ ሆና አገልግላለች፡፡

የውጭ ወረራና ጥቃትን ፊት ለፊት የመመከት ብርታት ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ሕግና ደንብ ላይ ተመስርቶ በሚካሄድ ዲፕሎማሲያዊና ሕጋዊ መድረክ ተከራክሮ በማሳመንና በመርታት ሰለጠነ ለሚባለው አለም ሳይቀር ትልቅ ትምህርት ያስገኘ ተግባር ፈፅማለች፡፡ በኢጣሊያ የእብሪት ወረራ ስር ወድቃ ለ5 አመታት ከባድ ትግል ስታደርግ የቆየችውን ሀገራችንን ከወረራው ነፃ ለማድረግ በሊግ ኦፍ ኔሽን ፊት ያደረገችው የዲፕሎማሲ ተጋድሎ እስካሁን ሌሎች በአርአያነት የሚጠቅሱት ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ኤርትራን ከኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አላቆ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መድረክ የሚያኮራ ዲፕሎማሲያዊ ትግል አድርጋ የተሳካ ውጤት አስመዝግባለች፡፡ እነዚህና ሌሎችም የሀገራችንን ሰላም ወዳድነት፣ ተባባሪነትና አርአያነት የሚያረጋግጡ መልካም ገፅታዎች ለውጭ ግንኙነታችን መርህ መነሻዎች ሆነው የሚገለግሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም የውጭ ግንኙነታችን መርሆዎች የሚመሰረቱት በአንድ በኩል ባለፉት ጊዜያት ውስጥ ሀገራችን ለአለም አቀፍ ትብብርና ሰላም ባበረከተችው ገንቢ አስተዋፅኦ ላይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አሁንና ወደፊት በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ ለተመሰረተ አለም አቀፍ ግንኙነት መጫወት በሚገባት ሚና ላይ ነው፡፡

ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት ኢዴፓ የሚከተላቸው የውጭ ግንኙነት መርሆዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው የውጭ ግንኙነት መርህ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የሕዝቡን ብሔራዊ ጥቅሞች የሚያስጠብቅ የግንኙነት ፖሊሲ መከተል ነው፡፡ ይህ መርህ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ጥቅም መረጋገጥ እጅግ መሰረታዊ ነው ብለን እናምናለን፡፡

አሁን በሀገራችን ሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የሕዝቡን ብሔራዊ ጥቅሞች አሳልፎ በመስጠት በታሪካችን ውስጥ ወደር የማይገኝለት ክህደት እየፈፀመ በሚገኝበት በአሁኑ ጊዜ ይኸንን የውጭ ግንኙነት መርህ ማራመድ አንገብጋቢ ነው፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የሕዝቧን ብሔራዊ ጥቅም አሣልፎ እየሰጠ የሚገኘው ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ስለወደቀ፣ ያልተጠበቀና ድንገተኛ አደጋ ስላጋጠመው፣ ወይንም በታሪክ ማስረጃና በሕግ ድጋፍ እጦት አሊያም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለመደገፍ ቅን ፍላጎትና ትብብር የሚያሳዩ አለም አቀፍ አጋሮች በማጣትም አይደለም፡፡ ይልቁንም ሆን ብሎ አስቦበትና ተዘጋጅቶበት የሚፈፅመው ተግባር ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነን ኤርትራን ከኢትዮጵያ እንድትለይ ከበረሃ ትጥቅ ትግሉ ወቅት ጀምሮ ያካሄደው አፍራሽ እንቅስቃሴና በኋላም የመንግስት ስልጣን በኃይል በተቆጣጠረ ማግስት የኤርትራ መገንጠል አለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ በጥድፊያ ለተባበሩት መንግስታት በፅሁፍ ያቀረበው አቤቱ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ኤርትራ ከኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ከተላቀቀች በኋላ ከእናት ሀገሯ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሃድ የተወሰነው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ በ1950 ይኸንን ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት የኤትራን ሕዝብ ፍላጎት ለማወቅ እ.ኤ.አ በ1948 አጣሪ ኮሚሽን አቋቁሞ ወደ ኤርትራ በመላክ በቂ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህ ኮሚሽን ውስጥ በአባልነት የተሰየሙት ሀገሮች ፓኪስታን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኖርዌይ፣ በርማና ጓቲማላ የነበሩ ሲሆን በኤርትራ ተገኝተው የሕዝቡን ፍላጎት ካጣሩ በኋላ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ ተመስርቶ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ ወሰነ፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ ኤርትራ እንድትገነጠል ለተመድ አቤቱታ ሲያቀርብ ኢትዮጵያና ኤርትራ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ተሳስረው የቆዩ የአንድ ሉዓላዊ ሀገር አካል መሆናቸውን በመካድ እንደውም ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት

ስር ወድቃ በደል ሲፈፀምባት እንደቆየች በመቆርቆር ነበር። ኤርትራን የማስገንጠሉ ሂደት በሕወሓት/ኢህአዴግ ግፊት ከተጠናቀቀ በኋላም ኤርትራን የማቋቋም ሙሉ ኃላፊነት ኢትዮጵያ እንድትሸከም አደረገ። በኢትዮጵያ ስም አለም አቀፍ ብድር ለኤርትራ እስከመጠየቅ ጥረት አደረገ። የሀገሪቱን የመከላከያ አቅም አፍርሶ ወሰኗን ክፍት በማድረግ ለወረራ እንድትጋለጥ አመቻቸ። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሃድ የውሳኔ ሀሳብ ባቀረበበት ጊዜ ውህደቱ በተመድ ተቀባይነት ቢያጣ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ሊከበር ይገባዋል ብሎ ያቀረበውንና በሁሉም አባል መንግስታት ኢጣሊያን ጨምሮ ተቀባይነት ያገኘውን አለም አቀፍ ስምምነት ወደጎን በመተው የሀገሪቱን የባህር በር ለሻዕቢያ በስጦታ መልክ አቀረበለት።

ኢትዮጵያ በሚያሳዝን ሁኔታ የኤርትራ ወረራ ሰለባ ሆነች። ጉዳዩ በሰላም ሊያልቅ የሚችልበት እድል የነበረ ቢሆንም ለሕወሓትና ሻዕቢያ መሪዎች እልህ መወጫና ጉልበት መፈታተሻ ሲባል ትርጉም ወደሌለው የወንድማማቾች ጦርነት ውስጥ እንደገና መግባት ግድ ሆነ። በ30 ዓመታት የእርስ በርስ ጦርነት ጊዜ ካለቁት ወገኖቻችን በማይተናነስ ቁጥር በ2 ዓመቱ ጦርነት ከኢትዮጵያ ወገን ብቻ ወደ 70 ሺህ የሚጠጋ ህዝብ ለሞትና ለአካለ ጐደሎነት ተዳረገ። የትግራይና የአፋር ሕዝብ ቤት ንብረቱን በወራሪ ተቀምቶ ለስደት ኑሮ ተጋለጠ። በመቀሌ ከተማ የሃይደር ትምህርት ቤት ሕፃናትን ከአውሮፕላን የሚወርድ እሳት አቃጥሎ ፈጃቸው። ሀገሪቱ ለልማት ልታውለው የሚገባት ግዙፍ ሀብትና ንብረት ሕወሓትና ሻዕቢያ ለከፈቱት የማይረባ ጦርነት ዋለ። በሕዝቡ ተጋድሎ ወረራው በኃይል እንደተቀለበሰ በኢትዮጵያ ላይ ሌላ ተጨማሪ ክህደት ፈፀመ። ይህ አሳፋሪ የህውሓት ቅሌት (The Scandle of Woyane) የተፈፀመው እ.ኤ.አ በታህሳስ ወር 2000 አልጀርስ ላይ በተፈረመው ስምምነት ነው።

የአልጀርሱ ስምምነት በመሰረቱ የእብሪት ወረራ የተፈፀመባትንና ወረራውን በከባድ መስዋዕትነት የቀለበሰችውን ኢትዮጵያን የሚቀጣና ወራሪውን የሻዕቢያ መንግስት የሚሸልም ነበር። ምክንያቱም በተደጋጋሚ ጊዜ ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ በፈፀመቻቸው ወረራዎች፣ የኤርትራ ጉዳይ በተባበሩት መንግስታት ታይቶ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሃድ በተላለፈው አለም አቀፍ ውሳኔና በሌሎችም አሳማኝ ታሪካዊና ሕጋዊ ሁኔታዎች ውድቅ በተደረጉት የ1900፣ የ1902 እና የ1908 የቅኝ ግዛት ውሎች ላይ ተመስርቶ የተፈረመ ስምምነት ነው።

ይኸንን ስምምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚቃወምበት ጊዜ ከሻዕቢያ ይበልጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ተቃውሞ ያጣጣለውና በኃይል ያፈነው ህወሓት ነበር። ችግሩ በአለም አቀፍ ሕግና ስርዓት፣ በበቂ እርጋታና ጥንቃቄ መፍትሔ እንዲያገኝ ኢትዮጵያዊያንና የሌላ ሀገር ዜግነት ያላቸው የሀገሪቱ ወዳጆች በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች ማሳሰቢያ ባቀረቡ ቁጥር ከሻዕቢያ ቀድሞ የሚሰማው የህወሓት ምላሽ ነበር። የሚረቡ የመደራደሪያ ነጥቦችና ማስረጃዎች በአግባቡ ተሰባስበው፣ የኢትዮጵያን ጥቅም ለመከላከል በሙሉ ልብና በታማኝነት የሚከራከሩ ብቁ ጠበቆችና ዲፕሎማቶች ተመድበው ተገቢ ክርክርና ድርድር መካሄዱን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ውሳኔ ተላለፈ።

በድንበር ኮሚሽኑ ፊት በተደረጉ ክርክሮች የኤርትራ ጥቅም እንዲረጋገጥ ከሻዕቢያ በበለጠ በኢትዮጵያ ወገን የቆሙት ተቆርቋሪነታቸውን ለማሳየት ጥረት አደረጉ። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ሻዕቢያ ለክርክሩ ጠበቃና ዲፕሎማት መመደብ አይገባውም ነበር እስኪሉ ድረስ ህወሓት ሽንጡን ገትሮ ለሻዕቢያ ተከራከረ። በመጨረሻም ባድመን ጨምሮ በ10ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ሕይወታቸውን የገበሩባቸው በርካታ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አካል የሆኑ አካባቢዎች ለኤርትራ ተሰጡ። ለዚህ ግፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ አደባባይ ወጥቶ

እንዲጨፍርና ድጋፍ እንዲሰጥ በህወሓት ተጠራ። የደስታ መልዕክት በመገናኛ ብዙሃንና በአደባባይ ቀረበለት።

የኤርትራ ግንጠላ፣ የአልጀርሱ ስምምነትና የባድመ ቅሌት የተጠቀሱት ለአብነት እንጂ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማፍረስ ህወሓት የነደፈው አጀንዳና እያደረገ ያለው ጥረት ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ስለዚህ ኢዴፓ በህወሓት ግፊት ከዚህ ቀደም ሀገሪቱና ሕዝቧ ያጡትን ብሔራዊ ጥቅም ለማስመለስና አሁንም ሆነ ወደፊት ተመሳሳይ በደል እንዳይደርስ ለመከላከል የውጭ ግንኙነቶችን የመጀመሪያ መርህ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የሕዝቡን ብሔራዊ ጥቅሞች የሚያስጠብቅ መሆኑ አግባብነት አለው ብለን እናምናለም። በፓርቲያችን ፕሮግራም ክፍል 5 አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የሰፈረውም ይኸንኑ መርህ መሰረት በማድረግ ነው። የአልጀርሱን ስምምነት በአደባባይ የተቃወምነውና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ150 ሺህ ዜጎችን ፊርማ አሰባስበን ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት አቤቱታ ያቀረብነው ይኸንኑ መርህ መሰረት በማድረግ ነው። በፓርቲያችን ፕሮግራም አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 4 ለኢትዮጵያ ሕዝብ የባህር በር የማግኘት መብት ማንኛቸውንም ሕጋዊና ዲፕሎማሲያዊ ትግል እንደምናደርግ በግልፅ ያስቀመጥነው ከዚህ መርህ ተነስተን ነው።

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለኢትዮጵያ የባህር በር የባለቤትነት መብት የምናደርገው ትግል እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ጉዳያችን የሩቅ ግብም ያለአግባብ ወንድማማች የሆኑት የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች እንዲነጣጠሉ መደረጉ በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ አግኝቶ ወደነበረበት እንዲመለስ፣ ያለአግባብ ለሁለት እንዲከፈል የተደረገው የአፋር ሕዝብ ጉዳይም ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ ኢዴፓ ትግል ያደርጋል።

የሀገራችንን ሉዓላዊነትና የሕዝባችንን ብሔራዊ ጥቅሞች የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት መርህ እንከተላለን ስንል የእኛን መብት ለማስጠበቅ የሌሎችን መብት ወደመፃረር እንገባለን ማለት እንዳልሆነ መታወቅ ይኖረበታል። መብታችንን ማስከበር የምንችለው ለሌሎችም መብት ከበሬታ በመስጠት እንደሆነ እናምናለን። የሌሎችን መብት የሚጎዳ ተግባር እየፈፀምን ለእኛ መብት መረጋገጥ በጎ አመለካከት ያላቸው አጋሮችና ወዳጆች ልናፈራ አንችልም። በአለማችን ውስጥ የራሱን ሀገር ሉዓላዊ መብትና ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችል እድል መኖሩን ሳያረጋግጥ ለሌሎች ጥቅም ብቻ ብሎ በአጋርነትና በወዳጅነት የሚቆም ሀገርና መንግስት ይገኛል ለማለት አይቻልም። ስለዚህ የብሔራዊ ጥቅማችንን መሰረት አድርጎ የሚቆም የውጭ ግንኙነት መርህ የጋራ ጥቅሞችንም በእኩልነት የማራመድ ኃላፊነትን የሚጨምር መሆን አለበት። በዚህም ምክንያት ሌላው የውጭ ግንኙነት መርሃችን በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የጋራ ጥቅም እንዲጠናከር ማድረግ ይሆናል ማለት ነው።

# 6. የፓርቲ ሥርዓትና ዴሞክራሲ

የፖለቲካ ሥርዓት ሲባል የሕብረተሰቡ መሰረታዊና አንገብጋቢ ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚቀየሱ ፖሊሲዎችን ለማመንጨትም ሆነ በስራ ላይ ለማዋል ኃላፊነት ያለባቸውን ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ድርጅቶችና ሂደቶችን የሚያጠቃልል እንደመሆኑ ፓርቲ የሚባለው ተቋም የዚሁ ሥርዓት አንድ ገጽታ ነው። በማንኛውም የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ደግሞ የሥልጣን ዋነኛ ማዕከል መንግስት መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ሥርዓት ውስጥ መንግስት በሚባለው ተቋም አማካይነት ዋነኛ የሆነውን የሥልጣን ማዕከል በመያዝ የተለያየ አላማ ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ ልዩ ልዩ ፓርቲዎች ሊደራጁ ይችላሉ። በተለይም ዴሞክራሲያዊ በሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የሚመሰረት መንግስት ሥልጣን የሚመነጨው ከሕግና ከመራጩ ሕዝብ ስምምነት እንደመሆኑ ይኸንን ሕጋዊነትና የዜጎች

ስምምነት ለማግኘት ከሚቻልባቸው መንገዶች መካከል በፓርቲዎች የሚደረገው የተደራጀ እንቅስቃሴ አንደኛውና ዋነኛው ነው::

የፖለቲካ ፓርቲ በጠባብ ትርጉሙ ሕጋዊ የመንግስት ሥልጣን ለማግኘትና ለመያዝ ሰዎች በራሳቸው ፈቃድና ስምምነት በጋራ የሚመሰርቱት ተቋም ነው:: በሰፊ ትርጉሙ ደግሞ አንፃራዊ በሆነ መንገድ ቋሚ ሊባል የሚችልና ከፖለቲካ ጋር በተያያዙ በርካታ ጉዳዮች ወይንም በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ ሰዎች ያሏቸውን አንድነቶች መሰረት በማድረግ እንደየዝንባሌያቸውና ፍላጎታቸው ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በጋራ የሚፈጥሩት ተቋም ነው:: በሌላ አገላለፅ ፓርቲ ማለት የጋራ ጥቅምንና አላማን በጋራ ለማሳካት በወሰኑና መሰረታዊ በሆኑ መርሆዎች ላይ የጋራ ስምምነት ባላቸው ሰዎች ትብብር የሚመሰረት ድርጅት ነው:: ይህ ሲባል የፖለቲካ ፓርቲ ማለት በማንኛውም ሁኔታና ጊዜ አንድ ወጥ አስተሳሰብ ብቻ የሚከተሉ ወይንም ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ብቻ ነው ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተደራጅተው የሚሰሩ ፓርቲዎች በሁሉም ጉዳዮች ላይ ምንም አይነት የተለየ አስተያየት የሌላቸውና አንድ አይነት አስተሳሰብ ብቻ የሚከተሉ ሰዎች ስብስብ ሳይሆኑ በአንድ በኩል የግል አስተያየት ሰፊ ነፃነት መኖሩን የተቀበሉ በሌላ በኩል ደግሞ የጋራ ኃላፊነትን ለመሸከም የተስማሙ ሰዎችን ያስተሳሰሩ አካላት ናቸው::

ሰፊና ውስብስብ በሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ፓርቲዎች በርካታ ቁልፍ ተግባሮችን የሚያከናውኑ ሲሆን ከእነዚህም ተግባሮች መካከል ሕዝብና መንግስትን ማገናኘት፣ የሕዝብ አስተያየት ውሳኔ በሚሰጥባቸው መድረኮች ሁሉ እንዲደርስ ማድረግ፣ ሐሳቦች ሁሉ የሕዝብን አስተያየት መሰረት አድርገውና አገናዝበው እንዲወጡ ማስቻል፣ በከፍተኛው የመንግስት ስልጣን አካል (በሕግ አውጭው አካል) የሚተላለፉ የፖሊሲ ውሳኔዎች በሕዝብ እንዲደገፉ ሕዝቡን ማንቀሳቀስ፣ ዜጎች የማይፈልጓቸው የፖሊሲ ውሳኔዎች እንዳይተላለፉና በሆነ መንገድ ተላልፈው ከተገኙም ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚከላከል ሕዝባዊ ግፊት እንዲኖር የሚያስችል እንቅስቃሴ ማስተባበርና መምራት በመንግስት ልዩ ልዩ አካላት ማለትም በሕግ አውጭውና በሕግ አስፈጻሚው፣ በፌዴራልና በክልል መካከል እንዲሁም መደበኛ በሆኑ የመንግስት ስልጣን አካላትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋሞች መካከል እንደመገናኛ ድልድይ ሆኖ ማገልገል፣ ለፖለቲካ ስልጣን የሚተዳደሩ ሰዎችን አዘጋጅቶ ለሕዝብ ምርጫ መቅረብ ወዘተ. ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ማንኛውም ሕዝብ የፖለቲካ ስልጣን ማዕከል ከሆነውና መንግስት ከሚባለው ተቋም በሚፈልገው ጉዳይ ላይ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ አመለካከት አለ:: ይኸውም መንግስት የዜጎችን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ፣ ከውጭ ወረራ የመከላከል፣ ዜጎች ከፍ ያለ የኑሮ ደረጃ እንዲቀዳጁና የመሳሰሉትን የማድረግ ተግባር እንዲያከናውን ይጠበቃል:: በዜጎች ፈቃድና ነፃ ምርጫ የፖለቲካ ስልጣን ለማግኘትና ለመያዝ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች እነዚህን አላማዎች ለማሳካት እንደሚችሉ በመራጩ ሕዝብ ሲታመንባቸው ይመረጣሉ:: የመራጩን ሕዝብ እምነት ባጡ ጊዜ ደግሞ አንድም ሊመረጡ አይችሉም አሊያም በአንድ ወቅት ተመርጠው ስልጣን ያገኙትም ቢሆኑ በድጋሚ የመመረጥ እድል ያጣሉ:: ፓርቲዎች የፖለቲካ ስልጣን ለማግኘት የሚያደርጉት ትግል ውጤታማ መሆን አለመሆን በቅድሚያ የሚወሰነው በራሳቸው ተፈጥሯዊ ባህርይና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው:: የመራጩ ሕዝብ የመጨረሻ ብይን የሚመሰረተው ፓርቲዎቹ ራሳቸው ባላቸው ማንነትና በሚፈፅሙት ተጨባጭ ተግባር ነው:: አንድ ፓርቲ በሀገር፣ በአካባቢና በግለሰብ ደረጃ የሚከተለው አቅጣጫ እየተገመገመና የሚያስገኘው ጥቅምና ጉዳት በመራጮች እየተመዘነ ድጋፍ ሊሰጠው ወይንም ድጋፍ ሊነፈገው ይችላል:: የሀገርን አንድነትና የሕዝቡን ሰላም ለመጠበቅ በሚይዘው ፕሮግራም፣ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በሚያወጣው የኢኮኖሚ ዕቅድ፣ ስራ አጥነትና ድህነትን

ለመከላከል ወይንም የትምህርትና የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋት በሚዘረጋው የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም ወዘተ. እየተመዘነ ሊደገፍና አሊያም ሊነቀፍ ይችላል።

ፓርቲዎች ከሚያራምዱት ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካትና የመንግስትን የተለየ ችግር ለመፈታት ከሚከተሉት የአሰራር ዘዴ አኳያ በተለያየ ምድብ ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ። አንዳንዶቹ የመንግስት ስልጣን ጥቂት ግለሰቦችን ባቀፈ ቡድን እጅ ተጠቃሎ የተያዘበትን ወይንም ብዙሃኑ በጥቂቶች የሚገዙበትንና ኦሊጋርኪ ተብሎ የሚጠራውን የመንግስት ዐይነት ለመመስረት ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ አለ። አንዳንዶቹ ደግሞ የመንግስት ስልጣን በአንድ ግለሰብ እጅ ውስጥ የገባበትና አምባገነን የሆነ የመንግስት አይነት ለመትከል ይቆማሉ። ሌሎች ደግሞ በአገዛዙ ስር ያሉትን ሰዎች የግል ንብረቱ አድርጎ የሚመለከት፣ በአገዛዙ ስር ያሉ ዜጎች እንዲኖሩ ወይም እንዲሞቱ ለመወሰን የሚያስችል ፍፁማዊ ስልጣን ያለውና የሞናርኪ አገዛዝ የሚባለውን አይነት መንግስት ለማቋቋም ይሰራሉ። ኦሊጋርኪ፣ አምባገነንና ሞናርኪ የሚባሉት የመንግስት አይነቶች አንድ የጋራ ባህርይ ደግሞ ሁሉም አባጠቅል (ቶታሊታሪያን) የሆነ የመንግስት አገዛዝ ሲሆኑ ማዕከላዊውን ስልጣን ጥቂት ቡደኖች ወይም አንድ አምባገነን ወይም በአንድ ፍጹማዊ ሞናርክ አማካኝነት ጠቅልለው በመያዝ በዜጎች ላይ በሕግ የማይገዛ ሙሉ ቁጥጥር ያሰፈኑበትን የተለየ አመለካከት ላላቸው ፓርቲዎችና ግለሰቦች ሀቀኛ በሆነ መንገድ እውቅና ለመስጠትም ሆነ ከእነዚህ ጋር ተቻችሎ ለመስራት ፍላጎት የሌለበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በተወሰነ ደረጃ ለየት ባለ መንገድ ልዩ ተፈጥሯዊ ችሎታና ተሰጥኦ እንዳለው ተደርጎ በሚቆጠር ግለሰብ አመራር ስር የሆነ መንግስት ለመመስረት የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች አሉ። እነዚህ ካሪዝማቲክ የሚባሉ ግለሰቦች ከሌሉ የአለም ፍፃሜ እንደሚመጣ የሚሰብኩ፣ የእነዚህን ሰዎች ንግግር፣ ምስልና ስም በአርአያነት እንዲታይና እንዲመለክባቸው ሰፊ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ስራ በመስራት ጊዜያቸውን የሚያባክኑ ፓርቲዎች ያጋጥማሉ።

በእኛ ሀገር ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የመንግስት ስልጣን የያዘው ፓርቲ ከጐሰኝነቱ በተጨማሪ ከቶታሊታሪያን አገዛዝና ከካሪዝማቲክ አመራር ባህርያት አብዛኛዎቹን የሚያሟላ በመሆኑ አሰላለፉና ምድቡ በዚሁ ጎራ ውስጥ የሚካተት ነው።

ከዚህ በተቃራኒው የሚሰሩ ፓርቲዎች ምድብ የዴሞክራሲ ስርዓት ነው። በዚህ ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ የሚመደቡ ፓርቲዎች የመጨረሻ ግባቸው አንድ ቢሆንም ወደግባቸው ለመድረስ በሚከተሉት ፖሊሲና የአፈፃፀም ዘዴ ልዩነቶች አሏቸው። ፓርቲዎች የመንግስትን የተለየ ችግር ለመፍታት በሚጠቀሙበት ዘዴ የሚለያዩበት የዘመኑ አስተሳሰብ ከማደጉ በፊት በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከፖለቲካ አስተሳሰብ ይልቅ በታሪክ፣ በቤተሰብና በአካባቢያዊ ትስስር የሚለያዩበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን አካባቢያዊ ትስስርን፣ የጎሳና የሃይማኖት መስመርን የተከተለ አደረጃጀት ዛሬም ጨርሶ ከስሟል የሚባል አይደለም። ይሁን እንጂ የዚህ አይነቱ አደረጃጀትና አሰራር የ21ኛው ክፍለ ዘመን ዋነኛ የፓርቲ ስርዓት ባህርይ ተደርጎ የሚታይ ሳይሆን የ18ኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ ነፀብራቅ ነው። በዘርም ይሁን በቋንቋ መስመር ወይንም በሌላ የመሰባሰቢያ መሰረት ላይ ቆሞ መደራጀት ከሰዎች የመደራጀት መብት ተለይቶ የማይታይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዘመናችን የሰው ልጅ ከደረሰበት የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የመረጃና የቴክኒዎሎጂ መወራረስ ጋር ተያይዞ በሀገሮች ሕዝቦች መካከል ከዚህ በፊት ያልነበረ ትስስር በመፈጠሩ ነገሮች ሁሉ እየተቀየሩ ናቸው። አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ በክልሎች መካከል የነበረው ጂኦግራፊያዊ ልዩነት እየጠበበ እንዲሄድ የዘር ልዩነትን ተከትለው የተገነቡ አጥሮችን እንዲሰባብሩና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ትስስር እንዲጠናከር በማድረጉ የዘርና ቋንቋን መስመር ተከትሎ መደራጀት ከፍተኛ ትኩረት የሚስብ መሆኑን እያስቀረው ነው። አሁን ያለው ሁኔታ በሀብት ደረጃ በዘርና በክልል የተገደቡ ፓርቲዎችን ሳይሆን እነዚህን ልዩነቶች ሊያጠቡና ሊያቻችሉ

በሚችሉ አመለካከቶች ዙሪያ ለሚደራጁ ፓርቲዎች ሰፊ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ የአምባገነኖች፣ የኦሊጋርኪዎች፣ የሞናርኪዎች በአጠቃላይ የቶታሊታሪያን አመለካከቶች እየተዳከሙና የዴሞክራሲው ክልል እየሰፋ ነው ቢባልም አሁንም በአመለካት ዙሪያ ያሉት ልዩነቶች ቀላል አይደሉም፡፡

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የፖለቲካ ሰዎች በአመለካከታቸው የተነሳ ከፊሉ በተጠናና በሰከነ መንገድ የሚመራ ለውጥ እንዲኖር የሚፈልጉ ሊበራሊስቶች ተደርገው የሚታዩበትና ከፊሉ ደግሞ የተለመደው ሁኔታ እንደተጠበቀ እንዲቀጥል ፍላጎት ያላቸው ወግ አጥባቂዎች ተደርገው የሚታዩበት አመለካት እንዳለ ነው፡፡ በእነዚህ አመለካከቶች ዙሪያ የሚሰሩ ፓርቲዎች አንድም ሊበራል አሊያም ወግ አጥባቂ እየተባለ የሚፈረጁበት ሁኔታ አለ፡፡ የሊበራል ዴሞክራሲ እሴቶችን የሚጋሩት ሳይቀሩ ወደግራ ያዘነበሉ፣ ወደቀኝ ያዘነበሉና መካከለኛ አቋም የያዙ ወዘተ. እየተባሉ ሲፈረጁ ይታያል፡፡ ይኸንኑ አሰላለፍ በመከተል የሚጠሩበት ስያሜም የተለያየ ነው፡፡ ሊበራል ዴሞክራሲ (የውክልና ዴሞክራሲ) ቀጥተኛ ዴሞክራሲ (አሳታፊ ዴሞክራሲ) ወይም ደግሞ የብዙሃን ዴሞክራሲ ሞዴል አሊያም የስምምነት ዴሞክራሲ ሞዴል ወዘተ. ከሚሉት ጥቅል ስያሜዎች አልፎ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲዎች፣ ክርስቲያን ዴሞከራቲክ ፓርቲዎች፣ ኒዎሊበራሊስቶች ወዘተ. እየተባሉ የሚጠሩበት ሁኔታ አለ፡፡ የቶታሊቴሪያን ባህርይ ከተላበሱት በተቃራኒው ምድብ የሚገኙት የዴሞክራሲ ፓርቲዎች በመካከላቸው የፈለገውን ያክል የስም ለውጥና የአፈፃፀም ልዩነቶች ቢኖሩም ዞሮ ዞሮ የሚደርሱበት ግብ አንድና ተመሳሳይ ነው፡፡ የሁሉም ግብ የፖለቲካ ስልጣን ምንጭና መሰረቱ ሕግና የሕዝብ ፈቃድ መሆኑ የተረጋገጠበት ወይም የፖለቲካ ስልጣን በዜጎች ፈቃድና ፍላጎት የሚያዝበትና የሚለቀቅበት ዴሞራሲያዊ ስርዓት በመፍጠር ለዜጎች ዘላቂ ሰላምና ብልፅግናን ማስገኘት ነው፡፡ በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ፓርቲዎች የመንግስት ስልጣን ለመያዝ ከሚያካሂዱት ውድድርም ሆነ ሥልጣን ከያዙ በኋላ ይኸንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚጠቀሙበት ሁኔታ ጋር በተያያዘ የመንግስት አመሰራረት ስርዓቱን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትና ባለሁለት ፓርቲ ስርዓት በሚል መፈረጅ የተለመደ ነው፡፡ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት የሚባለው የሁለት ፓርቲ ስርዓት የመራጮች ድጋፍና ታማኝነት በሁለት ዋነኛ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚከፈልበትና በውጤቱም አናሳ ቁጥር ድምፅ ያገኙ ፓርቲዎች የፖለቲካ ሰልጣን ከመጋራት የሚገለሉበት ነው፡፡

በአንፃሩ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ቢያንስ ሶስት እና ብዙውን ጊዜ ከዚያም በላይ የሆኑ ፓርቲዎች የሚወዳደሩበት እንዲሁም እያንዳንዳቸው የሚገኙበትና በመንግስት ስልጣን ውስጥ ትርጉም ያለው ውክልና የሚያገኙበትና ተሳትፎ የሚያደርጉበት ስርዓት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት የመንግስት ስርዓት ብዙውን ጊዜ ተመጣጣኝ ውክልና በሚባለው የምርጫ ስርዓት ላይ የሚመሰረት ሲሆን የመንግስት ስልጣን ለመምራት የሚያስችል የብዙሃን ውክልና የሚገኘው የተለያዩ ፓርቲዎች በሚፈጥሩት ጥምረት ነው፡፡ በተመጣጣኝ ውክልና ስርዓት በሚደረግ ምርጫ አንድ ፓርቲ ብቻውን የፓርላማ የበላይነት ማረጋገጥ የሚችልበት እድል ጠባብ በመሆኑ የተለያዩ ፓርቲዎች በፓርላማ ውስጥ ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው ከማድረግ አልፎ የመንግስት አስፈፃሚ አካሉንም በጋራ የሚመሰርቱበት የጥምር መንግስት አሰራር መከተል ይኖረባቸዋል፡፡ ጥምር መንግስት ለመመስረት የሚደረገው ስምምነት የተወሰኑ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን በጋራ ለመከተል፣ ለማሻሻል፣ ወይም ለመተው የሚያስችል የመቻቻል መስዋዕትነት መጠየቁ የማይቀር ነው፡፡ በእርግጥ ጥምረቶች በተመጣጣኝ ውልክና ስርዓት ተወዳድረው በሚያገኙት የሕዝብ ድጋፍ ላይ ተመስርተው የመንግስት ስልጣንን ለመጋራት ብቻ ሳይሆን ከዚያ በፊት በሚደረግ የትግል እንቅስቃሴም የመንግስት ስልጣን ከያዘው ፓርቲ የተሻለ አማራጭ ማቅረብ የሚችሉ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲኖሩ የሚያስችል የትግል ትብብር ለመፍጠር ይቋቋማሉ፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመካከላቸው ካለው ልዩነት ይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው የጋራ ጉዳይ ሲኖራቸው ይኸንኑ ለማሳካት የሚያስችል ጥምረት ፈጥረው ሊሰሩ ይችላሉ። ጥምረቱ እንደሚስማማበት ጉዳይ ሊረዝም ወይም ሊያጥር ይችላል። ጥምረቱ የተወሰኑ የጋራ ግቦችን ለማጠናከር ሲባል በመካከላቸው ያሉትን የልዩነትና የአለመግባባት መሰረቶች ለማስወገድ የሚፈጠር እንደመሆኑ አንዳንዱ ጥምረት ለረጅም ጊዜ ከመቆየት አልፎ የሁሉም የጥምረቱ አባላት ምኞት ተፈፃሚ መሆን ከቻለ ወደውህደትም ሊደርስ ይችላል። በማንኛውም ሁኔታ የሚፈጠር ጥምረት በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ ሲታይ በእያንዳንዱ የጥምረቱ አባል ፓርቲ መሰረታዊ መርሆዎች ላይ ስርነቀል ለውጥ ሳይደረግ የየራሳቸውን ፖሊሲ እንደያዙ በጋራ ሊያሳኳቸው በሚችሉ ግቦች ዙሪያ በትብብር ለመስራት የሚደረግ ስምምነትና ይኸንኑ ለማስፈፀም የሚያስችል የጋራ ፕሮግራም መቀየስን የሚመለከት ነው። ስለሆነም ጥምረቶች በማንኛውም ፖለቲካዊ ሁኔታ ውስጥ ከሞላ ጎደል በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ለመቀራረብና ለመስማማት በሚችሉ የተለያዩ ፓርቲዎች መካከል ሊፈጠሩ ይችላሉ። ቀደም ሲል እንደተገለፀው ጥምረቱ አንዳንዴ ለአንድ ጉዳይ ብቻ እንዲሁም ለአጭር ጊዜ ብቻ ይፈጠ ራል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ለበርካታ ጉዳዮችና ተከታታይ ለሆነ ረጅም ጊዜ ይቋቋማል።

ፓርቲዎች በተመጣጣኝ ውክልና ስርዓት ተወዳድረው የሚያገኙት የሕዝብ ድጋፍ በአንድ በኩል ብቻቸውን የፓርላማ የበላይነት እንዳይዙ እንቅፋት በሚፈጥርባቸው ጊዜ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፓርላማ የበላይነት ቢኖራቸውም የሚመሰረተው መንግስት ሰፊ በሆነ ማህበራዊ መሰረት ላይ እንዲቆም ለማድረግ የጥምር መንግስት እንዲኖር የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ። እንዲህ ዓይነቱ የጥምር መንግስት በፓርቲዎች መካከል ያለው የአመለካከት ልዩነት እየጠበበ እንዲሄድ፣ ጠንካራ መተማመን እንዲኖርና ሀገራዊ ስሜት እንዲጎለብት ስለሚረዳ ሰፊ መሰረት ያለው ብዙዎቹ የዴሞክራሲ ስርዓት የገነቡ ሀገሮች እየተጠቀሙበት ነው።

እንዲህ አይነቱ የመተማመንና የትብብር መንፈስ የሚንፀባረቅበት የጥምር መንግስት በፍላጎትና በምኞት ብቻ የሚፈጠር ሳይሆን ለዚህ የሚመች ሕገመንግስታዊ ስርዓት እንዲኖር ያስፈልጋል። የመንግስት ስልጣን በመስጠትና በመቀበል፣ ልዩነቶችን በማቻቻልና በማጥበብ፣ በመግባባትና በትብብር መርህ ላይ ተመስርቶ በዜጎች መካከል ያሉትን የተለያዩ ጥቅሞችና ፍላጎቶች በሚያቻችል መንገድ የተቀረፀ ሕገመንግስታዊ ስርዓት ከሌለ የእርስ በርስ ፍጥጫውና መጓተቱ ይቀጥላል። በዚህ መንፈስ የተዘጋጀ ሕገመንግስታዊ ስርዓት ከሌለ ሊኖር የሚችለው የአንድ ገዥ ፓርቲ ፕሮግራም ቅጅ ስለሚሆን ሕገመንግስት የሚያሰኘውን ይዘትና ባህርይ ያጣል።

በእኛ ሀገር አሁን ያለው ሁኔታም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። የተለያዩ አመለካከቶች፣ ፍላጎቶችና ጥቅሞች የሚቻቻሉበት የመድብለ ፓርቲ የፖለቲካ ስርዓት አልተፈጠረም። በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ባህሎች፣ እምነቶችና አመለካከቶች በአንድ በኩል የራሳቸውን ማንነት እየጠበቁ በሌላ በኩል ደግሞ እየተቻቻሉና እየተባበሩ በእኩልነትና በሰላም አብሮ ለመኖርም ሆነ በጋራ ለማደግ የሚያስችላቸውን ዴሞክራሲያዊ መብት የሚያረጋግጥ ፕሉራል ስርዓት አልተፈጠረም። አነስተኛ የአብላጫ ድምፅ ስርዓትን ሕገመንግስታዊ ግዴታ አድርጎ የደነገገ፣ የራሱን ፖለቲካዊ ፕሮግራም ካለዜጎች ፈቃድና ፍላጎት ሕገመንግስታዊ ሰነድ አድርጎ በሕዝብ ላይ የጫነ፣ የተለየ አመለካከት ላላቸው ሁሉ ሀቀኛ እውቅና የማይሰጥና አፈናን እንደዋነኛ የስልጣን ማስጠበቂያ ዘዴ የሚጠቀም፣ ሰፊ መሰረት የሌለውና የኃይል አገዛዝ የመሰረተ ቶታሊታሪያን የመንግስት ስርዓት በመተከሉ ይኸንን አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት መላው ሕዝብና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ከፍተኛ ትግል እያደረጉ ነው።

አሁን በሀገራችን ያለው ዋነኛ ትግል የዴሞክራሲ ስርዓት እንዳይፈጠር በሚፈልገው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ቶታሊታሪያን (አፋኝና አባጠቅል የሆነ አገዛዝ) አገዛዝና ለዴሞክራሲ ስርዓት መመስረት በቆሙ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች መከካል የሚካሄድ ትግል ነው:: በዴሞክራቲክ ኃይሎች የሚመራው ትግል የዜጎችን መሰረታዊ ጥቅሞችና ፍላጎቶች የሚወክል እንደመሆኑ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ሊኖረው የሚችልና ሰፊ በሆነ ማህበራዊ መሰረት ላይ ሊቆም የሚችል ነው:: በአንፃሩ የአብዮታዊ ዴሞክራቶች አገዛዝ የዜጎች ፈቃድና ነፃ ምርጫ ሳይኖር በኃይል የተያዘ አፈናን እንደዋኛ የሥልጣን ማስጠበቂያ ዘዴ የሚጠቀምና በጠመንጃ ድጋፍ የቆመ፣ ዜጎችን የሚከፋፍልና አንድነታቸውን የሚያዳክም፣ የሀገሪቱን ሉዓላዊ አንድነት የሚያናጋና ብሔራዊ ጥቅሞቿን አሳልፎ የሚሰጥ፣ ዘላቂ ሰላምና ልማት ሊያመጣ የሚችል ሀገራዊ ራዕይ ሳይኖረው በሕዝብ ላይ በግድ የተጫነ አገዛዝ ነው::

## 6.1 በዴሞክራሲና በኢህአዴግ አገዛዝ መካከል ያለው የማህበራዊ መሰረት ልዩነት

በዴሞራሲያዊያን ኃይሎች የሚመራው ትግል ዓላማ የዜጎችን መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በኃይል የነጠቀውንና ቶታሊቴሪያን (አፋኝና አባጠቅል) የሆነውን አገዛዝ በሕዝብ ትግል አስወግዶ በምትኩ ለዜጎች ነፃነት፣ እኩልነት፣ ዘላቂ ሰላምና ብልፅግና መረጋገጥ ዋስትና የሚሆን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማስፈን ነው:: ይህ አላማ በአፈና አገዛዝ ስር ወድቀው መሰረታዊ መብቶቻቸውንና ነፃነቶቻቸውን በኃይል የተነጠቁ የሁሉንም የሀገራችንን ዜጎች ፍላጎት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሰፊ የሕዝብ ድጋፍን ሊያሰባስብ የሚችል አላማ ነው:: በአሁኑ ጊዜ በሕወሓት/ኢህአዴግ ዙሪያ ከተሰባሰቡ ጥቂት ቡድኖችና አባሎቻቸው በስተቀር በአብዮታዊ ዴሞክራቶች መብቱን ያልተነጠቀ፣ ነፃነቱን ያልተገፈፈና እጅግ በሚዘገንን አፈና ውስጥ ያልወደቀ ዜጋ ማግኘት አይቻልም:: ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ማስከበር የሚፈልጉት ደግሞ ይኸንኑ በግፍ አገዛዝ ስር የሚማቅቅ ሕዝብ መብትና ነፃነት ነው:: በመሆኑም ትግላቸው ሰፊ የሕዝብ ድጋፍና ማህበራዊ መሰረት ይኖረዋል:: አብዮታዊ ዴሞክራቶች የዜጎችን የቆየ ወንድማማችነት አፍርሰው በምትኩ አስከፊ የእርስ በርስ መተላለቅ በማንገሳቸው ሳይታሰብ በሚፈነዳ ጦርነት ሀገርና ሕዝብ እየተናጡ ነው:: ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ ዜጎች መካከል የተዘራውን ይኸንን የጥላቻ ፖለቲካ አስወግደው በእኩልነት በመተማመንና በትብብር መርህ ላይ የቆመ አንድነት እንዲኖር ስለሚታገሉ ዓላማቸው ሰፊ የሕዝብ ድጋፍና ጠንካራ ማህበራዊ መሰረት ይኖረዋል:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከእስከዛሬዎቹ ንድፈ ሀሳባዊ ትንተናዎችና ተግባራዊ ልምዶች እንደታየው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ባህርይና ተልዕኮ የተሸከመ አመለካከት መሆኑ ይታወቃል:: አብዮታዊ ዴሞክራሲ የቀዝቃዛው ጦርነት ከማብቃቱና የቀድሞዋን ሶቭየት ሕብረት ጨምሮ በመላው ምስራቅ አውሮፓ ተንሰራፍቶ የቆየው የሶሻሊዝም ስርዓት ከመፈራረሱ በፊት በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ በተራዘመ የሽግግር ሂደት ኮምዩኒዝምን ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የተሳካ ለማድረግ ይረዳል ተብሎ በስራ ላይ ሲውል የቆየ አማራጭ አስተሳሰብ ነው:: በማርክሲስቶች ትንተና ይህ አመለካከት ራሱን ችሎ የሚቆም ቲዎሪ ተደርጎ ባይቆጠርም ከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስታዊ በሆነ ቅይጥ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ ሀገሮች ካፒታሊስታዊ ያልሆነ የእድገት አቅጣጫ እንዲከተሉና ቀስ በቀስ ወደሶሻሊዝም እንዲገቡ የሚያስችል የመሸጋገሪያ አብዮት ያስፈልጋቸዋል የሚለውን መላ ምት ወይም ግምት የሚወክል ነበር:: ትርጉሙም «አብዮታዊ ዴሞክራሲ ማለት ከከተማው ንዑስ ከበርቴ፣ ከገበሬውና ከተራማጅ ምሁራን መካከል ፀረ-ካፒሊስትና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት የሆነውን ትግል የሚደግፉትን ክፍሎች እንዲሁም የእነዚህን ፍላጎትና ጥቅም የሚጠብቁ ፓርቲዎችን፣ ድርጅቶችንና ቡድኖችን ለመግለፅ የሚያስችል አመለካከት ነው» በሚል በማሌ መዝገበ ቃላቶች ውስጥ በግልፅ ተቀምጧል:: ከዚህ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለካፒታሊዝም ስርዓት ባዕድ ብቻ ሳይሆን ፍፁም ተፃራሪ አቋም ያለው

አመለካከት መሆኑን ነው:: የካፒታሊዝም ስርዓት እንዳይመሰረት የመታገል ተልዕኮ የተሸከመ ብቻ ሳይሆን ሰዎች በማይታረቁ አጥፊና ጠፊ በሆኑ ተፃራሪ መደቦች የተከፋፈሉ ናቸው ከሚለው ማርክሳዊ አስተሳሰብ በመነሳት አንደኛው ወገን ሌላውን እንደጠላት እንዲመለከተውና አብዮታዊ በሆነ መንገድ እንዲያስወግደው ለማድረግ የቆመ በመሆኑ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ነው::

በዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የሚመራው ትግል የመሬት ባለቤትነቱን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ለተነጠቀው ገበሬ የቆመ ነው:: እውቀቱንና ጉልበቱን ተጠቅሞ ለመስራትና ኑሮውን ለመምራት የሚያስችል ነጻነትና መብት አጥቶ እንደአልባሌ እቃ ለሚታየው ሰራተኛ የቆመ ነው:: አብዮታዊ ዴሞክራሲን ከመስበክ በስተቀር ነፃ ሀሳብ እንዳይኖረው፣ በነፃነት እንዳያስተምር፣ በነፃነት እንዳይሰራና በነፃነት እንዳይመራመር በሚደርስበት ጫናና ወከባ ዕጣ ፈንታው ሀገር ጥሎ መሰደድ ለሆነው ምሁር የቆመ ነው:: በትምህርት ቤት ውስጥ ነፃ አስተሳሰብ፣ የሞያ ብቃትና አስተማማኝ እውቀት እንዲቀስም ሳይሆን የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ፖለቲካዊ አቋም የሆነውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጽንስ ሀሳብ በግድ እየተጋተ የወጣትነት ጊዜውን እንዲያባክን ለተፈረደበት ተማሪ የቆመ ነው:: ሀብቱንና ንብረቱን ለልማት በማዋል ራሱንና ሀገሩን ለመጥቀም በተንቀሳቀሰ ቁጥር እጅግ አስቸጋሪ በሆነ የመሬት ሊዝ፣ የቤት ኪራይና ልዩ ልዩ ታክስ እንዳይላወስ ሆኖ ለታሰረው የግል ኢንቨስተር የቆመ ነው:: ንግድና አገልግሎት ሰጥቶ ለመኖር እንዳይችል በፖሊሲ ማነቆዎች ተሰንጎ ለተያዘውና በኮምዩኒስት አመለካከት እንደ አጭበርባሪ ለሚፈርጀው ነጋዴ የቆመ ነው::

በአጠቃላይ ሀሳቡን የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ የመስራትና የመኖር፣ በፈለገው የሀገሪቱ ክልል ሀብት የማፍራት፣ በፈለገው ቋንቋ የመማርና የመጠቀም፣ የፈለጋቸውን መርጦ ለመንግስት ስልጣንም ይሁን ለሌላ ኃላፊነት የመወከል፣ ፍትህ የማግኘትና የመሳሰሉ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን የተነፈገው ዜጋ ሁሉ እነዚህ መብቶቹና ነፃነቶቹ እንዲከበሩለት የቆመ በመሆኑ ሰፊ ማህበራዊ መሰረትና ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ይኖረዋል::

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የአብዮታዊ ዴሞክራቶችን የጭካኔ በትር ያልቀመሰ፣ በዚህ ግፈኛ አገዛዝ ያልተንገሸገሸ፣ በመብትና ነፃነት እጦት ያልተሰቃየ ኢትዮጵያዊ የለም የሚል እምነት አለን:: ይህ አገዛዝ ሕፃንና ሽማግሌ፣ የተማረና ያልተማረ፣ ድሃና ሃብታም፣ ሲቪልና ወታደር፣ አርቦ አደርና ወዛደር፣ ተማሪና አስተማሪ፣ ወንድና ሴት፣ ሙስሊምና ክርስቲያን፣ ከተሜና ገጠሬ፣ ደገኛና ቆለኛ ወዘተ. ብሎ ሳይለይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የዜጎችን መብትና ጥቅም እየረገጠ የሚገኝ እንደመሆኑ ጠንካራ ማህበራዊ መሰረትና ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ሳኖረው በሕዝብ ላይ በግድ የተጫነ አገዛዝ ነው::

በሕወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ከሚቀርቡ ትንተናዎች በተደጋጋሚ ጊዜ ሲነገር እንደሚሰማው ከጠቅላላው ሕዝብ 85 ከመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ አርሶ አደር ይኸንን አገዛዝ ይደግፋል የሚል ነው:: እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው:: የአሁኑን አገዛዝ አምርረው ከሚጠሉትና ከሚታገሉት የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ናቸው:: ከማንም በላይ በአብዮታዊ ዴሞክራቶች የግፍ አገዛዝ የተሰቃዩት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ሲሆኑ ከዚህ አገዛዝ ለመገላገል ከማንም በላይ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውም እነርሱ ናቸው:: ካላቸው ሰፊ መሰረት ከሚደርስባቸው ግፍ አኳያ የዴሞክራሲ ኃይሎች ለጀመሩት ትግል ሰፊ የድጋፍ መሰረት ሆነው ሊቆሙ የሚችሉት እነዚሁ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ናቸው::

ማንኛውም መብቱንና ነፃነቱን የተነጠቀ ግለሰብ፣ ቡድንና ሕብረተሰብ መብቶቹን ነጥቆ የግፍ አገዛዝ ለተከለበት ፓርቲና መንግስት የድጋፍ ምንጭና ማህበራዊ መሰረት የሚሆንበት ምንም አይነት አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በሕወሓት/ኢህአዴግ በኩል ሰፊ በሆነ ማህበራዊ መሰረት ላይ የቆመ ስርዓት እየተገነባ መሆኑን አስመልክቶ የሚቀርበው ገለፃ ባዶ ፕሮፓጋንዳና ለሕዝብ ግንኙነት ፍጆታ ብቻ የሚውል ነው፡፡ በግልፅ ለመናገር ሕወሓት/ኢህአዴግ የዚህን ወይም የዚያን ሕብረተሰብ ክፍል ጥቅም ሙሉ በሙሉ የሚወልክና በእዚህና በዚያ ማህበራዊ መሰረት ላይ ተደላድሎ የቆመ አይደለም፡፡ ከአገዛዙ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ሕልውና የመሰረቱ የድርጅቱ አባላትና ጥቂት ደጋፊዎች እንኳ ሳይቀሩ የጊዜ ቅደም ተከተል ካልሆነ በስተቀር በየተራ ወደ አገዛዙ የማረጃ ቄራ ከመውረድ እንደማያመልጡ በማመናቸው በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ራሳቸውን ለማግለልና ሀገር እየጣሉ ለመኮብለል ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው፡፡

አገዛዙ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ 85 ከመቶ ለሚሆነው አርሶ አደር ለበርካታ አመታት ባዶ ተስፋ ሲሰጥ በመቆየቱና አንድም የሚጨበጥ ነገር ለማምጣት ባለመቻሉ በአብዛኛው አርሶ አደር ሕብረተሰብ እምነት የማይጣልበት ብቻ ሳይሆን የተጠላ ነው፡፡ ሕወሓት/ኢህአዴግ አማፂ ቡድን ከነበረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን በገበሬው ጫንቃ ላይ የተጫነ ሸክም እንጂ እንደአጋርና እንደ ተወዳጅ መሪ ድርጅት የሚታይ አይደለም፡፡ በገበሬ ጀርባ ላይ በግድ ተጣብቆ አልላቀቅ ያለ እንጂ እንደሚወደድ ልጅ ታዝሎ እሽሩሩ የሚባል አይደለም፡፡

ለሕወሓት በረሃ መግባት እንደ መሰረታዊ ምክንያት ሲነሳ የቆየውና አሁንም የሚነገረው በሀገሪቱ ላይ ሰፍኖ የነበረው የዘር ጭቆና እንደሆነ ተደርጎ ነው፡፡ አሁን በተግባር እንደሚታየው ከዚህ ነጥብ አኳያ ሲመዘን ሕወሓት ማንንም ከዘር ጭቆና የማውጣት ሁነኛ ተልዕኮ ያልነበረው ብቻ ሳይሆን እንደውም ራሱ በከፋ ዘረኝነት ልክፍት የተነደፈ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ የሕወሓት ዋነኛ ተልዕኮና የአመፁ መዳረሻ ግብ የዘር ጭቆናን ታግሎ ማስወገድ ነው በሚል ከፋፋይ ካባ ሥር ሳይሆን ዘረኝነትን እየዘራ ማብቀል እንደሆነ በተግባር እየታየ ነው፡፡ ይኸንን ሀቅ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተገነዘበው በመምጣቱ የሕወሓት መነሻ የነበረው የዘር ጭቆና (ፀረ የዘረኝነት ጭቆና) መፈክር ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍ በመላ ሀገሪቱ ሊያስገኝ ቀርቶ ሕወሓት ለአመታት በመሸገባት የደደቢት ዋሻ አካባቢ ያሉትን ገበሬዎች እምነት እንኳ ጠብቆ ለማቆየት እንዳልቻለ ግልፅ ነው፡፡ ዛሬ በሕወሓት ላይ ተቃውሞ የማያሰማ ሕዝብና አካባቢ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡

ይህ አገዛዝ እንዲወደድና እንዲታመን የሚያደርገው መልካም ነገር ለመስራት ያልቻለ ነው፡፡ አርሶ አደሩን የመሬቱ ባለቤት አደረግሁት እንዳይል ራሱን በመንግስታዊ የመሬት ከበርቴ ያደረገና አርሶ አደሩን ደግሞ ወደ መንግስት ጭሰኝነት የቀየረ ነው፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ አርሶ አደር የመሬት ግብር ከመክፈልና ለሕወሓት/ኢህአዴግ ኩባንያዎች የትርፍ ምንጭ ከመሆን በስተቀር ያገኘው ነገር የለም፡፡ የጉልበቱ፣ የመሬቱና የምርቱ ባለቤት ለመሆን ነፃነት የተነፈገው አርሶ አደር የሕወሓት/ኢህአዴግ ማህበራዊ መሰረት የሚሆንበት ሁኔታ ጨርሶ የማይታሰብ ነው፡፡ በዚህ አገዛዝ ዘመን አርሶ አደሩ ሰላም አገኘ እንዳይባል ልጆቹን፣ የስራ ጊዜውንና የኢኮኖሚ አቅሙን የሚበላ ጦርነት አልቀረለትም፡፡ ምርታማነትና የኑሮ ሁኔታ መሻሻል አግኝቷል እንዳይባል ከየትኛውም ጊዜ በባሰ ሁኔታ ለረሃብና ሞት የተጋለጠው በዚህ አገዛዝ ወቅት ነው፡፡

አሁን አሁን እንደትልቅ የልማት ጥረት እየተነሳ ያለው ረሃብና ድርቅ መምጣቱን ለለጋሾች በጊዜ አሳውቀናል የሚል ነው፡፡ ይኸ በእውነቱ በአርሶ አደር የታቀፍኩና የተደገፍኩ ነኝ ለሚል መንግስት እጅግ አሳፋሪ ነው፡፡ አስራ ሁለት ዓመት ሙሉ የመንግስት ስልጣን በብቸኝነት ይዞ የቆየና የገበሬ ጥቅም ግንባር ቀደም ጠባቂ ነኝ የሚል አገዛዝ ለገበሬ

*ሕይወት መሻሻል ጠብ የሚል የልማት መፍትሔ ማቅረብ ተስኖት የልመና ጥሪ ለአለም ሕብረተሰብ በፍጥነት ማሰማቱን እንደ ትልቅ ቁምነገር የሚቆጥር ከሆነ ይህ አገዛዝ የሚያፍርበትንና የሚኮስስበትን ለመለየት አስቸጋሪ ነው:: ሕዝቡ ያጋጠመውን ችግር ሳይደብቁ መግለፅ የአንድ መንግስት ግዴታ ነው:: ከግዴታዎቹ መካከል አንደኛውን መፈፀሙ ተገቢ መሆኑ ባይካድም እንደትልቅ የልማት ውጤት ደረትን ነፍቶ የሚፎከርበት ግን አይደለም::*

*ድርቅ በየትኛውም የአለም ክፍል ሊከሰት የሚችል የተፈጥሮ ክስተት ቢሆንም አስከፊ ርሃብና ሞት ሊያስከትል የሚችለው ግን ምንም አይነት የረባ የልማት መሻሻል በሌለበት ሀገር ብቻ ነው:: የኢትዮጵያን ድርቅ ወደ አስከፊ ረሃብና ሞት የሚለውጠው ልማት ማምጣት ያልቻለ አገዛዝ በመኖሩ ነው:: የገበሬውን የልማት እድል ክርችም አድርጎ የዘጋና ሃላፊነቱን ሁሉ ለአለም አቀፉ እርዳታ ለጋሽ ማህበረሰብ አሳልፎ የሰጠ አገዛዝ የረሃብ ጥሪ በወቅቱ አሰምቻለሁ ማለት በራሱ የመንግስትን ኃላፊነቱን በብቃትና በተሟላ መልክ መወጣትን አያረጋግጥም:: እንደውም ለበጎ አድራጊዎቹ ርህራሔና ሰብዓዊ ጥረት ዝቅተኛ ግምት እንደመስጠት የሚቆጠር ነው:: እርዳታ ሰጪዎቹ እርዳታ የለገሱት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰቆቃ ተገንዝበውና ሰብዓዊ በሆነ ርህራሄ ላይ ተመስርተው ሳይሆን «ለእኔ ባላቸው ፍቅርና አክብሮት ተነሳስተው ያደረጉት ነው» እንደማለትም ይመሰላል:: በመሰረቱ ለመወደድና ለመከበር መጀመሪያ የሚያስወድድ ነገር ማድረግን ይጠይቃል:: እርዳታ ለጋሾች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብዓዊ ርህራሔ በሚያሳዩበት ጊዜ በአፋኝ አገዛዝ ስር መውደቅ የሚያስከትለውን አስከፊ ውጤት እያሰላሰሉና ልባቸው እየደማ መሆኑን ማንም ሊገነዘበው የሚችል ነው:: ሠዎች ለተቸገሩ ወገኖች ቁሳዊ እርዳታ መለገስ ብቻ ሳይሆን ፈጣሪ ከአገዛዝ ቀንበር ነፃ እንዲያደርጋቸውም ፀሎት እንደያሚደርሱ ይታወቃል:: ፀሎቱ በአንድ በኩል ለሚራቡና ለሚሞቱ ወገኖች የሚደረግ የአጋርነት መግለጫ ሲሆን በሌላ በኩል ድርቅን ወደ አስከፊ ርሃብና ሞት ለሚያሸጋግሩ ገዥዎች እንደ እርግማን የሚቆጠር ነው:: «ጌታ ሆይ የሚራቡትና የሚሞቱትን አስባቸው፣ ለዚህ ያጋለጣቸውን ጨካኝ አገዛዝ ከላያቸው ላይ አውርዳቸው» በሚል ለፈጣሪ የሚቀርብ ፀሎትና ምህላ ለገዥዎች ፍቅርና አክብሮት መግለጫ ሊሆን የሚችልበት መንገድ የለም:: ስለዚህ ጥሩ ለማኝ በመሆን ክብርና ውዳሴ ማግኘት የሚፈልግ አገዛዝ የልማት መፍትሔዎች ያለቁበት ብቻ ሳይሆን መጀመሪያውኑ መፍትሔ የሚል ነገር ኖሮት የማያውቅ መሆኑን መጠራጠር አይቻልም::*

*ለህወሓት/ኢህአዴግ ጠንካራ ማህበራዊ መሰረት ሆኖ የሚያገለግለውና ጥቅሙ የተከበረለት የማህበራዊ ክፍል ይኸኛው ነው ብሎ በግልፅ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ቢሆንም በቢሮክራሲው ውስጥ ቁልፍ ቁልፍ ስልጣን የያዘውና ለአገዛዙ ታማኝነቱን እስካልቀነሰ ጊዜ ድረስ ስልጣኑን መከታ እያደረገ የሕዝብ ገንዘብና ንብረት እንዲቦጭቅ፣ ንግድ እንዲከፍትና ጥሪት እንዲያፈራ እድል ያገኘ ታዳጊ የቢሮ ከበርቴ እያቆጠቆጠ ነው:: ይሁን እንጂ ይኸኛው ማህበራዊ ክፍል አብዛኛው ከአገዛዙ ጋር ግንኙነት የመሰረተው ዘግይቶ ከመሆኑም በላይ ሕወሓት/ኢህአዴግ ከበረሃ ቆይታ ጊዜው አንስቶ ያነገበውና በኋላም ወደመሀል ሀገር ይዞት የመጣው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለው አመለካከት የሚዋጥለት ስላልሆነ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አገዛዝ ታማኝ ዘብ ተደርጎ የሚታይ አይደለም:: በዚህ ማህበራዊ ክፍል ውስጥ የሚታየው አብዛኛው ወገን ሕወሓት ከደደቢት መጥቶ ከበርቴ ሲሆን እኛስ የማንን ጎፈሬ እያበጠርን እንቀመጣለን በሚል ስሌት ለራሱ ጥሪት የማፍራት አላማ ይዞ ጠጋ ያለ እንጂ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከጠፋ እኔም እጠፋለሁ ብሎ የሚጨነቅና ለዚህ አመለካከት አሸናፊነት ለመሟሟት ቆርጦ የተሰለፈ አይደለም:: እንደውም ሕወሓት ያለበትን የቢሮ አመራርና አሰራር ድክመት በማወቅ በዚህ ክፍተት ተጠቅሞ በቂ ጥሪት መቆንጠር ከቻለ ራሱን ወደ ኢንዱስትሪ ከበርተኔት የመቀየር አላማ የያዘ እንጂ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር እስከአለም ፍፃሜ እየተጓተትኩ እኖራለሁ ብሎ የሚያስብ አይደለም:: ከበረሃ በመጣው ጠበንጃ አንጋችና የትምህርትና የስልጠና ዝግጅት አሟልቶ መሀል አገር በተገኘው ታዳጊ የቢሮ ከበርቴ መሀል*

ብዙ ጊዜ የሚታየው ፍጥጫና መጓተት የዚሁ የእምነትና የአመለካከት አለመጣጠም ውጤት ነው፡፡

ሌላው ከዚህ አገዛዝ ተጠቃሚ መሆን የቻለ ማህበራዊ ክፍል ሕወሓት በከፈታቸው የኢኮኖሚ ኩባንያዎች ውስጥ ባለድርሻና የኩባንያ ባለስልጣን የሆነው ክፍል ነው፡፡ የነዚህ ተቋማት ተጋሪ ክፍል በአብዛኛው ከበረሃ የመጣውን ጠብመንጃ አንጋች የያዘ እንደመሆኑ በሀገሪቱ ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ሌሎች ተወዳዳሪዎችን እየሰበረ ለማስተኛትና በብቸኝነት ራሱን ችሎ የሚቆም የሞኖፖል አቅም ለመገንባት አልሞ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ በእጁ ያስገባው ጥሪት አብዛኛው በነጠቃ የተገኘ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መጠኑም በተነፃፃሪነት ሲታይ ከፍተኛ ነው፡፡ ወደገበያ የሚገባው በነጠቃ በተገኘ ሀብትና ንብረት በመሆኑ የሚደርስበት ኪሳራ እንደሌለ አውቆ የሚገባ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከሞላ ጎደል አገዛዙን የሚመሩት ሰዎች የተካተቱበት ክፍል በመሆኑ ሙሉ መንግስታዊ ድጋፍና የተለየ ጥበቃ የሚደረግለት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በእጁ ያስገባውን ካፒታል በፍጥነት ለማሳደግና መሪ ከበርቴ ለመሆን የተመቻቸ ሁኔታ የተፈጠረለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ውስጥ የታቀፉት አብዛኞቹ ሰዎች እትበታቸው ከአገዛዙ ጋር የተሳሰረ አብዮታዊ ዴሞክራቶች ቢሆኑም በተሰማሩበት የንግዱና የአገልግሎት ዘርፍ ባህርይ ምክንያት ከውጫዊው ሁኔታ ጋር በሂደት መተሳሰራቸው ስላማይቀር በነባሩ አቋማቸው ፀንተው እስከመጨረሻው ለመዝለቅ የሚቸገሩ ሰዎች ከመካከላቸው ብቅ ማለታቸው የማይቀር ነው፡፡ በተለይ የስራው ስፋትና ክብደት የተለየ ችሎታና እውቀት እየጠየቀ በሄደ ቁጥር ከውጭ አዳዲስ ሞያተኞችን የመሳብ ግዴታ ስለሚያስከትል ከስር ከስር የሚገባው አዲስ ኃይል በቴክኒክ እውቀት ብቻ ሳይሆን በቁጥርም ከነባሮቹ እያየለ ስለሚሄድ ይህ ማህበራዊ ክፍል የአብዮታዊ ዴሞክራሲን አመለካከት በቋሚነት የሚሸከም ልዩ ኃይል የመሆኑን እድል እያጠበበው ይመጣል፡፡ በዚህ መንገድ ከውስጥና ከውጭ ከፍተኛ ግፊት በበዛ መጠን ይህ ማህበራዊ ክፍል ከሁለት ቀጭን አማራጭ አንደኛውን እንዲቀበል ግድ ይሆንበታል፡፡ አንደኛው አማራጭ እያደገ ከሚሄደው አዲስ ከበርቴ ጥቅም ጋር የማይጣጣመውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመለካት ተሸክሞ መንቀርፈፍ ሲሆን ይኸንን አማራጭ የሚያስቡ አይኖሩም ባይባልም ሁሉንም የሚያስማማ አማራጭ ሊሆን መቻሉ አጠ ራጣሪ ነው፡፡ በአዲስ ካፖርት ላይ አሮጌ ጨርቅ እንደመጣፍ ያህል መሆኑ ስለማይቀር ብዙዎቹ የሚደግፉት ፋሽን የመሆን እድሉ አነስተኛ ነው፡፡

ሁለተኛው አማራጭ አብዮታዊ ዴሞክራሲን እርግፍ አድርጎ በመጣል ለአዲሱ ከበርቴ ማህበራዊ ክፍል ጥቅም በሚስማማ ሁኔታ ራሱን አስተካክሎ ወደፊት ለመግፋት መሞከር ነው፡፡ እዚህ ደረጃ ሲደረስ የሚፈጠረው የጥቅም ባህርይ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንዲኖር ከሚፈልገው ጥቅም ጋር መጣጣም ስለማይችል እንኳንስ በአቋራጭ ወደከበርቴነት ለመንጠ ላጠል እያሰቡ በኋላ የተጠጉት ሰዎች ይቅሩና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዋነኛ ባለቤቶች የሚባሉትም በቀድሞው አቋማቸው እንደፀኑ ሊቀጥሉ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ራሳቸው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማህበራዊ መሰረት መሆናቸውን የሚጠሉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በመጨረሻም አዝሎ ባሳደጋቸው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይ ፊታቸውን ማዞር ግድ ይሆንባቸዋል፡፡

ሌላው የዚህ አገዛዝ ጥቅም ተቋዳሽ የሆነው ክፍል በወታደሩ አመራር ኃላፊነት ላይ የሚገኘው ነው፡፡ የዚህኛው የተወሰነው ክፍል ገና ጥሩና መጥፎውን ለመለየት በሚያስችለው የትምህርትና የእድሜ ደረጃ ላይ ሳይደርስ በከበሮ፣ በክራና በዋሽንት እየተሳበ፣ በስኳርና በጠመንጃ (በኢትዮጵያ ውስጥ መጠንጃ እንደ ጀግንነት ምልክት ሆኖ ሲታሰብ የቆየ ነው) እየተታለለ ወደ በረሃ የገባና የሞተው ሞቶ የተረፈው አዲስ አገዛዝ በሀገሪቱ እንዲተከል

አስተዋፅኦ ያደረገ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፍትሓዊ ትግል እንዳደረገና ለሀገሪቱ ችግር የተሻለ መፍትሔ የሚሆን ድል እንዳስመዘገበ አድርጎ የኩራት መንፈስና ልበ ሙሉነት ሲታይበት የነበረ ነው። ይሁን እንጂ በአመራር ላይ ያሉት በሲቪል ስራ ከተሰማሩት ጓደኞቻቸው ጋር በጥብቅ ተሳስረው ሀብት በማካበትና የራሳቸውንም ሆነ የዘመድ አዝማዶቻቸውን ኑሮ በማመቻቸት ስላተኮሩ ራሳቸውን ከተራው ወታደር ጋር አቃቅረዋል። ተራው ወታደር ደግሞ በሂደት የቀድሞ እምነቱን የሚሸረሽሩ በርካታ ሁኔታዎች አጋጥመውታል። በትምህርትም በእድሜም እየበሰለ ሲመጣ በወጣትነት ጊዜ የነበረው ሕልምና አሁን በገሃድ አለም የሚታየው እውነታ የሰማይና የመሬትን ያህል የተራራቁ መሆናቸውን እየተገነዘበ ነው።

ከዚህ ሌላ በየጊዜው በርካታ አዲስ ኃይል እየተቀላቀለው በመምጣቱ በረሃ በቆየበት ጊዜ ከአንድ ምንጭ ብቻ በሚቀዳ ፕሮፓጋንዳ ተሸብቦ እንደጋሪ ፈረስ ነገሮችን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከሚመለከትበት ሁኔታ እየወጣ ነው። ሲነገረው ከነበረው ውጪ ሌሎች አማራጭ ልምዶች መኖራቸውን ማየት እየቻለ ነው። ከሁሉም በላይ ነባሩም ሆነ አዲሱ ኃይል በአንድነት የሚጋሩት አመለካከት አለ። ይኸውም ሁሉም ከኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የወጡ መሆናቸውንና በሕዝቡ ውስጥ ያለው ጥሩና መጥፎ ነገር እነሱንም መጨመሩ የማይቀር መሆኑ ነው። ወላጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው፣ ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ጎረቤቶቻቸው፣ በአጠቃላይ ተወልደው ያደረጉበትና የኖሩበት ሕዝብ በአገዛዙ የሚደርስባቸው ከባድ ጭቆና በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በእነሱም ላይ የሚደርስ ነው። በሚሰሩበት ወታደራዊ ተቋም ውስጥ የሚፈፀመው ብልሹ አሰራር አገዛዙን ተሸክመው እሸሩሩ እንዲሉት የሚያስችል አይደለም። በወታደራዊ አመራር፣ በኃይል ስምሪት፣ በግዳጅ አፈፃፀም፣ በእድገትና ሽልማት አሰጣጥ ወዘተ. ያለውን አድሎና ዘረኝነት ሁልጊዜ እየታገሉ ይኖራሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም። ሁሉም ወታደር የአገዛዙን ነፋስ እየጠበቀ ሊኖር ቀርቶ እንደሳዳም ሪፐብሊካን ዘብ ልዩ ልዩ መደለያና እንክብካቤ የሚቀርብለት የሕወሓት ቅልብ (ልዩ ኃይል) ጦር እንኳ ሕዝቡ በአገዛዝ ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ ማሳደር በሚችልበት የመጨረሻው ቀውጢ ሰዓት ላይ ሲደርስ የመሳሪያውን ኢላማ ወደ አገዛዙ እያዞረ የሚያነጣጥርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

እዚህ ላይ በአጭሩ ለማለት የተፈለገው ሕወሓት/ኢህአዴግ ለሕልውናው ሲል የዚህን ወይም የዚያን ማህበራዊ ክፍል ጥቅም የምወክል እኔ ነኝ እያለ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም በተጨባጭ የሚያስጠብቀው ጥቅም የጫካ ትግል ሲመሩ የነበሩትንና አገዛዝ ላይ የተንጠላጠሉትን ጥቂት ግለሠቦች ብቻ እንጂ የሌላን ማህበራዊ ክፍል አለመሆኑን ነው። አሁን ስልጣን በያዘው ጠምንጃ አምላኪ አገዛዝ ዙሪያ የተኮለኮሉት ሌሎች ክፍሎች ግን ከሕወሓት መሪዎች የተለየ ዘላቂ ጥቅምና አላማ ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ነገሩ ሳይገባቸው ዘው እያሉ የገቡ ሲሆኑ በጊዜ ሂደት ስህተት መስራታቸውን እያወቁ አንድ በአንድ ራሳቸውን ከገቡበት አዘቅት ለማውጣት ሙከራ በማድረግ ላይ ያሉ ናቸው። ለመውጣት የቻሉም እንዳሉ ይታወቃል። ሌሎቹ ከልብ ወደሚደግፉትና በዘለቄታው ወደሚፈልጉት የራሳቸው መስመር እስኪገቡ ድረስ ጊዜያዊ ጥቅም እያገኙ ለመቆየት አስበው የተጠለሉ ናቸው። የተጠለሉበት አገዛዝ የሚያናድ መሆኑን ቢያውቁም ወደራሳችን ዘላቂ አቅጣጫ ለመሸጋገር ከባለጠመንጃ ጋር እየተጋፈጥን ሳይሆን በደካማ ጎኑ እየተጠቀምን መሆን አለበት በሚል ስሌት የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ያሰቡት ሲሳካ አይንህን ላፈር እንደሚሉት የታወቀ ነው። ያም ባይሆን ከውስጥ ገብተው ይገዝግዙታል እንጂ ልባዊ ድጋፍ እያደረጉ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ውጤታማ ያደርጉታል የሚባሉ አይደሉም።

ስለዚህ ሕወሓት አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለው አስተሳሰቡ ጠንካራ በሆነ ማህበራዊ መሰረት ላይ ተደላድለው የተቀመጡ ሳይሆኑ ጠመንጃና ተቋማዊ ሙስና በሚባሉ ሁለት ባላዎች ተደግፈው የሚኖሩ ናቸው። ጠመንጃና ሙስና ደግም የዴሞክራሲና የልማት እድልን

የሚነፍጉ እንጂ ለዴሞክራሲና ለልማት የሚመቹ ስላልሆኑ የተቃውሞ ዋነኛ ምንጭ መሆናቸውና በሕዝቡ ውስጥ የማያባራ ማህበራዊ ቀውስና ብጥብጥ ማስከተላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው:: በመጨረሻም ሕዝቡ በጠመንጃና በሙስና ላይ ያለውን ተቃውሞ በተበታተነና ተከታታይነት በሌለው መንገድ ማቅረቡን ትቶ በተቀናጀ አደረጃጀትና በማያቋርጥ እንቅስቃሴ መተካት በሚችልበት ጊዜ የጠመንጃና የሙስና ባላዎች ከስራቸው ተነቅለው መውደቃቸው የማይቀር ነው:: ጠመንጃና ሙስና ተሸነፉ ማለት ደግሞ የሕወሓት እግርና እጅ ሊጠገን በማይችልበት ሁኔታ ወላልቆ ወደቀ ማለት ነው::

የሕወሓት ሕልውና አጀማመርና አጨራረስ በአጭሩ ይኸንን ይመስላል ቢባልም ነገሩ ሁሉ በወረቀት ላይ እንደሚቀርበው ቅልብጭ ያለና ቀላል አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ሕወሓት ከበረሃ ተነስቶ እስከ አራት ኪሎ ለመድረስ በፈጀበት 17 ዓመታት ውስጥ ስንት ጊዜ መልኩንና ባህርይውን ሲለዋውጥ እንደከረመ የሚታወቅ ነው:: በመላው አለም ካለው መልካም ነገር ሁሉ የበለጠ ለማድረግ ልዩ አቅምና ችሎታ አለኝ እያለ የተስፋ ዳቦ ለማጉረስ ያላደረገው ጥረት አልነበረም:: በተቃራኒው አራት ኪሎ ከገባ ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በመላው አለም ካለው መጥፎ ነገር ሁሉ የበለጠ ለማድረግ አቅምና ችሎታ እንዳለው በተግባር እያሳየ ነው::

የሕወሓትን የበረሃ ትግልና የመንግስት ስልጣን በሚመለከት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው አመለካከት ሁልጊዜም በስጋትና በጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ መሆኑ የታወቀ ነው:: አሁን ደግሞ ስጋቱንና ጥርጣሬውን ተጨባጭ የሚያደርጉ ከበቂ በላይ ማስረጃዎችን ስለጨበጠ ከዚህ አገዛዝ ለመገላገል በሚያስችል ትግል ውስጥ ገብቶ በተለያየ ደረጃ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው:: ትግሉ ውስብስብና አስቸጋሪ ቢሆንም በሕዝቡ አሸናፊነት እንደሚጠናቀቅ ደግሞ የታመነ ነው:: ለሕዝቡ ትግል አሸናፊነት መተማመኛው ደግሞ ምኞትና ባዶ ተስፋ ሳይሆን በሰላማዊ የትግል ስልት የተቃኘና የተደራጀ ተከታታይ ትግል ማድረግ ነው::

# 7. ሠላማዊ ትግልና ዴሞክራሲ

በዴሞክራሲና በሰላም መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዳለ የታወቀ ነው:: ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ ዘላቂ ሰላም እንደማይኖርም ግልፅ ነው:: በጭቆናና በአፈና ላይ የተመሰረተ አገዛዝ እስካለ ድረስ ጥላቻ ቂምና በቀል እየተኮተኮቱ ማደጋቸው የማይቀር ነው:: እነዚህ ጠንቆች እስካሉ ድረስ ሰዎች በመካከላቸው በሚፈጥሩትም ሆነ ከመንግስትና ከሌሎች ፖለቲካዊ ኃይሎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት መተማመን ሊፈጠር አይችልም:: አለመተማመንና ጥርጣሬ ስር እየሰደደ ሲሄድ ደግሞ ሁከትና ብጥብጥ ይከተላል:: እነዚህን ሁሉ ዘርቶ የሚያበቅላቸው ደግሞ በጭቆናና አፈና ላይ የተመሰረተ አገዛዝ ነው:: የዴሞክራሲ ስርዓት የሚያስፈልገው ለጥላቻ፣ ለቂም በቀል፣ ለብጥብጥና ለጦርነት መከሰት ዋነኛ ምንጭና መሰረት የሆነው የጭቆናና የአፈና አገዛዝ እንዲወገድ ነው::

ዘላቂ ሰላም የሚኖረውም በጭቆናና አፈና ምትክ ሀቀኛ ዴሞክራሲ ሲመሰረት ብቻ ነው:: ስለዚህ የዘላቂ ሰላም መሰረትና ዋስትና የዴሞክራሲ ስርዓት ነው:: ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ ዘላቂ ሰላም የለም የሚባለውም ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት ነው::

የሠላም መኖር ደግሞ በተራው የዴሞክራሲ ስርዓት ጥልቀት እንዲያገኝ፣ የማያቋርጥ ልማትና ብልፅግና እንዲረጋገጥ አስፈላጊ ሁኔታ ነው:: ዴሞክራሲ የሰላም መሰረትና ዋስትና እንደሆነ ሁሉ ሰላምም ለዴሞክራሲ ማበብና ስር መስደድ አስፈላጊ ሁኔታ ነው:: የማይናወጥ ሰላም ካለ ዘላቂ ለሆነ ልማትና እድገት የሚያመች ዴሞክራሲ በማይቀለበስ መንገድ እንዲተከል የሚያስችል አንድ ተፈላጊ ሁኔታ ተሟልቷል ማለት ነው::

በዚህም የተነሳ በዴሞክራሲና በሰላም መካከል ያለው ግንኙነት አንዱ ለሌላው መሰረትና ዋስትና በመሆኑ ወይም የአንዱ ዘላቂነትና አስተማማኝነት በሌላው መኖር የሚጋገጥ በመሆኑ ወይም የአንዱ ዘላቂነትና አስተማማኝነት በሌላው መኖር የሚረጋገጥ በመሆኑ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ይልቁንም አንዱ ከሌላ ሌላኛው ከነአካቴው የሚኖርበት እድል የተዘጋ መሆኑም እንደዚሁ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ዴሞክራሲ ሳይኖር የሚፈጠር ሰላም ካለ እውነተኛ ሰላም ሳይሆን ለአፈናና ጭቆና ሽፋን ሆኖ የሚገለግል የገገዎች ሰላም ብቻ ነው። በሌላ በኩል ለዘላቂነቱ አስተማማኝ ዋስትና ያለው ሰላም ሳይኖር የሚፈጠር ዴሞክራሲ ካለ እውነተኛ ዴሞክራሲ ሳይሆን ለማስመሰል ብቻ የሚያገለግል የታይታ ዴሞክራሲ ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው እውነታ ሲታይ ሀቀኛ ዴሞክራሲና ዘላቂ ሰላም እንዲኖር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የለም። በመላ ሀገሪቱ የተንሰራፋ የጭቆናና አፈና አገዛዝ በመኖሩ ዴሞክራሲና ሰላም በቀላሉ የሚኙበት ሁኔታ የለም። ዴሞክራሲና ሰላም እንዲገኙ ከአገዛዝ ጋር ወሳኝ ትግል ማድረግና ከባድ መስዋዕትነት መክፈል ይጠይቃል። ምንጊዜም ቢሆን ዴሞክራሲና ሰላም ከጭቆናና አፈና አገዛዝ ውስጥ ሊፈጠሩ ስለማይችሉ አሁን በሀገራችን ከነገሰው ጨቋኝ አገዛዝ እንደምናገኛቸው ተስፋ ልናሳድር አይገባም። ዴሞክራሲንና ሰላምን በልመናና በችሮታ እንድናገኝ መጠበቅ የአገዛዝን እድሜ ከማራዘም በስተቀር የተለየ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። ዴሞክራሲና ሰላም ከማንም የሚለመኑና በችሮታ መልክ የሚገኙ የስጦታ እቃዎች ሳይሆኑ በማንም የማይሰጡና በማንም ሊነጠቁ የማይገቡ የሰው ልጅ መሰረታዊ መብቶች መገለጫዎች ናቸው። ኢትዮጵያዊያንም ለረጅም ጊዜ ያጣናቸውና እንዲሟሉልን የምንታገልላቸው እነዚህ የሰው ልጅ መሰረታዊ መብቶች ናቸው። እነዚህን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማንም እንዲሰጠን ተስፋ ማድረግ እንደማይገባን ሁሉ ማንም እንዲነጥቀን ልንፈቅድ አይገባንም።

ኢዴፓ ሀቀኛ ዴሞክራሲና ዘላቂ ሰላም በሀገራችን እንዲኖር በቅድሚያ የጭቆናና የአፈና አገዛዝ እንዳይመለስ ሆኖ መወገድ አለበት ብሎ ያምናል። የጭቆናና አፈና አገዛዝ እንዳይመለስ ሆኖ ሊወገድ የሚችለው ደግሞ ሰላማዊ በሆነ የፖለቲካ ትግል ስልት ነው የሚል ጠንካራ አቋም አለው። ይኸንን ሰላማዊ የትግል ስልት የመረጥነው ካለበቂ ምክንያት አይደለም። አላማችን ሀቀኛ ዴሞክራሲና አስተማማኝ ሰላም በሀገራችን እንዲሰፍን በማድረግ የዘላቂ ልማትና ብልፅግና ባለቤት የሆነ ሰላማዊ ሕብረተሰብ ለመፍጠር በመሆኑ ነው። ሰላማዊ የትግል ስልት የመረጥነው ይኸንኑ አላማ ለማሳካት የተሻለው ብቻ ሳይሆን ትክክለኛው አማራጭ በመሆኑም ነው። ሰላማዊ የትግል ስልትን የምንደግፈው ሞትን ስለምንፈራ ሳይሆን ሰውን በመግደል ዘላቂ ሰላምና ሀቀኛ ዴሞክራሲ ማግኘት እንደማይቻል እርግጠኞች በመሆናችን ነው። ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆነውን ሰላም ለሀገራችን እናመጣለን የሚለውን አቋማችንን የሰውን እምነትና ልቦና የሚገዛ ትክክለኛ አስተሳሰብ እያቀረብን በምንቀዳጀው የመንፈስ ድል ካልሆነ በስተቀር ሰው እየገደልን እንደማናሳካው ስለምናምን ነው። እንዳውም ሰላማዊ የትግል ስልትን መምረጥ ከፍርሃት፣ ከድክመትና ከጥንካሬ አልባነት ጋር የሚያያዝ ሳይሆን በራስ ከመተማመን፣ ከቁርጠኝነትና ከልበ ሙሉነት የሚመነጭ መሆኑን በሚገባ ስለምናምንበት ነው።

ብዙ ሰዎች እስከአፍንጫው ጠመንጃ የታጠቀንና አፈናን እንደ ዋነኛ የስልጣን ማስጠበቂያ ዘዴ አድርጎ የሚጠቀምን አገዛዝ በሰላማዊ የትግል ስልት ለመታገል መሞከር የዋህነት ነው ብለው ያስባሉ። በአለማችን በሥልጣኔና በብልጽግና ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሀገሮች አሁን ወደ ደረሱበት ደረጃ የደረሱት ከጠመንጃ ይልቅ ለሀሳቦች ግጭትና ፍጭት ትኩረት በመስጠ ታቸው ነው። በሰለጠነው አለም እንደሚታየው በፖለቲካ ምክንያት የሚጋጩት ሀሳቦች፣ አስተያየቶችና እምነቶች በመሆናቸው ሰዎች ጠመንጃና ሰይፍ እስከመማዘዝ የሚወርዱበት

ምክንያት የለም። በእኛም ሀገር እንዲለመድ የምንፈልገው በሰለጠነው አለም ተቀባይነት ያገኘውና ውጤ ታማ የሆነው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ነው።

ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በጠመንጃ ከሚደገፍ አመፅ በመሰረቱ የተለየ ነው። ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በሀገራችን መለመድ አለበት ስንል የጠመንጃ ትግል ከሚጠይቀው መስዋዕትነትና ዋጋ በቀለለ መንገድ ውጤት ያስገኛል ከሚል ስሌት አይደለም። የጠመንጃ ትግል መስዋእትነት እንደሚጠይቅ ሁሉ ሰላማዊ ትግልም የሚጠይቀው ዋጋ አለ። ሰላማዊ የትግል ስልት ከጠመንጃ ትግል የተሻለ ነው የምንልበት መመዘኛ አነስተኛ መስዋዕትነትና ዝቅተኛ ዋጋ በማስከፈሉ አይደለም። ይልቁንም የሰላማዊ ትግል ስልት ተመራጭ የሚሆነው ከጠመንጃ ትግል ጋር ሲወዳደር የላቀ ውጤት እንዳለው ስለሚታመን ነው። በትጥቅ ትግል የሚጋጩት ሃሳቦች፣ አስተያየቶችና እምነቶች ሳይሆኑ ሰውና ሰው ናቸው። በሰዎች መካከል በሚያካሄደው አካላዊ ግጭት በሕይወትና በንብረት ላይ ከባድ ጉዳት ከመድረሱ በስተቀር አንዱ ከሌላው ለመማር የሚችልበት መንገድ የተዘጋ ነው። የጠመንጃ ትግል አንዱን ኃይለኛ በሌላ ኃይለኛ የመተካት አዙሪት ውስጥ የሚያስገባና ጡንቻን ከጡንቻ ሚያወዳድር ዘዴ እንጂ ለመንፈስ ሃይልና አሸናፊነት እድል የሚሰጥ አይደለም። ሰላማዊ ትግል ደግሞ ኃይልን በኃይል ከመተካት ይልቅ በሀሳቦች ዙሪያ በሚደረግ ክርክርና ፍጭት የሰውን እምነት የሚገዛው ሀሳብ አሸናፊ እንዲሆን የሚያስችል ነው።

በጠመንጃ ኃይል የተገኘ ስልጣን ሕጋዊነት የሌለው እንደመሆኑ ለሕግና ሕጋዊነት ቦታ አይሰጥም። የተጠላውን የጠመንጃ አገዛዝ አውርዶ ገና ማንነቱ ባልተፈተነ የጠመንጃ አገዛዝ ይተካል እንጂ የሕዝቡን ስልጣን ባለቤትነት አያረጋግጥም። በጠመንጃ ትግል የሚገኝ ውጤት በቂምና በቀል መንፈስ ለተሞሉ ሰዎች ጊዜያዊ ደስታ ከማስገኘት አልፎ አዲስ ቂምና በቀል ተዘርቶ እንዳይበቅል ሊከላከል አይችልም። በሰላማዊ ትግል የሚገኝ ስልጣን ግን በሕዝብ ፈቃድና ምርጫ የሚገኝ በመሆኑ ሕጋዊነቱና ተቀባይነቱ አጠራጣሪ ሊሆን አይችልም። የመጨረሻ ውጤቱም ቂምና በቀል እንዲያቆጠቁጡ እድል የሚሰጥ አይደለም።

የትጥቅ ትግል በመጀመሪያው የፍልሚያ ወረዳ የሚያሰልፈው መሪዎቹን ሳይሆን ተከታዮቹንና ደጋፊዎቹን ነው። መሪዎቹ ከማንም በላይ ግንባር ቀደም ሆነው የሚሰለፉት ከድል በኋላ የሚገኘውን የስልጣን መንበር ለመያዝ ብቻ ነው። በሰላማዊ ትግል ደግሞ በትግሉ ግንባር ቀደም ስፍራ ቀድመው የሚገኙት መሪዎቹ እንጂ የትግሉ ተከታዮችና ደጋፊዎች አይደሉም። ተከታዮችና ከደጋፊዎች የሚጠበቀው የመሪዎቹን አርአያነት እየተከተሉ የማያቋርጥ ድጋፍ መስጠትና በተለያየ ዘዴ ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ መንቀሳቀስ ነው።

በትጥቅ ትግል ወሳኙ ኃይል ጠመንጃ በመሆኑ ለሕዝብ ተጠያቂነትና ኃላፊነት የለም። በሰላማዊ ትግል ደግሞ ወሳኙ ኃይል ራሱ ሕዝቡ ስለሚሆን ለሕዝብ ተጠያቂነትና ኃላፊነት እንዲኖር የሚያስገድድ ሃይል አለው። የጠመንጃ ትግል የተገነባን በማፍረስና ለልማት የሚደረግን ጥረት በማዳከም ሁልጊዜ ከዜሮ ለመጀመር የሚያስገድድ ነው። ሰላማዊ ትግል ደግሞ አንዱ ትውልድ በጣለው በጎ መሰረት ላይ ሌላው ትውልድ እየገነባ በእድገት ጎዳና ወደፊት ለመጓዝ ስለሚረዳ ሁልጊዜ ከዜሮ የሚጀመርበትን የእድገት አዙሪት የሚበጥስ ነው። የትጥቅ ትግል አካሂዶ የሕዝብ የስልጣን ባለቤትነትን ማረጋገጥ የማይታለም እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን ከእኛ ሀገር የተሻለ ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም። የሕወሓት መሪዎች ለሕዝብ ስልጣን አንሰጥም ብለው ከሚያቀርቧቸው መከራከሪያዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የፖለቲካ ሥልጣንን የደም ካሣ አድርገው የሚመለከቱበት ሁኔታ ነው «በትጥቅ ትግል ያገኘነውን ሥልጣን ለማንም አሳልፈን አንሰጥም» በሚል የሕዝቡን ሥልጣን ርስታቸው አድርገው መቀመጥን የመረጡት በትግሉ ወቀት ለፈሰሰው ደምና ለጠፋው ሕይወት የተከፈላቸው ካሣ

እንደሆነ አድርገው በመውሰድ ነው። የሕዝብ ስልጣን ባለቤትነት ይረጋገጣል በሚል ተስፋ ከፊት ለፊት እየቀደመ ራሱን እንደሚፍ ያቀለጠው ህዝብም ሆነ ከጦርነት በህይወት የተረፈው ህዝብ ያገኘው ውጤት ቢኖር በቀድሞው የጠመንጃ አገዛዝ ከደረሰበት የአካል ጉዳትና የመንፈስ ስብራት ሳያገግም ወደ አዲስ የጠመንጃ አገዛዝ መሸጋገር ብቻ ነው። ያ ሁሉ ድካምና መስዋዕትነት ያስገኘው ውጤት «ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁ» ከሚባለው አነጋገር የማይለይ በመሆኑ እንደገና ከአዲሱ ባለጠመንጃ ጋር ለመጋፈጥ ለሌላ መስዋዕትነት እየተዘጋጀ ነው።

ከዚህ በኋላ ጠመንጃን በጠመንጃ ከመተካት አዙሪት ወጥተን በሀገራችን ሀቀኛ ዴሞክራሲና ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ማድረግ ካለብን ትግሉ በጠመንጃ ሳይሆን በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል መካሄድ ይኖርበታል ብለን እናምናለን። ያለጠመንጃ ኃይል ሀሳቦችና አስተያየቶች ብቻ ተፋጠውና ተጋጭተው በነፃ ፍትሐዊ ምርጫ ሕዝቡ የደገፈው ወደ ፖለቲካ ስልጣን የሚወጣበት፣ የሕዝቡን ፈቃድ ያላገኘው ደግሞ ከስልጣን የሚወርድበት አልያም ለሌላ ዙር ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ውድድር እራሱን የሚያዘጋጅበት የሰለጠነ የስልጣን ሽግግር ባህል በሀገራችን ሊገነባ የሚችልበት የተሻለ አማራጭ ሰላማዊ የሆነ የፖለቲካ ትግል ነው ብለን እናምናለን። እንደእኛ በድህነትና በረሃብ የሚጠበስ ሕዝብ፣ በመብት ረገጣና በአስከፊ ጭቆና ስር ወድቆ የሚማቅቅ ሕዝብ፣ ወንድማማችነትና ዝምድና ቀርቶ ላቻና ቂም በቀል እንዲነግሱ የሚያደፋፍር ዘረኛ አገዛዝ የተጫነበት ሕዝብ፣ ታሪካዊ አንድነቱን ሉዓላዊነቱ እየተሸራረፉ ሕልውናው አደጋ ላይ የወደቀ ሕዝብ፣ መተማመን እንዲጠፋና ርጣሬ እንዲስፋፋ በሚደረግ ፖለቲካዊ ግፊት ለማያባራ የእርስ በርስ ግጭት የተጋለጠ ሕዝብ ከዚህ አስከፊ ሁኔታ መውጣት የሚችለው አገዛዝን በዴሞክራሲ በመተካት ብቻ ነው። ዴሞክራሲ ማለት ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት ሆኖ የፈለገውን መርጦ የሚሾምበትና ያልፈለገውን የሚሽርበት ስርዓት ማለት ነው። እንዲህ አይነቱን ስርዓት መገንባት የሚቻለው ደግሞ ጠመንጃን በጠመንጃ በመተካት ሳይሆን በሰላማዊ ትግል ነው። በሰላማዊ ትግል የሚገነባ ዴሞክራሲ አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂ ልማት እንደሚያመጣ በንድፈ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የተረጋገጠ ነው። በመሆኑም ከእስከዛሬው ጦረኛ ባህላችን ወጥተን ሰላማዊና ሕጋዊ የሥልጣን ሽግግር እንዲኖር ዋስትና ወደሚያስገኝልን ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል መግባት ይገባናል።

ሰላማዊ ትግል ውጤት የሚያስገኘው አስፈላጊነቱን ከልብ ተቀብለን ትግሉ የሚጠይቀውን የመስዋዕትነት ዋጋ ለመክፈል ቁርጠኝነት ሲኖረን ነው። ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል መቻቻልን፣ መግባባትን ማመዛዘንን ሆደሰፊነትንና ብስለትን የሚጠይቅ ከባድ ትግል ነው። እርስ በርስ ለመማማር፣ የጎበጠውን ለማቃናት፣ የጎደለውን ለማሟላት እድል የሚሰጥ በመሆኑ ይኸንን ጠቃሚ ጎኑን በብልሃት የመጠቀም ስልት ይጠይቃል። አገዛዝን በመፀየፍና በማጥላላት ብቻ ሳይወሰኑ እምቢተኝነትን በተግባር ማሳየት ይጠይቃል። የራስን መብት ከማስከበር አልፎ ለሌሎች እኩልነት፣ ፍትህና ነፃነት፣ ሰብዓዊ ክብር መረጋገጥና በአጠ ቃላይም ለተሟላ ሰላም መስፈን ሲባል መስዋዕትነት መክፈል ይጠይቃል። ለአገዛዝ እየተንበረከኩ በደልና ጥቃትን ተሸክሞ ላለመኖር ሲባል በአገዛዝ ላይ የተቀናጀ ተቃውሞ ማቅረብና ውጤታማ ተፅዕኖ ማሳረፍ ይጠይቃል። እንደ ተጨባጩ ሁኔታ ተስማሚ የሆነውን ሰላማዊ የትግል ስልት እየመረጡ በተገቢው ጊዜ፣ ፍጥነት፣ ብቃትና ደረጃ ጥቅም ላይ ማዋል ይጠይቃል።

## 7.1 የሰላማዊ የትግል ስልት ልዩ ልዩ አማራጮች

የሠላማዊ ትግል ዋነኛ ግብ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቹ የተረጋገጡትና ለዘላቂ ልማት ዋስትና የሚሆን አስተማማኝ ሰላም የተሟላለት ሕብረተሰብ እንዲኖር ማድረግ ነው። ይኸንን

ግብ ለማሟላት ሰላማዊ ትግል አንድ ወጥ በሆነ ዘዴ ብቻ መመራት አለበት ማለት አይደለም። እንደትግሉ ስፋትና ጥበት፣ ተጨባጩ ሁኔታ እንደሚጠይቀው ብቃትና ዝግጁነት፣ ትግሉ እንደሚፈልገው ስክነትና ፍጥነት፣ ወዘተ. የተለያዩ አማራጭ ዘዴዎች በተናጠልም ሆነ በቅንጅት መጠቀም ይገባል። ከሚለወጡ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣሙ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን፣ አቀራረቦችንና የአሰራር ቅደም ተከተሎችን አዘጋጅቶ መጠቀም ያስፈልጋል። ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች እጅግ በርካታ ከመሆናቸውም በላይ እንደሁኔታው ሊቀያየሩ ስለሚችሉ ሁሉንም እዚህ ላይ መዋቀስ ባያስፈልግም ጥቂት አብነቶችን ብቻ በማንሳት የአማራጮችን ስፋት ለመገንዘብ ይቻላል።

## 7.2 ሕዝብን ለሰላማዊ ትግል ማዘጋጀትና አደራጅቶ ማንቀሳቀስ

በፍትህ አልባ ስርዓት ላይ በሚደረግ ሰላማዊ ትግል የመጀመሪያው እርምጃ ለአገዛዝ የተጋለጡት ወገኖች ስለራሳቸው መብት በድፍረት እንዲከራከሩና ያሉበትን ሁኔታ በጥልቀት እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። ከእንዲህ ዓይነቱ የማዘጋጀት እርምጃ ቀጥሎ ለሚመጣው ሕዝብን የማደራጀትና ለለውጥ የሚንቀሳቀስ ተግባር ንቁ መንፈሳዊ አቅም እንዲኖር ለሚያስችለው ሰፊ ሂደት እንደመጀመሪያ እርምጃ ተደርጎ የሚታይ ነው። በሕዝቡ ውስጥ የመንፈስ መነቃቃትና ዝግጁነት ከመፍጠር ጎን ለጎን በተከታታይ መሰራት የሚገባው ስራ ሕዝቡን ለሰላማዊ ትግል ማንቀሳቀስ ነው። ሕዝቡን ለማንቀሳቀስ ደግሞ ከመንፈስ ዝግጁነት በተጨማሪ አስፈላጊ የሆነውን ድርጅት መመስረት ይገባል። ለሰላማዊ ትግል የመንፈስ ብቃትና ዝግጁነት ያለው ሕዝብ ተደራጅቶ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ገዥዎች በሚያሳድሩበት ተፅዕኖና ጥቃት ፊት የተቀናጀና የማይታጠፍ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አቅም፣ እምነትና ቁርጠኝነት ይኖረዋል። ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ጥያቄ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ የሚያበቃ የመንፈስ ዝግጁነትና የተደራጀ አቅም የፈጠረ ሕዝብ ለትግሉ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ምን አይነት ስልቶችን ተግባራዊ ያደርጋል? የሚለው ነው።

## 7.3 ፍትህ አልባነትን ለማጋለጥ የሚያስችል ውይይትና ክርክር ማድረግ

በተቀላጠፈ ሰላማዊ ትግል ውስጥ ክርክር መጀመሪያና መጨረሻ ሆኖ ሊመጣ ይችላል። ከአገዛዝ ጋር ፊት ለፊት የሚደረግ ክርክር ከመጀመሩ በፊት በሕዝቡ ውስጥ በርካታ የውይይት መድረኮች እንዲዘጋጁና በፍትህ አልባነት ላይ የሚነጣጠሩ ፈታኝ ጥያቄዎች በየመድረኩ እንዲነሱ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህም አማካይነት ሕዝቡ በሞራል፣ በቁጥር፣ በፖለቲካ፣ በፋይናንስ ወዘተ. ያለው ኃይል እንዲቀናጅና ከጥያቄዎቹ ጋር በተያያዘ መንገድ በአገዛዝ ላይ ጠንካራ ጫና እንዲያሳርፍ በማድረግ ለለውጥ የሚያስፈልገውን ግፊት አጠናክሮ መሳለፍ ይቻላል።

በዚህ መንገድ ከገዥዎች ጋር ክርክር ለመጀመር የሚረዳ የኃይል አሰላለፍ ግንኙነት ለውጥ እንዲኖር ማድረግ ይገባል። ይህ ምቹ ሁኔታ ሲፈጠር ገዥዎች ከሕዝብ የሚነሳባቸውን ተቃውሞ ትክክለኛነት እንዲያምኑበትና ተገቢ ምላሽ እንዲሰጡበት የተቃውሞ ሀሳቦችን ፊት ለፊት እያቀረቡ መከራከር ያስፈልጋል። በእርግጥ ከአገዛዝና ከጭቆና የሚጠቀሙ ክፍሎች ጥቅማቸውን አሳልፎ እንደመስጠት ስለሚቆጥሩትና ስልጣናቸውን የመነጠቅ ስጋት ስለሚያድርባቸው ለክርክር የተዘጋጁና ፈቃደኝነት ያላቸው ሊሆኑ አይችሉም። እንዲህ አይነቱ ችግር ሲያጋጥም እንደ ትግሉ ደረጃና እድገት ስልጣን ላይ ያሉትን ገዥዎች ለመጋፈጥ የተለየ መልክ ያላቸውን ሰላማዊ እርምጃዎች ከሕዝቡ ጋር ሆኖ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል።

ከእነዚህ ሰላማዊ ዘዴዎች መካከል ፔቲሽን አሰባስቦ መላክ፣ ተቃውሞን ለመግለፅ የሚደረግ ሕዝባዊ ስብሰባ መጥራትና ሕዝባዊ ተቃውሞ ሰልፍ ወይም ጉዞ ማዘጋጀት፣ የስራ ማቆም አድማ መምታት፣ የረሃብ አድማ ማድረግ፣ የመገናኛና ትራንስፖርት ግንኙነትና እንቅስቃሴ እንዳይኖር የሚያስችል እገዳ (ማዕቀብ) መጣል፣ የአገዛዝን ገመናዎች የሚያጋልጡ በአንፃሩ የሰውን ሰብዓዊና ዴክራሲያዊ መብት ለማስከበር የሚያግዙ ሌሎች አብነታዊ (ምሳሌያዊ) ተግባሮችን መፈፀም፣ በገዥዎች አማካይነት ለብክነት ወይም ለአደጋና ለከባድ ጉዳት እንደተጋለጠ የሚታመንበትን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ወይም ማህበራዊ ተቋም እየተቆጣጠሩ እውነቱ ለሕዝብ እንዲወጣ ማድረግ፣ ሀገርንና ሕዝብን ይጎዳሉ ተብሎ በሚታመንበት ማንኛውም ተግባር ላይ ራሱን ከተሳትፎ ማግለል፣ በአገዛዝ ላይ ሲቪል እምቢተኝነትን ማሳየት፣ ከገዥዎች ጋር በተለያዩ መድረኮችና አጋጣሚዎች መከራከር፣ ወቅታዊ መግለጫዎችን በመገናኛ ብዙሃን አማካይነትና በቀጥታ ለሕዝቡ ማቅረብ፣ የተቃውሞ መግለጫዎችን በፅሑፍና በቃል ማሰራጨትና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በመሰረቱ ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች በዓይነትም ሆነ በብዛት በርካታ በመሆናቸው ሁሉንም በዚህ ፅሁፍ መዘርዘር ተገቢና አስፈላጊም አይደለም፡፡ የትኛው ሰላማዊ የትግል ስልት ለየትኛው ጥያቄ እንደሚስማሙ፣ መቼና በምን ቅደም ተከተል ተግባራዊ እንደሚሆን፣ ለአንድ ጥያቄ የተለያዩ ስልቶችን በተናጠል ወይንም በቅንጅት መጠቀም እንደሚያስፈልግ ወዘተ. የሚወሰነው በትግሉ ባህርይ፣ ደረጃና አላማ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ዘዴዎች ተጠቅሞ ሰላማዊ ትግል ማድረግ ዞሮ ዞሮ አላማው አንድ አይነት ነው፡፡ ይኸውም አገዛዝ የሚያደርሰውን ጭቆና ታግሎ በማሸነፍ የዜጎችን መብትና ነፃነት ማረጋገጥ ነው፡፡ እነዚህ የተለያዩ ሰላማዊ የትግል ዘዴዎች ውጤት የሚያስገኙትና በገዥዎች ዓይን ዋጋና ክብደት ሊሰጣቸው የሚችሉት በተደራጀ መንገድ፣ በተጠና ስልትና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ጥቅም ላይ ሲውሉ ነው፡፡ በአገዛዝ ላይ ትርጉም ያለው ተፅዕኖ ለማሳረፍ በማያስችል፣ በተበታተነና ተከታታይነት በሌለው ያልተጠና ስልት ተግባራዊ እንዲሆኑ ሲደረግ የሕዝቡን የትግል ስሜት የማቀዝቀዝና ተስፋ የማስቆረጥ አፍራሽ ውጤት ይኖራቸዋል፡፡ እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ደግሞ የአገዛዝ እድሜ እንዲራዘም አስተዋፅኦ ስለሚደርግ በከፍተኛ ብስለትና በተጠና ሁኔታ ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

## 7.4 ገንቢ የሆነ አማራጭ ፕሮግራም ማቅረብ

የጭቆና አገዛዝ የሚጠቀምባቸውን ፍትህ አልባ ሕጎችና ስርዓቶች ማውገዝም ሆነ ማስወገድ ብቻውን እንደመጨረሻ ግብ የሚቆጠር አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገር ተቃውሞ በሚቀርብበትና በትግል በሚወገደው ፍትህ አልባ ስርዓት ምትክ የሚቀርበውን አማራጭ ስርዓትና የመፍትሔ አቅጣጫ አዘጋጅቶ ይፋ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለነፃነትና ለመብት መረጋገጥ የሚደረገው ትግል የተሻለ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውጤት ሊያስገኝ በሚችል አማራጭ ፕሮግራም ካልታጀበ ሕዝቡን ለተቃውሞ ማነሳሳት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ሕዝቡ በሚቃወመው ምትክ ምን እንደሚፈልግ በማወቅ ተቀባይነት ያለው አማራጭ ፕሮግራም ማቅረብና ለዚህም ተፈፃሚነት መታገል ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ሰላማዊ ትግል የማድረግ ሀሳብ ማቀፍ ያለበትን የፖለቲካ ለውጥ እርምጃዎችን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋ በማህበረሰቡ ደረጃ ገንቢ ድርጊት ለመፈፀም የሚያስችሉ የግል ኃላፊነቶች እንዳሉበት ሊያስገነዝቡ የሚችሉ ማህበራዊ ግዴታዎችንም ጭምር መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም በሚወገደው ምትክ መቅረብ ያለበት አማራጭ ፕሮግራም የዜጎችን የግልና የጋራ ኀላፊነቶች በሚገባ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡

*በሠላማዊ ትግል አመራር ግንባር ቀደም ምሳሌ ከሆኑት መካከል አንዱ የሆነው ማህተመ ጋንዲ ሰላማዊ የትግል ዘዴን አስመልክቶ ካቀረባቸው በርካታ ነጥቦች የተወሰኑትን እዚህ ላይ መጥቀስ ተገቢ ነው። እንደጋንዲ እምነት አንደኛ ሰላማዊ ወደ ሆነ ግብ ለመድረስ ሰላማዊ ያልሆነ የትግል ስልት መጠቀም ሀገርን ለማዳን ሲባል ሀገርን ማጥፋት ይሻላል ብሎ ለማሳመን እንደመሞከር የሚቆጠር ነው። በአመፅ የሚገኘው ውጤት የፈለገውን ያክል የተቀደሰና የተወደደ ቢሆንም እንኳ የአመፅን መጥፎነት ሊያስቀረውና አመፅን የተወደደ ሊያደርገው አይችልም። በመሆኑም ሰላማዊ ሕብረተሰብ ለመፍጠር ትክክለኛው መንገድ ሰላማዊ የትግል ዘዴን መጠቀም ነው። ሁለተኛ የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት ሲባል አመፅን እንደ ስትራቴጅ በመጠቀም መፍጠር የሚቻለው በአመፅ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ስርዓት ነው። ይኸውም አመፅ የሚወልደው አመፅን ነው እንደማለት ነው። በሰላም ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ስርዓት ለመመስረት ከተፈለገ ከአመፅ የተለየ ስትራቴጂ መኖር አለበት። ሶስተኛ በትግል ስልትና በትግል ውጤት መካከል ያለው ግንኙነት ሜካኒካዊ የሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ተደርጎ መታየት የለበትም። በትግል ስልትና ውጤት መካከል ያለው ግንኙነት በዘርና ከዚሁ በበቀለው ዛፍ መካከል እንዳለው ግንኙነት ተፈጥሯዊ ነው። ይኸውም አመፅን ዘርቶ ሰላምን ማጨድ አይቻልም እንደማለት ነው።*

*ሰላም የሚገኘው በሰላማዊ ትግል ሲሆን ከአመፅ የሚወለደው ደግሞ አመፅ ብቻ ነው። አራተኛ የትግል ዘዴያችን ራሱ በትግሉ ውጤት ማግኘት እንደምንፈልገው አይነት ሀቀኝነትን የተላበሰ መሆን አለበት። በሸፍጥና መሰሪነት የተሞላ የትግል ዘዴ እየተጠቀሙ ሀቀኛ የሰላም ውጤት ለማግኘት አይቻልም። በትግሉ ውጤት እንዲመጣ የሚፈለገው ሰላም ሀቀኛ ሰላም ሊሆን የሚችለው የትግሉ ዘዴ ራሱ ሀቀኛ ሲሆን ብቻ ነው።*

*ኢዴፓም እነዚህን የጋንዲ እምነቶች ይጋራል። በፓርቲያችን አመለካከት አመፅን እንደትግል ዘዴ የመረጠ ሕብረተሰብ የአመፅን ስርዓት ለመሸከም በራሱ ፈቃድ ውሳኔ እንዳደረገ ይቆጠራል። ከራሳችን ሀገር ልምድ በተጨባጭ የታየውም ይኸው ነው። የሕወሓት አመፅ ሕወሓት/ኢህአዴግ የሚለውን የአመፅ ሥርዓት ወለደ። ሕወሓት የአመፅ ውላጅ በመሆኑ ሰላማዊ የፖለቲካ ስርዓት ለመመስረት እንዳልቻለ ሁሉ ሕወሓትን በአመፅ ለመለወጥ የሚደረግ የአመፅ ትግልም አመፅን በአመፅ ከመተካት የተለየ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም።*

*ሰላማዊ ትግል የራሱ ሕጎችና መመሪያዎች ያሉት ሲሆን እነዚህን ለመከተልና ተግባራዊ ለማድረግ ካልተቻለ ውጤታማ መሆን አይታሰብም። ከሰላማዊ ትግል መሰረታዊ ሕጎች መካከል የመጀመሪያው ተቃውሞን ማጥፋት አይገባም የሚል ነው። ተቃውሞን በጥላቻ መመልከትም ሆነ ተቃዋሚዎችን በጠላትነት መፈረጅ የሰላማዊ ፖለቲካ ስርዓት ባህርያት ሳይሆኑ የአመፅ ስርዓት መለያዎች ናቸው። ሁለተኛው ውሣኔ ሕግ የመወሰን ችሎታ ይኑርህ መወሰን የሚገባህንም ጉዳይ በፍጥነት ወስን የሚል ነው። አንድ ጊዜ ውሳኔ ላይ ከተደረሰና የውሳኔውም ይዘት ከታወቀ በኋላ በዚሁ ላይ የተመሰረተ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ከማድረግ መቆጠብ አይገባም። ስትራቴጂውን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የሚያጋጥመውን ችግር እንደየአመጣጡ መጋፈጥ እንጂ ማመንታት አስፈላጊ አይደለም። ሶስተኛው ሕግ ደግሞ ተቀናቃኝህን ዘላለማዊ ጠላት አድርገህ ሳይሆን የወደፊቱ አጋር እንደሚሆን አድርገህ ተመልከተው የሚል ነው። ተቀናቃኝህን ሆን ብለህ ለመጉዳትና ለማራቅ በማሰብ አንድም ነገር ማድረግ አይገባም። ግብህ ትግሉን የማጠናከር እንጂ አንዱን እየጠለፉና ሌላውን እየደገፉ ለመነጣጠል እንዳልሆነ አስታውስ የሚል ነው። አራተኛው ሕግ የትግል ታክቲክህ ከትግሉ ግብ ጋር የተጣጣመ መሆኑን እርግጠኛ ሁን። የሚቻል ሆኖ ሲገኝ የትግሉን ግብ እንደትግል መሣሪያ ተጠቀምበት። የማይቻል ሲሆን ደግሞ ከግቡ ጋር የተጣጣሙ የትግል ዘዴዎችን ብቻ ጥቅም ላይ አውላቸው የሚል ነው። ስድስተኛው ከሚለዋወጡ ሁኔታዎች ጋር የሚስማማ ለውጥ የማድረግ ፈጣን ችሎታ ይኑርህ። ቴክኒክህን እንደተጨባጩ ሁኔታ*

*ለመቀያየር ፈቃደኛ መሆን አለብህ። አስፈላጊ ከሆነ የቅርብ ጊዜ ግብህን ለመቀየር ድፍረት ይኑርህ፣ ስለተቀናቃኞችህ ማንነት ያለህን አስተሳሰብ እንደ ተጨባጩ ሁኔታ ከልሰው። የዛሬው ተቀናቃኝ ለነገ አጋር ሊሆን እንደሚችልና የዛሬው አጋር ለነገው ተቀናቃኝ ሊሆን እንደሚችል ግምት ስጥ የሚባል ነው። ሰባተኛው መርህ ራስህን የመቆጣጠርና የመግዛት ችሎታ ይኑርህ። ተግባራዊ ጥረትህ ደረጃ በደረጃ እድገትና ፍጥነት እየጨመረ እንዲመጣ አድርገው። በአንዴ እመርታ የማሳየት ሙከራ ውጤቱ አስተማማኝ ላይሆን ስለሚችል ደረጃውን የጠበቀ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ብልህትና ትዕግስት እንዲኖርህ ያስፈልጋል። ተቀናቃኝህ እንደምትዝትበትና ጉዳት እንደምታስከትልበት ካለው ስጋት እንዲጠበቅና ለአንተ አፀፋውን በመመለስ ራሱን እስከመጨረሻው ለመከላከል በመሞከር ፋንታ በግልጽነት እንዲቀርብህና ለውይይት በር እንዲከፈት እድሉን አትዝጋበት። ስምንተኛ የትግል እንቅስቃሴህን የመመጠን ችሎታ ይኑርህ። የትኛው ጉዳይ እንደተራ ነገር ሊታይ እንደሚችል፣ የትኛው ደግሞ በቂ ጊዜና ጉልበት ተመድቦለት በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ አመዛዝነህ ወስን። ከተቀናቃኝህ እኩል ጥንካሬ ያለውና እንደውም የበለጠ ጥራትና ብቃት ያለው የትግል እንቅስቃሴ አደራጅተህ ተግባራዊ አድርግ። ዘጠነኛ ዲስፕሊን ይኑርህ። የአቋም አንድነት አንዱ የጥንካሬ መለኪያ እንደመሆኑ መሰረታዊ አቋምህ የማይናወጥ መሆን አለበት። በተለይም የጋራ ጥረት ለማድረግ በርካታ ቁጥር ያለው ኃይል አንድ ላይ በሚሰለፍበት ጊዜ ካንተ ወገን ለሰላም ያለህን ቁርጠኝነት ማረጋገጥ ይገባል። አስረኛ አንድ አይነት የትግል ዘዴ መቼ ሊቋረጥ (ሊቆም) እንደሚገባው የማወቅ ችሎታ ይኑርህ። ውጤት አልባ የሆነ ወይንም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል እንቅስቃሴ ታክቲክህን እንድትከልስ ምን አልባትም የአጭር ጊዜ ግብህን እንደትቀይር የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ ይኸንኑ አድርግ። ከመርህ ጋር የማይስማማ ማካካሻ ማድረግ ድል ሊሆን ስለማይችል የምታደርገው የታክቲክ ክለሳ መሰረታዊ መርህ የማያፋልስ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብሃል። በትግሉ ሂደት አሸናፊ ሆነህ ድል እንዳገኘህ መናገር የምትችለው ተቀናቃኝህ አንተ ከምትለው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነገር መናገር ሲችል መሆን አለበት የሚል ነው።*

*ኢዴፓ እነዚህን የሰላማዊ ትግል ሕጎች ይጋራቸዋል። ፓርቲያችን በሰላማዊ ትግል የሚገነባ ሰላማዊ ሕብረተሰብ መፍጠር የሚፈልገው ሰላም የሚያስገኘውን መልካም ነገር ሁሉ ለብቻው ለመጠቀም ሳይሆን የሰላምን በረከት ሁሉም እንዲያገኝ በመሻት ነው። ስለሆነም የሰላምን በረከት በጋራ ለማግኘት እንድንችል በብሔራዊ እርቅ መንፈስ የትግል ትብብር ፈጥረን አገዛዝን ለመጣልና ሰላማዊ የፖለቲካ ስርዓት ለመመስረት በጋራ መቆም አለብን።*

# 8. ለውጤታማ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ህብረት የኢዴፓ የመፍትሄ ሃሳቦች

*መንግስትን የሚቀናቀኑ ፓርቲዎች በሃገራችን መቋቋም ከጀመሩ ከ30 ዓመት በላይ መሆኑ ነው። በ1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ በርካታ ፓርቲዎች በይፋ በፓለቲካ ትግሉ ተሣታፊዎች የነበሩ ቢሆንም ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በሚያግዝ መልኩ መቀጠል አልቻሉም። የፖለቲካ ትግሉ መስመሩን ስቶ ዜጐችን ወደ እርስ በርስ መጨፋጨፍ ያስገባ ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ ከፖለቲካ ትግል እርቃ ለ17 ዓመት በወታደራዊው የደርግ መንግስት አገዛዝ ስር በመማቀቅ በርስ በርስ ጦርነት ለመታመስ ተገዳለች።*

*የደርግ መንግስት ወድቆ የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስት በጠበንጃ ኃይል ወደ ስልጣን ለመውጣት ከበቃም በኋላ የአለም ተጨባጭ ሁኔታ በፈጠረው አስገዳጅነት ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ፓርቲዎች ተቋቁመው ለመንቀሣቀስ ውስን እድል ቢያገኙም ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሚጫወቱት ሚና ብዙም ሚዛን የሚደፋ አልሆነም። በፓርቲዎች መካከል*

የሚካሄደው ትግል ከአፈና፣ ከዘረኝነት ፣ከጥላቻ፣ ከፍጥጫ፣ከሸኩቻና ከተለያዩ ተፅኖዎች ነፃ ሆኖ እውነተኛ የፖለቲካ ትግል መሆን አልቻለም። በዚህም ምክንያት ዛሬ ሃገራችን ኢትዮጵያ የመልካም አስተዳደር ባለቤት መሆን ካለመቻልዋም በላይ ከዚህ ችግሯ የምትላቀቅበት ወቅትም የቀረበ መስሎ አይታይም።

በሃገራችን በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስታዊ ኃይል ሃገሪቱን በብቃት ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ መምራት ባልቻለበት በአሁኑ ወቅት የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ኃላፊነቱ በዋናነት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚጠበቅ ቢሆንም ተቃዎሚዎች (ኢዴፓን ጨምሮ) የወቅቱ ትግልና ህዝቡ በሚፈልገዉ መጠን ጠንካራ ሆነው መገኘት አልቻሉም።

በአሁኑ ወቅት በሃገሪቱ የምንገኝ ተቃዋሚዎች የሚፈለገውን ያህል ጠንካራ መሆን ያልቻልነውን በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው ማለት ይቻላል። የመጀመሪያው በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከውጭ ሃገር መንግስታት ብድርና እርዳታ ለመቀበል ሲል ከማስመሰል በስተቀር የብዙሃን ፓርቲዎችን መኖር ገና ከልቡ ያልተቀበለና ተቃዎሚዎችን እንደጠላት የማየት ፀረ- ዴሞክራሲ ባህሪ ያለው በመሆኑ የተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴ ለማዳከም ከተለያዩ ጥቃቅን እንቅፋቶች ጀምሮ ግድያ አስከመፈፀም የሚደርስ ተፅዕኖ የሚያሣድር መሆኑ ነው። ሁለተኛው ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ በሰላማዊ መንገድ ተደራጅቶ አምባገነናዊውን ስርዓት የመታገል ባህሉ ገና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለና መብቱን ለማስበከበር በሚያደርገው ተሣትፎም ሊደርስበት የሚችለውን ተፅዕኖ ለመቋቋም የማያስችሉት በርካታ ምክንያቶች ስላሉ ነው። ሶስተኛውና ዋናው ምክንያት የፖለቲካ ድርጅቶች ያለብን ውስጣዊ ድክመት ነው። ውስጣዊ ድክመታችን ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት ውጫዊ ምክንያቶች ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ቢሆንም ዞር ዞሮ የአንድ ፓርቲ ጥንካሬ የሚለካው ውጫዊው ችግሮችን ተቋቁሞ ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣት በሚኖረው ብቃት ነው። ነገር ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአሁኑ ወቅት ከገዥው ፓርቲ የሚደርስብንን ተፅዕኖ በብቃት ተቋቁመንም ሆነ በህዝቡ ውስጥ ለትግሉ እንቅፋት የሆኑትን የአስተሣሠብ እንቅፋቶች አልፈን የሚጠበቅብንን ጥንካሬ በመፍጠር ትግሉን ወደበለጠ ውጤት ማሸጋገር አልቻልንም። ተቃዋሚዎች ከውስጣዊ ድክመታችንን ተላቀን ከወቅቱና ከህዝቡ ፍላጐት ጋር የሚመጣጠን የጥንካሬ ደረጃ ላይ እንዳንደርስ ካደረገን አንዱ ምክንያት እርስ በርሳችን ተደጋግፈንና ተባብረን ለመታገል አለመቻላችን ነው። በዚህ ፅሁፍ ለማየት የተፈለገውም እስካሁን ተቃዋሚዎች ትርጉም ያለው ትብብር በመካከላችን ለምን መፍጠር እንዳልቻልን ወደፊትስ እስካሁን ከተሞከሩት የትብብር አንቅስቃሴዎች የተሻለ ትርጉምና ውጤት የሚኖረው ህብረት እንዴት መፍጠር እንደምንችል የመፍትሄ ኃሣቦችን ለመጠቆም ነው። ስለሆነም ኢዴፓ እስካሁን ተሞክረው ከተዳከሙት ወይም ከፈረሡት ህብረቶች የተሻለ ውጤት ሊያመጣ የሚችል ህብረት ለመፍጠር በሚከተሉት አስራ አንድ ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ የግድ ነው ብሎ ያምናል።

## 8.1 በውጫዊ ችግሮች ላይ ብቻ የማተኮር ድክመት

ተቃዋሚዎች ብዙውን ጊዜ ትግሉን ለማጠናከር ስለገጠመን ፈተና ስናወራ ትኩረት የምንሠጠው ስለውጫዊ ችግራችን ማለትም በዋናነት ከገዥው ፓርቲ በኩል ስለሚደርስብን ተፅዕኖ፣ ከዚያ አለፍ ሲልም በህዝቡ ውስጥ ስላለው የትግል ተሣትፎ ድክመት ነው። በተቃዎሚዎች መከካል እርስ በርስና በእያንዳንዳችን ፓርቲ ውስጥ ስላለው ድክመት ግን የሚገባውን ያህል ትኩረት ሠጥተን በድፍረት ስንነጋገር አንደመጥም። እንዲያውም በእርስበርሳችንና በውስጣዊ ድክመታችን የተሠከቱትን ችግሮች ሁሉ በደፈናው ጠቅልለን ተጠያቂነቱን ወደ ውጫዊ አካል የመወርወር (externalize የማድረግ) ድክመት ይታይብናል። የተቃዋሚዎች ህብረት እንዳይፈጠርም ሆነ እንያንዳንዱ ፓርቲ በራሱ ጠንክሮ

እንዳይዎጣ ባደረጉት ውስጣዊ ችግሮች ዙሪያ መነጋገርን እንደገንቢ ጐን ከማየት ይልቅ በአፍራሽነት መፈረጅ ይስተዋላል፡፡ ከዚያም በላይ ስለውስጣዊ ችግሮች መነጋገር ገዥውን ፓርቲ የሚያስደስትና የህዝቡን ሞራል የሚጐዳ ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ በዚህም ምክንያት ስለ ውስጣዊ የእርስ በርስ ችግራችን በግልፅ ለመነጋገር እንፈራለን፡፡ በእርግጥ በውስጥ ድክመት ዙሪያ በይፋ መነጋገር ለጊዜው ገዥውን ፓርቲ የሚያስደስት፣ የህዝቡንም ሞራል የሚጐዳ መስሎ ሊታይ ይችላል፡፡ ነገር ግን በሂደት ውጤቱ የገዥውን ፓርቲ ህልውና የሚፈታተንና ህዝቡንም ሊያረካ ወደሚችል የትግል ደረጃ የሚያሸጋግር በመሆኑ ተቃዎሚዎች ስለውስጣዊ ድክመታችን በግልፅ መነጋገር መጀመር አለብን፡፡ ሁልጊዜ ለሁሉም አይነት ድክመታችን ውጫዊ አካልን ብቻ ተጠያቂ ማድረግ የምንፈልግ ከሆነ በውስጣችን ያለው ድክመትና ችግር ውስጣችንን የበለጠ ስለሚሸረሽረው ተጠናክረን ለድል መብቃት አንችልም፡፡ ከአሁን ቀደም ተመስርተው እንደፈረሡት ወይም የትም ሣይደርሱ ተዳክመው እንደቀሩት የተቃዋሚ ህብረቶች ተመሣሣይ ስህተት ላለመስራት ከተፈለገም በቅድሚያ ቀደም ሲል የተመሠረቱት ህብረቶች ዛሬ የት እንዳደረሡ፣ ለህብረቶቹ መፍረስ ወይም መዳከም ትክክለኛው ምክንያት ምን እንደሆነ፣ አስካሁን ለፈረሡት ወይም ለተዳከሙት ህብረቶችስ ትክክለኛው ተጠያቂ ድርጅት ወይም ግለሠብ ማን እንደሆነ በድፍረት መመርመርና መነጋገር ካልቻልን ከስህተታችንና ከችግሮች መማር ስለማንችል ወደፊትም የተሻለ ህብረት አንፈጥራለን ብሎ ለማሠብ ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ተቃዋሚዎች ከእስካሁኑ በተሻለ የጋራ ህብረት ለመፍጠርም ሆነ በተሻለ ደረጃ ትግሉን ለማጠናከር የ12 ዓመቱን ዝምታ ሠብረን ወደ ውጭ ብቻ ሣይሆን ወደ ውስጥ የማየቱም ድፍረት ያስፈልገናል፡፡

## 8.2 ለውጥን በትግል ከማምጣት ይልቅ መንግስት የመሆንን ፍላጐት የማስቀደም ድክመት

እስካሁን ህብረት ለመፍጠር በተደረጉ ሙከራዎች ተቃዎሚዎች በአብዛኛው ትኩረት ስናደርግ የሚታየው ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የታክቲክና ስትራቴጅ ስልቶች ላይ አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜያችንን የምናጠፋው አማራጭ መንግስት እንዴት መመስረት እንደምንችልና ታላላቅ ብሄራዊ አጀንዳዎችን አንዴት ማስታረቅ እንዳለብን ስናቅድ ነው፡፡ በቅድሚያ በህዝቡ ውስጥ በምን አይነት መንገድ ለፖለቲካ ትግሉ አመች ሁኔታ የሚፈጥር የአስተሣሠብ ለውጥ ማምጣት እንዳለብን፣ በመቀጠልም ህዝቡን በብቃት አደራጅተንና በዙሪያችን አታግለው ገዥውን ፓርቲ በህዝባዊ ትግል መጣል እንዳለብን ብዙም ስንጨነቅ አንታይም፡፡ በዚህም ምክንያት የፈጠርነው ስብስብ ወይም ህብረት ህዝቡ ውስጥ ገብቶ ምንም ዓይነት ተግባራዊ ለውጥ ሣያመጣ በአጭሩ ሲቀጭ ይታያል፡፡ እስካሁን የተፈጠሩት ህብረቶች በአገር ውስጥ አንድ የተጠናከረ ቢሮ እንኳ ሣይከፍቱና በህዝቡ ውስጥ አላማቸውን የማሣካት ሙከራ ሣያደርጉ ከጥቂት የህዝባዊ ስብሠባዎች ማካሄድና የፅሁፍ መግላጫዎች የማውጣት አንቅስቃሴ ሣያልፉ ሲፈርሱ ወይንም ሲዳከሙ ታይተዋል፡፡ የተቃዎሚ ፓርቲዎች ህብረቶች ወደፊት ስለሚያቋቁሙት መንግስት ዓይነትና ስለብሄራዊ አጀንዳዎች ከወዲሁ መነጋገራቸው አሰፈላጊ ቁም ነገር ቢሆንም ይህ አይነቱ ፍለጐታችን ገዥውን ፓርቲ በህዝባዊ ትግል ለማስዎገድ ከሚያስችለን የትግል ታክቲክና ስትራቴጂ ቀድሞና ገኖ የሚታይ ከሆነ ግን ከፈረሡ ጋሪው አይነት የተሣሣተ አቅጣጫ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከአሁን በኋላ የሚፈጠሩ ህብረቶች እንዴት አድርገው ወደ ህዝብ ውስጥ በመግባት የአስተሣሠብ ለውጥ ማምጣት እንዳለባቸውና ህዝቡን በፖለቲካ አጀንዳቸው ዙሪያ አደራጅተው ወደ ስልጣን ባለቤትነት ማሸጋገር አንደሚችሉ የቅድሚያ ትኩረት የሚሠጡ መሆን አለባቸው፡፡

## 8.3 ሁሉም ተቃዋሚ በአንድ ህብረት ውስጥ እንዲካተት የመፈለግ አዝማሚያ

የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተባብሮ የመታገል አስፈላጊነት እንደብቸኛና የመጨረሻ አማራጭ ተደርጐ ለረዥም ጊዜ ግፊት በመደረጉ ምክንያት በአሁኑ ወቅት በህዝባችን ዙሪያ ሁሉም ተቃዎሚዎች በጥቅል ወደ አንድ ህብረት እንዲሠባሠቡ የመፈለግ አዝማሚያ ይታያል፡፡ እንዲህ አይነቱ የህዝብ ግፊት በተቃዎሚ ፓርቲዎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ በማሣደሩ በትግል ስልትም ሆነ በብሄራዊ አጀንዳ ውሃና ዘይት የሆኑ ድርጅቶች ሣይቀር የጋራ ህብረት ሲፈጥሩና ለመፍጠር ሲሞክሩ ተስተውሏል፡፡ በኢትዮጵያ የመገንጠል መብት እንዲኖር የሚፈልገው ድርጅት በተቃራኒው በኢትዮጵያ ጠንካራ አሃዳዊ መንግስት መመስረት አለበት ብሎ ከሚያምነው ድርጅት ጋር፣ በሠላማዊ ትግል የመጣል እምነት አለኝ የሚለው ድርጅት በተቃራኒው በጠብመንጃ ኃይል ገዥውን ፓርቲ መደምሠስ አለብኝ ብሎ ከሚታገለው ድርጅት ጋር አንድ ህብረት ለመፍጠር ሲሞከር በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ አሁንም ተመሣሣይ ሙከራ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የህዝቡን ግፊት ለማርገብ ሲባል፣ ወይንም በተቃዋሚነት መሠለፍን ብቻ አንደ መሠረታዊ መመዘኛ በመውሠድ ሁሉንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንድ ህብረት አንዲካተቱ ግፊት ማድረግ የምንፈልገውን ውጤት የሚያስገኝ አይሆንም፡፡ እንዲያውም ውጤቱ ከአሁን ቀደም እንደታዩት ህብረቶች ገና ተመሠረቱ ሲባል በማግስቱ ፈረሡ ወይም ተዳከሙ የሚል መጥፎ ዜና የሚያስከትልና ህዝቡ በህብረት ጥያቄ ዙሪያ ያለውን ተስፋ የሚያጨልም ነው፡፡ ስለዚህ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጊዜያዊ ግፊትን ለማብረድ ሲባል ብቻ የማይዘልቅ የጅምላ ህብረት ከመፍጠር ይልቅ በቅድሚያ በስልትና በአመለካከት ከተቀራረቡት ጋር ህብረት መፍጠርና በሂደት ከሌሎቹም ጋር ያለውን ልዩነት አያጠበቡ ማምጣት የተሻለ ይሆናል፡፡ አንድ የጅምላ ህብረት ከመፍጠር ይልቅ ሁለት ወይም ሶስት ተቀራራቢነት ያላቸው ህብረቶች ቢኖሩ መጠ ላት የለበትም፡፡ እንዲያውም ለህዝቡ ከአንድ የበለጡ አማራጭ ህብረቶች መኖራቸው እንደተገቢ አማራጭ መቆጠር ይኖርበታል፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚገባው ችግር ተቃዋሚዎች በህብረት ካልታገሉ በስተቀር ትግሉ የትም ሊደርስ እንደማይችል ተደርጐ መታየቱ ነው፡፡ ተበታትኖ ከመታገል ይልቅ በህብረትና በትብብር መታገል የበለጠ ጥንካሬ እንደሚፈጥርና የምንፈልገውን የትግል ውጠ ቶትም የበለጠ የተፋጠነ እንደሚያደርገው የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ ነገር ግን ህብረትን እንደ ብቸኛና የመጨረሻ መፍትሄ አድርገን ስንወስደው በራሱ የሚያስከትለው ጉዳት አለ፡፡ ይኸውም ሁሉም ፓርቲ ህብረትን ለመፍጠር ብቻ ሲደክምና ሲዋትት ፓርቲዎች በተናጠል ያላቸውን አንፃራዊ ጥንካሬም እያጡ ይመጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሚፈለገው ህብረት ውጤታማ ሣይሆን ከቀረ ትግሉን ከሁለት ያጣ ያደርገዋል፡፡ ህብረቱም ሣይፈጠር፣ ፓርቲዎችም በተናጥል ሣይጠናከሩ ይቀሩና ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዘነ ውጤት ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ህብረት ለመፍጠር የሚደረገው ሙከራና ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ፓርቲዎች የየራሣቸውን ድርጅታዊ ጥንካሬ የማጐልበቱንም ተግባር ለአፍታ ሣይዘነጉ ትግሉን ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ ህዝቡም ተቃዋሚዎች ካልተባበሩ በስተቀር ትግሉ ሊጠናከር አይችልም በሚል የተሣሣተ ድምዳሜ ፓርቲዎችን በተናጠልም ከመርዳት መቆጠብ የለበትም፡፡ ህዝቡ በአንድ በኩል የምንመኘው እውነተኛ ህብረት እንዲፈጠር ጠንካራ ግፊት እያደረገ ከዚሁ ጐን በጐን የሚያምንባቸውን ፓርቲዎች በተናጠልም የማጠናከሩን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል፡፡ የተሻለ ትርጉምና ውጤት የሚኖረው ህብረት ለመፍጠር ከተፈለገ ተቃዋሚዎች እነዚህን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባትና ህዝቡም በትክክል እንዲገነዘባቸው ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

## 8.4 ከእርስ በርስ ሽኩቻ ያልፀዳ ህብረት

የተቃዋሚዎች ህብረት ውጤታማ ካልሆነባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው የድርጅቶችና የግለሠቦች ሽኩቻ ነው:: እስካሁን ተመሥርተው የፈረሡት ወይንም የተዳከሙት ህብረቶች በዋናነት ለዚህ አይነቱ ችግር የተዳረጉት ድርጅቶችና ግለሠቦች ከራሣቸው ቡድናዊና ግላዊ ፍላጐትና ጥቅም በላይ የሃገርና የህዝብን ጉዳይ ማስቀደም ተስኗቸው በሚፈጥሩት ሽኩቻ ነው:: ለሚፈጠረው ሽኩቻ በአብዛኛው ጠረንጴዛ ላይ የሚቀርበው ሌላ ምክንያት ቢሆንም ጠለቅ ብሎ ሲመረመር ግን መሠረታዊው ምክንያት የሚመሠረተውን ህብረት ሁሉ እኔ ካልመራሁትና ካልተቆጣጠርኩት የሚል የቡድንኝነትና የግለኝነት ባህሪ ነው:: ከእንግዲህ እንዲህ አይነቱ ስህተት እንዳይደገምና የተሻለ ህብረት እንዲፈጠር ከተፈለገ ሁለት መፍትሄዎችን መከተል ያስፈልጋል:: ይኸውም በአንድ በኩል በሽኩቻና በቅራኔ የሚታዎቁትን ድርጅቶችና ግለሠቦች በግልፅ መድረክ አወያይቶ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቅራኔአቸውን በዕርቅ እንዲፈቱ ማድረግ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ አይነት የሽኩቻ ታሪክ ያላቸውን ድርጅቶችና ግለሠቦች የህብረት መሪ እንዳይሆኑ ለተወሠነ ጊዜ ማገድ ነው:: አለበለዚያ ወደፊትም የሚፈጠረው ህብረት በተለመደው አይነት የድርጅቶችና የግለሠቦች የእርስ በርስ ሽኩቻ ችግር እንደማይገጥመው ዋስትና ማግኘት አይቻልም::

## 8.5 የትግሉ ሜዳ አገር ውስጥ መሆኑን የመዘንጋት ድክመት

ለህብረቶች መፍረስ ወይም መዳከም እንደ አንድ ምክንያት ሊጠቀስ የሚገባዉ ሌላው ነጥብ የትግሉ ሜዳ አገር ውስጥ መሆኑን የመዘንጋት ድክመት ነው:: እስካሁን ድረስ የተመሠረቱት ህብረቶች በአብዛኛው በውጭ ሃገር የተመሠረቱ ከመሆናቸው በተጨማሪ የህብረቱ ጽ/ቤትና የህብረቱ መሪዎች መቀመጫም በአብዛኛው በውጭሃገር ሲሆን ነው ያየነው:: ማንኛውም የፓርቲዎች ህብረትም ሆነ ፓርቲ መቀመጫውን በውጭ ሃገር አድርጐና ትግሉንም ከባህር ማዶ መርቶ በየትኛውም መመዘኛ የኢትዮጵያን ህዝብ ነፃ ሊያወጣ አይችልም:: በውጭ ሃገር የሚካሄደው ትግል የራሱ የሆኑ በሃገር ውስጥ የማይተኩ ጠቃሚ ጐኖች ያሉት ቢሆንም በዋናነት ግን ትግሉ መካሄድና መመራት የሚገባው እዚሁ አገር ውስጥ በህዝቡ ውስጥና በአፈሩ ላይ ባለ አመራር ነው:: ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ የተቃዋሚ ህብረቶች የተሻለ ውጤትና ትርጉም እንዲኖራቸው ከተፈለገ ሰሜን አሜሪካ ወይም አውሮፓ በተቀመጠ ቢሮና አመራር የሚመሩ መሆን የለበትም:: የህብረቱ ዋና ጽ/ቤትም ሆነ የህብረቱ መሪዎች መቀመጫቸው አገር ውስጥ መሆን አለበት::

## 8.6 የድርጅቶችንና የግለሠቦችን ህብረት ለይቶ ያለመገንዘብ ድክመት

እስካሁን ድረስ በተግባር እንደታዩው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህብረት ለመፍጠር ጥረት በምናደርግበት ወቅት በህብረቱ ውስጥ አባል ለሚሆኑ ድርጅቶች ተቃዋሚ ከመሆናቸው ያለፈ ድርጅታዊ ቅርፅና ይዘትን የሚመዝን መስፈርት ሲቀመጥ አይታይም:: የሚቋቋሙት ህብረቶች የድርጅቶች ህብረት እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠሩ እንጂ በህብረቱ ውስጥ አባል ሆነው የሚገኙ አንዳንድ አካሎች ፈፅሞ ድርጅታዊ ቅርፅ፣ ይዘትና ትርጉም የሌላቸው ናቸው:: አንዳንዶቹ በህብረቱ ውስጥ የአንድ ድርጅት ድምፅ ይዘው ይወከሉ እንጂ በስራቸው የተሠባሠቡ አባላትና ተግባራዊ የትግል እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት አካባቢ የሌላቸው ጥቂት ግለሠቦች ናቸው:: እንዲህ አይነቶችን ግለሠቦች ብዙ ሺህ አባላትና መሬት ላይ በተግባር የሚታይ እንቅስቃሴ ካላቸው ድርጅቶች ጋር እኩል ድምፅ ሠጥቶ በድርጅት ስም በህብረት ውስጥ ማካተት በምንም መመዘኛ ተገቢ አይሆንም::

የሚፈጠረው ህብረት የግለሠቦች ህብረት ሣይሆን በትክክል የድርጅቶች ህብረት መሆን ስላለበት የተጋነነና የብዙዎችን ተሣትፎ የሚገድብ ሣይሆን መሠረታዊ የድርጅት መስፈርቶችን ግምት ውስጥ ያስገባ መመዘኛ መኖር አለበት፡፡ አንድ ድርጅት የውስጥ አሠራሩን በራሱ የመወሰን መብት ያለው ቢሆንም እንደ ድርጅት የህብረት አባል እንዲሆን ሲፈለግ ቢያንስ ቢያንስ የተወሠኑ አባላትን በስሩ ያቀፈ፣ ተግባራዊ የትግል እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኝ፣ ጊዜን የጠበቀ ጉባኤ የሚያካሂድና በአባላቱ መካከል ምርጫ የሚያካሂድ፣ የፖለቲካ ኘሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ያለው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ አለበለዚያ ግለሠቦችን በድርጅት ስም አሠባስቦ የሚቋቋም ህብረት የግለሠቦች እንጂ የድርጅቶች ህብረት ባለመሆኑ በትግሉ ሂደት ውስጥ ትርጉም ያለው ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡ ግለሠቦች በድርጅት ስም የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የግለሠቦችን የስልጣን ጥም ከማርካት፣ የግለሠቦቹ የሥም መጠሪያና መነገጃ ከመሆንና የህዝቡን ትግል ከማዘናጋት ያለፈ ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡ ግለሠቦች በድርጅት ስም በየህብረቱ እየተሰገሰጉ ትግሉን ከማደናቀፍ ይልቅ በተጠናከረ ትግል ትክክለኛ ድርጅት ፈጥሮ የህብረቱ አባል መሆን፣ አለዚያም ሚናቸው ከግለሠብ ያለፈ አለመሆኑን ተገንዝበው በሌሎች በሚያምኑባቸው ድርጅቶች ውስጥ በአባልነት መደራጀት አለባቸው፡፡

## 8.7 ተደራራቢ ውክልና በኅብረት ውስጥ የሚፈጥረው ችግር

በተቃዋሚዎች ኅብረት ውስጥ ለአለመግባባት መንስዔ የሚሆነው ሌላው ችግር አባል ድርጅቶች ተደራራቢ ውክልና በመፍጠር በኅብረት ውስጥ የወሳኝነት ወይም የአብላጫ ድምጽ ውክልና እንዲኖራቸው የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡ አንዳንድ ድርጅቶች በተናጠልና ከሌሎች ጋር በጋራ በፈጠሩት ሌላ ኅብረት አማካኝነት ተደራራቢ ውክልና ለማግኘት የሚጥሩ ሲሆን አንዳንድ ድርጅቶች ደግሞ እራሳቸውን ከሁለትና ከሶስት ሰንጥቀው በማባዛት በኅብረቱ ውስጥ ተደራራቢ ውክልና ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ የውክልና ሽሚያ ኅብረቱን ሚዛናዊ ላልሆነ የውሳኔ አሰጣጥ የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ በኅብረቱ ውስጥ አለመግባባትና ቅራኔ ለመፍጠር መነሻ ምክንያት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ወደፊት በሚፈጠር የተቃዋሚዎች ኅብረት ውስጥ አንድ ድርጅት በምንም ሁኔታ ከአንድ ድምጽ በላይ ውክልና እንዳይኖረው ጥብቅ ክትትልና ክልከላ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ኅብረቱ የጥቂቶች ዓላማና ፍላጐት የማስፈጸሚያ መድረክ ይሆንና ወደሚፈለገው ዓላማ ሳያመራ በአጭሩ ይቀጫል፡፡

## 8.8 የአመራር ኃላፊነትን የትርፍ ጊዜ ስራ አድርጐ የመያዝ ድክመት

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚካሄደውን ትግል ለመምራት ኃላፊነት የሚሸከሙ ሰዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት እንኳን በትርፍ ጊዜ በሙሉ ጊዜ ስራም በቀላሉ የሚችሉት አይደለም፡፡ እስካሁን ድረስ ፓርቲዎች በተናጠልም ሆነ በኅብረት በሚያካሂዱት ትግል የሚጠበቀውን ያህል ጥንካሬ ማግኘት ካልቻሉበት ምክንያት አንዱ የአመራር አባላቱ ኃላፊነታቸውን በሙሉ ትኩረትና ጊዜ ሳይሆን በተለያዩ አስገዳጅ ምክንያቶች በትርፍ ጊዜ ስራነት የሚያከናወኑ በመሆናቸው ነው፡፡ በተለይም ብዙ ፓርቲዎች በስራቸው ያቀፉ ኅብረቶችን የሚመሩ ግለሠቦች በትርፍ ጊዜ ስራ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይችላሉ ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ ከእንግዲህ የሚመሰረቱ ኅብረቶች የተሻለ ወጤትና ትርጉም እንዲኖራቸው ከተፈለገ ኅብረቶቹን ለመምራት ኃላፊነት የሚረከቡ አመራሮች (በተለይም የኅብረቱ ቁጥር 1 መሪ) የሙሉ ጊዜ አመራር ሰጭ መሆን አለባቸው፡፡ ይህንን መሰረታዊ ነጥብ ወደ ተግባር ለመለወጥ የመሪነቱን ድርሻ የሚረከቡት ሰዎች ይህንን ከፍተኛ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍለው የሙሉ ጊዜ አገልግሎት መስጠት የሚገባቸው ሲሆን በኅብረቱ በኩልም ግለሠቦቹ የኑሮ ችግራቸውን ለመቋቋም የሚያስችላቸው ክፍያ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል፡፡

## 8.9 በኀብረት ውስጥ የአባል ድርጅቶች ነጻነትና የአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ግጭት

በመካከላቸው በርካታ የአስተሳሰብና የአሠራር ልዩነቶችን ያካተቱ ድርጅቶች በኀብረት እንቅስቃሴ ውስጥ ውሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ ሲገጥማቸው ውሳኔው ሌሎችን ሳያስከፋ የሚከናወንበትና በመካከላቸው የሚፈጠሩ ልዩነቶች የኀብረቱን ሕልውና በማይጎዳ ሁኔታ እንዲፈቱ ለማድረግ የሚገጥማቸው ችግር ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ በሚወሰኑበት ጊዜ ነው:: በአሁኑ ወቅት ውሳኔዎችን በአብላጫ ድምጽ መወሰን ተገቢ እንዳልሆነ አሠራር የመገንዘብ አዝማሚያ እየዳበረ ስለመጣ ውሳኔዎችን በመግባባትና በመስማማት የመወሰን አማራጭ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል:: በተለይም ከግለሰቦች ስብስብ በላይ የሆኑ የየራሳቸወ ውስጣዊ ነፃነት ያላቸው ድርጅቶች የጋራ ውሳኔ የሚሰጡበት ሁኔታ ሲኖር ከአብላጫ ድምጽ ይልቅ በመቻቻልና በመስማማት ውሳኔዎችን መስጠት ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል:: ይህም የሆነበት ምክንያት በአንድ በኩል የራሳቸው ድርጅታዊ ህልውና ያላቸውን አካላት የውስጥ ነጻነት ለመጠበቅ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተፈጠሩትን ልዩነቶች በአብላጫ ድምጽ ሰበብ ሌሎች ያለፍላጎታቸው እንዲቀበሏቸው ማድረግ ሊፈጥረው የሚችለውን ያለመግባባት ችግር ለመፍታት በማሰብ ነው::

የተቃዋሚ ኀብረቶች በመካከላቸው ልዩነቶች ሲፈጠሩ የተፈጠሩትን ልዩነቶች በአብላጫ ድምጽ እንዲወሰኑ ከማድረግ ይልቅ በመቻቻልና በመስማማት መወሰን በጣም ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም የኀብረቱ አባል ድርጅቶች በኀብረቱ አማካኝነት እንዲፈፀሙላቸው የሚፈልጓቸው ጉዳዮች በጋራ የሚግባቡባቸውን ጉዳዮች ብቻ ስለሚሆን በመካከላቸው ልዩነት በተፈጠረ ቁጥር ልዩነቱ የኀብረቱን ህልውና የሚፈታተንበት እድል አይኖርም:: በስምምነት ሊወሰን የማይቻል ልዩነት ሲያጋጥማቸው ልዩነታቸውን በተናጠል በመያዝ ለሌሎች የጋራ ጉዳዮቻቸው ተፈጻሚነት ኀብረቱን በመጠቀም ሊቀጥሉ የሚችሉበት እድል ስለሚኖር ልዩነቱ በተፈጠረ ቁጥር የኀብረቱን ሕልውና የሚፈታተን አደጋ አይፈጠርም:: አለበለዚያ ግን አባል ድርጅቶች በመካከላቸው ተፈጥሯዊ የሆነ የአስተሳሰብና የአሰራር ልዩነት መኖሩ ስለማይቀር እንዲህ አይነቱ ልዩነት በተፈጠረ ቁጥር ለኀብረቱ ሕልወና አደጋ የሚፈጥር አለመግባባት መከሰቱ አይቀርም:: ስለዚህ የኀብረቱ አባል የሆኑ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸውና የውስጥ ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚያስማሙአቸውና የጋራ በሆኑ ጉዳዮች በኀብረቱ እየተገለገሉ ለመቀጠል እንዲችሉ ከአብላጫ ድምጽ ይልቅ የመግባባትና የመቻቻል የውሳኔ አሰጣጥን መከተል ይኖርባቸዋል:: ይህ አሠራር በከፍተኛ ደረጃ የአለመግባባትን በር የሚያጠብ ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውን ተደራራቢ ውክልና የማግኘት ተገቢ ያልሆነ ጥረትም በአስተማማኝ ሁኔታ ያስቀራል::

## 8.10 ለኀብረት ትግል ቅንነትና ሃቀኝነት የማጣት ድክመት

እስካሁን ድረስ በሀገራችን ኀብረትን ለመፍጠር የተደረጉ ጥረቶች ውጤታቸው ያላማረው ተጀምረው እስኪጨረሱ ድረስ ቅንነትና ሃቀኝነት የጎደላቸው በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል:: ህብረትን በመፍጠር ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በሃገራችን ለመንግስታዊ ስልጣን የበቁም ሆኑ በተቃዋሚነት የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች የፓርቲ ታሪክ ከተጀመረበት ከ1960ዎቹ ጀምሮ የሚያካሂዱት የፖለቲካ ትግል በአብዛኛው በሸፍጥ፣ በጥላቻ፣ እርስ በርስ በመጠላለፍና በመናቆር፣ በቂም በቀልና በፈጠራ አሉባልታ የታጨቀ ነው ማለት ይቻላል:: እንዲህ አይነቱ አስቀያሚና የተሳሳተ የትግል አሰራር ለውጤት እንደማያበቃና ሃገሪቱን ለበለጠ ችግር እንደሚዳርግ ለ3 አስርት ዓመታት ያህል በተግባር ካረጋገጥንም በኋላ ዛሬም ከዚያው አይነት የተበላሸ አሠራርና አስተሳሰብ አልተላቀቅንም::

በቅንነትና በሃቀኝነት ኅብረት ለመፍጠርም ሆነ በአጠቃላይ ትግሉን ለማጠናከርና ለድል ለመብቃት ከምናጠፋው ጉልበት በላይ አንዳችን የሌላችን እንቅስቃሴ ለማዳከምና ለማራከስ የምናጠፋው ጊዜና ጉልበት የበለጠ ነው:: ህዝቡን በማንቃትና በማደራጀት በስልጣን ላይ ያለውን አምባገነናዊ ስርዓት ለመታገል ሊደረግ የሚገባውን ትግል ጭራሽ ርግፍ አድርገው ትተው በየወቅቱ ተጠናክሮ ብቅ የሚለውን ፓርቲ ሁሉ በተለያየ አፍራሽ ዘዴዎች በመተናኮል ለማዳከም ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያጠፉ የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች መኖራቸው በገሃድ የሚታወቅ ሃቅ ነው:: እነዚህ ቡድኖችና ግለሰቦች ካለፈ ታሪካቸውና ስሃተታቸው ተምረው ወደ ገምቢ የትግል አቅጣጫ ካልመጡ በስተቀር አጠቃላይ ትግሉን ለማጠናከርም ሆነ የተሻለ ውጤት የሚያስገኝ ኅብረት ለመፍጠር ወደፊትም አስቸጋሪ ሁኔታ መኖሩ የማይቀር ነው:: እነዚህ ኃይሎች ትግሉን እያደናቀፉ የሚቀጥሉበት ሁኔታ ዘላለማዊ ሆኖ የሚቀጥል ባይሆንም ለጊዜው የትግሉን ሂደት አስቸጋሪና አዝጋሚ እንደሚያደርገው አያጠራጥርም:: እንዲህ አይነት ቅንነትና ሃቀኝነት የጐደላቸው ቡድኖችና ግለሰቦች በስመ ተቃዋሚ ስለሆኑ ብቻ ችላ ተብለው የሚቀጥሉ ከሆነ ወደፊትም የሚፈጠሩ ኅብረቶች ካለፉት ኅብረቶች የተለየ ዕጣ ፋንታ ይገጥማቸዋል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው::

እነዚህ ኃይሎች ከማንም በላይ ሀገር ወዳድና ታጋይ መስለው በመታየት ትግሉን የግል ኑሮና የእንጀራ ምንጭ አድርገው ይዘውታል:: ሬዲዮና ጋዜጣ ሳይቀር እያቋቋሙ አሉባልታ ይነግዳሉ:: የነሱን ተሰሚነትና ተናፋቂነት የሚቀንሱ የህዝብ ትኩረት የሚስቡ ፓርቲዎች በተፈጠሩ ቁጥር እነርሱን ለማዳከም ሌት ከቀን ተግተው ይሰራሉ፣ ሁልጊዜ በየህብረቱ ውስጥ እራሳቸውን በመሰግሰግ የኅብረቱን የበላይነት ድርሻ ለመቆጣጠር ይጥራሉ፣ ይህን ማድረጉ ካልተሳካላቸውም በኅብረት ላይ ሌላ ኅብረት የመፍጠር አዲስ ጅምር ይወጥናሉ:: ቀደም ብለው በነሱ ምክንያት ለፈረሱት ወይም ለተዳከሙት ኅብረቶች እራሳቸውን ከደሙ ንፁህ አስመስለው በማቅረብ ሌሎችን ሲያወግዙ ይደመጣሉ::

እንዲህ አይነቱ የተበላሸ የትግል ልምድ በአሁኑ ወቅትም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በገሃድ ይታይል:: እንዲህ አይነቱ የጥፋት እሽክርክሪት አንድ ቦታ ላይ ቆሞ ተቃዋሚዎች ቅንነትና ሃቀኝነት የተሞላበት ትክክለኛ የፖለቲካ ትግል ማካሄድ ካልቻልን ህዝቡ የሚፈልገውን ህብረት መፍጠርም ሆነ ትግሉን በአሸናፊነት መወጣት አንችልም:: ሁልጊዜም የገዥዎቻችን መሣቂያና መሣለቂያ ከመሆንና ታጥቦ ጭቃ ከመሆን አንድንም:: ስለዚህ ይህ ትውልድ ካለፉት ስህተቶች ተምሮ፣ በአዲስ የትግል ተነሳሽነትና ባህሪ፣ እውነተኛ የፖለቲካ ትግል አካሄዶ ለድል ለመብቃትና ታሪክ ለመስራት ከፈለገ በተቃዋሚው ጐራ ያሉትን ድክመቶችና ችግሮች ሁሉ በግልጽ መድረክ በድፍረት በመተቸትና በመገምገም ቅንነትና ሃቀኝነት የተሞላበት አዲስ የትግል አቅጣጫ መያዝ ይገባዋል::

## 8.11 ለህብረት ትግል ውጤታማነት የህዝብ ቁጥጥር አስፈላጊነት

እስካሁን ድረስ ተሞክረው ለፈረሱት ወይንም ለተዳከሙት የተቃዎሚ ፓርቲዎች ህብረቶች ተጠያቂና ተዎቃሽ ሲደረጉ የሚታዩት በጥቅል ሁሉም ተቃዋሚዎች ናቸው:: ፓርቲዎችም አንዳችን ሌላኛችን ተጠያቂ ከማድረግ አልፈን የየራሣችን የጥፋት ድርሻ ለመውሥድ ስንደፍር አይታይም:: እያንዳንዱ ፓርቲ ለህብረቱ መጠናከር የየራሱ የማይናቅ ድርሻ ያለው መሆኑ የሚያጠያይቅ ባይሆንም ሁሉንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለህብረት እንቅፋት እንደሆኑ አድርጐ በጥቅሉ መክሥስ ግን ተገቢ አይሆንም:: የህብረት ጥያቄው በሚፈለገው መልኩ ተግባራዊ እንዳይሆን ሆን ብለው ችግር የሚፍጥሩ አካሎች በውል ተለይተው ሊታዎቁና የተጠያቂነቱንም ሆነ የመወገዙን ድርሻ እነርሱው እንዲዎስዱት ማድረግ ይገባል:: ይህ መሆን ሳይችል ቀናውንና እኩዩን በጭፍን በጥፋተኝነት ማውገዝ ዞሮ ዞሮ ትግሉን የበለጠ የሚያዳክም ከመሆን አያልፍም:: ስለዚህ በኢዴፓ እምነት ከእንግዲህ ተቃዋሚዎች ህብረት ፈጥረው እንደገና ሲፈርሱ ወይም ሲዳከሙ ጥፋቱ የማን እንደሆነ በውል መታዎቅ ስላለበት

ሂደቱን የሚከታተልና የሚታዘብ የህዝብ ዓይን ያስፈልጋቸዋል:: የህዝብን ውክልና ሊያንፀባርቅ የሚችል ገለልተኛ ኮሚቴ ተቋቁሞ የህብረት እንቅስቃሴዎችን በሚገባ እየተከታተለ እውነተኛውን መረጃ ለህዝብ ማቅረብ አለበት:: ይህ ሲሆን ብቻ ነው ሁሉም ተቃዋሚዎች በጥቅል መወገዛቸው ቀርቶ ለህብረት እንቅፋት የሆኑት ኃይሎች በትክክል ተለይተው ሊታወቁ የሚችሉት:: እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አስራ አንድ ነጥቦች ተገቢው ትኩረት ከተሠጣቸው የተሻለ ውጤትና ትርጉም ያለው ህብረት መፍጠር እንደሚቻል ኢዴፓ በፅኑ ያምናል::

# 9. የብሔራዊ እርቀ- ሰላም ጥያቄ

## 9.1 መግቢያ

የብሔራዊ እርቀ- ሰላም ጥያቄ በደርግ ጊዜም አልፎ አልፎ በፖለቲካ ጥያቄነት ሲነሳ ነበር:: ከፍተኛ የፖለቲካ ጥያቄ እሆነ የመጣው ግን ባለፉት 12 ዓመታት ኢሕአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ነው:: ጥያቄው በተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የአገር ሽማግሌዎች በተለያየ ጊዜና በተለያዩ መድረኮች በተደጋጋሚ ተነስቷል:: ሆኖም በጥያቄው ትርጉምና ይዘት ላይ አሁን ድረስ ሕዝቡ በቂ ግንዛቤ አለው ማለት አይቻልም:: በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያም እስካሁን ጥያቄውን ጥቅል በሆነ ሁኔታ ከማንሳት ያለፈ ዝርዝር መግለጫ ሲሰጥ አልተስተዋለም:: በዚህም ምክኒያት ብሔራዊ እርቀ ሰላምን በተመለከተ ሕዝቡ ውስጥ ወጥ የሆነ ግንዛቤ የለም:: በመሆኑም ኢሕአዴግ የጥያቄውን መሠረታዊ ዓላማ ለራሱ በሚጠቅመው መንገድ በማቅረብ ብዥታ ለመፍጠር ሲሞክር ይታያል::

የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄ የአገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ ጥያቄ መሆኑን የተገነዘበና ጥያቄውንም የፖለቲካ ፕሮግራሙ አካል ያደረገ ፓርቲ ነው:: በአሁኑ ወቅት በጥያቄው ዙሪያ ያለውን አቋም ለሕዝብ ማሳወቅ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል:: ይህንን ማብራሪያ የሚያቀርበውም ሌሎች ፓርቲዎችም በጥያቄው ዙሪያ ያላቸውን አቋም ወደ መድረክ አውጥተው ግልጽ ውይይት እንዲደረግበትና ሕዝቡም በጥያቄው ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ በማሰብ ነው::

ብሔራዊ እርቅ በተለያዩ አገሮች፣ ለተለያዩ ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሔነት ጥቅም ላይ ውሎ ውጤት ሲያገኝ ታይቷል:: ነገር ግን በእነዚህ አገሮች ለብሔራዊ እርቅ መፈጠር ምክኒያት የሆኑት ጉዳዮች ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎችና ወቅታዊ ችግሮች ጋር ተቀራራቢነት እንጂ ተመሳሳይነት የላቸውም:: ስለሆንም እኛ ኢትዮጵያውያን ከራሳችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የብሔራዊ እርቀ ሰላም ቀመር ያስፈልገናል የሚል እምነት ኢዴፓ አለው::

የእርቀ ሰላም ጥያቄና በእርቅም አማካኝነት ቅራኔዎችን፣ ግጭቶችንና ጦርነቶችን ማስወገድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ አስተሳሰብ አይደለም:: ከረጅም ዘመን ጀምሮ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ኗሪ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግለሰቦች፣ ከጎሣዎችና ከአካባቢ መሪዎች ግጭት ጀምሮ እስከ ንጉሦች ድረስ የዘለቁ ቅራኔዎችን በእርቅ የመፍታት ባሕል ነበረው:: ከዘመናዊ የአስተዳደርና የፍትሕ ተቋማት መጠናከር አኳያ የእርቅ ሚና አገራዊ ችግሮችን የመፍታት አቅሙ እየተዳከመ ቢመጣም፣ የእርቅ ባሕል እስካሁን በሕዝቡ ውስጥ ያለውን መሠረት አላጣም:: አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአገራችን በአሁኑ ወቅት በፍርድ ቤት መፍትሔ ከሚያገኙት አለመግባባቶች ይልቅ በሽምግልናና በእርቅ የሚፈቱት አለመግባባቶች በቁጥር በእጅጉ የላቁ ናቸው:: በተጨማሪም የእርቅ ባሕላችን ከዘመናዊው የፍትሕ ተቋም የበለጠ አለመግባባትን፣ ግጭትን፣ ጥላቻንና ቂም በቀልን የማምከን ኃይል አለው:: ነገር ግን ይህን በጎና ነባር ባሕላችንን በአግባቡ በመጠቀም በአገራችን ሥር የሰደደው

የጥላቻና የቂም በቀል አዙሪት ተወግዶ ለልማትና ብልጽግና መሠረት የሚሆን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ አልቻልንም።

ኢትዮጵያውያን ነፃነታችንን በውጭ ኃይሎች ላለማስደፈር የተዋጣለት ትግል ማድረግ የመቻላችንን ያህል የውስጥ ሰላማችንን ለማስጠበቅና ለሕዝብ ጥቅም የሚበጅ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመፍጠር አልቻልንም። አገራችን ከጥንት ጀምሮ በተለያዩ የእርስ በርስ ጦርነቶች ውስጥ ያለፈችና በርካታ የሥርዓት ለውጦችን አስተናግዳለች። ይሁ እንጂ ሥልጣን ላይ የወጣውን ኃይል ከመደምሰስ ወይም ከማውረድ አልፎ በምትኩ የተሻለና ዘላቂነት ያለው ሥርዓት የመፍጠር ብቃት አልታየም። ለዚህም በዋነኛነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ድክመቶች አንዱ የሕዝቡን መብት የሚያረጋግጥ፣ የሕግ የበላይነትን የሚያሰፍንና ሁለንተናዊ የአገር እድገትና ብልጽግናን የሚያመጣ፣ ቀጣይና ወጥ የሆነ ሥርዓትን ለማምጣት የሚያስችል ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ባለቤት ያለመሆን ነው። በዚህም ምክኒያት፣ በኢዴፓ እምነት፣ የወቅቱ ቀዳሚ አጀንዳ በአገራችን ዘላቂ ሰላምና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሊያሰፍን የሚችል ለሕገ-መንግሥት ተገዥ የሆነ ሥርዓት እንዴት እንፍጠር? ለሚለው ጥያቄ ገቢውን መልስ ማስገኘት ነው።

ኢዴፓ የኢህአዴግ ከሥልጣን የመወገድ ጉዳይ አይቀሬ ስለሆነ ብዙም አያስጨንቀውም። ኢዴፓ ስለ ኢሕአዴግ መወገድ ብዙም የማይጨነቀው በሁለት ምክኒያቶች ነው። የመጀመሪያው ምክኒያት የተለያዩ አገሮች በሕዝብና በአምባገነኖች መካከል የተደረጉ ትግሎች ልምድ እንደሚያሳየው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም የኢሕአዴግን አገዛዝ በአንድ ታሪካዊ ወቅት በሰላማዊ ትግሉ እንደሚያሸንፈው በመተማመን ነው። ሁለተኛው ምክኒያት ደግሞ ለጠባብ ቡድናዊ ጥቅምና ፍጎት የቆመው ኢሕአዴግ ተመቻችቶ የረገጠው ሕዝባዊ መሠረትና አገራዊ ራዕይ የሌለው በመሆኑ በአንድ ወቅት በራሱ የውስጥ ችግርና በሰላማዊ ትግሉ መጠናከር ከመፈራረስ እንደማይድን በማመናችን ነው። ይሁን እንጂ በኢዴፓ እምነት ይህ ትውልድ ካለፉት ትውልዶች የተሻለ የትግል ውጤት አምጥቷል ወይንም ትግሉን በአስተማማኝ ድል ተወጥቷል የሚያስብለው ከሥርዓቱ መውደቅ በኋላ የተሻለ ሥርዓት መፍጠር ሲችልና መፍጠር እንደሚችልም ከወዲሁ እርግጠኛ መሆን ሲችል ነው። ስለዚህ የህዝቡ የመጨረሻ ግብ ኢህአዴግን በመጣል ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የተሻለ ሥርዓትን በእርግጠኝነት መፍጠር መሆን አለበት።

ከዚህ እምነታችን ስንነሳ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተማማኝና ዘላቂ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት የሚያስችል ዝግጅት አድርጓል ወይንም ይህንኑ ብቃት ፈጥሯል ማለት አይቻልም። በዚህም ምክኒያት በረጅሙ ሕዝባዊ ትግል ከሚመጣው የማይቀር የሥርዓቱ ውድቀት በመለስ ገዢው ኃይል በራሱ የውስጥ ችግር እንዳይጠገን ሆኖ ሊፈራርስ ይችላል። በዚያው ልክ ከፍተኛ የጎሰኝነት፣ የጥላቻና የመነጣጠል ስሜት በተንሰራፋበት በአሁኑ ወቅት አገሪቱን ተረክቦ የተረጋጋ አስተዳደር ለመመሥረት የሚያስችል ዝግጅት ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። የወቅቱ ትግል በተቻለ ፍጥነት ከዚህ ዓይነቱ ሥጋት ተላቆ ወደ ተሻለ በራስ የመተማመን ደረጃ መሸጋገር ካልቻለ ኢህአዴግ በመውደቁ ብቻ የሚገኘው ለውጥ ትርጉም የለሽ ነው። በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በአገራችን ሥር እየሰደደ የመጣው ጎሠኝነት፣ አምባገነንነት፣ ጥላቻና ተበቃይነት ወደ ባሰ የብጥብጥ ደረጃ ተሸጋግሮ አገራዊ ህልውናችን የባሰ አደጋ ላይ ላለመውደቁ ዋስትና የለም። በኢዴፓ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስተማማኝ ሁኔታ የፖለቲካ ሥልጣኑ ባለቤት ለመሆን ሁለት አማራጭ ዋስትናዎች ይኖሩታል። እነርሱም የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ መፈጠር እና ምናልባት ጊዜው ሊራዘም ቢችልም የሕዝቡ ሰላማዊ ትግል አሸናፊነት ናቸው።

በአጭር ጊዜና ያለተጨማሪ የሕይወትና የሀብት (ሪሶርስ) ኪሣራ ሊገኝ የሚችለው ዋስትና በብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ መፈጠር የሚገኘው ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ሕዝቡ ተደራጅቶ በሰላማዊ መንገድ ለረጅም ጊዜ በመታገልና ትግሉንም በአሸናፊነት በመወጣትና በአገሪቱ

ዘላቂነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመመሥረት የሚገኘው ዋስትና ነው፡፡ በዚህም ምክኒያት የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ትክክለኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊያሸጋግሩ ከሚችሉት ሁለት ወሳኝ አማራጮች ውስጥ አንዱ እንጂ ብቸኛው አማራጭ እንዳልሆነ ኢዴፓ ይገነዘባል፡፡ ስለሆነም ኢዴፓ በተራዘመ ሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል አስተማማኝ ለውጥ የማምጣቱን አማራጭ ቀዳሚና ዋና ዓላማው አድርጎ፣ የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄን ደግሞ እንደ አንድ ተጨማሪ የትግል ሥልት በመቁጠር የፕሮግራሙ አንድ አካል ማድረግን መርጧል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነቱን ገደብ የለሽ በሆነ መስዋዕትነት ማስከበሩ የማይቀር ነው፡፡ ቢሆንም፣ ከዚህ በመለስ ለብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ መፈጠር ተገቢ ትኩረት በመስጠትና ለውጤታማነቱም ጠንክሮ በመታገል በተራዘመ ትግል ሊባክን የሚችለውን ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብት የማዳን ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የሕዝቡን አመለካከት እንወክላለን የምንልና በገዢነትም ሆነ በተቃዋሚነቱ ጎራ የምንገኝ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ብቸኛው አማራጭና መፍትሔ የኔ ብቻ ነው ከሚል የግለኝነትና የግትርነት ስሜት በመውጣት በአጭር ጊዜ አዲስ የሥልጣን ሽግግር ባሕል ባለቤት ሊያደርገን ለሚችለው የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄ ልባዊና ቁርጠኛ ፈቃደኝነትን ማሳየት ይጠበቅብናል፡፡ በእርስ በርስ ጦርነት ወንድም ወንድሙን ገድሎ የድል ሐውልት የሚተክልበት አሳዛኝ የታሪክ ሂደት ቆሞ አገራችን ለምትናፍቀውና ለትውልድ በማስታወሻነት ለሚቆመው የሰላም አርበኝነት ሐውልት ባለቤትነት ልትበቃ ይገባል፡፡

አምባገነኖች የሕዝብንና የአገርን ጥቅም ከራሳቸው የሥልጣን ጥቅም አብልጠው የማየት ተፈጥሮ ስለሌላቸው የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄን የመቀበል ፍላጎትም ሆነ ድፍረት የላቸውም፡፡ ደርግ ራሱም ሆነ አገሪቱን ከባሰ ውድቀት ማዳን እንዲችል እስከ መጨረሻው ግብዓተ መሬቱ ድረስ የቀረበለትን የእርቀ ሰላም ጥያቄ በሸሙጥና በእምቢተኝነት እንደነቀፈው ሁሉ ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ ኢሕአዴግ የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥየቄን እየነቀፈው ይገኛል፡፡

## 9.2 የብሔራዊ እርቀ ሰላም መፈጠር ወቅታዊነት

በኢዴፓ እምነት የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ ጥያቄ ሥልጣን የመጋራትም ሆነ የመጋፋት ጥያቄ አይደለም፡፡ ጥያቄው ላለፉት 12 ዓመታት ኢሕአዴግ የፈጠራቸውን ችግሮች የመፍታት ጥያቄ ብቻም አይደለም፡፡ ጥያቄው ለዘመናት በአገራችን ፖለቲካ ሥርዓት ሥር እየሰደደ የመጣውን የጥላቻ፣ የመናናቅ፣ ያለመተማመን፣ የቂም በቀልና የመገዳደል ስሜትን የማስወገድና የኃይል የሥልጣን ሽግግርን ወደ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ለመለወጥ የሚያስችል ታሪካዊ መሠረት የመፍጠር ጥያቄ ነው፡፡ የእርቀ ሰላም ጥያቄ ለሌላ ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀሚያነት የምናነሳው ሳይሆን በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጥያቄውን እንደ ጥያቄ ለማንሳት የሚያስገድዱ መሠረታዊ ምክኒያቶች በመኖራቸው ነው፡፡

የወቅቱ የአገራችን ሁኔታ ገዢው ፓርቲ ጧት ማታ እንደሚነግረን ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት አይደለም፡፡ በታሪካችን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ጎሠኝነትን መሠረት ያደረገ የጥላቻና የቂም በቀል ስሜት የታመቀበት፣ ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ሳይሆን በጎሣ ማንነታቸው የተባደኑበት፣ ከብሔራዊ ጥቅምና ስሜት በላይ የጎጥ ተቆርቋሪነት በእጅጉ የዳበረበት፣ የአንድነት መገለጫ ከሆኑት እሴቶቻችን ይልቅ ልዩነቶቻችን ትኩረትና ቦታ ያገኙበት ወቅት ነው፡፡ ወቅቱ፣ የፍቅር፣ የትብብርና የእኩልነት ስሜት እየሟሸሸ መጥቶ የጎሣ ልዩነትን መሠረት ያደረገ የገዢነትና የተገዢነት ስሜት የዳበረበት ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ አፋዊ እንጂ ልባዊ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ጥቂቶች የብዙሃኑ ገዢዎች የሆኑበት፣ በአጠቃላይ በዚች አገር ዘላቂ ሰላምን የመፍጠር ቅን ልቦና በመጥፋቱ ዛሬም የሥልጣን ምንጭ የምርጫ ሳጥን ሳይሆን ጠመንጃ የሆነበት መሆኑ በግልጽ ይታያል፡፡

ገዢው ፓርቲ ገና ወደ ሥልጣን በወጣ ማግስት የተለየ አስተሳሰብ ያላቸውን ኃይሎች «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» በማለት በጦረኛነትና በቀይ ሽብር ተዋናይነት በመፈረጅ መሠረታዊ የሆነ ሰላማዊ ሂደትን የመፍጠር ፍላጎት አላሳየም፡፡ በረጅሙ የአገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የሃምሳ ዓመት ዕድሜ ያለውን የአገሪቱን ሠራዊት በመበተን ሥር የሰደደ የቂም በቀልተኛነት ባሕሪ ያለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሥልጣን ላይ በቆየባቸው ተከታታይ 12 ዓመታትም የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት በማጠናከር ፈንታ ሕዝቡን በጎሣ በመከፋፈል በውጤቱ የራሱን ሥልጣን አስጠብቆ የማቆየት ፍላጎቱን በግልፅ አሳይቷል፡፡

ሰላማዊ የትግል መድረኩን የተነፈጉ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ «በጠመንጃ የመጣን በጠመንጃ» ወደሚል አቅታጫ ተገፍተዋል፡፡ ትናንት በአንድነቱ ኮርቶ ይኖር የነበረው ሕዝብ ዛሬ ደምና አጥንቱ እየተቆጠረ ወንድሙ ከሆነው ሕዝብ ተለይቶ አዲስ የጎጥ መንግሥታት እንዲፈጥር እየተገፋ ነው፡፡ በኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ ከፊታችን የተጋረጠው አደጋ እንዲህ ቀላል አይደለም፡፡ የፖለቲካ ትግል የአምባገነኖችን ጫናና አፈና ታግሎ አገርን ነፃ ማውጣት መሆኑ ቀርቶ መፍትሔው የመገንጣጠል ጥያቄን በማንሳት በነፃነት ስም ነፃነትን መሸሽ ከሆነ የነገዋ ኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ነው? በሕዝባችን ልብ ውስጥ የተዘራው ጥላቻ ምክኒያት አንዱ በሌላው ላይ ጥርሱን እነከሰ «ነገም የእኛ ቀን ይመጣል» በሚል የበቀል ስሜት ሲያደባ ይታያል፡፡ ጥያቄው ይህንን አደጋ እንዴት እናስወግድ? የሚል ነው፡፡

## 9.3 የብሔራዊ እርቀ - ሰላም መድረክ ዓላማ

የእርቀ - ሰላም ዓላማ፣ ገዢዎች እንደሚሉት፣ ሥልጣንን በአቋራጭ ለማግኜት ወይንም ተፃራሪ ዓላማዎችን ለማስታረቅና ልዩነቶችን ከነአካቴው ለማጥፋት አይደለም፡፡ የእርቀ ሰላም ዓላማ እስካሁን የማሠሪያ ውል ልናበጅለት ያልቻልነው ያልተቋረጠ የሕዝብ ለቅሶና ዋይታ እንዴት እንውጣ? እንደ አንድ የተከበረና በረጅም ጊዜ አንድነቱና ነፃነቱ የሚኮራ ሕዝብ ጠቃሚ የታሪክና የባሕል እሴቶቻችንን ጠብቀን እንዴት እንቀጥል? በብዙ ዓይነት የውስጥና የውጭ ቅራኔዎች ተተብትባ ወደ መበታተንና መፈራረስ እየተገፋች የምትገኘውን አገራችንን ሕልውና እንዴት እናትርፍ? ለሚሉና ለመሳሰሉ ፈታኝ ጉዳዮች የጋራ መፍትሔ ለማስገኘት ነው፡፡

በእርቀ ሰላም ጥያቄ አቀራረብ፣ በመድረኩ ተሳታፊዎች ማንነት፣ በመድረኩ የውሳኔ አሰጣጥ ሥልቶችና በመሳሰሉት ቴክኒካዊ ሂደቶች ላይ በተለያዩ አካሎች የተለያዩ አስተሳሰቦች ቢኖሩም መሠረታዊው የእርቀ ሰላም መድረክ በአገራችን በእጅጉ የተለመደውንና የታሪካችንም ዓይነተኛ አካል የሆነውን የኃይል የሥልጣን ሽግግር በሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር እንዲተካ ከማድረግ የተለየ ዓላማ የለውም፡፡ በኢዴፓ እምነት የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ ዓላማ በፓለቲካ ኃሎች መካከል ከልማዳዊ የጦርነት አስተሳሰብ ይልቅ ሰላማዊና ዘመናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዲፈጠር፣ ከጠባብ ቡድናዊ አስተሳሰብ ይልቅ ብሔራዊ ራዕይ እንዲዳብር ማድረግ ነው፡፡ በአገራችን ታሪክ አሸናፊው ወደ ቤተ መንግሥት፣ ተሸናፊው ወደ እስር ቤት የሚወርድበት የታሪክ ሂደት እንዲቆም ማድረግ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከኃይል የሥልጣን ሽግግር አዙሪት ውስጥ ወጥታ አዲስና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ባሕል ባለቤት እንድትሆንና ዘላቂነት ወዳለው የልማትና የብልጽግና ጎዳና እንድታመራ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም መሠረታዊ ዓላማ መነሻነት፡-

1. ቅራኔዎችና ልዩነቶች በሠለጠነና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያዙበትና የሚስተናገዱበት፣ ባለፉትም ሆነ በአሁኑ አገዛዝ የቀጠለውን መናናቅ፣ መጠላለፍ፣ መገዳደል፣ ጥላቻና ቂም በቀልን አስወግዶ በምትኩ መቻቻል፣ መተማመን፣ መከባበርና መደማመጥ የሠፈነበት፣ በሕግ የበላይነት የሚመራና ሰብአዊ መብቶች ከለአንዳች ገደብ የሚከበሩበት ዴሞክራሲያዊና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መመሥረት፤

2. በሽኩቻና በመጠላለፍ ተጠምደን በከንቱ የምናባክነው የአገር ሀብት (ሪሶርስ)፣ ጊዜና እውቀት ሙሉ በሙሉ ለአገር ልማትና ለእድገት በማዋል በብልሹ ፖለቲካ ያጣነውን ብሔራዊ ክብርና ኩራት መልሰን እንድንጎናፀፍ፣ አሁን ከምንገኝበት አሳፋሪ ኋላ-ቀርነት ወጥተን እንደ ሕዝብና እንደ አገር ራሳችንን ችለን የምንቆምበትና ለዘላቂ ሕልውናችን የሚያስፈልገንን በራስ የመተማመን መንፈስ ገንብተን ለትውልድ የሚተላለፍ፣ በሰላምና በመረጋጋት ላይ የተመሠረተና ያለማቋረጥ እድገት የሚታይበት አስተማማኝ የልማት አቅጣጫ እንድንከተል ማስቻል፤

3. የተወሰነን ቡድን፣ ጎሣ፣ ሃይማኖት፣ አካባቢ፣ ወዘተ. ልዩ ተጠቃሚ፣ ሌላውን ግን የበይ ተመልካች የሚያደርገውን ጠባብና የተዛባ የሪሶርስ አመዳደብና አጠቃቀምን፣ አድልዎ የሰፈነበት የፖለቲካ ዘይቤን፣ የልማት ሥርጭትን፣ አንዱን ግንባር ቀደም ተዋናይ ሌላውን ደግሞ አያገባህም ወይንም አይመለከትህም በሚል ጭፍን አሠራር የሚያገለውንና ወደ ዳር የሚገፋውን በታኝ ፖሊሲ አስወግዶ በምትኩ ሁሉንም በእኩል ዐይን የሚመለከት፣ ለሁሉም እኩል መብት የሚያጎጽፍ በሚዛናዊነት መርህ ላይ የተመሠረተ አቀራራቢና አሰባሳቢ የፖለቲካ አቅጣጫን በጋራ ለመንደፍ ማስቻል፤

4. ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የመብት ጥያቄዎች ቢያቀርቡም መንግሥት በጎ ምላሽ ለመስጠት አለመቻሉ ይታወቃል:: በሌላ በኩል የሕዝቡ ብሶት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እንደመሄዱ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ከወዝአደሩ፣ ከአርሶ አደሩ፣ ከአርብቶ አደሩ፣ በንግዱ ሕብረተሰብና ከሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች መነሳታቸው አይቀርም:: ይህን ሁኔታ ወደባሰ ችግርና የእርስ በርስ ግጭት ሳያመራ ከወዲሁ ማስቀረት፤

5. በተለያየ የፓለቲካ ጎራ ተሰልፈው ሕዎታቸውን ላጡና በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ እርስ በርስ ለተገዳደሉት ዜጎች «ያለፈው ይብቃ» በሚል ቁርጠኛ ውሳኔ ያለፈው ምዕራፍ የሚዘጋበትና አዲሱ የመቻቻልና የመደማመጥ ምዕራፍ የሚከፈትበት ልዩ ማስታወሻ ሆኖ የሚያገለግል፣ በአንዱ ወይም በሌላው ጎራ ቆሞ ሕይዎቱን ባጣው ኢትዮጵያዊ ወገን ሀዘን ላጋጠማቸው ቤተሰቦች እንባ ማድረቂያ የሚሆን፣ ከፖለቲካ ተሳትፎ ጋር በተያያዘ በአንዱ ወይንም በሌላው ጎራ ተሰልፈው የአካል ጉዳትና የሞራል ስብራት ለደረሰባቸው ወገኖች ማካካሻ የሚሆን፣ ለሁሉም ዜጎች ትምህርት የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን በመጪው ትውልድም ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይደገም ማስጠንቀቂያ ሆኖ የሚያገለግል የመተሳሰብና የመቻቻል ዘመን መክፈቱ የሚዘከርበት «ብሔራዊ እርቀ ሰላም ሐውልት» በጋራ እንዲቆም ማድረግ፣ ይህም ዕለት ብሔራዊ በዓል ሆኖ በየዓመቱ እንዲከበር በመወሰን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም አርአያ ሊሆን የሚችል ኢትዮጵዊ መፍትሔ ማስገኘት፤ የሚሉት ነጥቦች ኢዴፓ ለብሔራዊ እርቀ ሰላም መነሻ አድርጎ ከሚመለከታቸው ዓላማዎቹ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

## 9.4 የብሔራዊ እርቀ - ሰላም ማስፈፀሚያ ሥልቶች

የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ ዓላማ ማስፈጸሚያ ሥልቶችን አስመልክቶ ወጥነት ባለው መልክ ባይሆንም እስካሁን በተለያዩ መድረኮች ሦስት መልክ ያላቸው አስተሳሰቦች ሲነሱ ተደምጠዋል:: ሦስቱም አማራጮች አሰተሳሰቦች በአገራችን መካሄድ የሚገባው የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ መቋጫዎች ውስጥ ዋነኛው አገሪቱን ወደ ትክክለኛ የሕዝብ መንግሥት የሚያሸጋግር ሁኔታ መፍጠር መሆኑን ይቀበሉታል:: ይሁን እንጂ፦

የመጀመሪያው አስተሳሰብ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች ያካተተ ጥምር የሽግግር መንግሥት መፍጠር አስፈላጊ ነው የሚል ነው:: ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ፣ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች በእኩልነት የሚያስተናግድና የተመቻቸ የውድድር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ የሚችል በሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች በሚመረጡ ሽማግሌዎች ምክር ቤት የሚቋቋም የአደራ የሽግግር መንግሥት ሊሆን ይገባዋል የሚል ነው:: ሦስተኛው አስተሳሰብ ደግሞ፣ ገዢው

ፓርቲ በሥልጣን ላይ እንዳለ ሆኖ፣ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች በእኩልነት የሚስተናገዱበት የተመቻቸ የውድድር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ የሚል ነው፡፡

የመጀመሪያውና ሁለተኛው አማራጭ ወደ ተግባር ሲለወጡ በሥልጣን ላይ ያለው ገዢ ፓርቲ ብቸኛ የሥልጣን ባለቤትነት ደረጃውን ወዲውኑ ለቆ በምትኩ የጥምር ወይም የአደራ የሽግግር መንግሥት እንዲፈጠር ማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ የጥምርም ሆነ የአደራ የሽግግር መንግሥቶች ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች በእኩልነት የሚያስተናግዱ የተመቻቸ የውድድር ሜዳ ፈጥረው በነፃና በፍትሓዊ የምርጫ ሥርዓት ለተፈጠረው አካል የፖለቲካ ሥልጣንን ያስረክባሉ የሚል ነው፡፡ ሦስተኛው አማራጭ በቀጥታ ወደ ጥምር ወይም የአደራ የሽግግር መንግሥት ምሥረታ የሚያመራ ሳይሆን በሥልጣን ላይ የሚገኘው ገዢ ፓርቲ የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረኩን ውሳኔዎች መሠረት አድርጎ ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች በእኩልነት የሚያስተናግድ የተመቻቸ የውድድር ሜዳ ፈጥሮ በነፃና በፍትሓዊ ምርጫ አሸናፊ ለሆነው አካልም የፖለቲካ ሥልጣኑን የማስረከብ ግዴታና ኃላፊት እዲጣልበት የሚያደርግ ነው፡፡

የመጀመሪያውና ሁለተኛው አማራጮች ለብሔራዊ እርቀ ሰላሙ መድረክ ውሳኔ (የቃል ኪዳን ሰነድ ወይም ቻርተር) ተፈፃሚነት የተሟላ ዋስትና የመስጠት ዕድላቸው የተሻለ ሲሆን በሌላ በኩል ግን ተቃራኒ ኃይሎች (ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚዎች) ወደ ስምምነት እንዳይመጡ የማድረግ ጉድለት ይኖራቸዋል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክኒያትም በሥልጣን ላይ ያለው ገዥ ኃይል እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብ በቀላሉ የመቀበል ችግር ስለሚኖርበት ነው፡፡ ሦስተኛው አማራጭ ለብሔራዊ እርቀ ሰላሙ መድረክ ውሳኔ ተፈፃሚነት የሚኖረው ዋስትና ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው አማራጮች ያነሰ እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ተቃራኒ ኃይሎች፣ ማለትም በተለይ ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በቀላሉ ወደ ስምምነት እንዲመጡ የማድረግ ዕድሉ የሠፋ ይሆናል፡፡ በሦስቱም አማራጮች ውስጥ ለስምምነቱ መፈጠር የሚቀለውን መንገድ ለማወቅ የምንጠቀምበት መለኪያ በገዢው ፓርቲ በቀላሉ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው አማራጭ የትኛው ነው? የሚል ሆናል፡፡ ይህን ለማድረግ የምንገደድበት ምክኒያትም ብዙውን ጊዜ የእርቀ ሰላም ጥያቄን ለመቀበል የማይፈልገውም፣ ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ተግባር እንዲለወጥ የማድረጉ ሠፊ ዕድል ያለውም ገዢው ፓርቲ ስለሚሆን ነው፡፡ በኢዴፓ እምነት የነዚህ ሦስት አማራጮች ውጤት የሚሆኑት ጥምር የሽግግር መንግሥቱም ሆነ ወይም የአደራ የሽግግር መንግሥቱ ወይም በሥልጣን ላይ ያለው ገዢው ፓርቲ፣ ሰላማዊ የሽግግር ሂደትን ለመፍጠር የሚያስችል የፖለቲካ አስተሳሰብና የባሕሪ ቅንነት እስከፈጠሩና በብሔራዊ እርቀ ሰላሙ መድረክ ውሳኔ (የቃል ኪዳን ሠነድ ወይም ቻርተር) ተገዥ እስከሆኑ ድረስ ሦስቱም አማራጮች ወደ እሚፈለገው ግብ የሚያደርሱ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡

በኢዴፓ እምነት ብሔራዊ እርቀ ሰላም ስለመፍጠር ሲታሰብ፣ ትልቁና መሠረታዊው ቁምነገር አንዱ የሌላውን ሥልጣን መጋራቱ ወይም ማስለቀቁ ሳይሆን ለአገራችን አጠቃላይ ችግሮች መድኅን የሚሆነውን የፖለቲካ አስተሳሰብና የባሕሪ ቅንነት መፍጠር በመሆኑ ከሦስቱ አማራጮች አንዱን ብቻ እንደ አማራጭ ከመውሰድ ይልቅ ሦስቱንም አስተሳሰቦች ወደ ተፈላጊው ግብ የሚያደርሱ አማራጮች እንደሆኑ አድርጎ መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በገዢው ፓርቲና በአንዳንድ ተቃዋሚ ኃይሎች ዙሪያ የሚደመጡትን «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» እና «በጠመንጃ የመጣን በጠመንጃ» የሚሉ ጽንፈኛ አስተሳሰቦችን ለማቀራረብ ያስችላል ብለን እናምናለን፡፡

## 9.5 ኢሕአዴግ የእርቀ - ሰላም ጥያቄውን ለመቃወም የሚያቀርባቸው ነጥቦች

ኢሕአዴግ የእርቀ ሰላም ጥያቄን ለመቃወም የሚያቀርበው አንዱ የመከራከሪያ ነጥብ «አገራችን ሰላም አግኝታለች፣ ማን ከማን ተጣልቶ ነው እርቅ የሚያስፈልገው?» የሚል ነው፡፡ ነገር ግን በአንድ በኩል እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ እያቀረበ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ አገር የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጦርነት አውጀውብኛል በሚል ሰበብ ወደ አገራቸው

እንዳይገቡ በመከልከል የጠመንጃ አማራጭን እንዲከተሉ ሲገፋፉቸው ይታያል፡፡ በተጨማሪም አገሪቱ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ያልሰፈነ በመሆኑ ላለፉት 11 ዓመታት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ግጭቶችን ሊያስቆሙ ያልቻሉ «የሰላም ኮንፈረንሶች»ን በየክልሉ በማካሄድ ሲደከም ታይቷል፡፡ ዘጠና ስምንት በሆነ ድምፅ ተመርጠናል የሚሉ ገዢዎቻችንም አፋዊ እንጂ ልባዊ ሰላም ያላገኙ በመሆናቸው በታሪካችን አይተነው በማናውቀው ሁኔታ በርዕሠ ከተማችን አዲስ አበባ ሳይቀር ራሳቸውን በጦር ሠራዊት ሲያስጠብቁ ይታያሉ፡፡ መሪዎቻችን ከቤተ መንግሥት ምሽጋቸው ወጥተው ወደ አውሮፕላን ማረፊያ በተጓዙ ቁጥርም በመንገዶች ላይ የሚታየው ሕዝብን ማንገላታት ትናንት በታሪካችን ያላየነው፣ ዛሬ ግን የለመድነው የዕለት ተዕለት ድርጊት ሆኗል፡፡

ባለፉት 12 ዓመታት ከኦነግ፣ ከአልኢቲሃድ፣ ከሻዕቢያና ከተለያዩ ታጣቂዎች ጋር በይፋ የተካሄዱ ውጊያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በተለያዩ ሥፍራዎች፣ በተለያዩ ጎሣዎች የተፈጠሩ የእርስ በርስ ግጭቶችና መንግሥት የተለያዩ ሰላማዊ ተቃውሞዎችን ለማፈን የወሰዳቸው የኃይል እርምጃዎች በጣም በርካታ ናቸው፡፡ ግጭቶቹ ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋትም ምክኒያት ሆነዋል፡፡ በአገዛዙ አስካሁን የተካሄዱ የሰብአዊ መብት ረገጣ ድርጊቶች በመላው ሕዝብ የሚታወቁ፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ተቋማት ከሞላ ጎደል የተመዘገቡ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን አሁንም ይበልጥ አስከፊ ገፅታ እየያዙ፣ እየተጠናከሩና እየተስፋፉ መቀጠላቸው የሚታይ ነው፡፡ ይህ ሁሉ እውነታ በገሃድ እየተፈፀመ እያለ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም ሰፍኗል ብሎ ለመናገር መድፈር ለሕዝባችን ትርጉም የለውም፡፡ በአንድ አገር ሰላም የለም ብሎ ለመናገር የግድ ጥይቶች ሲተኮሱ መስማትና ሰዎችንም ሲጥሉ ማየት አያስፈልግም፡፡ እንደ «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» እና «በጠመንጃ የመጣን በጠመንጃ» የሚሉ የከረሩ ቃሎችን በፖለቲካ መድረኮች ሲነገሩ ማድመጥ ብቻ በአገሪቱ ሰላም ላለመኖሩ በቂ ምስክር ይሆናል፡፡

እርቀ ሰላም ሊካሄድ የሚችለው አገር ቀውጢ ሲሆንና ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ አይደለም፡፡ በኢዴፓ እምነት የእርቀ ሰላም አስፈላጊነት ውጥረትና ግጭቶች አድገው ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ ከመሆናቸው በፊት ለመከላከል እንጂ አገር ቀውጢ ከሆነና ኪሣራ ከደረሰ በኋላ መሆን አይገባውም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ከማንኛውም ለአገር ደህንነት እቆረቆራለሁ ከሚልና አገራዊ ኃላፊነት ከሚሰማው ወገን የሚጠበቅ አይደለም፡፡

ሁለተኛው የኢሕአዴግ የመከራከሪያ ነጥብ የተቃዋሚዎች የእርቀ ሰላም ጥያቄ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች በሕግ ተጠያቂ እንዳይሆኑ ለማድረግ ነው የሚል ነው፡፡ አስካሁን ድረስ ኢዴፓ ሆነ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለአግባብና ለመበቀል ተብሎ እንዲጓተት የሚደረግን የፍርድ ሂደትና ፈራጅም ተፋራጅም ሆኖ የቀረበውን ኢሕአዴግን ከመቃወም በስተቀር የቀይ ሽብር ወንጀለኞች በሕግ ተጠያቂ መሆንን ፈፅሞ አልተቃወሙም፡፡ ኢዴፓ አሁንም ሆነ ወደፊት ወንጀለኞች ከሕግ ተጠያቂነት ማምለጥ እንደሌለባቸው በፅኑ ስለሚያምን የእርቀ ሰላም ጥያቄ ወንጀለኞችን ነፃ ከማውጣት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡፡

በመሠረቱ ኢዴፓ ማንኛውንም ዓይነት ሽብር አይደግፍም፡፡ ምንም ያህል የተለያየ ስም ቢሰጠውም (ቀይ ሽብር፣ ነጭ ሽብር፣ ጥቁር ሽብር፣ ወዘተ)፣ በማንኛውም የመንግሥታት ዓይነት ቢፈፀምም፣ በማንኛውም የፖለቲካ ቡድን ቢካሄድም፣ በምንም ዓይነት መፈክር ሥር የተጠቀለለ ቢሆን፣ የሰውን ልጅ መብት እስከተጋፋ ድረስ በኢዴፓ እምነት ተቀባይነት የለውም፡፡ ሁሉም ዓይነት ሽብሮች በአገሪቱ ላይ ጉዳት እስካስከተሉ ድረስ ሕገ-ወጥና ሰብአዊነት የጎደላቸው ናቸው ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንድን ዓይነት ሽብር ከሌላው ዓይነት ሽብር አብልጦ ወይንም አሳንሶ አያይም፡፡ አሁን የሚካሄደው ቀይ ሽብርን የመፋረድ ሂደት ራሱ በኢትዮጵያ ያለውን የፖለቲካ ችግር ለዘለቄታው ይፈታል ለማለት አይቻልም፡፡ ቀድሞ በተፈፀመውም ሆነ አሁን በቀጠለው ወንጀል አጥፊ ናቸው የተባሉ ሁሉ በሕግ እንዲዳኙ፣ የተጎዱ ወገኖች እንዲካሱ በማድረግ የፍትሕን ልዕልና በአገራችን ማረጋገጥና ከሂደቱም ትምህርት መውሰድ ቢቻል ትልቅ ቁም ነገር እንደሆነ ኢዴፓ ይገነዘባል፡፡

ከዚህ በፊት በፖለቲካ ምክኒያት የተፈፀመውም ሆነ አሁን በመፈፀም ላይ ያለው ሽብርና ያስከተለው አሳዛኝ ውጤት ወደድነውም ጠላነውም የታሪካችን አንድ ገፅታ እንደሆነ መቀበል ይኖርብናል፡፡ የእነዚያ ሽብሮች መንስዔዎችና ዓላማዎች ደግሞ ከግል ጠብና ከዕለት ግጭት በመነሳት የተፈፀሙ ተራ ወንጀሎች ሳይሆኑ የፖለቲካ ልዩነት ያበቀላቸው ነገር ግን በሠለጠነ መንገድ ሳይያዙ በመቅረታቸው ወደ አስከፊ ደረጃ የተሸጋገሩና በባሕሪያቸውም የተወሳሰቡ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በኢዴፓ እምነት ትልቁ ቁም ነገር ያለው ችግሩብ እየመላለሱ ማገላበጡ ላይ ሳይሆን ጉዳዩን በመጨረሻ መልኩ ለመቋጨት ቁርጠኝነትና ፈቃደኛነት ማሳየቱ ላይ ነው፡፡ በእነዚህና በመሳሰሉት ምክኒያቶች ኢዴፓ ከዚህ ዓይነቱ የተወሳሰበ አካሄድ ይልቅ በሰብአዊ መብት ረገጣና ከዚህ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ዓይነት ወንጀል የተሳተፉ ወገኖች ሁሉ ጥፋታቸው ይፋ ወጥቶና ተጣርቶ ተመጣጣኝ ቅጣት ወይም ሌላ ውሳኔ የሚሰጠው፣ ከዚህ ጥፋትም ትምህርት ለመቅሰም የሚቻለውና ለወደፊትም ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይፈፀም ዋስትና የሚገኘው የብሔራዊ እርቅ መድረክ ሲፈጠር ነው ብሎ ያምናል፡፡

ሦስተኛው የኢሕአዴግ የመከራከሪያ ነጥብ የእርቀ ሰላም ጥያቄ የማይታረቁ የፖለቲካ ፕሮግራሞችን የማስታረቅና ሕገ-መንግሥትን የማስለወጥ ጥያቄ ነው የሚል ነው፡፡ የእኛ እምነትና ትልቁ የእርቀ ሰላም ጥያቄያችን መሠረት የፖለቲካ ፕሮግራም ልዩነቶቻችን የተከበሩ፣ ጤናማና አስፈላጊ መሆናቸው ታምኖ ለሕዝብ ምርጫ የሚቀርቡበት ሁኔታ እንዲመቻች ማድረግ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥትም ከሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ውጭ የሚገኝበት መንገድ ስለሌለ በእርቀ ሰላም ጥያቄም ሆነ በሌላ የተለየ መንገድ የፖለቲካ ግሮግራምን የማስታረቅም ሆነ ሕገ-መንግሥትን የማስቀየር አስፈላጊነት አይኖርም፡፡

አራተኛው የኢሕአዴግ የመከራከሪያ ነጥብ በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና ስላገኙ ተቃዋሚዎች በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ዓላማቸውን ማራመድና ሥልጣን መጨበጥ ይችላሉ የሚል ነው፡፡ ይህን መከራከሪያ ነጥብ በተመለከተ ከላይ የጠቀስናቸው ፀረ-ዴሞክራሲና ኢ-ሰብአዊ የሆኑ በርካታ ድርጊቶች በራሳቸው በቂ ምስክር ናቸው፡፡ ተጨማሪ ማረጋገጫ ካስፈለገ የተለያዩ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና መንግሥታት ያወጧቸውን ተደጋጋሚ መግለጫዎችና ዓመታዊ ዘገባዎች ማየት ይቻላል፡፡

አምስተኛው የኢሕአዴግ የመቃወሚያ ነጥብ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የእርቀ ሰላም ጥያቄ በአቋራጭ ሥልጣንን ለማግኘት የሚቀርብ ጥያቄ ነው የሚል ነው፡፡ በኢዴፓ እምነት የሕዝባዊ ሥልጣን ብቸኛ ምንጭ የምርጫ ሳጥን ብቻ በመሆኑና ይህንንም እምነቱን በፕሮግራሙ ውስጥ በግልፅ ያካተተና በተደጋጋሚም በየመድረኩ የሚገልፀው እውነታ በመሆኑ በምንም መልኩ የእርቀ ሰላም ጥያቄና የሥልጣን ጥያቄ ግንኙነት የላቸውም፡፡ ይልቁንስ የሥልጣን ጥያቄው ያለው የእርቀ ሰላም መድረክ ተፈጥሮ የሥልጣን ምንጭ ሕዝቡ ብቻ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች በሚጠይቁት ወገኖች በኩል ሳይሆን ሥልጣኔን አጣለሁ በሚል ሥጋት የእርቀ ሰላም ጥያቄን ያለበቂ ምክኒያት በሚነቅፈው ኢሕአዴግ በኩል ነው፡፡

## 9.6 በብሔራዊ እርቀ - ሰላሙ መድረክ እነማን ተሳታፊ ይሁኑ?

የብሔራዊ እርቀ - ሰላም ጉዳይ የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን በአጠቃላይ የአገሪቱን ሕዝብ የሚመለከት ታላቅ ብሔራዊ ጉዳይ ነው፡፡ የእርቀ ሰላም መድረኩ በተለይ ኢሕአዴግንና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ብቻ የሚያስታርቅ መድረክ አይደለም፡፡ በእርግጥ በአገራችን ለተፈጠረው ጥላቻና ፍጥጫ ዋናዎቹ ምክኒያቶች የፖለቲካ ኃይሎች ቢሆኑም ችግሩ ግን በነሱ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡

ለማሳየት እንደሞከርነው በአሁኑ ወቅት መንግሥትና ሕዝብ ሆድና ጀርባ ሆነዋል፡፡ ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚዎች ደም ሊያፋስስ ወደሚችል ፍጥጫ ተሸጋግረዋል፡፡ በራሳቸው በተቃዋሚ ኃይሎችም አካባቢ ውስጥ ውስጡን የሚብላላ ቀላል የማይባል የጥላቻና የመናናቅ

ስሜት ይታያል:: እንደተባለው የችግሩ ዋና መንስዔዎች የፖለቲካ ኃይሎች ይሁኑ እንጂ በራሱ በሕዝቡ ውስጥም ለብዙ ሰዎች መሞትና መፈናቀል ምክኒያት የሆነና ወደፊትም ሊሆን የሚችል የእርስ በርስ ጥላቻ፣ ፍጥጫና ውጥረት አለ:: በአጠቃላይ በእነዚህ ሁሉ ምክኒያቶች በየአንዳንዳችን ልብ ውስጥ የጥላቻና የተበቃይነት ስሜት ሥር ሰዷል:: ስለዚህ እርቀ ሰላሙ የተወሰኑ የፖለቲካ ኃይሎችን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን መንግሥትን ከሕዝብ፣ ገዢውን ፓርቲ ከተቃዋሚ ኃይሎች፣ ተቃዋሚዎችን ከተቃዋሚዎች፣ ሕዝብንም ከሕዝብ እና እንዳንዳችንንም ከየራሳችን ጋር የሚያስታርቅ መድረክ ነው ማለት ይቻላል:: ስለዚህ በእርቀ ሰላሙ መድረክ ላይ የሚሳተፉት ውሱን ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: እያንዳንዳችን ያለፉ በደሎቻችንን ይቅር ብለን አዲስ የፍቅርና የአንድነት ስሜት ፈጥረን፣ የፖለቲካ ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሆነው በጋራ አገራችን ውስጥ በጋራ ለመኖር የሚያችለንን፣ የሰላምና የብልጽግና ባለቤት የሚያደርገንን የጋራ የቃል ኪዳን ሠነድ የምንፈራረምበት ክቡር መድረክ ነው ማለት ይቻላል::

በኢዴፓ በኩል የዚህ ታላቅ ብሔራዊ መድረክ ተሳታፊዎች ገዢው ፓርቲ፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ምሁራን፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሙያ ማኅበራት መሪዎች፣ የተለያዩ የጎሣ ወይም የአካባቢ መሪዎች፣ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማኅበራት መሪዎች፣ እንዲሁም ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች መሪዎች ተሳታፊ ቢሆኑ መድረኩ የተሟላ ብሔራዊ ይዘት ይኖረዋል ብለን እናምናለን::

## 9.7 ለመድረኩ ስኬታማነት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ጉዳዮች

1. በመድረኩ ተሳታፊ በሚሆኑ ማናቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታና እገዳ እንዳይጣልባቸውና ለተሳታፊቸውም ሙሉ የደህንነት ዋስትና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

2. የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረኩ፣ የመድረኩ አጀንዳና የሚመራበት ሥርዓት ከገዥው ፓርቲ፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ከገለልተኛ ድርጅቶች ወይንም ግለሰቦች በተውጣጡና በመድረኩ አባላት ተሳትፎ በተመረጡ የኮሚቴ አባላት እንዲዘጋጅና እንዲመራ ማድረግ፤

3. የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረኩ የስብሰባ ሂደት ለሕዝብ እይታ ክፍት የሚሆንበትን ሁኔታና ሕዝቡም ቀጥተኛ አስተያየቱን የሚሰጥበትን ዕድል ማመቻቸት፤

4. ከብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረኩ የሚመነጨው ውሳኔ (የቃል ኪዳን ሰነድ) በነፃና ፍትሓዊ ምርጫ የሚመረጡት ኃይሎች ሥልጣን እስከሚረከቡ ድረስ በሥልጣን በሚገኘው ገዢ ፓርቲ ወይም ጥምር የሽግግር መንግሥት የበላይ ሕግነት ደረጃ እንዲኖረው ማድረግ፤

5. የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረኩ ውሳኔ (የቃል ኪዳን ሠነድ) የመጀመሪያ እርምጃ የፖለቲካ ኃይሎች በመገናኛ ብዙሃን በእኩልነት የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማመቻቸትና በሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ተሳትፎ ወይንም ነፃና ገለልተኛ በሆነ አካል የምርጫ ቦርድ እንዲቋቋም የሚያስችል እንዲሆን ማድረግ፤

6. አሁን ሥራ ላይ ያለው የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊት ብሔራዊ ሠራዊትነቱ የሚቀጥል ስለመሆኑ ዋስትና መስጠት፣ ሞያዊ አገልግሎታቸው ተፈላጊ የሆነና ያለአግባብ የተባረሩ የቀድሞ የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊት አባላት ወደ ሥራ የሚመለሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ አገራቸውን ያገለገሉ የቀድሞ ሠራዊት አባላት በቂ ካሣ የሚያገኙበትን ወይንም የጡረታ መብታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

7. በግል ተነሳሽነትና ፍላጎት ሕገ-ወጥ ድርጊት ከፈፀሙ ወንጀለኞች በስተቀር በመንግሥት ወይንም በፓርቲ ውሳኔ መሠረት የተፈፀሙ ወንጀሎች ለሕዝብ ትምህርት ሰጭ በሆነ ሁኔታ ታምነውና ይቅርታ ተጠይቆባቸው ምሕረት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

8. ባለፉት 11 ዓመታት ፖለቲካ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የታሰሩ የህሊና እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ ማድረግ፤

9. ብሔራዊ እርቀ ሰላሙ መድረክ ላይ የተለያዩ አገሮች መንግሥታት ተወካዮች፣ የታዋቂ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የጎረቤት አገር ተወካዮች፣ የታዛቢነት ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

10. የብሔራዊ እርቀ ሰላሙ መድረክ የተከፈተበት ወይም በአስማሚ ውጤት የተጠናቀቀበት ዕለት የአገሪቱ ብሔራዊ «የእርቀ ሰላም ቀን» ሆኖ እንዲከበርና ታሪካዊነቱን ለትውልድ የሚዘክር የመታሰቢያ ሐውልት እንዲቆምለት ማድረግ ናቸው፡፡

## 9.8 ማጠቃለያ

በአገራችን ሆነ በዓለማችን ታሪክ ሥልጣንን ይዞ የኖረ አምባገነናዊ ሥርዓት የለም፡፡ የአምባገነኖች እጣ ፈንታ ከሦስት አማራጮች የሚዘል አይሆንም፡፡ ይኸውም እስከመጨረሻው ግብዓተ-መሬታቸው ድረስ በአጥፍቶ ጠፊነት ባሕሪያቸው ቀጥለው አይቀሬው ተፈጥሮአዊ ሞት መሞት፣ ወይንም ጊዜና ሁኔታ እንደከዳቸው ሲገነዘቡ ሻንጣቸውን አንጠልጥለው መሰደድ፣ ወይንም የሽንፈታቸውን አይቀሬነት ሲረዱት እየተንመዘዛቸውም ቢሆን ለሕዝባዊ ትግሉ መንበርከክና እጃቸውን ለምሕረትና ለእርቅ መዘርጋት ይሆናል፡፡ ኢሕአዴግ ከዚህ በፊት የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄን የመቀበል ፍላጎት እንደሌለው በተደጋጋሚ ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ ቢሆንም ወደፊት በዚህ አቋሙ እንደማይገፋበት ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በእኛ እምነት በብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ የመጀመሪያ ተጠቃሚ ከሚሆነው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቀጥሎና ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች በበለጠ የሚጠቀመው ኢሕአዴግ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በዚህ ዕድል ተጠቅሞ በታሪክ ተጠያቂ ከመሆን ይልቅ በአዲስ የእርቀ ሰላም ምዕራፍ በወደፊቷ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ህልውናውን አስጠብቆ የሚቀጥልበትን ሁኔታ እንዲያመቻች በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

ለመግለጽ እንደተሞከረው የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ እንደ አንድ አማራጭ የትግል ሥልት የሚታይ እንጂ ብቸኛ የትግል አማራጭ አይደለም፡፡ የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄውም ተገቢ መልስ የሚያገኘው አምባገነኖች ጥያቄውን ከመቀበል ሌላ አማራጭ የሌላቸው መሆኑን ለማሳየት የሚያስችል ጠንካራ ትግል ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተናጠል ድርጅታዊ አቅማቸውን ከማጠናከር ጎን ለጎን የወቅቱን የተቃዋሚዎች የኅብረትና የውህደት ጥያቄን በተሻለ ፍጥነት መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የትግል መሠት ደግሞ ሕዝቡ በመሆኑ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የቻልተኝነትና የዝምታ ድባቡን ሰብሮ፣ ተዓምራዊ በሆነ የማይዳሰስ ኃይል ሳይሆን፣ በራሱ የትግል ርብርብ የሚመኘውን ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አዲስ ተነሳሽነትን ፈጥሮ መንቀሳቀስ ይገባዋል፡፡

ኢዴፓ፣ የተዘረዘሩት የብሔራዊ እርቀ ሰላም መድረክ መሠረተ ሃሳቦች እውነተኛ ሰላማዊ የሽግግር ሂደትን ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ሃሳባቸውን በይፋ ገልፀው ሕዝብ ይፋዊ ውይይት እንዲያደርግበትና የሕዝቡን የብሔራዊ እርቀ ሰላም ጥያቄ በተጠናከረና መልክ ባለው ሁኔታ ማካሄድ የሚያስችል ብሔራዊ ኮንፈረንስ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ማዘጋጀት አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑን ኢዴፓ ለማሳሰብ ይወዳል፡፡ ኮንፈረንሱን ያዘጋጀቱን ኃላፊነትም አገር ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጋራ ወይም ለብሔራዊ እርቀ ሰላሙ መድረክ መፈጠር ድጋፍ የሚሰጡ ገለልተኛ ታዋቂ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ለዝግጅቱ መሳካት በኢዴፓ በኩል አቅሙ የፈቀደውን ትብብር ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነው፡፡